

# ከመስከረም እስከ መስከረም

ጥር ፳፻፲፭ ዓ.ም
ቅጽ 5 VOL 5

የኢፌድሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ክቡር ዐቢይ አህመድ (ዶ/ር) ከመስከረም 24 ቀን 2014 ዓ.ም እስከ መስከረም 24 ቀን 2015 ዓ.ም. ድረስ ያደረጓቸው ንግግሮች እና ያስተላለፏቸው መልእክቶች

# ከመስከረም እስከ መስከረም

የኢፌዴሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ክቡር ዐቢይ አሕመድ ከመስከረም 2014 ዓ.ም. እስከ መስከረም 2015 ዓ.ም. ያደረጓቸው ንግግሮችና ያስተላለፏቸው መልእክቶች

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የጠቅላይ ሚኒስትር ጽሕፈት ቤት

ቅንብር፣ አርትዖትና ዝግጅት የኢፌዴሪ
የጠቅላይ ሚኒስትር ጽ/ቤት

**የዚህ መጽሐፍ ገቢ ለበጎ**
**አድራጎት የሚውል ነው።**

ISBN 978-99990-985-8-8
Copyright©2023 FDRE Office of the
Prime Minister
ጥር ፳፻፲፭ ዓ.ም. ታተመ

# ማውጫ

**መግቢያ** i

## ክፍል አንድ – የአማርኛ ንግግሮች

1. የመንግስት ምስረታ በአል 1
2. በአዲሱ መንግሥት የተካተቱ ሚኒስትሮች እና ሚኒስትር ዴኤታዎች የሥራ ማስጀመሪያ ስብሰባ ላይ ያደረጉት ንግግር። 21
3. የጥቅምት 24/2013 ዓ.ም መታሰቢያ ንግግር በመከላከያ ሚኒስቴር 41
4. ኢትዮጵያ አትፈርስም 45
5. የአብርሆት ቤተ መጻሕፍት ምርቃት 49
6. የመከላከያ ሚኒስቴር መስሪያ ቤት ምርቃት 55
7. ወደ ሀገር ቤት የእራት መርሃግብር ላይ የተደረገ ንግግር 69
8. ለዘማች የሚዲያ እና ኪነጥበብ ባለሞያዎች የተደረገ የምስጋና ንግግር 84
9. የህዳሴ ግድብ የመጀመሪያ ተርባይን የኃይል ማመንጨት መርሃግብር ላይ የተደረገ ንግግር 91
10. የአቡነ መርቆሬዮስ የቀብር ስነስርአት ላይ የተደረገ ንግግር 99
11. ማዕድ ማጋራት 101
12. የዋር ኮሌጅ ምርቃት 106
13. የፌዴራል ፖሊስ የእውቅና እና ምስጋና ስነ-ስርዓት 110
14. የህዳሴ ግድብ ሶስተኛው ተርባይን ሙሌት 116
15. የአረንጓዴ አሻራ መርሃግብር ማጠናቀቂያ በድሬዳዋ ከተማ 121
16. የድሬዳዋ ነጻ ቀጠና ምርቃት ንግግር 127
17. የሞጆ–ሀዋሳ የስንዴ ማሳ ጉብኘት 131

## Kutaa Lama – Haasaawwan Afaan Oromoo

18. Akkuma Kaleessaa Har’as Qormaatota Injifinnoon Ceenee, Harka Keenya Galataaf ni Bal’ifna 139

## Part Three - English Speeches

19. New Government Formation Ceremony Speech 149
20. A statement with respect to the Joint Investigation Team Report of the EHRC and UNOHCHR 162

21. Glory to our heroes who paid the ultimate sacrifice for Ethiopia! 167
22. Prime Minister Abiy Ahmed's remarks at Stockholm+50 171
23. The GERD as a site of cooperation 173
24. The Opening of the 35th Ordinary Session of the AU 176
26. A Call for Restraint 186
27. Ethiopia's Green Legacy Initiative - Planting Our Print for Future Generations 188
28. Hands that are Greening a Nation 191

v

27 . ሎሚ እውን ከም ትማሊ ፈተናታት ብዓወት ተሳጊርና ኣእዳውና ንምስጋና ክንዝርግሕ ኢና 196

## Fooliisho ontte - Sidaamignuni Sa'inno sokka

25. Ayirrado sidaamu daga, hattono Ayirrado gobbanke Tophiyu daganna dagoomu 204

## ክፍል ስድስት - መልዕክቶች

26. እንኳን ለ1496 ኛው የመውሊድ በዓል በሰላም አደረሳችሁ 208
27. ክብር ኢትዮጵያን ሲሉ ለተሠዉ ጀግኖቻችን 211
28. "ኢትዮጵያ የሚለውን የነጻነት ስም የማስጠበቅ የታሪክ አደራ አለብን 214
29. "በድል የታጀበው የመጀመሪያው ምእራፍ" 217
30. በወቅታዊ ጉዳዮች ላይ የተሰጠ መግለጫ 221

31. ወደሀገር ቤት ጥሪን ተከትሎ ለመጡ እንግዶች የተላለፈ መልእክት 225
32. ኢትዮጵያ የምትገነባው በዕውቀት ማዕከላት ውስጥ ነው 229
33. "ጀግና ሕዝብ - በቀኝ እጁ ድልን የሚጨብጥ፣ በግራ እጁ ይቅርታና ምህረትን የሚቸር ነው።" 232
34. የከንደ ብርቱዎች እናት ኢትዮጵያ በልጆቿ ትንፋሽ ሰንደቋ ዳግም ከፍ ብሎ ይውለበለባል 236
36. የአፍሪካ ህብረት ጉባኤ በአዲስ አበባ 242
37. የአፍሪካ ኅብረት የመሪዎች ጉባኤ በሰላም እና በስኬት እንዲጠናቀቅ አስተዋጽዖ ላበረከታችሁ ምስጋና ይድረስ 245
37. ኢትዮጵያ በታላቁ ሩጫ ላይ ናት 247
39. "ድርቅ በተፈጥሮ ቢመጣም ርሃብ ግን የሥንፍናችን ውጤት ነው" 250
40. እንኳን ለዐድዋ ድል 126ኛ ዓመት አደረሳችሁ 252
41. የብሔራዊ ምክክሩ አሳታፊነት የሚሳካው ሁሉም ኢትዮጵያዊ በቀናነትና በባለቤትነት ሂደቱን መደገፍ ሲችል ነው 257
42. እንኳን ለብርሃነ ትንሣኤው በሰላም አደረሳችሁ 260
43. እንኳን ለዒድ አል ፈጥር በዓል በሰላም አደረሳችሁ 264
44. እንኳን ለ1443ኛው ዓመተ ሒጅራ የዒድ አል አድሐ ዐረፋ በዓል በሰላም አደረሳችሁ፣ አደረሰን 268
45. ዛሬም እንደ ትናንቱ ፈተናዎችን በድል ተሻግረን፣ እጃችንን ለምስጋና እንዘረጋለን 270
46. እንኳን ለአዲሱ ዓመት አደረሳችሁ፣ አደረሰን 277
47. እንኳን ለብርሃነ መስቀሉ አደረሳችሁ 281
48. እንኳን ለኢሬቻ በዓል አደረሳችሁ 285

# መግቢያ

ቃል ሚዛን ነው፤ የንግግር ምርትን ከግርድ ላይቶ የሚለካ። ቃል ኃይል ነው የደከሙትን የሚያበረታ የዛሉትን የሚያጀግን። በተለይ አገርን በርዕይ ከከፍታ ማማ ለማድረስ፣ ህዝብን በጋራ ለማሠለፍ ቀን ተሌት ከሚደክሙ መሪዎች የሚወጣ ቃል ደግሞ ኃይሉም ብርቱ፤ ሚዛኑም ጥብቅ ነው። በመሪዎች የሚነገር ሃሳብ አንድም የቀጣይ ተግባራት የሚለኩበት ሚዛን ሲሆን፤ በሌላ መልኩ ደግሞ በህዝብና መንግስት መካከል ያለውን የአስተዳደር ኮንትራት በመተማመን ላይ እንዲመሰረት የሚያደርግ ውል ነው።

ቃል መሪዎች ንግግራቸውን ተከትለው መስመር ሳይስቱ እንዲሄዱ በማድረግም ልጓም ሆኖ ያገለግላል። እንደ ኢትዮጵያ ባሉ አገራት ደግሞ ቃል የሰው ልጅ ልከኛ መስፈርት ሆኖ የሚያገለግል ብርቱ ኃይል ነው። ኢትዮጵያዊያን “መከበር በከንፈር” “ያሉት ከሚጠፋ የወለዱት ይጥፋ” የሚሉና ሌሎች ጠንካራ አባባል ያላቸውና በእለት ተእለት የኑሮ መስተጋብራቸው ውስጥም ቃል የትስስራቸው አካል ሆኖ አገልግሏል፤ አሁንም እያገለገለ ይገኛል።

በኢትዮጵያ መሪዎች በተለያዩ ጊዜያት የሚያደርጓቸውን ንግግሮች በተደራጀ መልኩ ሰንዶ በማቅረብ ረገድ ብዙም እንዳልተሰራበት እሙን ነው፤ በርግጥ የፖለቲካ ታሪካችን ካለፉት ጊዜያት መልካም ጎኖች ላይ የራስን ጡብ እየጨመሩ ከመሄድ ይልቅ ያለፈውን በማጠልሸት ላይ የተመሰረተ መሆኑ የአደባባይ ሃቅ ነው። ይህም የመሪዎችን ንግግር ሰንዶ ከማቆየት ይልቅ ካለፉ መሪዎች ጋር የተያያዙ ጉዳዮች በተደራጀ መልኩ ለቀጣዩ ትውልድ እንዳይሸጋገሩ እንቅፋት ፈጥሮ ቆይቷል። ለዚህም ይመስላል ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አህመድ “መደመር” በተሰኘው እሳቤያቸው ያለፉት ጊዜያትን በዜሮ አባዝቶ ከማየት ይልቅ እድልም እዳም አድርጎ መውሰድ እንደሚገባ ያስቀመጡት። እሳቤው ከትናንት የተሻገሩ እድሎችን አገርን ለመገንባት ሁነኛ መሰረት አድርጎ መጠቀም እንደሚገባ የሚያመላክት ሲሆን፤ ከእዳዎች ደግሞ ትምህርት በመውሰድ እንዳይደገሙ መስራትን ይጠቁማል።

ይህ ብቻ አይደለም መደመር የታሪክን እርግማን ውይም ምርቃት ብቻ ከመመልከት ይልቅ ታሪክን በሚዛኑ ማስቀመጥ እንደሚገባ በግልጽ ያመላክታል።

ለዚህ ደግሞ የተሰነዱ ማስረጃዎችን ለቀጣዩ ትውልድ የማስቀመጡ ስራ ለነገ የሚተው ሳይሆን የዛሬ የቤት ስራ መሆኑ ግልጽ ነው።

ከዚህ አኳያ አገራዊ ለውጡን ተከትሎ በተለይ ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ

አህመድ በተለያዩ ጊዜያት ያደረጓቸውን ንግግሮች ሰንዶ በማስቀመጥ ዛሬን በተግባር እየተጓዙና በቃሉ እየተመሩ፣ ነገን ደግሞ ከትላንት የሚማር ትውልድ እየፈጠሩ በመጓዝ ረገድ ይበል የሚያስብል ጅምር እየታየ ነው፡፡
ከዚህ ቀደምም በጠቅላይ ሚኒስትር ጽህፈት ቤት ፕሬስ ሴክሪታሪያት አማካይነት “ከመጋቢት እስከ መጋቢት” በተሰኙ ርዕሶች የተዘጋጁ ሶስት ጥራዝ መጽሃፎች መልካም አብነቶች ናቸው፡፡
መጽሃፍቱ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ ወደ መሪነት ከመጡበት መጋቢት 24 ቀን 2010 ዓ.ም ጀምሮ በተለያዩ ጊዜያት ያደረጓቸውን ንግግሮች እና ያስተላለፏቸውን መልዕክቶች የያዙ ናቸው፡፡ ዛሬ ላይ መለስ ብሎ ለተመለከታቸው ኢትዮጵያ ለውጡን ተከትሎ በምን አይነት ሂደት እንዳለፈች ጥቆማ ይሰጣሉ፡፡ መሰል መጻሃፍትም ከታሪክነት ባሻገር ለምርምር ስራዎች አይተኬ ሚና እንዳላቸው አጠያያቂ እንዳልሆኑ ያመላክታሉ፡፡
“ከመስከረም እስከ መስከረም “የተሰኘው ይህ መጽሃፍም  በኢትዮጵያ የፖለቲካ ታሪክ ውስጥ አዲስ ምዕራፍ እንደከፈተ የሚታመነው 6ኛው አገራዊ ምርጫ በስኬት መጠናቀቁን ተከትሎ ከተከናወነው የመንግስት ምስረታ ጀምሮ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ በተለያዩ መድረኮች ያስተላለፏቸውን መልዕክቶች የያዘ ነው፡፡ መጽሃፉ ኢትዮጵያ እያንዳንዱን ቀን ሳታባክን ህዝቧ ሊደርስበት ወደሚሻው ብልፅግና ለመሻገር በደም የተከፈለውን መስዋዕትነት በላብ ማፅናት የግድ እንደሚላት በፅኑ የሚያስገነዝብ ነው፡፡

## ከመስከረም እስከ መስከረም...

የመንግስት ምስረታ በዓል

መስከረም 24/2014 ዓ.ም



# ከመስከረም እስከ መስከረም

ንግግሮች ፡ አማርኛ

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የጠቅላይ ሚኒስትር ጽሕፈት ቤት

# የመንግስት ምስረታ በዓል ንግግር

**የተከበሩ ፕሬዝዳንት ሳህለወርቅ ዘውዴ፣**
**የተከበሩ ፕሬዳንት ዩዌሪ ካጎታ ሙሴቪኒ፣**
**የተከበሩ ፕሬዝዳንት እስማኤል ኦማር ጌሌ፣**
**የተከበሩ ፕሬዝዳንት ሳልቫኪር ማየርዲት፣**
**የተከበሩ ፕሬዝዳት ማኪሳ፣**
**የተከበሩ ፕሬዝዳንት ኡሁሩ ኬንያታ፣**
**የተከበሩ ፕሬዝዳንት ሙሃመድ ቡሃሪ፣**
**የተከበሩ ፕሬዝዳንት ሞሃመድ አብዱላሂ ፎርማጆ፣**
**የተከበሩ የአፍሪካ ህብረት ሊቀመንበር ሙሳ ፋኪ መሃመት፣**
**የተከበሩ የኮንጎ ጠቅላይ ሚኒስትር ጂሚ ሼል ዛማል ኩንዴ፣**
**የተከበሩ ዶክተር ወርቅነህ ገበየሁ የኢጋድ ዋና ጸሐፊ፣**
**የተከበሩ ኦሊሴንጎ ኦባሳንጆ የቀድሞው የናይጄሪያ ፕሬዝዳንት፣**
**የተከበሩ ራማታን ላማምራ የአልጄሪያ የውጪ ጉዳይ ሚኒስትር፣**
**የተከበሩ ሃይለማርያም ደሳለኝ የቀድሞው የኢፌዲሪ ጠቅላይ ሚኒስትር፣**
**የተከበሩ ዶ/ር ሙላቱ ተሾመ የቀድሞው የኢፌዲሪ ፕሬዝዳንት፣**

**የተከበራችሁ ኢትዮጵያዊያን፣ ክቡራት እና ክቡራን**

በኢትዮጵያ ረጅም የአስተዳደር ዘመን ለመጀመሪያ ጊዜ ግልጽና ተአማኒ ምርጫ በማካሄድ ህዝባዊ ቅቡልነት ያገኘ መንግስት በምንመሰርትበት ታሪካዊ ቀን ከፊታችሁ ቆሜ ንግግር ለማድረግ ያበቃኝን ፈጣሪ አስቀድሜ ላመሰግን እወዳለሁ።

በዚህ ወሳኝና ፈታኝ ወቅት በሀገራችን እና በህዝቦቿ ላይ የተቃጣውን የህልውና አደጋ ለመቀልበስ በዱር በገደሉ፣ በቁር በሃሩሩ ከፍተኛ ተጋድሎ እያደረጉ ለሚገኙት ለጀግናው የመከላከያ ሰራዊታችን፣ ለመላው የጸጥታ አካላት እና ለህዝባዊ ሃይላችን ያለኝን ታላቅ አክብሮት እና ምስጋና ልገልጽ እወዳለው። እናንተ የቁርጥ ቀን ልጆች ጀግና የምታከብረው ኢትዮጵያ ውለታችሁን መቼም ቢሆን አትረሳውም።

ሀገራችን እንደቀደሙ ጀግኖቿ ለዚህ ትውልድ ፈርጦችም ትልቅ ክብር እና ሞገስ ትሰጣለች የምትከፍለው መስዋእትነት በታሪክ ማህደር እና ብራና ላይ በደማቅ ታትሞ ይኖራል። እልፍ ጀግኖቻችን እልፍ ጀግኖችን ካፈራው አብራክ በመፈጠሬ ሁሌም እንድኮራ ከሚያደርጉኝ መካከል የህዝባችን ጽናት፣ አይበገሬነት እና አትንኩኝ ባይነት ቀዳሚውን ስፍራ ይይዛል።

ህዝባችን በየትኛውም ዘመን የእናት ሀገር ድም በሉአላዊነቱ የማይደራደር መሆኑ እሙን ነው። ከዚህም የተነሳ ህዝባችን መተማመኛችን፣ ጦር እና ጋሻችን፣ ተዋጊ ደጀናችን ለሆነው ለኢትዮጵያ ህዝብ ያለኝን ክብር እና አድናቆት በታላቅ ትህትና ልገልጽ እወዳለሁ። አቅም ባነሳት ጊዜ ምርኩዝ ለሆናችኋት፣ በመላው አለም ለምትኖሩ ኢትዮጵያዊያን እና የኢትዮጵያ ወዳጆች ሁሉ በህዝብ እና መንግስት ስም የከበረ ምስጋናዬን ላቀርብ እወዳለሁ።

በቀደመ ገናና ታሪኳ በመርከብ ትመሰላለች። በታላላቆቹ ቅዱሳን መጻህፍት እንደተነገረው መርከቧ ኢትዮጵያ የፍትህ፣ የእኩልነት፣ የነጻነት እና ነበር ዥንጉርጉርነቱን ኢትዮጵያዊ መልኩን አይቀይርም የተባለለት ጃንደረባን ያፈራች ሀገር ነች። ነብዩ መሃመድ አለይሷት እና የመጀመሪያው ሙአዚን ቢላል መነሻ የሆነች ሀገር ናት ኢትዮጵያ።

ጸሃፊ ፔድሮ አልቫሬዝ ኢትዮጵያዊያን የመሰከረልን ድንቅ ህዝብ ነን። ኢቱዮጵያ

በኤዞፕ ተረቶች ብልህ ህዝቦች ብሎ የጻፈላት ድንቅ ሀገር ናት ኢትዮጵያ። የዘመናችን አርኪዮሎጂስቶች ምድረ ቀደምትነቷን ያረጋገጡ ለአፍሪካ ነጻነት ከውስን ሃብቷ ሳትሰስት

ካላት ላይ ቀንሳ የሰጠች፣ በጥቁር ህዝቦች መብት ትግል ውስጥ ትልቅ ቦታ ከነበራቸው ማርከስ ጋርቬይ እና ዱ ቦይስ ልቦና ውስጥ ጎልታ የተሳለች ድንቅ ሀገር ናት ኢትዮጵያ።

የተወደሰች የእውነት እና የአፍሪካዊት ሞገስ እና ፈርጥ የሆነች ናት ኢትዮጵያ። አንድም ከታሪክ መዝገብ ገልጠን የአባቶቻችንን ገድል በማጣቀስ ወደውጤ በመቀየር መቻላችንን እና ኢትዮጵያ መሆናችንን ነገ ላይ የሚጠብቀን ተስፋ ቢበልጥ እንጂ አያንስም ዋናው ጥያቄ ተስፋውን አይተን እውን ለማድረግ ዋናው ጥያቄ ቁርጠኞች ነን የሚለውን ጥያቄ ደጋግመን ራሳችንን መጠየቅ ነው።

ኢትዮጵያ የምትበለጽገው እኛ ሀገራችንን ለመለወጥ በፈለግነው መጠን እና የጋራ ራእይ በሰነቅንበት ልክ ብቻ ነው። ኢትዮጵያ ካዘመመችበት ቀና የምትልበት ጊዜ ጊዜው አሁን ነው። ይሄ ለማሳካት የዛሬ ህያው ኢትዮጵያውያን ታላቅ አደራ ተጥሎብናል። ይሄንን አደራ ተቀብለን የዘመናት ድምር ውጤቶችን አበርክተን ኢትዮጵያ የተባለችውን መርከብ ሞተሯን አድሰን፣ ማእበል ወጀቡ ፍጹም እንዳያናውጣት አንጸን፣ መልህቋን አንስተን ጉዞዋን ማስጀመር የኛ ድርሻ ሲሆን ለዘለቄታው በጽናት እንድትጓዝ ማድረግ ደግሞ የየትውልዱ የኢትዮጵያ ልጆች አደራ ይሆናል።

ውድ ኢትዮጵያዊ በስርአቷ መንግስትን ለመትከል ከፍተኛ ተጋድሎ አድርጋለች። ተስፋ እና ስጋት እድል እና ፈተና እየተፈራረቁባት አያሌ ውጣ ውረዶችን፣ ፍትሃዊ ተጠቃሚነት ጥያቄዎች ከአርሶ አደር እስከ እስከ አርብቶ አደር፣ ከከተሜ እስከ ባለሀገር፣ ከመለዮ ለባሽ እስከ ምሁር፣ ከወጣት እስከ ጎልማሳ፣ ከልሂቅ እስከ ደቂቅ መላው የሀገራችን ህዝቦች የተሳተፉበት እና መስዋእትነት የከፈሉበት የዘመናት የህዝብ ጥያቄ ነበር።

ምንም እንኳን ስድስተኛው ሀገራዊ ምርጫ ከእንከኖች የጸዳ እና የምኞታችንን ያህል እጅግ የተሳካ ነበር ባይባልም እጅግ የተሳካ ምእራፍን ከፍቷል፣ አንድ እርምጃም ወደፊት

አራምዶናል። ስልጣን ከዘር ሃረግ ወይንም ከጠብመንጃ አፈሙዝ አልያም በሴራ እና ተንኮል ሳይሆን በእውነተኛ የህዝብ ድምጽ ከምርጫ ኮሮጆ ብቻ የሚመነጭ በማድረግ የህዝብን

የፖለቲካ ሉአላዊ የስልጣን ባለቤትነት ያረጋገጥንበትዘመን ላይ ደርሰናል።

ህዝባችን በልዩ ልዩ ሰው ሰራሽ ግጭቶች ሳይረበሽ እንደኮቪድ ወረርሺኝ ባሉ ተፈጥሮአዊ አደጋ ሳይበገር በሀገራዊ ሉአላዊነት ላይ በተጋረጠው አደጋ ሳይረታ ከውጪ ሃይሎች በሚደርስበት ተጽእኖ ሳይንበረከክ በሂደቱ የገጠሙትን እንከኖች ሁሉ ተጋፍጦ የዜግነት ድርሻውን አኩሪ በሆነ እና ኢትዮጵያዊ በሆነ መልኩ ተወጥቶታል። ውድ የሀገሬ ልጆች በምርጫው የተመዘገበው ድል የአንድ ፓርቲ ድል ብቻ አይደለም፣ የመንግስት ብቻም አይደለም። ድሉ ኢትዮጵያ እንደሀገር፣ ኢትዮጵያዊያን እንደ ህዝብ በአንድነት ያሸነፍነበት መሆኑን ተገንዝበን ይሄን አጋጣሚ እንደ ሀገር በጥንቃቄ ጥቅም ላይ ካዋልነው ብዙ ቀዳዳዎችን መድፈን የሚያስችል ትልቅ እድል መሆኑን መገንዘብ ያሻል።

ለዘመናት እየተከማቹ የመጡትን የፖለቲካ እና የኢኮኖሚ ችግሮች በአንድ ፓርቲ መሪነትና የመጡብንን ችግሮች ተባብረን እና ተደምረን መነሳት ይኖርብናል። አሳታፊ እና አካታች አካሄድ ለመከተል አጥብቀን እንሰራለን። የፖለቲካ ስርአታችን የአሸናፊዎች ፍላጎት ነጸብራቅ ብቻ ሳይሆን የመግባባታችን ውጤት እንዲሆን አበክረን እንሰራለን። በታሪካችን ውስጥ የኦሮሞ አባቶች “ወሊ ገለን አላ ገለን” ይላሉ የተግባባ ከውጪ ይገባ የተነጋገረ የመከረህ ለአንገብጋቢ ችግሮቹ ሃሳባችንን አስታርቀን፤ መከበር የሚገባው ልዩነቶቻችንን አክብረን ህብረብሄራዊነታችንን አጠንክረን ወደ ከፍታ የምንተምበት ጊዜ ይሆናል።

ይህም እንዲሳካ የፖለቲካ ልዩነታችንን በማጥበብ አካታች ብሄራዊ የውይይት መድረክ እናካሂዳለን። የውይይት ሂደቱ ችግሮቻችንን በጠረጴዛ ዙርያ ይፈታሉ ብለን የሚያካትት በፖለቲካ ልሂቃን መካከል አካታችና የሚከናወን በክህደትና በእብሪት ጥቂት ግለሰቦች እኛ የማንቆጣጠራት፣ እንዳሻን የማናሾራት ሀገር ልትኖር አይገባም ብለው የጦርና አውዳሚ መሳርያዎችን ታጥቀው እንደ አይናችን የምንሳሳለትን የሰሜን እዝ ሠራዊታችንን የግፍ ግፍ ፈጸሙ።

በቅርቡ እንኳን የጥሞና እድል ብንሰጠው ከፉ ደጉን ያልለዩ ህጻናት የጦር መሳርያ አስታጥቆ

የህዝብ መገልገያ መሳሪያዎችን እየናደ ትምህርት ቤቶችን እና ጤና ኬላዎችን እያፈረሰ፣ ቤተሰብን እየበተነ፣ ንጹሃንን እየረሸነ አርሶ አደሩ ከልጆቹ ለይቶ የማያያቸውን ከብቶች በጥይት እየገደለ፣ የሃይማኖት ተቋማትን እያረከሰ ኢትዮጵያን ሲወጋት ወደን ሳይሆን ተገደን ህልወናችንን ወደ ማስጠበቅ ዘመቻ መግባታችን ሊታወቅና ሊሰመርበት ይገባል።

ሰልፍ ይዘን ስንዘምትም ሆነ ሰይፍ ይዘን ስንነሳ ዋና ጸባችን ሀገር ሊያፈርሱ፣ ወገን ሊያናክሱ፣ ወንበራቸውን ሊያደላድሉ፣ ኪሳቸውን ሊሞሉ ከተነሱ የሴራ ቁንጮዎች እና ኢትዮጲያ ጠል ሃይሎች ጋር ብቻ መሆኑን ሊታወቅ ይገባዋል። ሀገራችን ከውጪ እና ከውስጥ የገጠሟትን ፈተና ተቋቁማ አለማለፍ እና በቀጣይም ብሄራዊ ጥቅሟን በአስተማማኝ ሁኔታ ማስከበር እንድትችል ትክክለኛ አቋምንና የተሟላ አቅም ያለው የጸጥታ እና ደህንነት ሃይል ትገነባለች።

ክቡራት እና ክቡራን

ሉአላዊነታችንን እና የግዛት አንድነታችንን የሚገዳደረውን ክፉ መሻት በምንከላከልበት በዚህ ሰአት ከአለም አቀፍ ሃይሎች እያስተናገድን ያለነው የዲፕሎማሲ አዝማሚያ ወደኋላ መለስ ብለን የኋላ ታሪካችንን እንድንገልጥ አስገድዶናል። በዘመናት ዲፕሎማሲያዊ ግንኙነታችን ውስጥ ሁለት ተቃራኒ ሃቆች አሳልፈናል። ዛሬም እንደትላንቱ የወዳጅነት ታሪክና በምታደርገው ጉዞ የወዳጆቿን አጋርነት አጥብቃ ትሻለች። ነገርግን ማንኛውም ወዳጅነት የኢትዮጵያን ክብር እና ሉአላዊነት በሚሰዋ መልኩ መሆን የለበትም፤ ሊሆንም አይችልም።

በራችን ለድጋፋቸው፣ ለምክራቸውና ለመልካም ምኞታቸው ሁሌም ክፍት ነው። ውድ አፍሪካዊ እህቶቻችን እና ወንድሞቻችን እኛ ኢትዮጵያዊያን ጥቅሟን የምታስከብር ሀገር እንድትኖረን ከመቼውም ጊዜ በላይ ሃላፊነታችንን ለመወጣት እንጥራለን። በቀጣናችን ከሚያጋጩን ይልቅ የሚያስታርቁን፣ ከሚለያዩን ይልቅ የሚያስተሳስሩን ነገሮች ብዙ ናቸው። የጋሞ አባቶች “ከሰው ጋር አንድ አመት ያላረሰ ለብቻው ሰባት አመት ያርሳል” እንዲሉ እጣ ፈንታችን የተሳሰረ ስለሆነ በቀጠናችን ያለውን ሰብሰብ አድርገን ብንተባበር ያሉብን ችግሮች

በንስር ፊት እንደቆመች ድንቢጥ ይኮሰምናሉ።

ክቡራት እና ክቡራን

የህዳሴ ግድብ እንደሀገር ከሚያስገኝልን ዘርፈ ብዙ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጠቀሜታ ባሻገር ቀጣናዊ ትስስር እና መልካም ጉርብትና የሚያጠናክር ግዙፍ ፕሮጀክት ነው። ለእኛ ለኢትዮጵያዊያን የአባይ ወንዝ ከኢኮኖሚያዊ ፋይዳነቱ ባለፈ ተምሳሌታዊ ትርጉሙ ብዙ ነው። አባይ ማለት የመነሳታችን ምሳሌ በራሳችን አቅም የመቆማችን አምሳያ፣ የህብረታችን ገመድ ነው። አባይ በማይታይ ምትሃቱ ስላስተሳሰረን በማይዳሰስ ሃይሉ ስላበረታን እናም በራስ መተማመናችን ስለጨመረ ከህጻናት እስከ አረጋዊያን፣ ከገጠር እስከ ከተማ፣ ከቆላ እስከ ደጋ፣ ከደቡብ እስከ ሠሜን፣ ከምስራቅ እስከ ምእራብ ሁሉም ኢትዮጵያዊ የእለት ጉርሱን እና ከመንፈቅ ልብሱ ቀንሶ ግድቡን ለማጠናቀቅ ቆርጧል። ግድቡም ይጠናቀቃል።

ጎረቤቶቻችን እና የአባይ ልጆች ይሄንን ሃቃችንን እስከተረዳችሁልን ድረስ በአባይ ወንዝ የጋራ ተጠቃሚነትን በሚያረጋግጥ ቀጣናዊ ትስስርን በሚያጠናክር እና ሁሉንም አሸናፊ በሚያደርግ መልኩ ለመስራት ሁሌም ኢትዮጵያ እና ኢትዮጵያዊያን ዝግጁ መሆናቸውን በድጋሚ ላረጋግጥላችሁ እወዳለሁ።

ውድ የሀገሬ ልጆች

ሀገራችንን በብልጽግና ጎዳና የማሸጋገር እቅዳችንን ወደ ውጤት ለመቀየር ኢኮኖሚያችን በብዙ መልኩ የተዋቀረ ብዝሃ ተዋናይ የሚሳተፉበት እና ብዙዎችን ተጠቃሚ እንዲያደርግ አበክረን እንሰራለን። ኢኮኖሚያችን በግል ዘርፍ ተጠቃሚነትና ገበያን በሚደግፍ መንግስት ኢጋዥነት የሚመራ ተወዳዳሪና ከአለም አቀፍ ንግድና ኢንቨስትመንት ጋር የተሳሰረ ፈጣንና ፍትሃዊ እድገትን የሚያረጋግጥ ለዜጎቻችን በቂ እና አስተማማኝ የስራ እድል የሚፈጥር ምጣኔ ሃብት እንዲሆን እንሰራለን። ባለፉት አመታት የዋጋ ንረትን በመቆጣጠር እና የኑሮ ውድነትን ከመቀነስ አንጻር የተወሰዱት እርምጃዎች የሚፈለገውን ውጤት እንዳላመጡ እና ደሃው የህብረተሰብ ክፍል የችግሩ ገፈት ቀማሽ መሆኑን መንግስት በውል ይገነዘባል።

ይህንን የህብረተሰብ ክፍል ከጫና ለመታደግ በሚቀጥሉት አመታት መንግስት ቅድሚያ ሰጥቶ ከሚሰራቸው የኢኮኖሚ አስተዳደር ስራዎች መካከል አንዱ የዋጋ ንረትን መግታት ይሆናል።

ውድ ኢትዮጵያዊያን

ክቡራት እና ክቡራን

የምናልመውና እንደግብ የምናስቀምጣቸው አላማዎች ትርጉም የሚኖራቸው ባለን የማስፈጸም እና የማድረግ አቅም ነው። አዲሱ መንግስት የሚያስብ፣ የሚያቅድ፣ የሚከውን እንጂ በጎ ብቻ የሚያልም ህልመኛ ሊሆን አይገባም። እስከዛሬ ታቅደው ከጠረጴዛ ላይ ያልወረዱ እና ተጀምረው የተሰናከሉ እቅዶቻችን ባለንበት የምንረግጥ እና አንዳንዴም ወደኋላ የምንሸራተት አድርገውናል። ዜጎቻችን ላይ የሚደርስ ምሬትን እና መንገላታትን ለመቅረፍ ጀምሮ የመጨረስ ባህል በመላበስ በቴክኖሎጂ የታገዘ ግልጽ እና ቀልጣፋ የአገልግሎት አሰጣጥ እና ምቹ የህዝብ አስተዳደር እንዲኖር አበክረን እንሰራለን። በተለይ በተለይ ሌብነትን እንደ ቀላል ድክመት ሳይሆን እንደ ከፍተኛ የህልውና አደጋ በማየት በቀጣዩ አመታት ትልቅ ትኩረት ሰጥተን እንሰራለን።

**ውድ የሀገሬ ልጆች**

ክቡራት እና ክቡራን

ባሳለፍነው የለውጥ ጉዞ ሰፋፊ ስኬቶች የነበሩ ቢሆንም በርካታ ፈተናዎች አጋጥመዋል። ፍትህ ከሰፈነ እርቃናቸውን የሚቀሩ ዲሞክራሲ ከተተከለ እስትንፋስ የማይኖራቸው እኩልነት ጭቆና የሚመስላቸው ቁጥራቸው ቀላል ያልሆነ ግለሰብ እና ቡድኖች አሁንም በሀገራችን ይገኛሉ። ወደፊትም በብልጽግና ጉዟችን ውስጥ ሊደቅኑ የሚችሉት ፈተና ጨርሶ እንደማይጠፋ ልንገነዘብ ይገባል።

ባለፉት ድሎቻችን ላይ አከማችተን፣ ስህተቶቻችንን አርመን በአዳዲስ ሃሳብ በአዳዲስ እይታ ትውልዱን በሚመጥን እይታ፣ ዘመኑን በሚዋጅ ቅኝት ለመጪው ትውልድ የተሻለ ሀገር

ለማስረከብ ተደምረን ቀን ከሌት እንተጋለን። የምናመጣው ለውጥ ተቋማዊ መደላድል እና ህዝባዊ መሰረት ያለው እንዲሆን ስንሰራም ሆነ ለለውጥ ስንንቀሳቀስ አላማችን በጎ ቢሆንም አልፎ አልፎ ማጥፋትና መሳታችን አይቀርም። ሁሌም እንከን የለሽ ስራ እንሰራለን የሚል መታበይ የለንም። ነገርግን ከኛ በኋላ የሚመጡትን እና የሳትነውን የሚያርሙ የጀመርነውን እንደሚያጎለብቱ ሙሉ እምነትና ተስፋ አለን። ቀጣዮቹ አምስት አመታት ባሳለፍነው መልካም ጉዞ የታዩ እንቅስቃሴዎች ተጠናክረው የሚቀጥሉበትና ፍሬ የሚያፈሩበት ኢትዮጵያም እንደ ትላንቱ ከፍ ብላ የምትታይበት ጊዜ ይሆናል።

በመጪዎቹ አመታት አቅማችንን በሚገባ ተጠቅመን አንድነታችንን የሚፈታተነውን ጥላቻ እንደ ህዳር አህያ ሃብት ያለው ሁሉ የፈለኳችሁም ካልጫንኳችሁ እያለን እንዲመኝ ያደረገውን ድህነታችንን እና ለጠላት ተጋላጭ የሚያደርገንን የውስጥ እና የውጪ ሁኔታ ተገዳድረን ድል ለማድረግ እንተጋለን። ጥላቻን በመግባባት ጭቆናን በዲሞክራሲ ድህነትን በብልጽግና ለጠላት ተጋላጭነታችንን በጠንካራ ብሄራዊ የጸጥታ ሃይል ለመተካት ሁላችንም በአንድነት በኢትዮጵያዊ መንፈስ ልንረባረብ ይገባል።

የተከበራችሁ ኢትዮጵያዊያን

በመጪዎቹ አመታት ኢትዮጵያ የሚለው ስም ከአይበገሬነት ጋር የተሳሰረ መሆኑን የምናስመሰክርበት እንደሚሆን አልጠራጠርም። ፈተናዎች እንደሚያስፈነጥሩን እንጂ አስረው እንደማያስቀሩን የምናሳይበት ጊዜ ይሆናል። መጪዎቹ አመታት ኢትዮጵያ ሰንኮፏን የምትነቅልበት፣ ቁስሏን የምትታከምበት፣ ህብረ ብሄራዊ አንድነቷን በአለት ላይ የምታጸናበት ገናናው ስሟን በሰፊው አለም ላይ እንዲናኝ የምታደርግበት ዘመን ይሆናል።

በመጪዎቹ አመታት የድህነት አከርካሪ፣ የጥላቻ አንገት፣ የመከፋፈል ወገብ፣ የመፈናቀል ወሽመጥ፣ የመገዳደል ክንድ፣ በከንቱ የመወነጃጀል ጉልበት በሀገር ልጆች ብርቱ ትብብር ይሰበራል። አባቶቻችን “አከዱሪፍ ሃርቀቱሪቲ ነፈኒ” እንደሚሉት “የቆሸሸ እጅ እና የትላንት ደካማ ማንነት መጥራቱ አይቀርም” እንደሚሉት ፈተናዎች እንደ ወርቅ አንጥረው ያበሯት ሀገር የአቧራው ብዛትና የቆሻሻው ክምር ወርቅነቷን የማይለውጣት ኢትዮጵያ ትላንት ነበረች ዛሬም አለች፣ ነገ አቧራዋን አራግፋ እና የቆሻሻዋን ክምር ንዳ ስትነሳ ያኔ ከፊቷ

የሚቆም ምንም አይነት ምድራዊ ሃይል አይኖርም። ለዚህ ደግሞ አደራ አለብን። ዝናቡ እና ብርዱ ሳይበግራቸው ቁር እና ጸሃይ ሳያማርራቸው በለሊት እንቅልፍ ሳይሰንፉ ኢትዮጵያን ከመረጡ ዜጎቻችን የተሰጠ አደራ፣ ኢትዮጵያንም ለኢትዮጵያ መዳን ሲሉ ደማቸውን ካፈሰሱ ህይወታቸውን ከገበሩ ውድ የሀገር ልጆች የተጣለብን አደራ ሌት ከቀን ስለኢትዮጵያ ሰላም በእንባ የሚማልዱ እናቶች የሰጡን አደራ እንዲሁም ከወዝ እና ላባቸው በጨለፉት ትጋትና ሀገር ከሚያገለግሉ እናቶች የተላለፈልን አደራ እኛን ተስፋ አድርገው በኮልታፋ አንደበታቸው፣ ስለኢትዮጵያ ከሚዘምሩ ልጆቻችን የተሰጠን አደራ አለብን። አዎ ከባድ አደራ አለብን። ስለዚህ በቀጣይ አመታት የተጣለብንን አደራ ለመጠበቅ እና በላቀ ብቃት ለማስፈጸም እንደማናቀላፋ ያለንን ሁሉ ያለስስት እንደምንሰጥ ለአፍታ እንደማንዘናጋ በዚህ አጋጣሚ ቃላችንን እንደምናድስ በመንግስታችን እና በፓርቲያችን ስም በድጋሚ ላረጋግጥላችሁ እወዳለሁ።

አትጠራጠሩ በቀጣዩ አመታት ተስፋችንን አጎልብተን፣ ስጋቶቻችንን ቀርፈን፣ እድሎቻችንን አሟጠን፣ ፈታኞቻችንን አሸንፈን ሀገራችንን በብልጽግና ጎዳና የምናስኬድበት ዘመን ይሆናል። በኢትዮጵያ ልክ በህዝቧ ልክ መታመን ሌብነትን መጠየፍ ሀገር እና ህዝብን መውደድ በቅንነት ማገልገል፣ ህዝብን ሳይለዩ ኢትዮጵያን ከፍ ማድረግ እንዳይወሰድብን በጸሎታችሁ እንድታግዙን ፈጣሪም እንዲረዳን በታላቅ ትህትና እማጸናችኋለሁ።

የተከበሩ ፕሬዝዳንት ሳህለወርቅ ዘውዴ፣

የተከበሩ ፕሬዳንት ዩዌሪ ካጎታ ሙሴቪኒ፣

የተከበሩ ፕሬዝዳንት እስማኤል አማር ጌሌ፣

የተከበሩ ፕሬዝዳንት ሳልቫኪር ማየርዲት፣

የተከበሩ ፕሬዝዳት ማኪሳ፣

የተከበሩ ፕሬዝዳንት ኡሁሩ ኬንያታ፣

የተከበሩ ፕሬዝዳንት ሙሃመድ ቡሃሪ፣

የተከበሩ ፕሬዝዳንት ሞሃመድ አብዱላሂ ፎርማጆ፣

የተከበሩ የአፍሪካ ህብረት ሊቀመንበር ሙሳ ፋኪ መሃመት፣

የተከበሩ የኮንጎ ጠቅላይ ሚኒስትር ጂሚ ሼል ዛማል ኩንዴ፣

የተከበሩ ዶክተር ወርቅነህ ገበየሁ የኢጋድ ዋና ጸሐፊ፣

የተከበሩ ኦሊሴጎን ኦባሳንጆ የቀድሞው የናይጄሪያ ፕሬዝዳንት፣

የተከበሩ ራማታን ላማምራ የአልጄሪያ የውጪ ጉዳይ ሚኒስትር፣

የተከበሩ ሃይለማርያም ደሳለኝ የቀድሞው የኢፌዲሪ ጠቅላይ ሚኒስትር፣

የተከበሩ ዶ/ር ሙላቱ ተሾመ የቀድሞው የኢፌዲሪ ፕሬዝዳንት፣

የተከበራችሁ ኢትዮጵያዊያን፣ ክቡራት እና ክቡራን

በኢትዮጵያ ረጅም የአስተዳደር ዘመን ለመጀመሪያ ጊዜ ግልጽና ተአማኒ ምርጫ በማካሄድ

ህዝባዊ ቅቡልነት ያገኘ መንግስት በምንመሰርትበት ታሪካዊ ቀን ከፊታችሁ ቆሜ ንግግር ለማድረግ ያበቃኝን ፈጣሪ አስቀድሜ ላመሰግን እወዳለሁ።

በዚህ ወሳኝና ፈታኝ ወቅት በሀገራችን እና በህዝቦቿ ላይ የተቃጣውን የህልውና አደጋ ለመቀልበስ በዱር በገደሉ፣ በቁር በሃሩሩ ከፍተኛ ተጋድሎ እያደረጉ ለሚገኙት ለጀግናው የመከላከያ ሰራዊታችን፣ ለመላው የጸጥታ አካላት እና ለህዝባዊ ሃይላችን ያለኝን ታላቅ አክብሮት እና ምስጋና ልገልጽ እወዳለው። እናንተ የቁርጥ ቀን ልጆች ጀግና የምታከብረው ኢትዮጵያ ውለታችሁን መቼም ቢሆን አትረሳውም።

ሀገራችን እንደቀደሙ ጀግኖቿ ለዚህ ትውልድ ፈርጦችም ትልቅ ክብር እና ሞገስ ትሰጣለች የምትከፍለው መስዋእትነት በታሪክ ማህደር እና ብራና ላይ በደማቅ ታትሞ ይኖራል። እልፍ ጀግኖቻችን እልፍ ጀግኖችን ካፈራው አብራክ በመፈጠሬ ሁሌም እንድኮራ ከሚያደርጉኝ መካከል የህዝባችን ጽናት፣ አይበገሬነት እና አትንኩኝ ባይነት ቀዳሚውን ስፍራ ይይዛል።

ህዝባችን በየትኛውም ዘመን የእናት ሀገር ድም በሉአላዊነቱ የማይደራደር መሆኑ እሙን ነው። ከዚህም የተነሳ ህዝባችን መተማመኛችን፣ ጦር እና ጋሻችን፣ ተዋጊ ደጀናችን ለሆነው ለኢትዮጵያ ህዝብ ያለኝን ክብር እና አድናቆት በታላቅ ትህትና ልገልጽ እወዳለሁ። አቅም ባነሳት ጊዜ ምርኩዝ ለሆናችኋት፣ በመላው አለም ለምትኖሩ ኢትዮጵያዊያን እና የኢትዮጵያ ወዳጆች ሁሉ በህዝብ እና መንግስት ስም የከበረ ምስጋናዬን ላቀርብ እወዳለሁ።

በቀደመ ገናና ታሪኳ በመርከብ ትመሰላለች። በታላላቆቹ ቅዱሳን መጻህፍት እንደተነገረው መርከቧ ኢትዮጵያ የፍትህ፣ የእኩልነት፣ የነጻነት እና ነበር ዥንጉርጉርነቱን ኢትዮጵያዊ መልኩን አይቀይርም የተባለለት ጃንደረባን ያፈራች ሀገር ነች። ነብዩ መሃመድ አለይሷት እና የመጀመሪያው ሙአዚን ቢላል መነሻ የሆነች ሀገር ናት ኢትዮጵያ።

ጸሃፊ ፔድሮ አልቫሬዝ ኢትዮጵያዊያን የመሰከረልን ድንቅ ህዝብ ነን። ኢቱዮጵያ በኤዞፕ ተረቶች እና ....ብልህ ህዝቦች ብሎ የጻፈላት ድንቅ ሀገር ናት ኢትዮጵያ። የዘመናችን አርኪዮሎጂስቶች ምድረ ቀደምትነቷን ያረጋገጡ ለአፍሪካ ነጻነት ከውስን ሃብቷ ሳትሰስት

ካላት ላይ ቀንሳ የሰጠች፣ በጥቁር ህዝቦች መብት ትግል ውስጥ ትልቅ ቦታ ከነበራቸው ማርከስ ጋርቬይ እና ዱ ቦይስ ልቦና ውስጥ ጎልታ የተሳለች ድንቅ ሀገር ናት ኢትዮጵያ።

የተወደሰች የእውነት እና የአፍሪካዊት ሞገስ እና ፈርጥ የሆነች ናት ኢትዮጵያ። አንድም ከታሪክ መዝገብ ገልጠን የአባቶቻችንን ገድል በማጣቀስ ወደውጤ በመቀየር መቻላችንን እና ኢትዮጵያ መሆናችንን .....ከኩራት ስሜት ጋር ሲነጻጸር ነገ ላይ የሚጠብቀን ተስፋ ቢበልጥ እንጂ አያንስም ዋናው ጥያቄ ተስፋውን አይተን እውን ለማድረግ ዋናው ጥያቄ ቁርጠኞች ነን የሚለውን ጥያቄ ደጋግመን ራሳችንን መጠየቅ ነው።

ኢትዮጵያ የምትበለጽገው እኛ ሀገራችንን ለመለወጥ በፈለግነው መጠን እና የጋራ ራእይ በሰነቅንበት ልክ ብቻ ነው። ኢትዮጵያ ካዘመመችበት ቀና የምትልበት ጊዜ ጊዜው አሁን ነው። ይሄ ለማሳካት የዛሬ ህያው ኢትዮጵያውያን ታላቅ አደራ ተጥሎብናል። ይሄንን አደራ ተቀብለን የዘመናት ድምር ውጤቶችን አበርክተን ኢትዮጵያ የተባለችውን መርከብ

ሞተሯን አድሰን፣ ማእበል ወጀቡ ፍጹም እንዳያናውጣት አንጸን፣ መልህቋን አንስተን ጉዞዋን ማስጀመር የኛ ድርሻ ሲሆን ለዘለቄታው በጽናት እንድትጓዝ ማድረግ ደግሞ የየትውልዱ የኢትዮጵያ ልጆች አደራ ይሆናል። ውድ ኢትዮጵያዊ መንግስቷን ለመትከል ከፍተኛ ተጋድሎ አድርጋለች። ተስፋ እና ስጋት እድል እና ፈተና እየተፈራረቁባት አያሌ ውጣ ውረዶችን፣ ፍትሃዊ ተጠቃሚነት ጥያቄዎች ከአርሶ አደር እስከ እስከ አርብቶ አደር፣ ከከተሜ እስከ ባለሀገር፣ ከመለዮ ለባሽ እስከ ምሁር፣ ከወጣት እስከ ጎልማሳ፣ ከልሂቅ እስከ ደቂቅ መላው የሀገራችን ህዝቦች የተሳተፉበት እና መስዋእትነት የከፈሉበት የዘመናት የህዝብ ጥያቄ ነበር።

ምንም እንኳን ስድስተኛው ሀገራዊ ምርጫ ከእንከኖች የጸዳ እና የምኞታችንን ያህል እጅግ የተሳካ ነበር ባይባልም እጅግ የተሳካ ምእራፍን ከፍቷል፣ አንድ እርምጃም ወደፊት አራምዶናል። ስልጣን ከዘር ሃረግ ወይንም ከጠብመንጃ አፈሙዝ አልያም በሴራ እና ተንኮል ሳይሆን በእውነተኛ የህዝብ ድምጽ ከምርጫ ኮሮጆ ብቻ የሚመነጭ በማድረግ የህዝብን የፖለቲካ ሉአላዊ  የስልጣን ባለቤትነት ያረጋገጥንበትዘመን ላይ ደርሰናል።

ህዝባችን በልዩ ልዩ ሰው ሰራሽ ግጭቶች ሳይረበሽ እንደኮቪድ ወረርሺኝ ባሉ ተፈጥሮአዊ

አደጋ ሳይበገር በሀገራዊ ሉአላዊነት ላይ በተጋረጠው አደጋ ሳይረታ ከውጪ ሃይሎች በሚደርስበት ተጽእኖ ሳይንበረከክ በሂደቱ የገጠሙትን እንከኖች ሁሉ ተጋፍጦ የዜግነት ድርሻውን አኩሪ በሆነ እና ኢትዮጵያዊ በሆነ መልኩ ተወጥቶታል። ውድ የሀገሬ ልጆች በምርጫው የተመዘገበው ድል የአንድ ፓርቲ ድል ብቻ አይደለም፣ የመንግስት ብቻም አይደለም። ድሉ ኢትዮጵያ እንደሀገር፣ ኢትዮጵያዊያን እንደ ህዝብ በአንድነት ያሸነፍነበት መሆኑን ተገንዝበን ይሄን አጋጣሚ እንደ ሀገር በጥንቃቄ ጥቅም ላይ ካዋልነው ብዙ ቀዳዳዎችን መድፈን የሚያስችል ትልቅ እድል መሆኑን መገንዘብ ያሻል።

ለዘመናት እየተከማቹ የመጡትን የፖለቲካ እና የኢኮኖሚ ችግሮች በአንድ ፓርቲ ችግሮች,,,,,, እና የመጡብንን ችግሮች ተባብረን እና ተደምረን መነሳት ይኖርብናል። አሳታፊ እና አካታች አካሄድ ለመከተል አጥብቀን እንሰራለን። የፖለቲካ ስርአታችን የአሸናፊዎች ፍላጎት ነጸብራቅ ብቻ ሳይሆን የመግባባታችን ውጤት እንዲሆን አበክረን እንሰራለን። በታሪካችን ውስጥ

የኦሮሞ አባቶች “ወሊ ገለን አላ ገለን” ይላሉ የተግባባ ከውጪ ይገባ የተነጋገረ የመከረህ ለአንገብጋቢ ችግሮቹ መፍትሄ አስታርቀን መከበር የሚገባው ልዩነቶቻችንን አክብረን ህብረብሄራዊነታችንን አጠንክረን ወደ ከፍታ የምንተምበት ጊዜ ይሆናል።

ይህም እንዲሳካ የፖለቲካ ልዩነታችንን በማጥበብ አካታች ብሄራዊ የውይይት መድረክ እናካሂዳለን የውይይት ሂደቱ ችግሮቻችንን በጠረጴዛ ዙርያ ይፈታሉ ብለን የሚያካትት በፖለቲካ ልሂቃን መካከል አካታች እና የሚከናወን በክህደት እና በእብሪት ጥቂት ግለሰቦች እኛ የማንቆጣጠራት፣ እንዳሻን የማናሾራት ሀገር ልትኖር አይገባም ብለው የጦር እና አውዳሚ መሳርያዎችን ታጥቀው እንደ አይናችን የምንሳሳለትን የሰሜን እዝ ሠራዊታችንን የግፍ ግፍ ፈጸመበት።

በቅርቡ እንኳን የጥሞና እድል ብንሰጠው ክፉ ደጉን ያልለዩ ህጻናት የጦር መሳርያ አስታጥቆ የህዝብ መገልገያ መሳርያዎችን እየናደ ትምህርት ቤቶችን እና ጤና ኬላዎችን እያፈረሰ፣ ቤተሰብን እየበተነ፣ ንጹሃንን እየረሸነ አርሶ አደሩ ከልጆቹ ለይቶ የማያያቸውን ከብቶች በጥይት እየገደለ፣ የሃይማኖት ተቋማትን እያረከሰ ኢትዮጵያን ሲወጋት ወደን ሳይሆን ተገደን

ህልወናችንን ወደ ማስጠበቅ ዘመቻ መግባታችን ሊታወቅ እና ሊሰመርበት ይገባል።

ሰልፍ ይዘን ስንዘምትም ሆነ ሰይፍ ይዘን ስንነሳ ዋና ጸባችን ሀገር ሊያፈርሱ፣ ወገን ሊያናክሱ፣ ወንበራቸውን ሊያደላድሉ፣ ኪሳቸውን ሊሞሉ ከተነሱ የሴራ ቁንጮዎች እና ኢትዮጲያ ጠል ሃይሎች ጋር ብቻ መሆኑን ሊታወቅ ይገባዋል። ሀገራችን ከውጪ እና ከውስጥ የገጠሟትን ፈተና ተቋቁመው አለማለፍ እና በቀጣይም ብሄራዊ ጥቅሟን በአስተማማኝ ሁኔታ ማስከበር እንድትችል ትክክለኛ አቋሟን እና የተሟላ አቅም ያለው የጸጥታ እና ደህንነት ሃይል ትገነባለች።

ከቡራት እና ከቡራን ሉአላዊነታችንን እና የግዛት አንድነታችንን የሚገዳደረውን ክፉ መሻት በምንከላከልበት በዚህ ሰአት ከአለም አቀፍ ሃይሎች እያስተናገድን ያለነው የዲፕሎማሲ አዝማሚያ ወደ ኋላ መለስ ብለን የኋላ ታሪካችንን እንድንገልጥ አስገድዶናል። በዘመናት

ዲፕሎማሲያዊ ግንኙነታችን ውስጥ ሁለት ተቃራኒ ሃቆች አሳልፈናል። ዛሬም እንደትላንቱ የወዳጅነት ታሪክና የምታደርገው ጉዞ የወዳጆቿን አጋርነት አጥብቃ ትሻለች። ነገርግን ማንኛውም የወዳጅነት የኢትዮጵያን ክብር እና ሉአላዊነት በሚሰዋ መልኩ መሆን የለበትም፤ ሊሆንም አይችልም።

በራችን ለድጋፋቸው፣ ለመከራቸው እና ለመልካም ምኞታቸው ሁሌም ክፍት ነው። ውድ አፍሪካዊ እህቶቻችን እና ወንድሞቻችን እኛ ኢትዮጵያዊያን ለ....ብሎም ለአለም ጥቅሟን የምታስከብር ሀገር እንድትኖረን ከመቼውም ጊዜ በላይ ሃላፊነታችንን ለመገንባት እንጥራለን። በቀጠናችን ከሚያጋጩን ይልቅ የሚያስታርቁን ከሚለያዩን ይልቅ የሚያስተሳስሩን ነገሮች ብዙ ናቸው። የጋሞ አባቶች "ከሰው ጋር አንድ አመት ያላረሰ ለብቻው ለብቻው ሰባት አመት ያርሳል" እንዲሉ እጣ ፈንታችን የተሳሰረ ስለሆነ በቀጠናችን ያለውን ሰብሰብ አድርገን ብንተባበር ያሉብን ችግሮች በንስር ፊት እንደቆመች ድንቢጥ ይኮሰምናሉ።

ከቡራት እና ከቡራን የህዳሴ ግድብ እንደሀገር ከሚያስገኝልን ዘርፈ ብዙ ኢኮኖሚያዊ እና ማህበራዊ ጠቀሜታ ባሻገር ቀጠናዊ ትስስር እና መልካም ጉርብትና የሚያጠናክር ግዙፍ ፕሮጀክት ነው። ለእኛ ለኢትዮጵያዊያን የአባይ ወንዝ ከኢኮኖሚያዊ ፋይዳነቱ

ባለፈ ተምሳሌታዊ ትርጉሙ ብዙ ነው። አባይ ማለት የመነሳታችን ምሳሌ በራሳችን አቅም የመቆማችን አምሳያ፣ የህብረታችን ገመድ ነው። አባይ በማይታይ ምትሃቱ ስላስተሳሰረን በማይዳሰስ ሃይሉ ስላበረታን እናም በራስ መተማመናችን ስለጨመረ ከህጻናት እስከ አረጋዊያን፣ ከገጠር እስከ ከተማ፣ ከቆላ እስከ ደጋ፣ ከደቡብ እስከ ሠሜን፣ ከምስራቅ እስከ ምእራብ ሁሉም ኢትዮጵያዊ የእለት ጉርሱን እና ከመንፈቅ ልብሱ ቀንሶ ግድቡን ለማጠናቀቅ ቆርጧል። ግድቡም ይጠናቀቃል።

ጎረቤቶቻችን እና የአባይ ልጆች ይሄንን ሃቃችንን እስከተረዳችሁልን ድረስ በአባይ ወንዝ የጋራ ተጠቃሚነትን በሚያረጋግጥ ቀጠናዊ ትስስርን በሚያጠናክር እና ሁሉንም አሸናፊ በሚያደርግ መልኩ ለመስራት ሁሌም ኢትዮጵያ እና ኢትዮጵያዊያን ዝግጁ መሆናቸውን በድጋሚ ላረጋግጥላችሁ እወዳለሁ።

ውድ የሀገሬ ልጆች ሀገራችን በብልጽግና ጎዳና የማሻጋገር እቅዳችንን ወደ ውጤት ለመቀየር ኢኮኖሚያችን በብዙ መልኩ የተዋቀረ ብዝሃ ተዋናይ የሚሳተፉበት እና ብዙዎችን ተጠቃሚ እንዲያደርግ አበክረን እንሰራለን። ኢኮኖሚያችን በግል ዘርፍ ተጠቃሚነት እና ገበያን በሚደግፍ መንግስት አጋዥነት የሚመራ ተወዳዳሪ እና ከአለም አቀፍ ንግድ እና ኢንቨስትመንት ጋር የተሳሰረ ፈጣን እና ፍትሃዊ እድገትን የሚያረጋግጥ ለዜጎቻችን በቂ እና አስተማማኝ የስራ እድል የሚፈጥር ምጣኔ ሃብት እንዲሆን እንሰራለን። ባለፉት አመታት የዋጋ ንረትን በመቆጣጠር እና የኑሮ ውድነትን ከመቀነስ አንጻር የተወሰዱት እርምጃዎች የሚፈለገውን ውጤት እንዳላመጡ እና ደሃው የህብረተሰብ ክፍል የችግሩ ገፈት ቀማሽ መሆኑን መንግስት በውል ይገነዘባል። ይህንን የህብረተሰብ ክፍል ከጫና ለመታደግ በሚቀጥሉት አመታት መንግስት ቅድሚያ ሰጥቶ ከሚሰራቸው ኢኮኖሚ አስተዳደር ስራዎች መካከል አንዱ የዋጋ ንረትን መግታት ይሆናል።

ውድ ኢትዮጵያዊያን ክቡራት እና ክቡራን የምናልመው እና እንደግብ የምናስቀምጣቸው አላማዎች ትርጉም የሚኖራቸው ባለን የማስፈጸም እና የማድረግ አቅም ነው። አዲሱ መንግስት የሚያስብ፣ የሚያቅድ፣ የሚከውን እንጂ በጎ ብቻ የሚያልም ህልመኛ ሊሆን

አይገባም። እስከዛሬ ታቅደው ከጠረጴዛ ላይ ያልወረዱ እና ተጀምረው የተሰናከሉ እቅዶቻችን ባለንበት የምንረግጥ እና አንዳንዴም ወደኋላ የምንሸራተት አድርገውናል። ዜጎቻችን ላይ የሚደርስ ምሬትን እና መንገላታትን ለመቅረፍ ጀምሮ የመጨረስ ባህል በመላበስ በቴክኖሎጂ የታገዘ ግልጽ እና ቀልጣፋ የአገልግሎት አሰጣጥ እና ምቹ የህዝብ አስተዳደር እንዲኖር አበክረን እንሰራለን።

በተለይ በተለይ ሌብነትን እንደ ቀላል ድክመት ሳይሆን እንደ ከፍተኛ የህልውና አደጋ በማየት በቀጣዩ አመታት ትልቅ ትኩረት ሰጥተን እንሰራለን። ውድ የሀገሬ ልጆች ክቡራት እና ክቡራን ባሳለፍነው የለውጥ ጉዞ ሰፋፊ ስኬቶች የነበሩ ቢሆንም በርካታ ፈተናዎች አጋጥመዋል። ፍትህ ከሰፈነ እርቃናቸውን የሚቀሩ ዲሞክራሲ ከተተከለ እስትንፋስ የማይኖራቸው እኩልነት ጭቆና የሚመስላቸው ቁጥራቸው ቀላል ያልሆነ ግለሰብ እና

ቡድኖች አሁንም በሀገራችን ይገኛሉ። ወደፊትም በብልጽግና ጉዞአችን ውስጥ ሊደቅኑ የሚችሉት ፈተና ጨርሶ እንደማይጠፋ ልንገነዘብ ይገባል።

ባለፉት ድሎቻችን ላይ አከማችተን፣ ስህተቶቻችንን አርመን በአዳዲስ ሃሳብ በአዳዲስ እይታ ትውልዱን በሚመጥን እይታ፣ ዘመኑን በሚዋጅ ቅኝት ለመጪው ትውልድ የተሻለ ሀገር ለማስረከብ ተደምረን ቀን ከሌት እንተጋለን። የምናመጣው ለውጥ ተቋማዊ መደላድል እና ህዝባዊ መሰረት ያለው እንዲሆን ስንሰራም ሆነ ለለውጥ ስንንቀሳቀስ አላማችን በጎ ቢሆንም አልፎ አልፎ ማጥፋት እና መሳታችን አይቀርም። ሁሌም እንከን የለሽ ስራ እንሰራለን የሚል መታበይ የለንም። ነገርግን ከኛ በኋላ የሚመጡትን እና የሳትነውን የሚያርሙ የጀመርነውን እንደሚያጎለብቱ ሙሉ እምነት እና ተስፋ አለን። ቀጣዮቹ አምስት አመታት ባሳለፍነው መልካም ጉዞ የታዩ እንቅስቃሴዎች ተጠናክረው የሚቀጥሉበት እና ፍሬ የሚያፈሩበት ኢትዮጵያም እንደ ትላንቱ ከፍ ብላ የምትታይበት ጊዜ ይሆናል።

በመጪዎች አመታት አቅማችንን በሚገባ ተጠቅመን አንድነታችንን የሚፈታተነውን ጥላቻ እንደ ህዳር አህያ ሃብት ያለውን ሁሉ የፈለኳችሁም ካልጫንኳችሁ እያለን እንዲመኝ ያደረገውን ድህነታችንን እና ለጠላት ተጋላጭ የሚያደርገንን የውስጥ እና የውጪ ሁኔታ

ተገዳድረን ድል ለማድረግ እንተጋለን። ጥላቻን በመግባባት ጭቆናን በዲሞክራሲ ድህነትን በብልጽግና ለጠላት ተጋላጭነታችንን በጠንካራ ብሄራዊ የጸጥታ ሃይል ለመተካት ሁላችንም በአንድነት በኢትዮጵያዊ መንፈስ ልንረባረብ ይገባል።

የተከበራችሁ ኢትዮጵያዊያን በመጨረሻም አመታት ኢትዮጵያ የሚለው ስም ከአይበገሬነት ጋር የተሳሰረ መሆኑን የምናስመሰክርበት እንደሚሆን አልጠራጠርም። ፈተናዎች እንደሚያስፈነጥሩን እንጂ አስረው እንደማያስቀሩን የምናሳይበት ጊዜ ይሆናል። መጪዎቹ አመታት ኢትዮጵያ ሰንኮፏን የምትነቅልበት፣ ቁስሏን የምታክምበት፣ ህብረ ብሄራዊ አንድነቷን በአለት ላይ የምታጸናበት ገናናው ስሟን በሰፊው አለም ላይ እንዲናኝ የምታደርግበት ዘመን ይሆናል።

በመጪዎቹ አመታት የድህነት አከርካሪ፣ የጥላቻ አንገት፣ የመከፋፈል ወገብ፣ የመፈናቀል ወሽመጥ፣ የመገዳደል ክንድ፣ በከንቱ የመወነጃጀል ጉልበት በሀገር ልጆች ብርቱ ትብብር ይሰበራል። አባቶቻችን አከዱሪፍ ሃርቀቱሪቲ ነፈኒ እንደሚሉት የቆሸሸ እጅ እና የትላንት ደካማ ማንነት መጥራቱ አይቀርም እንደሚሉት ፈተናዎች እንደ ወርቅ አንጥረው ያበሯት ሀገር የአቧራው ብዛት እና የቆሻሻው ክምር ወርቅነቷን የማይለውጣት ኢትዮጵያ ትላንት ነበረች ዛሬም አለች፣ ነገ አቧራዋን አራግፋ እና የቆሻሻዋን ክምር ንዳ ስትነሳ ያኔ ከፊቷ የሚቆም ምንም አይነት ምድራዊ ሃይል አይኖርም። ለዚህ ደግሞ አደራ አለብን። ዝናቡ እና ብርዱ ሳይበግራቸው ቁር እና ጸሃይ ሳያማርራቸው በለሊት እንቅልፍ ሳይሰንፉ ኢትዮጵያን ከመረጡ ዜጎቻችን የተሰጠ አደራ ኢትዮጵያንም ለኢትዮጵያ መዳን ሲሉ ደማቸውን ካፈሰሱ ህይወታቸውን ከገበሩ ውድ የሀገር ልጆች የተጣለብን አደራ ሌት ከቀን ስለኢትዮጵያ ሰላም በእንባ የሚማልዱ እናቶች የሰጡን አደራ እንዲሁም ከወዝ እና ላባቸው በጨለፉት ትጋት እና ሀገር ከሚያገለግሉ እናቶች የተላለፈልን አደራ እኛን ተስፋ አድርገው በኮልታፋ አንደበታቸው ስለኢትዮጵያ ከሚዘምሩ ልጆቻችን የተሰጠን አደራ አለብን። አዎ ከባድ አደራ አለብን ስለዚህ በቀጣይ አመታት የተጣለብንን አደራ ለመጠበቅ እና በላቀ ብቃት ለማስፈጸም እንደማናንቀላፋ ያለንን ሁሉ ያለስስት እንደምንሰጥ ለአፍታ እንደማንዘናጋ በዚህ አጋጣሚ ቃላችንን እንደምናድስ በመንግስታችን እና በፓርቲያችን ስም በድጋሚ ላረጋግጥላችሁ እወዳለሁ።

አትጠራጠሩ በቀጣዩ አመታት ተስፋችንን አጎልብተን፣ ስጋቶቻችንን ቀርፈን፣ እድሎቻችንን አሚጠን፣ ፈታኞቻችንን አሸንፈን ሀገራችንን በብልጽግና ጎዳና የምናስኬድበት ዘመን ይሆናል። በኢትዮጵያ ልክ በህዝቧ ልክ መታመን ሌብነትን መጠየፍ ሀገር እና ህዝብን መውደድ በቅንነት ማገልገል፣ ህዝብን ሳይለዩ ኢትዮጵያን ከፍ ማድረግ እንዳይወሰድብን በጸሎታችሁ እንድታግዙን ፈጣሪም እንዲረዳን በታላቅ ትህትና እማጸናችኋለሁ።

**ኢትዮጵያ በልጆቿ ጥረት ታፍራ እና ተከብራ ለዘለአለም ትኑር ፈጣሪ ኢትዮጵያ እና ህዝቦቿን ይባርክ! አመሰግናለሁ! ገለቶማ!**






acer

## በአዲሱ መንግሥት የተካተቱ ሚኒስትሮች እና ሚኒስትር ዴኤታዎች የሥራ ማስጀመሪያ ስብሰባ ላይ ያደረጉት ንግግር።

ታላቅ ህዝብ፣ ታላቅ ሀገር ለማገልገል እድል ስላገኛችሁ፣ እድል ስላገኘን እንኳን ደስ አላችሁ፣ እንኳን ደስ አለን ለማለት እፈልጋለሁ።

እንግዲህ "እድል ነው ወይ? ኢትዮጵያን ማገልገል" የሚል ጥያቄ አንዳንድ ሰዎች በአእምሯቸው ሊፈጠር ይችላል። ከመቶ ሚሊየን ህዝብ በላይ ባለበት ሀገር መቶ የማንሞላ ሰዎች ስንመረጥ ከአንድ ሚሊየን አንድ ሰው ነህ እና ከሌላው ህዝብ ስለምትበልጥ ነው  የሚል የተሳሳተ ግምት እንዳይዛችሁ አደራ በጣም ብዙ እድል ያጡ ግን ብቃት ያላቸው የተፈጠሩ ሰዎች አሉ። እድል ነው። ይህን እድል በምን ያክል ደርዝ እንጠቀምበታለን የሚለው የየግለሰቡ ውሳኔ ቢሆንም ታላቅ በህይወት ውስጥ አልፎ አልፎ ብቻ የሚገኝ እድል ነው የገጠመን። ይሄን መጠቀምና የሚያስፈልገውን ነገር ማድረግ ከሁላችንም የሚጠበቅ ይሆናል።

እዚህ ያለን ሚኒስትሮች፣ ሚኒስትር ዴኤታዎች እያንዳንዳችን ታሪክ የምንጽፍበት ባዶ ቼክ ተሰጥቶናል። አንዳንዶቻችን በቢሊየን፣ አንዳንዶቻችን በሚሊየን፣ አንዳንዶቻችን ደግሞ በሺህ ምናልባት አንዳንዶቻችን በመቶም እንጽፋለን። በጻፍነው ቁጥር ልክ የሚጸና ካፒታል እንዲኖር ይሆናል። ሰፋ ያለ በርከት ያለ ካፒታል ኢንቨስት ያደረጉ ሰዎች ለልጆቻቸው ለልጅ ልጆቻቸው ይተርፋሉ አስር ብር፣ ሃያ ብር፣ መቶ ብር፣ የምትጽፉ ካላችሁ ደግሞ ልክ ዛሬ ላይ ስትሻሩ በማግስቱ የሚረሳ ይሆናል። ዋናው

በዚህ ድል ውስጥ በምን ያክል ልክ ነው ካፒታል የምናቆየው ለኛ፣ ለልጆቻችን፣ ከዛም አልፎ ለብዙ ትውልድ እንዲሸጋገር አድርጎ የሚጻፍ ቼክ ተሰጥቶናል። በዚህ ቼክ ላይ በተገቢው ቦታ ላይ መጻፍ፣ ስርዝ ድልዝ እንዳይኖር ማድረግ የኛ ሃላፊነት ይሆናል። በስም ቦታ ቁጥር፣ በቁጥር ቦታ ስም ብትጽፉ ወይንም ስርዝ ድልዝ ካለው ንግድ ባንክ ስትሄዱ አይቀበሏችሁም። ቼክ በጣም ውድ ነገር ነው በጥራት በትክክለኛው ቦታ መስፈር ያለበት ቦታ ላይ ካልሰፈረ ቼኩ ቮይድ ይሆናል፤ ጥቅም ላይ አይውልም። ይሄን በትክክል መጠቀም የሚያስፈልገንን ቼክ እያንዳንዱ ግለሰብ በወሰነው አሃዝ ልክ ካስቀመጠ በኋላ ካፒታል መሆን እንደሚችል በኢትዮጵያም ታሪክ በሌላም ታሪክ በዝርዝር ለማየት በምሳሌዎች ማስቀመጥ ይቻላል።

በአንድ ወቅት በአንድ ሀገር በጣም ስመጥር ሃብታም ሰው ነበር። ይህ ሰው ከእለታት በአንድ ቀን አንዲት ጋዜጠኛ ኢንተርቪው ልታደርገው ትመጣለች። ካስተዋወቀች በኋላ የመጀመሪያው ጥያቄ እንዲሆን የወደደችው "የስኬትህ ምስጢር ምንድነው? የሚል ነበር። እና ሰውየውም የስኬቱን ምስጢር ለማስረዳት ቃላት ቢደረድር በቀላሉ እሷንም ተመልካቾቹንም ማሳመን ስለሚቸገር የሚያሳምን ምሳሌ መፈለግ ጀመረ። ከዚያም ደረቅ ቼክ ከኪሱ አውጥቶ የፈለግሽውን ቁጥር ጻፊበት የጻፍሽውን ቁጥር እሰጥሻለው አላት። የመጀመሪያውን ጥያቄ ሲያቀርብላት ምን ነካህ እኔ እኮ ኢንተርቪው ላደርግህ ነው የመጣሁት እንጂ ገንዘብ ልጠይቅህ አልመጣሁም አለችው። ለሁለተኛ ጊዜ ያሻሽን ቁጥር ጻፊ የጻፍሽውን ቁጥር እሰጥሻለው አላት አሁንም ቆጣ አለችና "ደሃ ናት ገንዘብ የላትም ብሎ የነገረህ ሰው አለ ወይ? ምን ማለት ነው ይሄ" ብላ ተቆጣች። እና እጥፍጥፍ አድርጎ ቼኩን ኪሱ መለሰ እና "የስኬቴ ምስጢር ይሄ ነው" አላት። ህይወት ቢበዛ አንዴ ምናልባት ለአንዳንዶች ሁለት ጊዜ ነው እድል የምትሰጠው። ያ እድል ሲመጣ የሚጠቀሙ ሰዎች የስኬት ጫፍ ላይ የደረሱ ናቸው። ያ እድል ሲመጣ ገንዘብ አልፈለግኩም እኮ ደሃ መሰልኩህ ወይ? የሚሉ ሰዎች በቃ አጡ። በዚህ ላይ የሃብቴን እኩሌታ ጽፈው እንኳን ቢሆን እሰጥሽ ነበር። አንቺ ግን የመጣውን

እድል ገፋሽው መጠቀም አልቻልሽም። ህይወት የሰጠችኝን እድል ሁሉ አሟጥጬ መጠቀሜ ነው። ለዚህ ነው ፈረንጆች "when opportunity comes grab it" ይላሉ። ቶሎ። አንዳንዴ እድል በራችንን ሲያንኳኳና ሲመጣ እኛ በኛ ፍልስፍና እና ግንዛቤ ከገፋነው በኋላ ብዙ ጊዜ የምናላዝንና የምናዝን እንሆናለን።

ኢትዮጵያን የማገልገል እድልና የተሰጠንን ቼክ በምን ያክል ልክ እንጠቀምበታለን? የሚለው በእያንዳንዳችን ጫንቃ ስር የወደቀ ይሆናል፤ እያንዳንዱ ግለሰብ የሚወስነው ይሆናል። የእያንዳንዱ ግለሰብ ውጤት በድምር ደግሞ የዚህን ቲም ውጤት የሚወስን ይሆናል። አሁን የዛሬ አስራ አምስት ቀን ሚኒስትር ወይንም ሚኒስትር ዴኤታ የነበሩ ሰዎች ሲይዙት ብር ነበር፣ ነሃስ ነበር፣ አፈር ነበር። እናንተ መጥታችሁ ደግሞ ሲያጡት አልማዝ ሆነባቸው። ግን አለጣቸው ያን እድል መልሶ ማግኘት በጣም ከባድ ነው። ሲሰጥ መጠቀም ያልቻለ ሰው ሲያላዝን ውሎ ቢያድርና "For Granted" እናንተ ልዩ ስለሆናችሁ የተሰጣችሁ ነገር አድርጋችሁ አትውሰዱት። እንደዚያ መውሰድ ስትጀምሩ ስልጣን ግብ ይሆንና የምታሳኩትን ሳታሳኩ ትቀራላችሁ። በተለይ የኢትዮጵያ ህዝብ መውደድም መጥላትም ያውቅበታል ። ሲወድ በአንቀልባ ይሸከመናል፣ ትከሻው ላይ ያወጣናል፣ ራሱ ላይ ያወጣናል፣ የሚያስቀምጥበት ቦታ ነው የሚቸገረው ከፍቅሩ ብዛት። አንቅሮ ሲተፋም ይተፋል። ሲጠላም ይጠላል። ከኛ የሚያስፈልገው ነገርና ጥንቃቄ የሚሻው ጉዳይ የኢትዮጵያን ህዝብ ፍቅር እና አክብሮት አትለማመዱት። ልምምድ አደገኛ የሚሆነው ለሲጋራ ብቻ አይደለም፣ ልምምድ አደገኛ የሚሆነው ለጫት ብቻ አይደለም፣ አታችመንት ለብዙ ነገር በሽታ ነው። ስልጣን አትለማመዱ ይሄዳል የጊዜ ጉዳይ ነው። ስልጣንን በጣም ስንለማመደው እና አታችድ ስንሆን ስናጣው መኖር ግራ ይገባናል። ሰፈር ውስጥ መቀመጥ እንቸገራለን። ስልጣንን ብቻ አይደለም መለማመድ የማያስፈልገን አታችመንት የጠነከረ ነገር እንዳይኖረን ማድረግ የሚኖርብን ሌብነትንም ጭምር ነው። ሌብነት ልምምድ ይሆናል። ብዙ ሰዎች በጣም ብዙ ብቃት እያላቸው በሌብነት

ልምምድ ተጠልፈው ከጉዟቸው የሚቀሩ አሉ። ባለፈው ምክርቤት ሾልከው ያለፉ አሉ ተብለናል አትርሱት። ከኔ እና ከእናንተ ውጪ አይደለም ሾልኮ ያለፈው ሰው ሌብነት እንደ ልምምድ ከሆነ እንደ ሲጋራ ነው።

የኢትዮጵያን ህዝብ ፍቅር እና አክብሮት ብቻ ሳይሆን መለማመድ የሌለብን ልመናንም ጭምር ነው። ልመና ሱስ የሆነበት ግለሰብና ማህበረሰብ ማበልጸግ አይቻልም። የሆነ ቦታ ልመናን በቃህ ብለን። ማቆም አለብን ለነገሩ እኛ እንኳን ልመናን፣ እንኳን ፍቅር እና አክብሮትን ፈጣሪንም እንለማመድና ጓደኛ እናደርገዋልን። እራሱ ፈጣሪን ከመቀራረባችን ብዛት ልንሸውደው እንፈልጋለን። ይሄንንማ አላየህም አይንህን ጨፍን ልንለው እንሞክራለን። ልምምድ አደገኛ ነገር ስለሆነ የኢትዮጵያን ህዝብ አክብሮትና ፍቅር የማንለማመድ ከሆነ ለረጅም ጊዜ ልናቆየው እንችላለን። ስልጣንን የማንለማመድ ከሆነ ለረጅም ጊዜ ልናቆየው እንችላለን። ወንበራችን እንኳን ቢቀር ካለንበት ቦታ ተፅዕኖ መፍተር ስለምንችል ልናቆየው እንችላለን። አታችመንት ግን ገዳይ ስለሆነ ስትነሳ የሞትክ ከመሰለህ ቤት ታኮርፋለህ፣ ጎረቤት ታኮርፋለህ፣ ጓደኛ ታኮርፋለህ እንኳን ኢንፍሉእንስ ልታደርግ ልትግባባ እንኳን ትቸገራለህ። ልምምድን ማስቀረት ለእያንዳንዱ ተሿሚ በጣም ወሳኝ ነገር ነው። በማንኛውን ነገር በማንኛውም ሰአት ልሄድ እችላለሁ። ሌላው የሚመጣና የሚሄድ ሰው ነው ብሎ የሚያስብ ከሆነ ለረጅም ጊዜ ሊያቆየው ይችላል። ኢትዮጵያ ውስጥ በጣም በርካታ ሰዎች ተኮፍሰው በሃላፊነት የመሩ ሰዎች አሉ። ኢትዮጵያ መውደድ እና ማክበር ብቻ ሳይሆን የተኮፈሰን ማስተንፈስም ስለምትችል ብዙዎቹ ተንፍሰዋል። በመኮፈስ መከበር፣ በመኮፈስ በአጃቢ ጋጋታ መከበር፣ የምናስብ ከሆነ የጊዜ ጉዳይ ነው ቀስ ብሎ የኢትዮጵያ ህዝብ ያስተነፍሳል። ብዙዎች ላይ ሆኗል፤ እኛም ላይ የማይሆንበት ምንም ምክንያት አይኖርም።

የተከበሩ ተብሎ መጠራት መብት የመሰላቸው የሚያስከብር አሻራ ግን የማያስቀምጡ ሰዎች የሚያስከብር አሻራ ስታኖር በአፉ የተከበሩ ባይልህም በልቡ እየሰማኸውም

ሳሰማውም ያከብርሃል። እንዲሁ የተከበሩ ከሆነ ግን ሸርደዳ ይሆናል። ለመከበር የሚያበቃ አሻራ ማስቀመጣችንን እርግጠኛ ካልሆንን ስሙን ለመቀበል የሚያስከብር አሻራ አለን ወይ? አሻራው ካለ ቢባልም ባይባልም ስለማይቀር ቀደም ብዬ እንዳነሳሁት ኢትዮጵያ የኢትዮጵያ ህዝብ የሚያገለግሉትንም የሚገለገሉበትንም ጠንቅቆ ያውቃል የሚያገለግሉትን፣ የሚገለገሉበትንም፣ የሚንገዋለሉበትንም መስፈርያ አለው፣ የሚለይበት ወንፊት አለው። በየትኛውም ቦታ ላይ የሚያስከብር አሻራ ለማስቀመጥ ከወሰናችሁና ከሰራችሁ የዚያን ጊዜ መንግስት አውቆ ሹመት አይሰጣችሁም። አንዳንዶች አላችሁ ለምሳሌ ሚኒስትር መሆን ሲገባኝ ሚኒስትር ዴኤታ ሆንኩኝ ብላችሁ በጣም ያዘናችሁ አላችሁ። እመኑኝ መሆን የሚገባችሁ ሚኒስትር ዴኤታ ነበር ሚኒስትር ቢሆን ትሆኑ ነበር። ይሄ ማለት በአቅም ቢሆን ከአንድ ሚሊየን ሰው ነው የወጣችሁት በችሎታ፣ በልምድ፣ በእናንተ መመዘኛ አይደለም በብዙ መመዘኛ መሆን የሚገባችሁን ህይወት ሰጥታችኋለች። ያን መጠቀም ስትችሉ የከለከላችሁ ሰው እንኳን ቢኖር የከለከላችሁ ማእረግ እንጂ የምትጥሉትን አሻራ እና የምትጥሉትን ክብር ማንም ሰው ሊወስድባችሁ አይችልም። ዴኤታ ሆኖ ይቅርና ወረዳ አስተዳድሮ ሰው አሻራ ማስቀመጥ የሚችል ከሆነ ዴኤታ ሆኖ ሚኒስትር ሆኖ ምን ተአምር ሊሰራ እንደሚችል ማሰብ ትችላላችሁ።

ይህ ነገር እንዲሳካ ስልጣን መሳርያ ብቻ ነው መሆን ያለበት ብቻውን ግብ መሆን የለበትም። ስልጣን ብቻውን ግብ ከሆነ አለቀ። እናንተ ሹመኞች እድሜ ልክ የተማራችሁለት የለፋችሁበት ጉዳይ ዛሬ ተሳክቷል። ከዛሬ በኋላ ምንም ጥረት አያስፈልጋችሁም ማለት ነው ግብ ከሆነ። ስልጣን መሻታችሁን መፈለጋችሁ የምታሳኩበት መሳርያ ደግሞ ከሆነ ዛሬ ትጀምራላችሁ። አንድ ብላችሁ። ስልጣንን እንደ መሳርያ የሚወስዱ ሰዎች የተከበረ ማንነት ያቆያሉ አሻራ ያስቀምጣሉ። ስልጣንን እንደ ግብ የሚፈልጉ ሰዎች ልክ ሚኒስትር ሲባሉ ፓርላማ ላይ ቃለ መሃላ ፈጽመው ሲወጡ የኋላ በር የሚከፍትላቸው ሌላ ሰው ይፈልጋሉ። አለቀ የነሱ አበቃ ማለት ነው። ብዙ የኋላ በር የከፈትንላቸው ሰዎች የደረስንበት ቦታ ያልደረሱት ለነሱ

ስልጣን ግብ እንጂ መሳርያ ስላልሆነ ነው። ስልጣንን እንደ ግብ ከወሰዳችሁ፣ የጠራ አላማ፣ የጠራ ራዕይ ካላችሁ አላማችሁ የሚሳካ ይሆናል። ስልጣን ግን ግብ ከሆነ አላማን መሻት ብቻ ነው የሚሆነው፣ ፍላጎት ብቻ ነው የሚሆነው። ስልጣን መሳርያ ከሆነ ግን አላማ የሚጨበጥ የሚዳሰስ የሚከወን ነገር ይሆናል። እኔ እኮ ራእይ አለኝ፣ እኔ እኮ ህልም አለኝ የምንለው በጠራ ግብ ላይ ተመስርቶ ከሆን ካለጥርጥር የሚሳካ ይሆናል። ያ ስኬት ደግሞ ለዘመናት የምንሻውን ክብር ያቆይልናል። እና ስልጣናችሁን ለፍላጎታችሁ መሳርያ ለማድረግ ከወሰናችሁና ከሰራችሁ ስኬት ይከተላችኋል።

አውሮፕላን በሚፈጠርበት ጊዜ አውሮፓ እና አሜሪካ ላይ ተመሳሳይ ጊዜ ውስጥ የአውሮፕላን ምርምር ይካሄድ ነበር። እና በዚያን ወቅት የሚመራመሩ ቡድኖች ጥያቄ ቀርቦላቸው ነበር። የአሜሪካውን ፕሮጀክት የሚመራውን ኢንጂነር ሲጠይቁት ለምንድነው ምርምር የምታደርጉት? ገንዘብ መድባችሁ የምትሰሩት? ሲሉት አውሮፕላን መፍጠር መቻል ብዙ ገንዘብ ያስገኛል፣ አውሮፕላን መፍጠር መቻል ብዙ ዝናም ያስገኛል። የመጀመሪያው ኢኖቬሽን ስለሆነ በዚህ ፈጠራ ውስጥ ብዙ ገንዘብና ብዙ ዝና እጠብቃለሁ" አላቸው። በዚያው ጊዜ ራይት ብራዘርስን "ለምን ምርምር ታካሄዳላችሁ?" "ሲባሉ የሰው ልጅ በርቀት እንዳይወሰን በተራራ እንዳይወሰን በአንድ ስፍራ እንዳይወሰን ርቆ መሄድ እንዳይችል ካለበት ቦታ ሌላ ስፍራ ባጠረ ጊዜ መድረስ እንዲችል ካለን ቁጭት ነው የምንሰራው" አሉ። ህልማቸው ትልቅ ነበር የሰውን ልጅ ካለበት መታሰር መፍታት ነበር እንጂ ዝና እና ገንዘብ ብቻ አልነበረም። እና ይሄ ህልም፣ ይሄ ግብ፣ ይሄ አላማ ዝም ብሎ አይደለም። ጉልበት ስለሆነ ራይት ብራዘርስ ቀድመው ያንን ፕሮጀክት እውን አደረጉት በአሜሪካ ፋይናንስ የሚደረገው ፕሮጀክት ተዘጋ። ያ ብዙ ገንዘብ የተመኘው፣ ያ ብዙ ዝና የተመኘው ሰው የሳተ አላማ ነበረው እና ፕሮጀክቱ ሳይሳካ ስሙ አይጠራም።

የጠራ አላማ ይዘን ማህበረሰብ ለመጥቀም የምንሰራ ከሆነ ራሱ ያ የጠራ አላማ ጉልበት ስለሚሆን ህልሞቻችንን ያሳካል፣ ብዙ ርቀት እንድንጓዝ ያደርጋል፣ ውጤታማም

እንድንሆን ያግዘናል። ታዲያ የዚህ ሚና ያልተገለጠ፣ የማይታይ፣ አቅምን መግለጥ ነው። ኢትዮጵያን ለመቀየር ሰማይ እንድትቧጥጡ አይጠበቅም። የሌለ ነገር እንድታመጡ አይጠበቅም ያለውን ነገር በጥልቀት አይታችሁ እንዲያዩ አድርጋችሁ ማውጣት ብቻ ነው የሚጠበቅባችሁ። የሩቅ ምስራቅ ሀገራት የመበልጸጊያው ጊዜ የዛሬ ሰላሳ አመት ነበረ። ሁለተኛው ጊዜ ደግሞ ዛሬ ነው ይላሉ። የዛሬ ሰላሳ አመት ለኢትዮጵያ ብልጽግና ምቹ ጊዜ የነበረ ሊሆን ይችላል። ያ አልፏል በዚያ አንቆዝምም። ሁለተኛው መበልጸግያ ጊዜ ዛሬ ነው። ዛሬን በትክክል መጠቀም፤ የተሸፈነን መግለጥ ከቻልን ስኬት እናመጣለን። ኢትዮጵያ ውስጥ በርከት ያሉ ሃብቶች አቧራ ለብሰዋል። አቧራ የለበሱ ቋጥኝ የተጫነባቸው በየስፍራው የሚታዩ አረሞች ሙጃዎች የበቀለባቸው የሚያስፈሩ ሃብቶች አሉ። ሙጃውን ነቅለን፣ አረሙን ነቅለን፣ አቧራውን አራግፈን እነዛን የሚያብረቀርቁ የብልጽግና መሰረቶች ማውጣት መቻል ነው የኛ ስራ የሚሆነው።

ምን ምሳሌ አለ? ኢትዮጵያ ውስጥ ሙጃ የበቀለበት፣ አረም የበቀለበት፣ ቋጥኝ የሸፈነው፣ አቧራ የሸፈነው ምን አለ ካላችሁ?እንጦጦ ለመቶ አመታት በሙጃ የተሸፈነ የሚያስደንቅ ሃብት ነበር። ሙጃውን ስንነቅል የሺዎች መዝናኛ ሆነ። ዩኒቲ ፓርክ ትክክለኛ የሙጃ፣ የቋጥኝና የቆሻሻ ማጠራቀሚያ ነበረ። ትላንትና ሶስት ሺህ ሰው ነው የጎበኘው። ከከፈትነው እስካሁን ከመቶ ሃያ ሚሊየን ብር በላይ ገቢ አስገብቷል ዩኒቲ ፓርክ። ትላንት ግን ሙጃ በቅሎበታል አዲስ ተአምር አይደለም የሚያስፈልገው ሙጃውን መንቀል ነው የሚያስፈልገው። መከላከያን የዛሬ ስድስት ወር አቧራ ሸፍኖት የብረታብረት ቆሻሻ ማጠራቀሚያ ነበር። ያንን ነገር ለማየት የሚያስችል ምንም ነገር አልነበረም። አዲስ የመከላከያ ቦታ አልተፈጠረም። ሙጃው ተነቀለ፣ አቧራው ተነሳ በአለም ላይ ምርጥ የሚባል ቦታ ተፈጠረ።

ባለፉት ሁለት አመታት የሄድንበትን ርቀት ካየን በኋላ በዚሁ መልክ በሁሉም ክልሎች ሁለት አመት ብንሰራ ሁለት ኪሎ ስንዴ ወደ ኢትዮጵያ አይገባም። የኛ ሚናና ድርሻ በጠራ አላማ፣ በጠራ መሻትና ፍላጎት የተሸፈኑ ጉዳዮችን ነቅሎ ማውጣት እንጂ

አዲስ ነገር ከሌላ ቦታ እንድንፈጥር አይጠበቅም። መሬቱም አለ፣ ውሃውም አለ፣ ጉልበቱም አለ፣ ወርቁም አለ፣ ነዳጁም አለ፣ ማእድኑም አለ። አይናችን ተገልጦ ማየትና ማውጣት ከቻልን የምናስበውን የኢትዮጵያን ብልጽግና ማረጋገጥ ይቻላል። ኢትዮጵያዊያን ከሰነፍ ደጅ ሞፈር ይቆረጣል ይላሉ። ይህ አባባል እውነት ነው።

በአንድ ገጠር መንደር ውስጥ አንድ አርሶ አደር ለረጅም ጊዜ የቆየች ሃውልት፣ በድንጋይ የተጠረበች ሃውልት ከቤቱ ደጃፍ ላይ አስቀምጦ ለረጅም ጊዜ አብሯት ኖሮ አንድ ቀን መንገደኛ አላፊ ሰው ሃውልቷን ያይና ባለቤቷን ሲያይ ከደጁ አንገቱን ደፍቶ ተቀምጧል። "እባክህ ወዳጄ ሆይ ይቺን ሃውልት ልግዛህ ሸጥልኝ" ይለዋል "ይሄን የማይረባ ድንጋይ ማን ይፈልገዋል ብለህ ነው?" ገንዘብ አውጥቶ ይሄንን ድንጋይ ማን ይገዛዋል ብለህ ነው? ይለዋል። ሰውዬውም ግድ የለህም ልግዛህ ብሎ አንድ ብር አውጥቶ በአንድ ብር ሸጥልኝ ይለዋል። በአንድ ብር ያን የተቀረጸ ሃውልት ሸጠለት ሰውየው ወደ አህያው ሲጭን አብሮ ነቅሎ ተሸክሞ ሸጠለት ገዢው ይሄዳል። ከብዙ ጊዜ በኋላ ይህ የገጠር ሰው ሊገበያይ ወደ ከተማ ይወጣል። እዚያም ሰዎች ተሰልፈው እጅግ የሚያስደንቅ፣ የእጅ ጥበብ ለማየት አምስት አምስት ብር ክፈሉ ይላል ማስታወቂያ ላይ። አይ እነዚህ ከተሜዎች ምን ጉድ ሰርተው ይሆን ብሎ ተሰልፎ አምስት ብር ከፍሎ ከገባ በኋላ በአንድ ብር የሸጣትን ሃውልት በአምስት ብር አያት።

በአንድ ብር ያረከስናት ኢትዮጵያ፣ በአንድ ብር የሸጥነት ኢትዮጵያ፣ ለአስር ኪሎ ስንዴ ያረከስናት ኢትዮጵያ ከዚያ ብዙ እጥፍ ከፍለን ለማየት ለመጎብኘት የምንቸገርባት ሀገር ናት ኢትዮጵያ። ምንም ከውጪ የሚመጣ ሃብት የለም። የኛኑ ሃብት ነው መልሰው የሚሰጡን ምንም። ነገርግን ከሞኝ ደጃፍ ሞፈር ስለሚቆረጥ በአንድ ብር እንሸጥና በአምስት ብር ደግሞ ተሰልፈን እናያለን። ከዚህ አመራር የሚያስፈልገው በአንድ ብር ከመሸጥ፣ በረከሰ ዋጋ ከመሸጥ፣ የራስን ልክና ዋጋ አውቆ የሀገርን ወርቅና የሀገርን አልማዝ ማውጣት መቻል ነው። ብዙ የሚሸጡ እና የሚሸጡ ሰዎች ስላሉ። ስንሸጥ እና ስንሸጥ ያለንን ወርቅ እናረክሰዋለን።

ወርቃችን በልኩ የተከበረ እንዲሆን በተቻለ መጠን የዚህ አመራር ዋነኛ አላማ መሆን ያለበት የተሸፈኑ ነገሮችን ገለጥ ገለጥ አድርጌ ይቺን ሀገር እንደስሟ ትልቅ አድርጌ ኢትዮጵያውያን እንዳይለምኑ እንዳይሰደዱ ማድረግ እችላለሁ። መሬት አለን፣ ውሃ አለን ሰብሰብ አድርገን ብንሰራ ቢያንስ “ስንዴ ብርቅ አይሆንብንም” ብሎ የቆረጠ የወሰነ ሊመራ የተዘጋጀ ሃይል እንዲሆን ነው የሚፈለገው። ይሄን ማሳካት ከቻላችሁ አዲሱ ትውልድ ደግሞ ላቅ ያለ ራእይ ስለሚሰንቅ በዛው ጉዞ ውስጥ ይገባ እና ይበልጥ ያማረ ከምናስበውም በብዙ የላቀ ነገር ሊፈጠር ይችላል። ጫናዎች፣ መከራዎች፣ ግፊቶች ብታምኑም ባታምኑም የኢትዮጵያ ብልጽግና የተዘጋውን መስኮት የሚከፍቱ እንጂ የሚያዳፍኑ ሊሆኑ አይችሉም። ማንኛውም የምንሰማው ጩኸት ወደሚገባን መዳረሻ የሚወስደን ነው። ጩኸት ስንሰማ የሚመጣ የሆነ ድል አለ ብለን ማሰብ እንጂ መሸማቀቅ መታሰር አያስፈልግም። መዘርጋት ነው የሚያስፈልገው ያላየኸውን፣ ያላወጣኸውን ለማውጣት ያን ማድረግ ስንችል በምናስበው ልክ ለብልጽግና የማይናወጥ መሰረት ማስቀመጥ እንችላለን። አቧራ የለበሰ ሁሉ፣ የተሸፈነ ሁሉ ሸክላ አይደለም። ከአፈር ውስጥ ወርቅ ከከሰል ውስጥ አልማዝ እንደሚወጣው ሁሉ የሸፈነውን ማራገፍ እና ገባ ብለን ማየት ከቻልን ለትውልድ ሊሸጋገር የሚችል እጅግ ውድ የሆነ ነገር ልናገኝ እንችላለን።

በታይላንድ ባንኮክ የሚነገር አንድ እውነተኛ ታሪክ አለ። ከመቶ አመታት በፊት በታይላንድ የተሰራ አንድ የሸክላ ሃውልት አለ። ይሄ የሸክላ ሃውልት እንደ እምነት ቦታ፣ እንደ ቅርስ ስለሚታይ ትውልድ እንዲሁ እየጠበቀው፣ እየጠበቀው እያየው ኖረ። ከመቶ አመታት በኋላ የዚያ የሸክላ ሃውልት ዋጋ ሲሰላ ከታሪካዊ ጭብጡ ባሻገር በገንዘብ ሲለካ 50 ሺህ ዶላር ያወጣ ነበር። እና ልማት መጥቶ ሀገር ሲሰራ ይሄ ሸክላ ሳይጎዳ ካለበት ስፍራ ተነቅሎ የሚሰሩ የልማት ስራዎች ተሰርተው ተመልሶ እንዲተከል መንግስት ይወስን እና ያንን ሸክላ ካለበት ቦታ በጥንቃቄ ማንሳት ሲጥሩ በማንሳት ሂደት ላይ እያሉ የሆነ ቦታ ላይ ይሰነጠቃል። የተሰነጠቀውን ቦታ በፍራቻ እንዳይነሳ በመስጋት በጥንቃቄ እውቀት ያላቸው ሰዎች ሲመራመሩ ከውስጡ ሌላ ነገር እንዳለ

ያያሉ። ትንሽ ሰፋ ሰፋ ሲያደርጉት ያ ሽክላ የተለበጠው ከውስጡ ያለው የሚከብደው ነገር ወርቅ ነበር። ከመቶ አመታት በፊት ሌላ የጎረቤት ሀገር ሀገራቸውን ልትወር ስትመጣ የልጆቻችንን ሃብት እንዳትወስድ ብለው በሽክላ ሰርተው ያስቀመጡት ወርቅ እንጂ ሃውልት አልነበረም። ሽክላው ሲራገፍ የሃምሳ ሺህ ዶላር የተገመተው ቅርስ ሁለት መቶ ሃምሳ ሚሊየን ዶላር የሚያወጣ ወርቅ ነበር።

ይሄ እውነተኛ ታሪክ ነው። በየቦታው የተሸፈኑ፣ በዊዝደም የተሸፈኑ እና በእውቀት የምንፈልጋቸው ሃብቶች አሉ። በጥበብና በእውቀት መካከል ባለው ትልቅ የማይገናኝ አመታት የሚፈልግ ድልድይ ምክንያት ሰዎች እየቆፈሩ እየቆፈሩ የማይደርሱበት ማለት ነው። በኛም ሀገር በዚያ ልክ በርከት ያሉ ሃብቶች በየቦታው እንዳሉ ተገንዝበን፣ በተለየ አይን ገልጠን አይተን ህዝባችንን አሳይተን፣ ተባብረን፣ ተግተን፣ ሰርተን፣ ኢትዮጵያን መቀየር የሚያስችል አቅም ላይ መገኘት ይኖርብናል። እድሉን ካበላሸን ቼኩ ከተቃጠለ ይቃጠላል፣ ቋሚ አይደለም አሁን ሶስት ቀን አራት ቀን ተቃጥሎባቸዋል ኦሬዲ ወደታች የሚቆጥረው፣ እያንዳንዷን ቀን ውድ በሆነ መንገድ መጠቀም ካልቻልን በዘላቂነት ይዘን የምንቆየው ነገር ስላልሆነ ይሄን ቼክ በርከት ያለ ካፒታል አስቀምጠን ለኛም ለልጆቻችንም የሚተርፍ ነገር ማምጣት እንድንችል መትጋት ይኖርብናል።

ለመትጋት ግን ቀደም ብዬ እንዳነሳሁት ሰው መሆን ያስፈልጋል፣ ባለስልጣን መሆን ሳይሆን ሰው መሆን ያስፈልጋል። ሰው ሆነን ሰውን ለማንሳት ከተጋን ይሆንልናል፣ ባለስልጣን ሆነን እላይ ሆነን ወደላይ ለመጎተት ከሆነ ግን አስቡት እኛ መቶ ነን የሚጎተተው ደግሞ መቶ ሚሊየን ነው። እኛን ወደሱ እንጂ እነሱን ወደኛ ልናመጣቸው አንችልም። ይከብዳል ሰው ሆነን ሳንንሳፈፍ አብረን አንድ ደረጃ እየመራን ሁለት ደረጃ እየተከተልን ከሄድን ተያይዘን መውጣት እንችላለን። ተያይዘን ለመውጣት እንድንችል ከዚህ እድለኛ ቡድን የሚጠበቀው እንደግልም እንደ ቡድንም በጠራ ግብ ሰው ሆኖ መትጋት መቻል ነው። ያንን ካሳካን ውጤቱ ከደጃችን ነው ቅርብ ነው

ይገኛል፣ ይጨበጣል፣ ይታያል ያ ደግሞ ከሆነ አሁን የምናስበው መበልጸግ፣ መሻሻል ይታያል።

ለልጅህ አንድ ሚሊየን ብር ባንክ ከማስቀመጥ የኢትዮጵያን ጂዲፒ ከመቶ ቢሊየን አምስት፤ አስር ትሪሊየን ብታደርስ ልጅህ ያችን ሚሊየን ብር በወራት ያገኛታል። ለሁላችንም የበለጸገች ሀገር ካለችን የበለጸገ ሀገር ውስጥ መኖር ይችላሉ። በደሃ ማህበረሰብ ውስጥ አንዳንድ ባለሃብቶች ቢኖሩ ግን ያው ጎረቤቶቻቸው ሁሉ ደሃ ስለሆኑ ከግቢ አልወጣም እስካላሉ ድረስ ከግቢያቸው ከወጡ መንገድ ላይ ሶፍት አለ፣ ሃይላንድ አለ፣ ቆሻሻ አለ፣ ሽታ አለ። በአጠቃላይ ሀገሩን ሊያጸዱት አይችሉም። ባልጸዳ ሀገር ውስጥ የሚያምር ቪላ እንጂ የሚያምር ከተማ ሊኖር አይችልም፣ የሚያምር ቪላ ደግሞ የሚያምር ከተማን ሊተካ አይችልም። ሰው መውጣት፣ ወክ ማድረግ፣ ማየት፣ መዝናናት ስለሚፈልግ የሚያምር ከተማን ካልሰራን የሚያምር ቪላ ብቻውን የተሟላ ደስታን ወይንም እርካታን አያስገኝልንም።

ሀገር እንገንባ፣ ከተማ እንገንባ በተገነባ ከተማ ውስጥ የእያንዳንዳችን ቪላ ቀርቶ አፓርትመንታችን የደስታ ምንጭ ይሆናል። ምክንያቱም ፎቁ ላይ ተቀምጠን የምናየው ነገር ለአይን ማራኪና ሳቢ ስለሚሆን ይሄን አስበን ስለምንሰራ ይሄን የአንድ ሳምንት በዚህ አካዳሚ የምናደርገው ቆይታ የጅማሮውን ፋውንዴሽን ይጥላል። ሶስት ዋና ዋና አላማዎች አሉ አንደኛው ማሳወቅ ነው። የማናውቀውን ነገር እንድናውቅ፣ የረሳነውን ነገር እንድናስታውስ፣ የምናውቀው ግን የማንገለገልበትን ነገር ለካ ለዚህ ጉዳይ መዋል ይችላል ብለን ማስታወስ ነው። አንዳንዱ በንኡስ አእምሯችን ላይ አለ በየእለቱ ስለማንጠቀምበት ፖፕ አፕ እንዲያደርግ እንዲወጣ ለማስታወስ፣ የማናውቀውን ለማወቅ ነው። ሁለተኛው ማነሳሳት ነው ዱክትርና ብቻውን፣ ልምድ ብቻውን፣ የቆየ ስልጣን እድሜ ብቻውን ተነሳሽነት ካልታጀበ ወደ ስኬት ስለማይወስድ ሰው እንዲነሳሳ፣ እንዲነቃቃ ብቻዬን አይደለሁም በርካታ ሰዎች አሉልኝ፣ ተሳስረን የላቀ ነገር ልንሰራ እንችላለን ብሎ እንዲያስብ ማነሳሳት ነው። ሶስተኛው ምንም ብትነሳሱ፣

ምንም ብታውቁ የቡድን ስሜት ከሌለ በስተቀር የምናስበውን ሀገር ልናሳካ አንችልም። ለቡድን ስራ ይሄንን ቲም ማዘጋጀት ነው። የመጀመሪያው ቀዳሚ ቲም ሚኒስትር እና ሚኒስትር ዲኤታዎች እንደ አንድ አንጓ፣ አንደኛው ሚኒስትሪ ከሌላኛው ሚኒስትሪ ደግሞ የተሰናሰለ ቲም አብዛኛው ስራ ይወራረሳል።

መንገድ ከሌለ ግብርና ምንም ያህል ቢሰራ ወደ ገበያ አይመጣም። ወደ ማርኬት ካልመጣ ደግሞ በአንድ አመት ምርታማነት አይቀጥልም። ውሃ ከሌለ መስኖ የለም። እያንዳንዱ የሚኒስቴር መሥሪያ ቤቶች አብሮ ይሰራል ማለት የንግድ ሚኒስቴር እርሻ በበቂ ካልተመረተና ወደ ገበያ ካልወጣ ኤክስፖርት የለውም። ቲም መሆን በግሩፕ መስራት፣ እንደ አንድ አካል መስራት ሶስተኛ አላማው ነው። የመጀመሪያው ማሳወቅ፣ ሁለተኛው ማነሳሳት እና ለቡድን ስራ ማዘጋጀት እዚህ ሚኒስትሮች ቡድን ከሆናችሁ፣ ሚኒስትር እና ሚኒስትር ዲኤታዎች ደግሞ ቡድን ከሆናችሁ አንድ ስቴፕ ዝቅ ዝቅ እያለ ይሄ ስራ ይቀጥላል ማለት ነው።

ሶስት ነገር ከሰልጣኝ ይጠበቃል። ቀደም ብዬ እንዳነሳሁት ሰው ለመሆን ስለወሰናችሁ ሰው ከሆንን አንድ ሳምንት አብረን ብንቀመጥ እንደ ቫኬሽን ነው መዝናኛ ነው። ለመተዋወቅ ስም የማንተዋወቅ፣ ባህርይ የማንተዋወቅ፣ ስፖርት የማንወድ፣ በግሩፕ መንቀሳቀስ የማንወድ ሰዎች ካለን እሱ እሱን ሰው የሆንን ሰው መሆን ስለምንጀምር ለመተዋወቅ ይጠቅመናል። ከዚያ ባሻገር ግን አካዳሚው ከእናንተ የሚጠብቀው የማደግ ጉጉትን ነው። ይሄንማ አውቀዋለሁ፣ ይሄንማ አንብቤዋለሁ፣ ይሄንማ ሰምቼዋለሁ ከሚል ተቸካይ እና ዘጊ አስተሳሰብ ወጥታችሁ ማንኛውም ከልምዱ፣ ከእውቀቱ የሚያካፍላችሁን ሰው አክብራችሁ ለማወቅ፣ ለማደግ ስትጓጉ ማለት ነው። ጉጉት ከሌለ እውቀትን መጨበጥ ስለሚያስቸግር። ለመለወጥ ፍላጎት ከሌለህ የሚረዳህ የለም። ለመረዳት የመጀመሪያው ሂደት መፈለግ ነው። ለመለወጥ የምትጓጓ ከሆነ ግን ሊያቆምህ የሚችል ሃይል የለም። ለጊዜው በር የሚዘጋ ሊኖር ይቻላል ግን ጠቅልሎ የሚያቆምህ አይኖርም። ዋናው ዋስጢር ያለው በአንተ ጉጉት ውስጥ ነው።

ለማወቅ ጉጉት ከሌለህ ማንም አያግዝህም ቢያግዝህም አይሳካም። ጉጉት ካለህ ደግሞ ማንም አያስቆምህም። አካዳሚው የሚፈልገው ለማደግ የሚጓጉ ሰዎች ካሉበት የላቀ ነገር ለማምጣት የሚሹ ሰዎች እንድትሆኑ ይፈልጋል፣ ይጠብቃልም።

ሁለተኛው ያወቅነውን ለመተግበር ቁርጠኛ ነው። መሆን እዚህ ስለ ኢንቲግሪቲ ተምረን እዚህ ስለውጪ ግንኙነት ልምድ ተካፍለን ያንን ወደ ተግባር የማንቀይረው ከሆነ ትርጉም የለውም። መስራት ይፈልጋል። በአንድ ሰፈር ውስጥ ያለች ትንሽ ኩሬ በላይዋ ላይ የተንሳፈፈ ሰፋ ያለ ቅጠል ነበር። በዚህ ቅጠል ላይ አምስት እንቁራሪቶች ቅጠሉን ተጠቅመው ተንሳፈዋል። ከብዙ ቆይታ በኋላ አንደኛው እንቁራሪት ወደ ውሃ ውስጥ ገብቶ መዋኘት ይሻላል ብሎ ወሰነ። አምስት እንቁራሪት ተንሳፏል አንደኛው ዘሎ ለመግባት ወሰነ ነው ያልኩት እንጂ ገባ አላልኩም፤ መወሰን መግባት አይደለም። እዚህ ሆናችሁ ወስናችሁ ይሆናል ወጥታችሁ ካላደረጋችሁት አይሆንም በሚሊታሪ "ኡዳሉብ" ይባላል። ለአንድ ውሳኔ መጀመሪያ "Observe" ታደርጋለህ፣ ከዛ "Orient" ከዛ "Decide" ታደርጋለህ፣ ከዛ "Act" ታደርጋለህ። Action ካልመጣ በስተቀር Decision ውጤት አያመጣም። አዎ አስቤ ነበር ወስኜ ነበር ሊባል ይችላል ነገርግን ውጤት አይመጣም። እና ሁለተኛው ከእናንተ የሚጠበቀው ያወቃችሁትን እውቀት እና ልምድ ለመተግበር መትጋት ነው። ለመወሰን ብቻውን በቂ ስላልሆነ በመተግበር ውጤት ለማምጣት ይሄ አካዳሚ ከእናንተ የሚጠብቀው ጉዳይ ነው።

ሶስተኛው ከእናንተ የሚጠበቀው ጉዳይ የአላማ ጽናት ነው። የአላማ ጽናት አንድ የምንፈልገውን ነገር ለማሳካት የሚገጥመንን ፈተና ለመቋቋም መቻል ማለት ነው።

የተከበራችሁ ሚኒስትሮች ዛሬ የኢትዮጵያን ህልውና ለማስጠበቅ ብዙ ጄነራሎች፣ ኮሎኔሎች ከእናንተ በላይ የቆዩ ልምድ ያላቸው ሰዎች በላስቲክ ውስጥ፣ በሽራ ውስጥ፣ በየተራራው እየተኙ ነው። እነሱን እዛ አስተኝተን ነው እዚህ ሶፋ ላይ ተቀምጠን የምንወያየው ብዙ አትደነቁ ቤቱ ጠባብ ቢሆን ከከፋ ድንኳን ውስጥም ስለሚተኛ፣

ላስቲክም ውስጥ ስለሚተኛ፣ ዛፍ ጥላ ስርም ስለሚተኛ ይሄን ያልተለማመደ ሰውና የአላማ ጽናት የሌለው ሰው የምንፈልገውንና የምንሻውን ሰው ለማምጣት ይቸገራል። ምክንያቱም ግብርና ሚኒስቴር እያልን ያለነው ቦቴ አድርገህ ከአርሶአደር ጋር ዋል ነው እንጂ በእንደዚህ በሚያምር ቦታ አይደለም ዋል እያልን ያለነው። ንግድ ሚኒስቴር በየቦታዎቹ ምርቶችን አይተህ እነዛን ምርት ከገዢ ጋር አገናኝ ነው እያልን ያለነው፡ ፡ የበለጠ ፈተና፣ የበለጠ ችግር፣ የበለጠ ተግዳሮት አልፈን ነው የምንለውን ነገር የምናሳካው እና የአላማ ጽናት ከሌለ ውጤት ማምጣት እንቸገራለን። እያንዳንዱ መሪና ራሱን ሥራውን ከውቅያኖስ ጋር እያገናዘበ ማየት አለበት።

ውቅያኖስ ሲደክመን ከዳርቻ ጋር ተቀምጠን ስናይ እጅግ የሚያዝናና፣ ገባ ብለን ስናይ፣ በመርከብ ስንጓዝ፣ በጀልባ ስንጓዝ፣ በወጀብ ስንጫወት በጣም የሚያስደስት ነገር ነው። ውቅያኖስ ማየት የማይፈልግ፣ በውቅያኖስ ዳር የመዝናኛ መስራት የማይፈልግ፣ ውቅያኖስ ዳር ቤቱን መስራት የማይፈልግ ሰው የለም። ደስ ይላል። ስልጣን መያዝም የማይፈልግ ሰው ብዙ የለም፣ ደስ ይላል። ኩብራ አለ፣ አጃቢ አለ፣ ብዙ ነገር አለ። ግን ውቅያኖስ እና ስልጣን ብዙ ጊዜ የተረጋጉ አይደሉም። ያ ያዝናናችሁ ውቅያኖስ አንድ ቀን በወጀብ ተነስቶ ፎቁን አፈራርሶ፣ መንደራችሁን ሊያጠፋ ይችላል።

አንድ ቀን ልጆቻችሁን ይዛችሁ ገብታችሁ አንዱን ወስዶ ሊሄድ ይችላል። ወጀብ አለ፣ አውሎ ነፋስ አለ፣ መናጥ አለ፣ ውበት ብቻ ሳይሆን ፈተና አለው። ለአይን መማረክ ብቻ ሳይሆን አይናችንን ገልጠን ማየት እስክንፈራ ድረስ የሚያስፈራ አደጋ እና ወጀብ አለው። በዚህ ስልጣን ውስጥ ሁለት ነገር አለው። አልፎ አልፎ የተረጋጋ እና የሚያምር የሚያስመስል ነገር አለ፣ አልፎ አልፎ ደግሞ ፈተናው ሲመጣ የምንቸገርባቸው ጊዜያቶች አሉ። እነዚህን ፈተናዎች እንደ አሳ ሳይሆን እንደ እንቁራሪት ሆነን መሻገር ይኖርብናል። አሳ እየዋኘ ከፊቱ ድንጋይ ከገጠመው በዋና ነው ድንጋዩን የሚያልፈው፣ እየዋኘ ከፊቱ እንጨት ቢገጥመው በዋና ነው እንጨቱን የሚሻገረው፣ መንገዱ አንድ ነው መዋኘት ነው። ወይም ባጠረ ወይም

በረዘመ መንገድ። እንቁራሪት ግን ትዋኝ ትዋኝ እና እንቅፋት ከገጠማት ትዘላለች። መሪ መዋኘት እና መስፈንጠር እየቻለ ከሄደ በፈተና ጊዜ፣ በጋሬጣ ጊዜ፣ በታኮ ጊዜ በኖርማል ከሚሄደው የላቀ መጓዝ የሚያስችል ሁኔታ ሊፈጠር ይችላል። አሁን ለምሳሌ እየሰማን ባለናቸው አንዳንድ ጩኸቶች ከኖርማል ዋና ወጥተን መስፈንጠር ብንችል ታሪክ ቀያሪ እውነት ሊሆን ይችላል። ለመዋኘት ብቻ ሳይሆን ለመስፈንጠር፣ ለመዝለል፣ ለመሻገር የሚያበቃ ጥበብን መልበስ ያስፈልጋል። ይሄንን ካደረግን በኢትዮጵያ ውስጥ የልመናን፣ የሌብነትን ቅርንጫፉን ሳይሆን ስሩን እንነቅላለን። ከስሩ ከነቀልን ልጆቻችን አይለምኑም፣ አንድ አመት፤ ሁለት አመት ስንዴ ለምነን ማስቀጠል ተስኖን ከተውን ግን ቅርንጫፉን ነው የምንቆርጠው እንጂ ስሩ ካልተነቀለ ይመጣል ተመልሶ።

ሌብነትን በእናንተ ደረጃ ብናስቆምና ከስር ያሉ ሰዎች ደግሞ በትናንሽ ሳንቲም የሚጫወቱ ከሆነ ትርጉም የለውም። ከስሩ መንቀል ነው። ሌብነትና ልመናን ከስሩ ስንነቅል የምናስበውን ብልጽግና ልናመጣ እንችላለን። የምናመጣው ብልጽግና ሊመጣ የሚችለው ግን በአንድ ቀላል ምሳሌ ነው። ጂኦሎጂስቶች እንደነገሩንና እንዳስተማሩን የአባይ ወንዝ ጀግንነት፣ የአባይ ወንዝ ማስፈራራት፣ የአባይ ወንዝ መፈለግ የመጣው ወንዝ ከመሆኑ ብቻ አይደለም። አንድ ወጥ ሆኖ ነው ለሚሊየን አመታት በአንድ ጅረት እየተጓዘ ሳያቋርጥ እየተጓዘ ሜዳውን ሸለቆ ስላደረገው። ይሄ አሁን ያየነው ሸለቆ ሲፈጠርም አልነበረም። አባይ እየተጓዘ እየተጓዘ ዳገቱን እያፈረሠ መንገድ እየመረጠ ሸለቆ አደረገው። ሸለቆ ሲያደርግ የራሱን መንገድ አበጀ ማለት ነው። ማንም ሰው ባሻው ወደፈለገበት እንዳይወስደው በተከታታይ በሆነ እርምጃ እዚህ ጎሃ ጽዮን አካባቢ አባይን እንኳን ልታርስበት ወርደህ ልትጠጣውም ፈተና የሆነበት ዋናው ምክንያት ለሚሊየን አመታት እየተጓዘ የተፈጠረው ጎርጅ ነው።

ራሱን የሚከላከልበት፣ የራሱን አውድ የሚጠብቅበት፣ አባይን ለመገደብ you have to go all the way down ድንበር ድረስ። ዘላቂ የሆነ የስራ

ልምምድ ዘላቂ የሆነ ውጤታማነት፣ ኮንቲኒየስ የሆነ ያለመርካት ልምምድ ካለን ካለጥርጥር ኢትዮጵያ የማትደፈር፣ ረጅም ርቀት መጓዝ የምትችል፣ የምትረዳ ሳይሆን የምትረዳ ሀገር ማድረግ እንችላለን። ይቻላል። ኢትዮጵያን ከልመና ታሪኳ ማውጣት ከቻላችሁ ኢትዮጵያን ስንዴ ረጂ ካደረጋችሁ፣ የኢትዮጵያ ህዝብ በልቶ ጠግቦ ማደር ልምምዱ ካደረጋችሁ የተሰጣችሁ ባዶ ቼክ ትሪሊየን ሳይሆን የማይቆጠር ቁጥር ተጻፈበት ማለት ነው። ያ ቁጥር ለእናንተም፣ ለልጆቻችሁም፣ ለዘር ማንዘራችሁም ተመንዝሮ የማያልቅ ስለሚሆን የኔ እና የእናንተ ስራ መሆን ያለበት ከዚህ አካዳሚ ስንወጣ በተባበረ፣ በተስማማ፣ በተከባበረ ማንነት እነዚህን ታሪኮች መቀየር የሚያስችል ረዘም ያለ ካፒታል ማስቀመጥ ነው። ለዚህ ደግሞ ትሁት መሆን፣ ቻይ መሆን፣ ሰው መሆን በጣም በጣም አስፈላጊ ነገሮች ናቸው።

ለምሳሌ እኔን ብትወስዱ መቀለድ አልፈልግም። የተሰጠኝን ካርድ መጠቀም እፈልጋለሁ። ባለፉት ሶስት አመታት እንደነበረው ጨዋታ ማስተናገድ አልፈልግም። አሁን ለዚህ ርዕይ የተሰጠ ሰው ካለ አብሮ መስራት ካልሆነ መንገድ መልቀቅ ነው እንጂ ከእንትን ሰፈር ስለመጣሁ፣ ሃይማኖቴ እንደዚህ ስለሆነ፣ ፌስቡክ አርበኛ ስለሆንኩ አይሰራም። እሱ ባለፈው ሶስት አመታት ቀርቷል። ይሄን ካርድ ማባከን ማለት የሚጻፈው ቼክ ላይ ስርዝ ድርዝ ማስቀመጥ ማለት ነው። ቼኩ እንዳይሰራ ማድረግ ማለት ነው። ለዚያ እኔ ፍቃደኛ አይደለሁም እናንተም እንደሱ አትፈልጉም ብዬ ተስፋ አደርጋለሁ። በተባበረ ክንድ ሰርተን ታሪክ ቀያሪ እንድንሆን እንድትጥሩ፣ እንድትለፉ፣ ባቃታችሁ ቦታ ደግሞ ወንድሞቻችሁን እንድትጠይቁ የኢትዮጵያ ህዝብ ደግሞ ልፋታችንን፣ ድካማችንን ካየ ለማገዝ ፍቃደኛ ስለሆነ በቅንነት ማገልገላችንን ካየ ተባባሪ ስለሚሆን በዛ መንፈስ ሰርተን ኢትዮጵያን የሚቀይር ነገር ማድረግ ይጠበቅብናል።

ይሄን ለማድረግ ሀ ብለን ጀምረን የዛሬ ሳምንት ስንወጣ የተለየ ማንነት እና ቅርጽ እንይዛለን። በዚያም  በተግባር ልምምድና ወጥነት ባለው ባህሪ የኢትዮጵያን

ብልጽግና ፋውንዴሽን እንጥላለን የሚል ጽኑ እምነት አለን። ይሄ አምስት አመት የፖለቲካል አውዱን ባህሪ የሚቀይር መሆን አለበት። አሁን ያለውን፣ ስትጣላ መተያየት የማትፈልግበትን አውድ መቀየር፣ ለመነጋገር፣ ለመወያየት ዝግጁ የሆነ የፖለቲካ ጸብ ሀገር የማያፈርስ እንዲሆን ፋውንዴሽን የምንጥልበት መሆን አለበት። ኢኮኖሚውን በሚመለከት ቢያንስ አምርተን መብላት የምንችል፣ ስንሸጥ ሌሎች የሚያስፈልጉንን ነገሮች ማምጣት የሚያስችል የመሸጥ አቅም እንዲፈጠር መስራት ይኖርብናል። ዲፕሎማሲውን በሚመለከት ሰጥቶ በመቀበል መርህ የምናምን፣ ሰው ባሻው ጊዜ የሚኮረኩመን ሳይሆን አይ ከኢትዮጵያ ጋር ስለሆነ ደጋግመን እናስብ ባረጀ ቀመር አይሳካም። አዳዲስ አልጎሪዝሞች መጻፍ አለብን ብለው እንዲያስቡ ማስገደድ የሚያስችል፣ በመከባበር ላይ፣ በመፈቃቀድ ላይና በጋራ በመተሳሰብ እና በብልጽግና ላይ የምንሰራ መሆን አለብን። ህግ አስፈፃሚው ኤጀንሲዎች መቶ ውጊያ የሚዋጉ ሳይሆኑ ውጊያን የሚያስቀሩ እንዲሆኑ አድርገን መፍጠር አለብን። ውጊያን እየተዋጉ የሚያሸንፉ ሳይሆኑ ውጊያን ሳይዋጉ የሚያስፈራሩ እና ውጊያን የሚያስቀሩ አድርገን መፍጠር አለብን።

ከፊታችን በጣም ብዙ ስራ ነው ያለው፣ አድካሚ ስራ ነው ያለው። ይሄንን ስራ በተሳካ መንገድ ለመስራት እጅ ለእጅ መያያዝ፣ መተባበር፣ በጋራ መስራት ያስፈልጋል። በጋራ ከቆምን እና ለውጥ ካመጣን የተሰጠን ቼክ ውጤታማ ይሆናል። ይሄን ለማድረግ የኢትዮጵያ ህዝብ ይረዳችኋል፣ ፈጣሪም ይረዳችኋል፣ ልባችሁን ማንጻት፣ አእምሯችሁን ማንጻት በቀና ልቦና ለመስራት መሞከር ይኖርባችኋል። መከናወን በፍላጎት ብቻ አይመጣም፣ መከናወን ከቅንነት ጋር የተሳሰረ ስለሆነ፣ ስኬት ከልብ ቅንነት ጋር የተሳሰረ ስለሆነ። ስታልም ብታድር ቅንነት ከሌለ መከናወን አይሰጥህም። መከናወን እንዲሰጠን የልብ ቅንነትና የእጅ ንጽህና ያስፈልጋል።

በመጨረሻም ይህ ካቢኔ፣ ይህ ሚኒስትር እና ሚኒስትር ዴኤታ የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሚኒስትሮች ናችሁ። ሚኒስቴር ውስጥ የአንድ ብሄር ተወካይ

የለም። ኢትዮጵያን ለማገልገል መዘጋጀት አለባችሁ ሁላችሁም። ከእንትን ሰፈር ነው የመጣሁት፣ ከእንትን ብሄር ነኝ እያልን የምናስብ ከሆነ ቼኩ ስርዝ ድልዝ ነው የሚሆነው አይሳካልንም። ሁሉም ኢትዮጵያዊ ማደግ አለበት፣ ሁሉም ኢትዮጵያዊ እኩል እድል ማግኘት አለበት፣ ሁሉም ኢትዮጵያዊ መለወጥ አለበት። ያንን ካላሳካን ሰፈራችን ብቻ ቢቀየር ለውጥ አናመጣም። የኢትዮጵያ ሚኒስትር፣ የኢትዮጵያ መሪ፣ የኢትዮጵያ አገልጋይ ለመሆን ራሳችሁን ማሳመን አለባችሁ። ሰፈር ውስጥ ከገባን እንቸገራለን። እነዚህን በማድረግ በሳምንት በምታገኟቸው ልምዶች እስካሁን ከነበርንበት የተሻለ ስራ ለመስራት የተመቻቸ ነገር ይፈጠራል ብዬ ተስፋ አደርጋለሁ።

እንግዲህ እኛ ጋር መሆን ሲገባቸው የቀሩ ሰዎች ስላሉ በስህተት የገባን ሰዎችም ካለን እየተሸጋሸግን እንሄዳለን ማለት ነው። በስህተት እዚህ ሥፍራ ያለ ካለ በየጊዜው በሚኖረው ጨዋታ እየተሸጋሸገ በስህተት የገባው እየወጣ በስህተት የወጣው ደግሞ እየገባ ይሄዳል ማለት ነው። ለምን? ቼኩ ላይ ስርዝ ድልዝ ስለማይፈቀድ። ቼኩ ላይ ረዘም ያለ ካፒታል ማስቀመጥ ስለሚያስፈልግ ይሄንን እድል ማጣት ስለማያስፈልግ እንደዛ አይነት ስራ ከፊታችን ሊኖሩ ይችላሉ። የተሳካ የስራ ዘመን እንዲሆንላችሁ እመኛለሁ፣ የተሳካና ያልተበላሸ ቼክ እንድታኖሩም እመኝላችኋለሁ። በትብብርና ትግግዝ መንፈስም የኢትዮጵያን የብልጽግና መሰረት ለመጣል እንድንነሳ አደራ እላችኋለሁ። መልካም የስልጠና ጊዜ ይሁንላችሁ፣ መልካም የመተዋወቂያ ጊዜ ይሁንላችሁ፣ ቀሪው ጊዜ የስኬት ይሁንላችሁ። ኢትዮጵያ በእናንተ አመራር በልጆቿ ጥረትና ትጋት ታፍራና ተከብራ ትኑር። በጣም ነው የማመሰግነው። በድል በሚቀጥለው ሳምንት ዲግሪያችሁን ስትይዙ እንገናኛለን!

**አመሰግናለሁ!**

ጥቅምት 1፣ 2014 ዓ.ም


ትውልደ መደመር

# የጥቅምት 24/2013 ዓ.ም መታሰቢያ ንግግር በመከላከያ ሚኒስቴር

ኢትዮጵያ የጀግኖች ሀገር ናት። ልባም ልጆችዋ አጥር ሆነው የጋረዷት፣ ዋጋ ከፍለው ያደመቋት፣ ተቆጥሮ በማያልቅ መሥዋዕትነት ታፍራና ተከብራ የኖረች ሀገር ናት። የሩቁ ቢዘነጋን እንኳን፣ አምና ጥቅምት 24 ግፍ የተፈጸመባቸው ጀግኖቻችን ታሪክ ፈጽሞ የሚረሳ አይደለም። እያንዳንዳችን የጀግኖቹ ዕዳ አለብን። ዛሬ የቆምነው ለእኛ ሲሉ የግፍ ጽዋን በተጎነጩ ጀግኖቻችን አጥንት ላይ ነው። እነዚያ ብርቅዬ የኢትዮጵያ ልጆች "ከወገኔ በፊት እኔ ልቅደም" ብለው ደማቸውን ለአፈር፣ ሥጋቸውን ለአሞራ ባይሰጡ ኖሮ የዛሬው ቀን ዛሬን ባልመሰለ ነበር።

የሰሜን ዕዝ ሠራዊት የተደራጀው ከአንድ አካባቢ አልነበረም። አማራና ኦሮሞው፣ ሲዳማና ወላይታው፣ አፋርና ጋምቤላው፣ ጉራጌና ሐድያው ከሁሉም ብሔር ተውጣጥቶ ሀገር እንዲጠብቅ የተደራጀ ሠራዊት ነበር። ሀገሬን ብሎ ለሃያ ዓመታት ከቤቱና ካሳደገው ቀዬ ተነጥሎ ዱር እያደረ ድንበር ሲጠብቅ ኖሯል። ሠራዊቱ ለትግራይ ክልልና ለሕዝቡ ከደግነት ውጭ ክፉ ሆኖ አያውቅም። ጠላት ሲመጣ የሚመክት፣ አዝመራ ሲደርስ የሚያጭድ፣ በማኅበረሰባዊ ተግባራት ላይ የሚካፈል ነበር። በደምና በላቡ ለከፈለው ደግነት በምላሹ ከሽብር ቡድኑ ሕወሐት የተቀበለው ክህደት ነው።

ኢትዮጵያን ለመውረር የመጡ ጠላቶች እንደ ሽብር ቡድኑ ዋነኛ የጦር ቤዛችንን በመደብደብ አልጀመሩም። ዋና ዋና መኮንኖችን በመግደልና ከባድ መሣሪያዎቻችንን ዘርፈው አልተነሡም። የጦርነት ቅዱስ ባይኖርም ለጭካኔም ልክ አለው። በሽብር ቡድኑ ልክ ኢትዮጵያ ላይ የጨከነ የለም። ጥቅምት 24 ሠራዊቱ ላይ የክህደት ጥቃት

ሲፈጸም የሞቱት እነዚያ ጀግኖች ከመላው ኢትዮጵያ የተውጣጡ እንደመሆናቸው የተፈጸመባቸው ግፍ በኢትዮጵያ ላይ የተፈጸመ ግፍ ነው።

የሽብር ቡድኑ በሰሜን ዕዝ ላይ የፈጸመው ጥቃት መሣሪያ ለመዝረፍ ብቻ የተደረገ ተራ ጥቃት አልነበረም። በተንኮል የተቀመመና በክፋት የሞላ መሆኑ የተለየ ያደርገዋል። የገዛ ጓዶቹን አስኮብልሎ በተኛበት ከመግደል ባለፈ ከሬሳው ላይ ልብሱን ገፍፎ የአውሬ ቀለብ እንዲሆን እርቃኑን ሜዳ ላይ ጥሎታል። ይኼን ሲያደርግ የሽብር ቡድኑ ዓላማ ሁለት ነው። አንደኛ ሠራዊቱ በሐፍረት በትር እየተቀጣ ሞራሉ እንዲላሸቅና የአቅመ ቢስነት ስሜት እንዲሰማው። ሁለተኛ ሠራዊቱ እርስ በእርስ እንዳይተማመንና "ክፋና ደጉን አብሮ ከተካፈሉኝ ጓዶቼ እንደዚህ ዓይነት ነውር ዛሬ ከተፈጸመብኝ ነገስ?" ብሎ እንዲጠራጠር ለማድረግ ታስቦ ነበር። ዳሩ ግን ሠራዊቱ እንደተጠበቀው አልሆነም።

የወንድሞቹ ደም በከንቱ መፍሰስ ያንገበገበው ሠራዊት በፍጥነት ራሱን አደራጅቶ በሦስት ሳምንት ጊዜ ውስጥ የሽብር ቡድኑ ያደራጀውን ኃይል ወደ በርሃ እንዲበተን ማድረግ ችሏል። የቡድኑን ቁንጮ አመራሮች አብዛኞቹን ይዞ ለሕግ አስረክቧል። የተፈጸመበትን ክህደት በበቀል ሒሳብ ሳይሆን የሕግ ማስከበር መርሕን በተከተለ መንገድ ሲያከናውን ነበር። በጦርነት ውስጥ ለመርሕ መገዛት ቀላል አይደለም። ሠራዊታችን ባለፈው አንድ ዓመት ውስጥ ከሽብር ቡድኑ ጋር እያሌ ውጊያዎችን ሲያደርግ ብዙ ዋጋ ከፍሏል። በየጦር ውሎው በጀግንነት እየተዋጋ ለእናት ሀገሩ ተሠውቷል። ለሀገርና ለወገን ያለውን አጋርነት በንግግር ሳይሆን በተግባር አሳይቷል። አሁንም በዱር በገደሉ እየተዋደቀ ነው።

ዛሬ ሽብር ቡድኑ የተሰጠውን የጥሞና ጊዜ እንደ እድል ከመጠቀም ይልቅ እንደ ድል ወሰደው። በአማራና በአፋር ክልል በሚኖሩ ወገኖቻችን ላይ የግፍ በትሩን ቀጥሎበታል። የጥፋት አጋሩ ሸኔም በኦሮሚያ ክልል ወለጋ አካባቢ ልዩ ልዩ አደጋዎችን

እየጣለ ኢትዮጵያና ኢትዮጵያውያንን ረፍት እየነሣ ነው። ሌሎችም የጥፋት ኃይሎች ከውስጥም ከውጭም ወኪሎቻቸውን አስተባብረው በሙሉ ዐቅማቸው ኢትዮጵያ ላይ መዝመታቸውን ገፍተውበታል።

ሠራዊታችን ብቻውን ተጋፍጦ የድል ዜና እንዲያበስረን መጠበቅም ሞኝነት ነው። ጠላቶቻችን ተባብረው የደቀኑብንን አደጋ ሁላችንም ተባብረን ካልመከትነው ድል የማይታሰብ ነው። የጠላቶቻችን ኅብረት ለፕሮፓጋንዳ የተፈበረከ ጉዳይ አይደለም። እውነት ነው። እነዚህ ኃይሎች ዓላማቸው ግልጽ ነው። ብረት ያነሡት ሀገር ለማፍረስ እንጂ ሀገር ለመገንባት አይደለም። የኢትዮጵያን ስም በክፉ የሚያብጠለጥሉ፣ ነገ የሊቢያና የሶርያን እጣ ሊያስታቅፉን እንዲመቻቸው የፈጠሩት ዘዴ መሆኑን ልናውቅ ይገባል። ጠላቶቻችን በዚህ ደረጃ ሲተባበሩብን እኛ አንድ የማንሆንበት ምንም ምክንያት የለም። የወንድምና የእኅቶቹ ጥቃት የሚያንገበግበው ሁሉ ጣት ከመጠቆም ወጥቶ ሀገር የማዳን ፍላጎቱን በተግባር መግለጥ አለበት።

ወደፊት ታሪክ ፍርዱን ይሰጣል። ፈሪውም በፈሪነቱ፣ ሴረኛውም በሴረኛነቱ እንደየግብሩ ይመዘገባል። የሽብር ቡድኑን ትውልድ በክህደት ሲያስታውሳቸው እንደሚኖር ግልጽ ነው። በተቃራኒው በግፍ የተሠውት የሰሜን ዕዝ አባላትን ጨምሮ ለሀገር የሚዋደቁ ጀግኖች ስማቸው በወርቅ ይጻፋል።

**ክብር ኢትዮጵያን ሲሉ ለተሠዉ ጀግኖቻችን!**
**ኢትዮጵያ በልጆቿ ጥረት ታፍራና ተከብራ ለዘላለም ትኑር!**
**ፈጣሪ ኢትዮጵያንና ሕዝቦቿን ይባርክ!**

ጥቅምት 24 ቀን 2014 ዓ.ም



# ኢትዮጵያ አትፈርስም

ኢትዮጵያን ማንበርከክ ይቻላል ብለው የተነሱ ሃይሎች አንዳንድ ጊዜ ምን ነካቸው ብለን እኛ ሰላማዊ ህዝቦች ስለሆንን በዚህ ልክ ሀገራችንንና ህዝቦቻችንን ለመጉዳት አስበው የሚነሱት የሚል ጥያቄ በውስጤ የሚፈጠር ቢሆንም ኢትዮጵያ የተፈተነችው በአቅሟ ልክ ነው ሌላው ቢሆን አይፈተንም፡፡ በፕሮፖጋንዳ ፈተኑን አዲስ አበባ ተከባለች ፈርሳለች ውጡ ወጥተዋል፣ ኬንያ ናቸው ጅቡቲ ናቸው ሸሽተዋል ያልተባለ ነገር የለም። በወሬ አንፈታም፤ ሊከፋፍሉን በጣም በርካታ ጥረት እያደረጉ ነው። ይበልጥ አንድ እየሆንን እናሳያቸዋለን። አሁን ሀገራችንን በብዙ መልኩ በኢኮኖሚ፣ በዲፕሎማሲ፣ በሚዲያ ፕሮፖጋንዳ ወይም በሳይኮሎጂካል ዋርፌር እንዲሁም በምድር ላይ ያሉትን ሃይሎች እንዲህ ብትገቡ በዚህ ብትወጡ እያሉ ጋይድ የሚያደርጉ ሃይሎች ተደምረው በኢትዮጵያዊያን የተባበረ ክንድ ይሸነፋሉ። ኢትዮጵያን ለማፍረስ የተባበረው ሀይል ኢትዮጵያን ለመዋጥ የተነሳው ዘንዶ በጣም በቅርብ ተወግቶ፣ ወድቆ፣ ፈርሶ ኢትዮጵያ ደግሞ ለምልማ ባንዲራዋም ከፍ ብሎ የምናይበት ጊዜ ይመጣል።

ሰዎች ህይወታቸውን ገብረው እኛን የሚያፈርሱን ከሆነ እኛም ህይወታችንን ገብረን ኢትዮጵያን እናቆያታለን። ዛሬ መሰባሰባችሁ እጅግ አግባብ ነው፣ ለመልካም ለበጎ ነገር ተሰባስባችኋል። ይህ መድረክ ጠያቂ መኖር የለበትም የተለየ መላሽ የለምና፡፡ ተጫዋች እና ተመልካች መለየት የለበትም፡፡ እያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ ሀገሩን የሚወድ ለትውልድ ነጻ ሀገር ማሸጋገር የሚፈልግ ገንዘብ ያለው በገንዘቡ፣ እውቀት ያለው በእውቀቱ፣ ጉልበት ያለው በጉልበቱ እያንዳንዱ ሰው ሰፈሩን ሀገሩን፣ መንደሩን ጠብቆ ማሻገር ሃላፊነት እንዳለበት እየተሰማው በተባበረ ክንድ ሰላማችንን፣ በተባበረ

ክንድ የተዘመተብንን ዘመቻ ለማሸነፍ በጋራ እንድንቆም እንደ ከዚህ ቀደሙ ጠያቂ ብቻ ሳይሆን አሁን ላለው አንገብጋቢ ጉዳይ መላሽም እንድትሆኑ አደራ ልላችሁ እፈልጋለሁ።

በመጨረሻም በቅርቡ እንዲሁ እንደእናንተ ሰብሰብ ያለ ሃይል ደሴ ሲያዝ፣ ኮምቦልቻ ሲያዝ የከተሞችን ስም ጠቅሰው ጠቅላይ ሚኒስትሩ ወዴት አሉ? ለምንድነው ወጥተው የማይናገሩት? ድምጻቸውን መስማት ያሉበትን ነገር መስማት እንፈልጋለን ብለውኝ ሰምቼ አንድ ቦታ ሄጄ ነበር እና የነገርኳቸውን መልእክት ነግሬያችሁ እጨርሳለሁ። በመጀመሪያ የሙስሊም ወንድሞቼ አሁን ለምናገረው ምሳሌ ልክ እንደታሪካው ምሳሌ ብቻ እንድትወስዱት ምንም አይነት ሃይማኖታዊ ትርጉም እንዳትሰጡት የሚመች ስለሆነ ምሳሌውን እንድጠቀም ፍቀዱልኝ።

እንደ ታሪክ ነው እንደ እምነት አይደለም። በመጽሃፍ ቅዱስ ውስጥ አንድ የሚገርመኝ ታሪክ አለ። እየሱስ ክርስቶስ ከሚከተሉት ሰዎች ጋር በአንድ ቦታ እየተሻገረ አንድ ላይ እየተሻገሩ ማእበል ይነሳ እና አብረውት ያሉት ሰዎች ስንጠፋ አይገድህም፣ ስንሞት አይገድህም ወይ? የሚል ጥያቄ አነሱለት። ሃይማኖታዊ አስተምህሮት አለውና ብዙ ጊዜ የሚሰብኩ ሰዎች ተነስቶ ማእበሉን እዘዘው ይላሉ። እኔን ግን የሚገርመኝ በዚያ ለሊት ከዚያ ማእበል ካለበት ስፍራ ራቅ ብሎ ሌላ ቦታ ላይ ተቀምጦ እያያቸው ቢሆንና መሞታችን አይገድህም ወይ ቢሉት አይገርመኝም። ከነሱ ጋር በአንድ ጀልባ እያለ ችግር ቢመጣም በአንድ ጀልባ እንደሚወሰዱ እያወቁ የኛ ህይወት ሲጠፋ አይገድህም ወይ አሉት? አንዳንዶች አይይ ጌታ መሆኑን ስለሚያውቁ ነው ይላሉ፡፡ እንደሱ አይደለም ምክንያቱም ተነስቶ ማእበሉን ካቆመው በኋላ ይሄ ሰው ማን ነው ብለዋልና። እና ጠቅላይ ሚኒስትሩ ወዴት አለ? ለምትሉ ጀልባዋ ላይ ነው ያለው። በእያንዳንዱ ማእበል መካከል ነው ያለው ህዝቡን፣ ሠራዊቱን፣ የሀገር ሽማግሌዎችን፣ ሴቶችን ሁሉ አስተባብሮ ነጻ ሆና የተረከባትን ሀገር ነጻ ሆና ያስረክባል። አርሶአደር ሳይደክም እጁ ሳይቆሸሽ እንደማይዘራው፣ እንደማያርሰው፣ እንደማያጭደው ሁሉ

ኢትዮጵያን የሚያክል ታላቅ ሀገር በነጻነት ለማቆም የሚከፈል መስዋእትነት የግድ ነው። ያን መስዋእትነት ለመክፈል ኢትዮጵያዊ ሁሉ ዝግጁ መሆን ይጠበቅበታል። ከፊታችን እጅግ የሚገርም ፈተና፣ እጅግ የሚገርም ማእበል አለ። ይሄ ማእበል የሚያስከፍለውን ማእበል ሁሉ አስከፍሎ ወደሚገባት ብልጽግና ወደሚገባት ሰላም ያስፈነጥራታል። ኢትዮጵያ አትፈርስም፣ ኢትዮጵያ አትበተንም፣ ኢትዮጵያ ዛሬም እንደ ጥንቱ ጠላቶቿን አሸንፋ የአፍሪካ ፈርጥና ምሳሌ ትሆናለች ።

**አመሰግናለሁ!**

ጥቅምት 29፣ 2014 ዓ.ም



# የአብርሆት ቤተ መጻሕፍት ምርቃት

በመጀመሪያ ማስጀመርም ብቻ ሳይሆን ማስጨረስም ያስቻለን በብዙ አታካች በማይመስሉ ነገሮች አሳልፎ ለማስመረቅ ያበቃን ፈጣሪ የተመሰገነ ይሁን። ይህ ላይብረሪ ሁላችሁም እንደምታዩት ኢትዮጵያን ይመጥናል። ልካችንን የሚመጥነን ነገር እንደዚህ ነው፣ ልካችንን ሳናውቅና በልካችን ስንሰራ ብዙ ቦታ አይተን የምንቀናበት ቢኖረን ብለን የምንመኘውን ነገር በሀገራችን መስራት እንደሚቻል ጥሩ ማሳያ ነው። የዚህ ላይብረሪ ስያሜ አብርሆት ነው። “አብርሆት” ብዙ የተቆለፉብን ታሪኮች፣ የሃብት መፍጠሪያ መንገዶች የሰላም መፍጠሪያ መንገዶች ሁሉ መክፈቻ ቁልፍ ነው። ትልቁ ችግራችን ድንቁርና ስለሆነ። በድንቁርና ምክንያት እርስበርስ እንባላለን፣ በድንቁርና ምክንያት የሌለ ሃብታችንን እናወድማለን፣ በድንቁርና ምክንያት የገዛ ሀገራችንን ለጠላቶቿ ተላላኪ ሆነን እናጠቃለን። ይሄ ሁሉ የሚፈታው በተለይ ልጆቻችን ኢንላይትንድ ሲሆኑ ነው፣ ሲበራላቸው ነው፣ የሀገር ምንነት፣ የነጻነት ምንነት፣ የታሪክ ምንነትና ወደ ብልጽግና የመጓዝ ጠቀሜታ እና ፍሬ እንዲገነዘቡ ማድረግ የሚያስችል መሰረት ሲጣል ነው። ለዛ መሰረቱ ደግሞ እውቀት ነው፤ ለእውቀት ደግሞ እንዲህ ያለው ላይብረሪ ያስፈልጋል።

እውቀት ከድንቁርና ቀንበር ነጻ የሚያወጣ መንገድ ነው። ታሪካችንን ካላወቅን፣ ሀገራችንን ካላወቅን፣ ህዝባችንን ካላወቅን፣ የማድረግ አቅማችንን ካላወቅን፣ ከድንቁርና ልንከላከል አንችልም። ስለዚህ እውቀት በእጅጉ ለኛ ያስፈልጋል። ድንቁርና ጭለማ ነው፣ ጭለማ ያስፈራል፣ ይጠላል በጭለማ ውስጥ ያለ ማህበረሰብ የነቃ ነገር ማሰብ አይችልም። ከጨለማ የሚያወጣን ኢንላይትንድ የሚያደርገን የሚያበራልን ደግሞ እውቀት ነው። በአለም ላይ ካሉ ከ190 በላይ ሀገራት 18ቱ ብቻ ናቸው የራሳቸው ፊደል ያላቸው፣ በአፍሪካ አንድ ሀገር ብቻ ናት የራሷ ፊደል ያላት ያቺ ሀገር ግን ላይብረሪ የላትም። ከ18ቱ አንዱ ያደረገንን የአባቶቻችንን ድንቅ የብርሃን ውጤት፣ የእውቀት ውጤት የሆነውን ለልጆቻችን ማሸጋገር የምንችለው እንደዚህ አይነት ስፍራ ሲኖረን ነው። ክብርት ከንቲባ ላይብረሪ የሚያስፈልገው በየክፍለ ከተማው ነው፡፡ ይሄ በቂ አይደለም ማሳያና ጅማሮ ነው። የሚያስፈልገን ደግሞ ትልቅ እና ንጹህ ነው። ከውጪ በዲዛይን እንዳያችሁት ከ18ቱ ሀገራት አንዷ

ኢትዮጵያ መሆኗን የ18ቱንም ሀገራት ፊደል በማስቀመጥ ለማሳየት ሞክረናል። ይሄን ለማድረግ የፈለግንበት አንዱ ምክኛት ከ18ቱ አንዷ የአፍሪካ ሀገር ኢትዮጵያ ብቸኛዋ መሆኗን በማሳየት ይህ ቋንቋ፣ ይህ ጥበብ የነሱም ጥበብ መሆኑን አውቀው እንዲጠብቁትም ጭምር ነው።

የአፍሪካ ህብረት ቋንቋ ሁሉ ከሌላ አለም የመጣ ነው። የአፍሪካ ቋንቋ የአፍሪካ ህብረት የስራ ቋንቋ አይደለም። ይሄን በስራ በማሳመን እንደዚህ አይነት ነገር ማሳየት ሊያነቃ ስለሚችል ይሄ ላይብረሪ መልከ ብዙ የሆነ ነገር ለማስተማር ተደርጎ የተሰራ መሆኑን ከግምት እንድናስገባ ነው። ኢትዮጵያ ውስጥ ያልፈረሰ ነገር የለም፡፡ መንግስታት ሲሄዱና ሲመጡ ተቋማት ይፈርሳሉ። የሀገር ሃብት ያፈርሳሉ፣ ያልፈረሱ ነገሮች ኢትዮጵያ ውስጥ ካሉ እስልምና እና ክርስትና ብቻ ናቸው፣ መንግስት ሲቀያየር ከዘመን ዘመን ሳይፈርሱ ከሺህ አመታት በላይ የዘለቁ ተቋማት ካሉ እነሱ ናቸው። እነዚህ ደግሞ በቆይታቸው ልክ ብዙ ጽፈዋል። ብዙ ታሪክ፣ ብዙ ያልተነገረ፣ ያልታየ ታሪክ ይዘዋል። ኦርቶዶክስም ይሁን የሙስሊም ተቋማት ለሃይማኖት የሚስፈልገንን ብቻ አይደለም የያዙት ታሪካችንንም ይዘዋል።

እነዛ ድርሳናት መመርመር አለባቸው። ለሃይማኖት ዓላማ ብቻ ሳይሆን ለታሪክ ዓላማም መታወቅ አለባቸው። ብዙ የተጻፉ ያልተጻፉ የተነገሩ ታሪኮች ኢትዮጵያ ውስጥ አሉ፡፡ እነሱ ሁሉ ተሰንደው ለልጆቻችን እንዲሸጋገሩ ማድረግ ይኖርብናል። ያን ማድረግ ስንችል ታሪካችንን ስናውቅ ልካችንን ስናውቅ በዛው ልክ ለመመላለስ የሚያስችል ብቃት፣ ትውልድ እንዲፈጥር ማድረግ ስለሚረዳ።

በአፍሪካ ነጻዋ ሀገር፣ በአፍሪካ የራሷ የሆነ ፊደላት የፈጠረች ሀገር ለሺህ ዘመናት የቆየ እምነት ይዛ የቆየች ሀገር መድፈር ተገቢ አይደለም ብለው ጠላቶቻችን እንዲያስቡ ቀድመን ልካችንን ከጦርነት ከግጭት በፊት እንዲያውቁ ማድረግ አለብን። ያን ስናደርግ ብዙ ነገር እየተፈታና እየተቀረፈ ይሄዳል። ይሄ ላይብረሪ ቅድም ክብርት ከንቲባ እንደገለጹት በትልቀቱም በጥራቱም በማንኛውም መስፈርት ከምናየው የሚያንስ አይደለም። ባይበልጥ አያንስም፡፡ ጥሩ አይነት ስራ ተሰርቷል፡፡

እንደዚህ አይነት ጥራት ያላቸውን ነገሮች መጀመር ብቻ ሳይሆን መጨረስን፣ መጨረስን ብቻም ደግሞ ሳይሆን መገልገልና መጠበቅም ነው። ከተመረቀ በኋላ

መጠበቅም አለበት። ከተመረቀ በኋላ የሚቆሸሽ ከሆነ ከተመረቀ በኋላ የሚሰባበር ከሆነ ኢንቨስትመንቱ ኪሳራ ይሆናል። ይህ እንዳይሆን መላው የከተማው ማህበረሰብ የዩኒቨርስቲ ፕሬዝዳንቶች፣ የትምህርት ሚኒስቴር በቅርበት ላይብረሪውን መከታተል አገልግሎቱን ማሳደግ ይበልጥ ደግሞ አዲስ ሻል ያለ ላይብረሪ መስራት የምንችልበትን መንገድ ማሰብ መዘጋጀት ያስፈልጋል።

ልጆቻችን እድለኞች ናቸው፡፡ ታሪካቸውንና ማንነታቸውን ለማወቅ የሚያስችል ተቋም እየተገነባላቸው ይገኛል። ከለውጡ በኋላ እጅግ ፋይዳ ካላቸው ግንባታዎች ውስጥ አንዱ ይሄ ነው፡፡ ከዚህ በይበልጥ ደግሞ የሳይንስ ሙዚየም ነው። በትልቀቱም፣ በጥራቱም እጅግ ያማረ የሳይንስ ሙዚየም ከሸራተን ከፍ ብሎ እየተገነባ ይገኛል። የኛ ፍላጎት በጥቂት አመታት ውስጥ ቤተ መንግስቶቹ ከዚህ አካባቢ ወጥተው፤ ቤተመንግስቶቹ ውስጥ ታሪክ የሚጠናበት፣ ላይብረሪ ውስጥ የሚጻፍበት የሚነበብበት በነዚህ ፓርኮች ውስጥ ደግሞ የፊዚካል እንቅስቃሴ የሚደረግበት እና ለአይን መልካም ነገር የሚገበይበት በሳይንስ ሙዚየሙ ትላንትናን ብቻ ሳይሆን ነገር አርቀን የምንጎበኝበት፣ የቱሪስት መንደር እንዲሆን ነው።

በቱሪስት መንደር ውስጥ ላይብረሪ ከሌለ፣ ሆቴል ከሌለ፣ ፓርክ ከሌለ፣ ታሪክ ከሌላ አይሆንም። እዚህ አካባቢ ያሉ ግንባታዎች በጥቂት አመታት ውስጥ ሲጠናቀቁ ለብዙዎች ክፍት እንዲሆኑ የሚያስፈልግበት ዋና ምክን ያት ከ18ቱ አንዱ ኢትዮጵያ ናት ከምንል ቦታውን ለቱሪስት መክፈት በቀላሉ ስለሚያስተምር መጥተው አይተው ምን አይነት ታላቅ ታሪክ ጠገብና ነጻ ሀገር መሆኗን ለማወቅ ያግዛል። ይሄ እንዲሆን ሁሌም እንደምለው መደመር ነው። ያልተደመር ህዝብ፣ በጋራ መቆም ያልቻል ህዝብ አያሸንፍም፡፡ በዚህ ጦርነት በጋራ ቆመን አሸንፈናል፣ ነገም በጋራ እንቁም። የሚከፋፍሉ ድምጾች ከግራም ከቀኝም ይሰማሉ እነሱ ጥፋቶች ናቸው።

በጋራ መቆም አንድ መሆን ለሰላም ለልማት፣ ለብልጽግና መስራት ሁሉንም ሃሳቦች በተቻለ መጠን አቃፊ መሆን ለሰላም የተዘረጋ እጅ እንዲኖር ማድረግ የይቅርታ፣ የፍቅር ልብ አሁንም ያስፈልገናል። ብልጽግናን የምንሻ ከሆነ በይቅርታና በፍቅር ለማቀፍ የሚዘረጋ እጅ ሊኖር ይገባል። ስሜት ከስሌት ቀድሞ እንዳይገዛን ራሳችንን መግዛትና ኢንላይትንድ መሆን ያስፈልጋል።

ይሄንን ካደረግን ኢትዮጵያዊያን ራሳችንን የሚያኮራ ታሪክ አለን፡፡ ወደፊትም አዳዲስ ታሪኮች እየተፈጠሩ፣ እየተሰሩ ልጆቻችን በሰላም በብልጽግና የሚኖሩባትን ሀገር እንፈጥራለን።

ይህ እንዲሆን በትብብር መንፈስ በጋራ እንስራ፡፡ ስላደረጋችሁት ሁሉ እጅግ አድርጌ

**አመሰግናለሁ! ቀጣዩ የድል ዘመን ይሁንልን!**
**አመሰግናለሁ!**
ታህሳስ 23፣ 2014 ዓ.ም





# በኢፌዴሪ መከላከያ ሠራዊትን የመዘከሪያ እና የመከላከያ ሠራዊት ዋና መሥሪያ ቤት የማስመረቅ ስነ-ስርዓት ላይ ያደረጉት ንግግር።

ክቡር የቀድሞው ፕሬዝዳንት ዶ/ር ሙላቱ ተሾመ

የቀድሞ ጠቅላይ ሚኒስትር ሃይለማሪያም ደሳለኝ

የፌዴሬሽን እና የህዝብ ተወካዮች ምክርቤቶች አፈጉባኤዎች

ክቡር አቶ ደመቀ መኮንን

ክቡር ፊልድ ማርሻል ብርሃኑ ጁላ

ክቡር ጄኔራል አበባው ታደሰ

የተከበራችሁ እንግዶች፣ ሚኒስትሮች፣ አመራሮች ከሁሉ በላይ የኢትዮጵያ

ኩራት የሆናችሁ የጦር መኮንኖች

በቃላችሁ በመዝሙራችሁ የማንጨበጥ ነበልባል፤ እሳት ነን ለጠላታችን

ፍሙ ከሩቅ ይፋጃል እሳት ያቀልጣል ክንዳችን፣

ኢትዮጵያ በኛ ደም ደምቃ በአጽማችን ፍላጻ ተማክራ፣

እንደታፈረች እንድትኖር ከዘመን ዘመን ተከብራ

ከመሞት በላይ እንሙት ደማችን ሺህ ጊዜ ይፍሰስ

አየር አፈሯ ይባረክ ስሟ ሺህ ጊዜ ይታደስ

ስሟን ለማደስ እጅግ ከፍተኛውን ጀግንነት ለማሰብ የሚከብደውን ብቃት ስላሳያችሁ ኢትዮጵያ አብዝታ ታከብራችኋለች። በሀገራችን ባህል ላሸነፈ ሽልማት፣ ለተሸነፈ ምህረት መስጦት የታሪካችን ከፋይና ኢትዮጵያ የሚለው

ስም ትርጉም አካል ሆኖ የቆየ ነው።

እኛ የዛሬ ትውልድ የኢትዮጵያ ልጆች ከአባቶቻችን ልንማር የሚገባው ቁልፍ ጉዳይ ዘላቂ ድል ለማረጋገጥ በጀግንነት ተዋግቶ ደሙን አፍሶ፣ አጥንቱን ከስክሶ፣ ህይወቱን ገብሮ ማሸነፍ ብቻ ሳይሆን ከኔ ይቅር ብሎ ጠላት ለተሸነፈ እጅ ለሰጠ ምህረት ማድረግንም ጭምር የአባቶቻችን መገለጫና የወረስነው የጀግንነት አካል መሆኑ ሁልጊዜ በልባችን ሊኖር ይገባል። አባቶቻችን በጦርነትም በሰላምም እያሸነፉ ነው ሀገር ያጸኑት፡፡ ኢትዮጵያን ለሺህ ዘመናታ ሳትገዛ በነጻነት እንድትኖር ያደረጉት በአውደ ውጊያ ብቻ ሳይሆን በሰላም መድረክም አሸናፊ ሃሳቦች እያፈለቁና ቀድመው እየተገኙ ነው። በጥቂቱ ወደኋላ መለስ ብለን ታሪካችንን ገለጥ ብናደርግ ራስ ወልደ ጊዮርጊስ እና የከፋው ንጉስ ጋኪ ሾሮኮ ሲዋጉ በነበረው ውጊያ ራስ ወልደ ጊዮርጊስ ያሸነፉ ቢሆንም ንጉስ ጋኪን ከማረኩ በኋላ እንደምርኮኛ ሳይሆን እንደ ንጉስ ነበር ወደ ሸዋ ያመጧቸው። በእምባቦ ጦርነት ንጉስ ምንሊክ እና ንጉስ ተክለሃይማኖት በገጠሙት ውጊያ ንጉስ ምንሊክ ያሸነፉ ቢሆንም የቆሰሉትን ንጉስ አቅፈው፣ አክመው ወደ ጎጃም እንደመለሷቸው ታሪክ ይናገራል። በአድዋ ጦርነት በርስበርሱ ብቻ ሳይሆን ከውጪም በተደረገው ጦርነት ፊታውራሪ ገበየሁ ጉርሙን ያጡት ንጉስ ምንሊክ በሺህ የሚቆጠር ወታደር የሞተና የቆሰለባቸው ቢሆንም በአወደ ውጊያ ተዋግቶ ማሸነፍ ብቻ ሳይሆን ሲያሸንፉ ከኔ ይቅር ማለቱን ለኛ ለልጆቻቸው አስተምረውን አልፈዋል።

ትላንት ክስ የተቋረጠላቸው፣ የተሸነፉ ሃይሎች ክስ እንዲቋረጥና ከእስር ቤት እንዲወጡ ሲደረግ ከፍተኛ ቁጣ ቀስቅሷል። ይህ ቁጣ የተቀሰቀሰው በሁለት ቡድኖች ነው። አንደኛው ቡድን ኢትዮጵያ ውስጥ ጭር ሲል የማይወድ ሁል ጊዜ እያጋጨ በሰበር ዜና ብር የሚሰበስብ የት እንዳለ የማይታወቅ ካለበት ሆኖ ስንዋጋ ጦርነት አቁሙ የሚል፣ ስናቆም ተዋጉ የሚል አጉል ብልጣብልጥነት የሚያጠቃውና እምብዛም ጆሮአችንን የማንገልጥለት ቡድን ነው። ሁለተኛው ቡድን ግን በዜናው

ድንገተኝነት የደነገጠ፣ በነበረው ተጋድሎና ሁኔታ ጊዜውን ገንዘቡን ህይወቱን ለመስጠት የወሰነ ከያለበት ሀገር እና ክልል ታሞ ከሀገር እና ከህዝብ ጋር የዘመተ ይህንን እኩይ ጠላት አምርሮ የሚጠላና ከዚህ ጠላት ጋር የሚደረግ ማንኛውም ንግግር ኢትዮጵያን ይጎዳል ብሎ የሚያምን ቅን ተቆጭቷል። የዚህን ቅን ተቆጭ ሃይል መንግስት ሙሉ በሙሉ ይረዳል ያደምጣል ለማስገንዘብም ጥረት ያደርጋል። እነዚህ ቅን ሀገር ወዳድ ኢትዮጵያዊያን በውስጥም በውጪም የሚገኙ የአንዳንዶችን ከኛ ይቅር ማለት አምርረው የጠሉና የደነገጡ ወንድሞቻችን እንዲገነዘቡልን የምንፈልገው ይህ ጉዳይ እኛ መጀመሪያ ስንሰማው ያስደነገጥገን መሆኑን ነው።

ነገር ግን ደጋግመን ስናመነዥገው ግራ ቀኙን ስንፈትሽ ለኢትዮጵያ የሚበጅ ለኢትዮጵያ ዘላቂ ጥቅም የሚያግዝ የኢትዮጵያን ዘርፈ ብዙ ጠላቶች የሚቀንስ በአውደ ውጊያ ያገኘነውን ድል በሰላሙም መድረክ እንድንደግም የሚያደርግ የአባቶቻችን ልጆች መሆናችንን የሚያረጋገጥ መሆኑን እየመረረን የዋጥነው እውነት ነውና እናንተም ለሀገራችሁ ዘላቂ ድል ስትሉ ለሀገራችሁ ክብርና አሸናፊነት ስትሉ ደጋግማችሁ በማሰብ ይሄንን ውሳኔ እንድትቀበሉ በትህትና እጠይቃችኋለሁ። ውሳኔውን ለምን ለምትሉ? ይሄ ውሳኔ ኢትዮጵያን በጠንካራ አለት ላይ ለማኖር ነው። ጠላቶቿን ለመቀነስ ነው፣ ጉልበት ለመሰብሰብ ነው፣ ያልገባውና የሚከተል ማህበረሰብ ካለ አይኑን ገልጦ ለማየትና ከጥፋት ጎዳና እንዲመለስ ለማድረግ ነው። ሌላም በርካታ ምክንያቶች አሉት፡፡

ነገር ግን ትላንት ክስ አቋርጠን ከእስር ቤት እንዲፈቱ ያድረገናቸው ግለሰቦች ሁሉም በሚባል ደረጃ የመንግስት ስልጣን ይዘው በዚህ ሁኔታ ውስጥ የተሳተፉ በቀጥታ የሚወስኑ በቀጥታ የሚያዙ፣ አይደሉም። አንዳንዶች በታሪካቸው ምክንያት አግዝፈን የምናያቸው ቢሆንም አሁን ባለው ተጨባጭ ሁኔታ ከሁሉ ውሳኔ ሰጪነት መድረክ በቀጣይ የማይሳተፉ ሃይሎች ናቸው። ከዚህ በላይ ኢትዮጵያዊ ማንነታችንና ደግነታችን ሽማግሌዎች በእስር ቤት እንዲሞቱ የሚፈቅድ አይደለም፡፡ና ጀግኖች

ስለሆንን አዛውንቶች ቢቻላቸው ወደ ገዳም አልያም ወደ ቤታቸው እንጂ በእስርቤት እንዳይቆዩ ወስነናል።

ይህ ውሳኔ ዛሬ የሚመረንም ቢሆን እንኳን ውሎ ሲያድር ልጆቻችንን የሚያኮራ፣ የኢትዮጵያን አንድነት የሚያጸና መሆኑን ቅንጣት እንኳን አንጠራጠርም። የተከበራችሁ የኢትዮጵያ ህዝቦች ከውጪም ከውስጥም ለዚህ ጉዳይ የተሰለፋችሁ ዜጎች ይቅር ከኛ ብለን የለቀቅናቸው ሰዎች በማሸነፋችን ያገኘነው ጸጋ መሆኑን አትዘንጉ። አሸንፈን ይቅር ለማለት ያበቃን ፈጣሪ የተመሰገነ ይሁን፡፡ ለአንድ አፍታ ከሳምንታት በፊት ወደነበረው ሁኔታ መልሻችሁ ደብረሲና የነበረው ሃይል አዲስ አበባን ተቆጣጥሮት ቢሆን ኖሮ፤ እኛ ተሸንፈን ይህ ሃይል አሸንፎ ቢሆን ኖሮ ምህረት ለመስጠት ሳይሆን ምህረት ለመቀበል እድል ማግኘት ይችል ነበር ወይ? ምህረት መስጠት ከማሸነፍ ጋር የሚያያዝ ነው። ምህረት መቀበል ግን መሸነፍ ብቻ ሳይሆን የአሸናፊውን ልብም የሚጠይቅ ነው። ፈጣሪ ለኛ ድል የሰጠን ብናሸንፍ እንደማያሰክረንና ይቅር እንደምንል ስለሚያውቅ ጠላቶቻችን ደግሞ ቢያሸንፉ ኢትዮጵያን ማፍረስ ብቻ ሳይሆን የምህረት ልብ እንደሌላቸው ስለሚያውቅም ነው። ጀግኖች አሸናፊዎች፣ ምህረት ሰጪዎችም ስላደረገን ፈጣሪያችንን እናመሰግናለን።

ለነገሩ ይቅር የሚል እኮ መበቀል እየቻለ፤ ማሰር እየቻለ፤ መግደል እየቻለ የሚተው ነው። ይቅር ያልነው እየቻልን መሆኑን ልንገነዘብ ያስፈልጋል። ያሸነፍከውን ማሰር፤ የበደለህን መቅጣት የተለመደ ማንም ሰው ሊያድርገው የሚችል ተግባር የኛ ተግባር ከዛ እንዲለይ የተፈለገበት ዋናው ምክንያት የጠላቶቻችን ባህሪ፣ የጠላቶቻችን ጸባይ እኛን እንዲወርሰን አንፈልግም። ዘራፊነት፣ ሌብነት፣ ነፍሰ ገዳይነት፣ ሀገርን አፈርሳለሁ ብሎ በአደባባይ በኩራት መናገርን የመሳሰሉ ጥዩፍ ጠባዮች እኛን እንዲወርሱን አንፍቅድም አንሻም። በዚህም ምክንያት ጠላቶቻችን በለመዱት መንገድ ሳይሆን በተለየ መንገድ በመሄድ ኢትዮጵያን በማጽናትና በማላቅ ምንም እንኳን በድንገት ሲሰማ የሚያስደነግጥ ቢሆንም በዘላቂነት ሀገራችንን የሚያቆይና የሚያጸና፣

የሚያስማማ ሆኖ ስላገኘነው የተወሰነ ነው፡፡ በዚህ ውሳኔ ክስ የተቋረጠላችሁ ወገኖች ስላሸነፍን፣ መበቀል እየቻልን ይቅር ማለትን ስለመረጥን ክስ አቋርጠን እናንተን ሳይሆን ከእናንተ ጀርባ ያለውን ህዝብ አክብረን የወሰንነው መሆኑን አውቃችሁ ይሄን ድል ሳታበላሹ እንድትጠቀሙበት ላሳስባችሁ እፈልጋለሁ። ክስ ማቋረጥ ማለት ምህረት መስጠት ማለት አይደለም። ክስ የተቋረጠለት ሰው በአግባቡ መጠቀም ካልቻል መልሶ የክስ መዝገቡን መምዘዝ የሚቻል ስለሆነ በዚህ ጉዳይ ያዘኑ የተቆጡ የኢትዮጵያ የቁርጥ ቀን ልጆች እንዲገነዘቡ የምፈልገው ነገር የወሰድነው መድሃኒት ማስታገሻ አይደለም። የወሰድነው መድሃኒት ፈዋሽ ስለሆነ የጎንዮሽ ጉዳት አለው። ይጎረብጣል ያማል ለማስታገስ ብቻ ሳይሆን በጎንም የመጎርበጥ ባህሪ አለው፡፡ ለጊዜው የሚያስታግስ ሳይሆን ለልጆቻችንም የድልና የአሸናፊነት መንፈስ የሚያላብስ ስለሆነ እንደእኛ ደጋግማችሁ ስታስቡት ጠቀሜታው ይበልጡኑ ጎልቶ ይታያችኋልና ደግማችሁ ለማሰብ ልባችሁና አእምሯችሁ እንዲከፈት ዋናው አላማ የምትወዷትን ሀገር አንድ አድርገን ለማጽናት ካለን ፍላጎት ብቻ የመነጨ መሆኑን እንድትገነዘቡ ቢያንስ ቢያንስ ጉቦ በልተን እንደለቀቅናቸው እንድታስቡ ላሳስባችሁ እፈልጋለሁ።

እነዚህ ከሰአቱን ሙሉ ስንናገርላቸው የቆየን የኢትዮጵያ ጠላት፣ የኢትዮጵያ የጥፋት ምልክት፣ በቅርበት ሁላችንም የምናውቃቸውና የምናያቸው ብቻ ሳይሆኑ ከአፍንጫችን ስር ሻገር አድርገን ስንመለከት ኢትዮጵያ ከአቀማመጧ ለነጻነት ባላት ክብርና በማንነቷ የተነሳ ከሩቅም፣ ከቅርብም በርካታ ጠላቶች ያሏት ሀገር ስለሆነች እያንዳንዱ ውሳኔ በመንግስት ሲወሰን አርቆ በማሰብና ኢትዮጵያን በማጽናት ላይ ብቻ የሚመሰረት መሆኑን ዜጎች እንዲገነዘቡ እጠይቃለሁ።

አርቀን በማሰብ፤ አሻግረን በማየት ኢትዮጵያን ማጽናት የሚያስፈልግበት ምክንያት በጥልቀት አስበን ካልሰራን በስተቀረ በጠላቶቻችን የተሰለፉ ሃይሎች ባላቸው ትጥቅ ባላቸው ጉልበት ባላቸው ሃብት መጠን ከሆነ ኢትዮጵያ ማሸነፍ

አትችልም። ኢትዮጵያ በርከት ያለ ሃብት ጉልበት ያላቸው ሀገራት ተቃርነዋት ቆመው እንድታሸንፍ ያደረጋት የመሳሪያ ብልጫ ሳይሆን የልብ ብልጫ ነው። ቀድማችሁ እንደሰማችሁት እጅግ ብዙ በዚህ ዘመን እንደዚህ አይነት ጀግኖች አሉ ወይ? ብሎ ለማሰብ የሚያስቸግሩ ወጣቶች እናቶቻቸውን ካለጧሪ አስቀርተው፣ ሚስቶቻቸውን፣ ልጆቻቸውን ካለደጋፊ አስቀርተው በሚያስደንቅ ጀግንነት ፈንጂ ላይ ተረማምደው፣ ህይወታቸውን ገብረው፣ አጥንታቸውን ከስክሰው፣ ደማቸውን አፍሰው የሰጡን ድል እንጂ እንደ ጠላቶቻችን ፉከራማ ቢሆን ኖሮ ዛሬ በዚህ ባማረ ሁኔታ ተገናኝተን ድል ለማብሠርና ጀግኖችን ለማወደስ ባልበቃን ነበር።

ኢትዮጵያ ከአንድ ወር በፊት ከካዛጊታ ወደ ባቲ በተደረገው እልህ አስጨራሽ የጥልቀት ውጊያ ሸንታቸውን እየጠጡ የሚጓዙ ጀግኖች ነበራት። ኢትዮጵያ የጭፍራን ምሽግ ሠብሮ ድሬ ሮቃ ላይ ለቁጥር በሚያታክት ደረጃ የተደረገባቸውን ጸረ ማጥቃት በቂ ድጋፍ ሳያገኙ ለሳምንታት ብቻቸውን ገትረው መያዝ የሚችሉ ጀግኖች ያላት ሀገር ናት። ኢትዮጵያ ቡርቃ ከተያዘ በኋላ 80-90 ኪሎ ሜትር በእግር ጉዞ ሀርቡ ላይ መቁረጥ የሚችል ጀግና ሠራዊትና ጀግና የጦር መሪዎች ያላት ሀገር ናት። ኢትዮጵያ ኮምቦልቻ ተይዞ ጠላት በደሴ ዙሪያ በሚንቀሳቀስበት ወቅት ብዙ በረሃ በማቋረጥ ዞብልን መቁረጥ የሚችል ጀግና ሠራዊትና መሪ ያላት ሀገር ናት። እነዚህ ጄኔራሎች ለድል ያበቁን በትጥቅ ብዛት ሳይሆን በልብ ነው። ጠላቶቻችን በሳተላይት ሁሉ ሲታገዙ እንደነበር ሁላችሁም የምትገነዘቡት ነውና። አርቀን ማሰብ የኢትዮጵያን መጽናት ደጋግመን በጥልቀት ማየት የሚያስፈልግበት ዋና ምክንያት ከተቃርኖ ጎራ የቆሙ ሃይሎች በብዙ ሙያተኞች በጥልቀት አስበው ሊበትኑን ተነስተው ነበርና ፈጣሪያችንን ይዘን፣ ህይወታችንን ሳንሰስት ለመስጠት ተዘጋጅተን ባገኘነው ድል ውስጥ አርቆ ማሰብና ብልሃት ከጀግንነት እኩል ትርጉም ነበራቸው።

አንድ አባት ሁለት ልጆች ነበሩት ታላቁ ልጅ ታታሪ፣ ታዛዥ፣ የዋህ ቢሆንም ብልሃት ይጎድለዋል። ነገርግን ታናሹ ታታሪነቱም፣ የዋህነቱም እንደ ታላቁ ቢሆንም

በብልሃት አርቆ በማሰብ ደግሞ ይልቅ ነበርና አባቱ ሃላፊነት በተደጋጋሚ የሚሰጠው ለታናሹ ነበር። በዚህ ምክንያት ታላቁ  አንድ ቀን አባቱን አስቀምጦ "ታላቅ ሆኜ ሳለሁ እድሜዬን ሁሉ ካንተ ጋር እየለፋሁ እየሰራሁ ሃላፊነት የምትሰጠው ለታናሽ ወንድሜ ነው ለምን ይሄን ታደርጋለህ" ብሎ ጠየቀው። አባቱም ይሄንን ጥያቄ ከመመለሱ በፊት አንድ ቦታ ልላክህ ይለዋል። አቶ አበበ ጋ ሂድና እንቁላል ለመጣል የደረሱ ዶሮዎች ካሉ ጠይቀህ ና። እንቁላል የሚጥሉ ዶሮዎች በማርባት ማትርፍ ይኖርብናል። ይህም ታላቅ ልጅ በታዘዘው መሰረት ወደ አቶ አበበ ጋ ሄዶ ጠይቆ ይመለሳል።

አባትም "ጠየቅህ ወይ?" ስንት ዶሮ አለው?"

ልጅ "አምስት"

አባት "ዋጋቸው ስንት ነው?"

ልጅ "እሱን አልጠየቅኩም"

አባትም "ተመልሰህ ጠይቅ" ይለዋል። በድጋሚ ሄዶ ይጠይቅና ይመለሳል።

አባት "ስንት አሉህ?"

ልጅ "150 ብር"

አባት "መቼ ሊያቀርብልን ይችላል?"

ልጅ "እሱንም አልጠየኩም"

ተመልሰህ ጠይቀህ ና።

"ነገ ሊያቀርቡ ይችላሉ።"

አባትም በዚህ ጊዜ ታናሹን ይጠራና "እስኪ አቶ አበበ ጋ ደርሰህ እንቁላል ሊጥሉ የደረሱ ዶሮዎች ካሉ ጠይቀህ ለኛ እንደቢዝነስ የምንሰራበትን መፍጠር የምንችልበትን ነገር አድርገህ ና" ብሎ ላከው። ልጁም ሄዶ አቶ አበበን ጠይቆ ይመለስና "አቶ አበበ አምስት ዶሮዎች አሉት፡፡ እያንዳንዱ 150 ብር ያወጣሉ። እነዚህን የምንገዛ ከሆነ ነገ እንደሚያቀርብልኝ ነግሮኛል። ነገርግን ተጨማሪ አንድ ሳምንት ብንሰጥህስ ስለው። እንደሱ ከሆነ 10 ዶሮዎች፣ በ120 ብር ላቀርብልህ እችላለሁ። በተጨማሪ ሁለት ሳምንት ብንሰጥህስ ስለው ዶሮዎቹን ወደ 25 ከፍ አድርጌ የእያንዳንዳቸውንም ዋጋ በ75 ላቀርብላችሁ እችላለሁ ሲለኝ። በዚህ ዋጋ ተስማምቼ መጥቻለሁ ብሎ ለዶሮዎቹ የሚሆን ቦታ ላዘጋጅ መጣሁ" ይለዋል።

በዚህ ሰአት ታዲያ አባት " አየህ ወይ ልጄ?" አንድን ጉዳይ ጨርሰህ ለመምጣት ሶስት ጊዜ ስትመላለስ ታናሽህ ግን ለዛው ጉዳይ ሄዶ ትርፋማ የሚያደርገንን ጉዳይ ተስማምቶ ተመልሷል። ለዚህ ነው ሃላፊነት የምሰጠው አለው ይባላል።

ስለዚህ የኢትዮጵያ ህዝብ ለይቶ ለመንግስት ሃላፊነት የሚሰጠው አርቀን አስበን መጀመር ሳይሆን ጨርሰን እንድንጀምር ስለሆነ ይህን ሃላፊነት የሰጠንን ህዝብ ለምንወስናቸው አንዳንድ ውሳኔዎች ለሱ ጥቅም ሲባል እንዳደረግው ማመንና መገንዘብ ያስፈልጋል። የኢትዮጵያ ጠላቶች ጥቂት ግለሰቦች አይደሉም። የኢትዮጵያ ጠላቶች ጥቂት ቡድኖች አይደሉም፡፡ ሁሉንም አሰናስለን ተመልክተን ለዘላቂ ድል የሚያበቁ ታክቲኮች፣ ስትራቴጂዎች ቀይሰን የኢትዮጵያን አንድነት ለማጽናትና ዘላቂ ድሏን ለማረጋገጥ የሚወሰዱ መራር እርምጃዎች ካሉ ለመረጠን ህዝብ ደህንነት ሲባል መሆኑን መረዳት ያስፈልጋል። የሀገራችን የህልውና አደጋ ጨርሶ አልተወገደም። ጊዜው አሁን ነው ወይ? ጥቃት ደርሶብን ሲያበቃ የሚሉ ድምጾችም ይደመጣሉ። እውነት ነው የሀገራችን የህልውና አደጋ ጨርሶ አልተወገደም። ለዚህም ነው ሃይልን መሰብሰብ፤ የዝግጅት ብልጫ ማድረግ ፣ የስትራተጂ ብልጫ ማድረግ ከሁሉ በላይ ሳይገነዘብ የተፈተነ የሚደግፍ ህዝብ ካለ ሀገሩን ለመታደግ ከመንግስት

ጎን እንዲቆም ለማድረግ የተወሰነበት ዋናው ምክንያት የህልውና አደጋው ጨርሶ ያልተወገደ በመሆኑ ነው። ነገርግን እኛ አስረን ነው ክስ የሰረዝነው አባቶቻችን ግን ማርከው ወዲያው ፈረሶቻቸው ላይ ጭነው ከቁስል እንዲያገግሙና እንዲድኑ አድርገው የመለሱት ኢትዮጵያዊ ከሆንን እንደ አባቶቻችን ይቅር ማለትንና በሰላም መድረክ ማሸነፍን የታሪካችን አካል አድርገን ለልጆቻችን ማውረስ እንደሚገባ ከሁላችንም ይጠበቃል። ጦርነት መልከ ብዙ ነው። በሁሉም ግንባር የመዘጋጀት ብልጫ ያስፈልጋል። በባለፈው ወጊያ የነበሩ ድክመቶች፣ ዋጋ ያስከፈሉንን ድካሞች ማረም ይጠይቃል።

የተከበራችሁ መኮንኖች ዜጎችና በዚህ ስፍራ የምትገኙ እንግዶች ከህወሐት ስህተቶች ስድስት ነገርን እንድንማር እጠይቃችኋለሁ። ህወሃት የያዘው ከፋፋይ ሃሳብ ያነሳው የሰፈር አጀንዳ የተጠናወተው ክፋት፣ ጥላቻ፣ ሌብነት፣ ለከፍተኛ ሽንፈት ያበቁት ወደፊትም ድል በሰፈሩ እንዳይደርስ የሚያደርጉት እኩይ ባህሪዎቹ ቢሆኑም ከዚህ ሁሉ ግን ባለፈው አንድ አመት ገደማ ምናልባትም ዘለግም ብሎ ሶስት አመት ገደማ ብንመለከት ህወሃት በትክክል ማሰብ ባለመቻሉ በህዝቡ ላይ ያደረሰውን ጫና ለማየት ስለሚያግዝ ነው፡፡

አንደኛ ለውጡ እንደመጣ የኢትዮጵያ ህዝብ ይቅርታ እንዲያደርግልን ጠይቀን ህዝቡም በደሉን ረስቶ በዳዮቹን አቅፎ ለመኖር ሲሰናዳ ያን የለውጥ ጉዞ ተቀብሎና ደግፎ መቆም ያልቻለው ህወሃት የመጀመሪያውን ታሪካዊ ስህተት ስርቷል። ያገኘውንም ይቅርታ እንዲያጣና ከፍተኛ ጥፋት እንዲደርስበት ሆኗል።

ሁለተኛው ብልጽግና ሲመሰረት ህወሃት ከራሱ ክብርና ስም ዘሎ ለትግራይ ህዝብ ለታገለለት ህዝብ ቢቆረቆር ኖሮ ከብልጽግና ለመውጣት ምናልበት የከፋ እንኳን እንደሆነ ለሁለት ተከፍሎ ከፊሉ ብልጽግና ጋር መቆየት ቢችል እንኳን ኖሮ በርካታ ዜጎቹን መታደግ ይችል ነበር። ይህን ማድረግ ባለመቻሉ የሌብነት ጥጉ ተከፍቶ

እንዲታይና የጥፋቱ ጥግ ተከፍቶ እንዲታይ ማድረግ ስላስቻለ ብዙውን ነገር አበላሽቷል።

ሶስተኛ ምርጫ ብልጽግና በትግራይ ክልል ውስጥ ለመወዳደርና ለማሸነፍ እምብዛም ዝግጁ ባልነበረበት ወቅት ራሱ ህወሃት በጻፈው ህገመንግስት በፌደራል መንግስት የሚተዳደሩ አንድ የሀገር መከላከያ ሰራዊት፣ አንድ የምርጫ ቦርድ መኖር አለበት ብሎ ሲያበቃ የምርጫ ቦርድን ጥሶ የምርጫ ኮሚቴ በመሰየም ምርጫ ለማድረግ የዳዳበት ሁኔታ እጅግ ከፍተኛ ዋጋ አስከፍሎታል። በጊዜውን የፌዴራል መንግስት ወጪ ሸፍኖ የሚያካሂደውን ምርጫ ራሱ አካሂዶ የጨረቃ ምርጫ ለማካሄድ ተገዷል። በዚያም ሳቢያ ብዙ መዘዝ አምጥቶበታል።

አራተኛ የሰሜን እዝ ጥቃት በብዙ መንገድ ተጠቅሷል፡፡ በአንድ መንገድ ብቻ እንመልከተው፡፡ በሺህ የሚቆጠሩ መኮንኖች ለሃያ አመትና በላይ መከላከያን ያገለገሉ መኮንኖች በዘር በደም ብቻ ተደራጅቶ ከመከላከያ ውጡ ማለት ህዝቡንም ራሱንም በእጅጉ የሚጎዳ ነገር ነበር። እያጠቃን እንኳን ቢሆን እነዛን ሃይሎች በውስጣችን አቆይቶ በሶስት ሳምንት ማሸነፍ የሚችል አልነበረም። ያ ብቻ አይደለም የወጡ ሃይሎች በከፍተኛ ሃላፊነት ያሉት ሃብት ያላቸው ይሆናሉ። በዝቅተኛ ላይ ያሉት ደግሞ ደሞዝ አልባ፣ ጡረታ አልባ፣ ከሃዲ እንዲሆኑና ከሚያሸንፈው የሀገር መከላከያ ተነጥለው ከሚሸነፈው ጎራ እንዲሆኑ ያስገደደ ደካማ ውሳኔ ነበር።

አምስተኛ ከመቀሌ ስንወጣ ውጡልኝ ብሎ ከሚከተል ደጋግሞ ቢያስብ ኖሮ የብዙ ወጣቶች ህይወትን ከመቀጠፍ ያድን ነበር። ስድስተኛ ወደ ደሴ ያለው ጉዞ ቁልቁለት ሆነልኝ ብሎ ሳይዘጋጅ ሳያስብ ራሱን በበቂ ሳያደራጅና እድል ቢቀናው እንኳን እንዴት አድርጎ እንደሚያስተዳድር እቅድ ሳይነድፍ እንዲሁ በእውር ድንብር መጓዙ ስላሸነፍክ ብቻ ከግብ በላይ መጓዝ ተገቢ እንዳልሆነ በእጅጉ የተማርንበትና ለመልሶ ማጥቃቱ ከአፋርና ከአማራ ክልል ካስወጣን በኋላ ተጨማሪው ጉዞ አያስፈልግም

ያልነው የእውር ድንብር ጉዞ ውጤቱ አደገኛ መሆኑን ከህወሃት በመማር ጭምር ነው።

ሰባተኛ እና የመጨረሻው አሁን ወደ ትግራይ ክልል ዘልቀን የማንገባበት በርካታ ምክንያቶች ያሉን ቢሆንም አንገባም ብለን ከቆምን በኋላ ነገሩን በተለየ መንገድ ለማየት ጥረት እያደረግን ባለንበት በዚህ ወቅት አሁንም ህወሃት አላረፈም። አሁንም ህወሃት በግራ በቀኝ ሊነካካን ይፈልጋል። ለሰባተኛ ስህተት የሚጓዘው በፍጹም ድል ማግኘት የማይችል እንኳን ቢሆንም በወጣት የትግራይ ልጆች ላይ የመቀጠፍ፣ የመቁሰል አደጋ የሚያስከትል ስለሆነ ሰባተኛው ስህተቱ መስመር ስቶ ሳይሄድ መማር የሚችልበት እድል መፍጠር የራሱ ቢሆንም እንኳን እንደ ባላንጣ አትንኩን እረፉ ለማለት እወዳለሁ። የነካካችሁን እንደሆነ በተለመደው መንገድ የከፋ ቅጣት ይደርስባችኋልና።

ትናንት እንኳን ከስ አቋርጠን እስረኞች ይውጡ ስንል የህወሃት ጀሌዎች ከፊሉ የአማራ አካውንት፣ ከፊሉ የኦሮሞ የሚመስል አካውንት በመክፈት እኛን ለማባላት ሳይተኙ አድረዋል። አማራ መስለው፣ ኦሮሞን መስለዋል ብዙ ጥረት አድርገዋል። በርግጥ አማራና ኦሮሞ በትናንሽ ጉዳይ የመኳረፍ ባህርይ አላቸው በንግግር ሊስተካከል የሚገባው። ነገርግን ኢትዮጵያ ስትነካ ሁሉ አጀንዳዎቻቸውን ጥለው በጋራ በአንድ ጉድጓድ ሞተው የኢትዮጵያን ነጻነት እንደሚያጸኑ ባሳለፍነው ጥቂት ወራት ከማንም በላይ ህወሃት ትምህርት ወስዷል። ከምንም በላይ ይህ ከንቱ ሙከራ እኛ ሊከፋፍለን እንደማይችል፣ ሊያስቆመን እንደማይችል ተገንዝቦ እኛን ከመነካካት እንዲቆጠቡና ሰባተኛውን ስህተት እንዳያደርጉ ለመምከር እወዳለሁ።

የተቀረው አለምም አይኑን እንዲገልጥ፣ እውነት እንዲፈልግ በባለፈው አንድ አመት በነበረው ጦርነት የኢትዮጵያ ህዝብ  መንግስት ሰላም እየፈለገና ለሰላም እጁን እየዘረጋ በተደጋጋሚ ጥቃት የተፈጸመበትና በአለም መድረክ ፍትህ ያጣበት በመሆኑ አሁንም የዘረጋነውን የሰላም እጅ ባለመቀበል ትንኮሳ የሚያደርገውን ሃይል አለም

አይኑን ገልጦ እንዲያይ እውነት እንዲፈልግ ለማሳሰብ እወዳለሁ። የትግራይ ህዝብ ባለፈው አንድ አመት በኢኮኖሚ፣ በዲፕሎማሲ፣ በፖለቲካ እጅግ ከፍተኛ ጉዳት ደርሶበታል። አሁን አይኑን መግለጥ ያለበት ጊዜ ይመስለኛል።

የትግራይ ህዝብም አይኑን እንዲገልጥ አደራ ለማለት እፈልጋለሁ። ለተቀረው የኢትዮጵያ ህዝብ አንደኛ እናቶች አሁንም ለኢትዮጵያ አንድነትና ሰላም ወደላይ ማንጋጠጥና መማጸናችሁን አታቋርጡ። ሁለተኛ ወጣቱ በተለይም የሀገር መከላከያ ሚኒስቴርና በየክልል ያሉ ልዩ ሃይሎች ክንዳቸውን ማበርታትና መናበብ እንዳያቋርጡ። ሶስተኛ ከሁሉ በላይ የድላችን ምስጢር አንድነታችንን መጠበቃችን ነውና አንድ መሆን፣ መደመር፣ በጋራ መቆም ለዘላቂ ድል ስለሚያበቃን ኢትዮጵያዊያን ሆይ ኢትዮጵያን መታደግ የምትችሉ ከሆነ አሁንም በመደመር አንድ መሆንን አበክራችሁ ፈልጉ። እኛ ነጻ ሀገር ተረክበናልና ነጻ ሀገር ለልጆቻችን ለማስረከብ ከፍላጎቶቻችን ባሻገር ሌሎች ፍላጎቶቻችንንም መገንዘብና ኮምፕሮማይዝ ማድረግ ይኖርብናል።

ትናንት በነበረው ውሳኔ እንኳን አንደኛው የኢትዮጵያ ጫፍ ሲያዝን ሌላኛው የኢትዮጵያ ጫፍ ሲስቅ ማየት የቻልነው ኢትዮጵያዊያን በአንዳንድ ውሳኔዎች በጋራ የመቆም፤ ስለወንድማችን ስንል የመተውና የማለፍ ልምምድ ገና ብዙ እንደሚቀረን ያመላክታል። እኛ በውጊያ ስንጠቃ ብቻ አንድ የምንሆን ብቻ ሳይሆን በወንድሞቻችን ደስታ የራሳችንን መሻት የምንቆጥብ ስለሌሎች ፍላጎት የኛ ፍላጎት የምንተውና በጋራ መቆም እንዲሁ በነጻ እንደማይገኝ የምናስብ ህዝቦች መሆን ይኖርብናል። ከዚያም ባሻገር የወደሙብን በርካታ ሃብት አለና እነዚህን ሃብቶች ለመገንባት የህዝቦቻችንን በደል እንዲሽር፣ ቁስል እንዲሽር ለማድረግ መሰብሰብ አመራር መስጠት ወደ ሌላ ግንባር ማተኮር ስለሚኖርብን ኢትዮጵያዊያን በጀመርነው ግንባር ብቻ ሳይሆን በበርካታ መንገድ መጓዝ እንዳለብን እንድታስቡ ከአደራ ጭምር ላሳስብ እወዳለሁ። የሀገር መከላከያ ሚኒስቴር እናንተ ጀግኖች ኢትዮጵያን የሚመጥን ዘመን የሚሻገር ነፃነታችን ምልክት የሚሆን የህልውናችን ምሶሶ የሆነ ለሁላችን ኩራትና

መመኪያ የሆነ የሀገር መከላከያ ሚኒስቴር እንድትገነቡ መንግስት በታላቅ ሃላፊነት ሊያሳስባችሁ ይፈልጋል።

የህወሃትን መንገድ ሳንከተል ኢትዮጵያዊ የሆነ ተቋም እንድንገነባ ልጆቻችን በሰላም እንዲኖሩ የሚያመቻች ስለሆነ ዛሬን ሳይሆን ነገን እያሰባችሁ እንድትገነቡ በሰላም ጊዜ ሰፊ ዝግጅት እንድታደርጉ በሰላም ጊዜ ሰፊ ዝግጅት ያደረገ ወታደር ድሉ ቅርብ ስለሚሆን እንዳትዘናጉ አደራ ልላችሁ እፈልጋለሁ።

በመጨረሻም በዚህ አስከፊ ጦርነት ኢትዮጵያን እናፈርሳለን ብለው የተነሱ ሃይሎች ኢትዮጵያ ዛሬም እንደትላንቱ የማትፈርስ መሆኗን በድጋሚ ለማረጋገጥ ህይወታቸውን የገበሩ አጥንታቸውን የከሰከሱ ደማቸውን ያፈሰሱ፣ ላባቸውን ያፈሰሱ ጭንቅላታቸውን አልቆ የማሰብ ውጤት ጨምቀው ያፈሰሱ አመራሮች ኢትዮጵያ አብዝታ ታመሰግናቸዋለች።

ዛሬ ባለንበት በመከላከያ ዋና መስሪያ ቤት የተገነባው ግንባታ ኢትዮጵያን የሚመጥን ጥራቱም ስፋቱም፣ ልኩም ተደርጎ የተሰራ ሲሆን ይህ ስራ አሁን ባለበት ደረጃ እንዲደርስ በርካታ ሰዎች የተለየ ሚና የነበራቸው ሲሆን በዲዛይን፣ በግንባታ እንዲሁም ወጣቶች ግቢውን በማስዋብ አመርቂ ስራ ስለሰሩ ከሁሉም በላይ የቀድሞውን መከላከያ ሚኒስትር ዶክተር ቀነአን እና የቀድሞ የመከላከያ ሚኒስትር ዴኤታ አቶ ጌታቸውን አብዝቼ ላመሰግን እወዳለሁ።

አሁን ያሉት ሚኒስትርና ሚኒስትር ዴኤታዎች ይሄንን ግቢ ባለበት ሁኔታ አልቆ የመገንባት፣ የመጠበቅ ሃላፊነት እንዳለባቸው እያስገነዘብኩ ተቋም መገንባት፣ ሃይል መገንባት፣ ሃይል ማባዛት፣ ሃይል ማዘመን፣ መዋጋት ሳይሆን ውጊያ ማስቀረት የሚችል የሀገር መከላከያ ሚኒስቴር መሆን እንዲችል መንግስት በቅርበት ይገነባል። የኢትዮጵያ ነጻነት፣ የኢትዮጵያ አንድነት፣ የኢትዮጵያ ሉአላዊነት ዛሬም እንደትላንቱ ዛሬም በልጆቿ ደምና አጥንት ተከብሮ ይኖራል። ኢትዮጵያ በልጆቿ ጥረት ታፍራና

ተከብራ ለዘለአለም ትኑር። ለዚህ ቀን፣ ለዚህ ድል፣ ለዚህ ማእረግ ያበቃን ፈጣሪያችን የተመሰገነ ይሁን ለእናንተም ልቦና ይስጣችሁ!

**እጅግ አድርጌ አመሰግናለሁ !**

ጥር 1፣ 2014 ዓ.ም

# ወደ ሀገር ቤት የእራት መርሃግብር ላይ የተደረገ ንግግር

**ክብርት ከንቲባ**
**ክቡራን ሚኒስትሮች**

ከሁሉ በላይ የእለቱ የክብር እንግዳ የሆናችሁ ትውልደ ኢትዮጵያዊያን እና ኢትዮጵያዊያን እንኳን በሰላም ወደዚህች ድንቅ ውብ ሀገር መጥታችሁ በዚህ መንገድ ያበቃን ልላችሁ እፈልጋለሁ።

እናንተ ጠንቅቃችሁ እንደምታውቁት እንደ ኢትዮጵያ ያለ ታሪክ፣ እንደ ኢትዮጵያ ያለ ቅርጽ ያላቸውና ልጆቻቸውን ቢጠሩ የማያፍሩ ሀገራት እንደዚህ አይነት ጥሪ ሲያደርጉ የመጀመሪያ አይደለም። በተለይ “ጺዮኒዝም” ወይንም “ዛዮኒዝም” የሚባለው የትውልደ እስራኤላዊያን ወደ ሀገር የመመለስ ጥሪ ከብዙ አስርተ አመታት በፊት የነበረ እንቅስቃሴ ነው። ትውልደ እስራኤላዊያን ወደ ሀገራቸው የመመለስ ጥያቄ ሲቀርብ ሃሳቡ እስራኤል ሀገር ውስጥ ያሉ አይሁዶች በቁጥር አነስተኛ ስለሆኑ የተበተነውን ሃይል ለመሰብሰብና መሬት እየገዛን ምድራችንን እናስመልስ የሚል እሳቤ ያለው ቢሆንም ከብዙ አስርት አመታት ጥረትና ልፋት በኋላ ለመጀመሪያ ጊዜ አሁን በሸኘነው አመት በእስራኤል የሚኖሩ አይሁዶች በውጪ ካለው ዲያስፖራ ለመጀመሪያ ጊዜ ቁጥራቸው በለጠ። እንቅስቃሴው ሲጀመር በጣም ጥቂት አይሁዶች በሀገራቸው ይኖሩ ነበር። ቀስ እያለ ግን በልጆች፣ በልጅ ልጆች እየሰራ ዛሬ በምድራቸው የሚኖሩ የአይሁድ ተወላጆች በውጪ ካሉት ቁጥር ልቆ አምና በከፍተኛ ሁኔታ ሲያከብሩት እንደነበር ይታወሳል። የኛ አላማ እንደሱ አይደለም። በውጪ ያሉት ጥቂት ናቸው በሀገር ውስጥ ያለን በጣም እንበዛለን። የኛ አላማ ልጆቻችሁን እንዳናጣ ሀገር እንዳላቸው ታሪክ አንዳላቸው፣ እያደገች ያለች ውብ ሀገር እንዳላቸው እንዲያውቁና ከወዲሁ በየአመቱ በሚደረገው ጥሪ ምናልባት ኢትዮጵያ ባጠረ ጊዜ ውስጥ ወደ ተሻለ ጊዜ ውስጥ ስትደርስ እናንተን እንኳን ሙሉ በሙሉ ባናገኝ ልጆቻችሁን ሙሉ በሙሉ ማስቀረት ነው። ይሄ በጀርመን፣ በጃፓን

በተለይ በኮሪያ በስፋት የሚታይ ነገር ነው። ኮሪያ በየትኛውም ቦታ ላይ ብትሄዱ በአውሮፓ፣ በአሜሪካ የተወለዱ ልጆች ናቸው ሀገሩን ይዘውት ያሉት። እኛም ልጆቻችሁን ስለምንፈልግ አሁን ስትሄዱ ልጆች ያላመጣችሁ ሰዎች ያያችሁትን በፎቶ፣ የሰማችሁትን ታሪክ ድንቅ ሀገር እንዳላቸው በመንገር በሚቀጥለው ለመምጣት እንዲዘጋጁ ልታነሳሷቸው ይገባል። አሁን እንደዋዛ የጀመርነው ወደ ሀገር የመመለስ ጥሪ በ10፣ 15 አመታት ውስጥ ተአምራዊ የሆነ ለውጥ እንደሚያመጣ ጥርጥር የለውም። አንድ ብለን ጀምረናል። አንድ ብለን የጀመርነው እያደገ ይሄዳል፣ የጀመርነው በእርግጠኝነት የምናገረው ዘንድሮ ሀገሬን ብላችሁ ጥሪያችንን አክብራችሁ የመጣችሁ ሰዎች ባላጋንን 90% እጅግ በጣም ደስተኛ ናችሁ። ምክንያቱም በልባችሁ የተሸከማችኋት ኢትዮጵያ እየፈረሰች እንደሆነች በተደጋጋሚ በሀገራችሁ ያሉ ሚዲያዎች ነግረዋችሁ ሲያበቁ ስትመጡ ጥላችሁ የሄዳችሁት ጽዳት፣ ውበት፣ አዳዲስ መዋያ ስፍራ ይሄንን ቦታ ጨምሮ ማየት ለማንኛውም ኢትዮጵያዊ የሚያስደስት ስለሆነ እንደሚያስደስታችሁ ጥርጥር የለኝም። ምን አልባት 10 ወይም 5 ለምን ቀነስከው ያላችሁ እንደሆነ? የመጀመሪያችን ስለሆነ ምን አልባት አየርመንገዳችን፣ የታክሲ ሰርቪስ፣ የሆቴል ሰርቪስ፣ እዚህ እንኳን ስትመጡ የፍተሻ ጉዳይ ረብሿችሁ ከሆነ ብዬ ነው።

ይሄ ጅማሮ እንዲቀጥል ኢትዮጵያዊያን በጥልቀት የማሰብ ብቃት መጠቀም መጀመር አለብን። በስሜት ብቻ ሳይሆን በማሰብ ሃይል ይሄንን ነገር ማስቀጠል ተቋማዊ ማድረግ ያስፈልጋል። አንደኛው "የኖሞር ሙቭመንት" እስከዛሬ ድረስ ሀገራችንን አትንኩ ከዛሬ በኋላ ግን መልኩን መቀየር አለበት። በውጪ ያላችሁ ዲያስፖራ ለጊዜው በአሜሪካ እና አውሮፓ ሊሆን ይችላል። ሲቀጥል በሁሉም በአንድ ድምጽ የምትደማመጡ አሁን ያለው የዘር፣ የሃይማኖት ክፍፍል የሌለበት ተቋም ቢኖራችሁ ባላችሁበት ሀገር ልክ እንደ አይሁዶቹ ተጽእኖ መፍጠር ማድረግና ፍላጎታችሁን ማስፈጸም ስለምትችሉ እዚህ ማገዝ ብቻ ሳይሆን ባላችሁበት መደማመጥ፣ ባላችሁበት የፈለጋችሁትን ጥያቄዎችን የማንሳት፣ የመደመጥ መብት እንድትፈጥሩ መደራጀት ያስፈልጋል። ሞክራችሁ አይታችሁታል ነገርግን በቂ አይደለም። አሜሪካ ላይ ትግራይ ነኝ፣ አማራ ነኝ፣ ኦሮሞ ነኝ አያስፈልግም። አሜሪካ ላይ ኢትዮጵያዊ ናችሁ አንድ ሆናችሁ መቆም አለባችሁ። አንድ ሆናችሁ ስትቆሙ ዘንድሮ እንኳን በጥቂቱ ያያችሁት በብዙ ውጤታማ ይሆናል። አይሁዶች ቁጥራቸው ያነሰ ቢሆንም የሚሰሙት አንድ በመሆናቸው ነው። እኛ ደግሞ በባህልም፣ በደምም ከነሱ ጋር

እንቀራረባለን ስለሚባል ቢያንስ መደራጀትን ከነሱ ተምረን ይበልጥ የምንደመጥ እንድንሆን አደራ ልላችሁ እፈልጋለሁ።

ሁለተኛው፣ ከልማት ጋር ተያይዞ ሰሞኑን በርካታ ሲምፖዚየም ላይ ስትሳተፉ እንደነበር ሰምቻለሁ። ያላያችኋቸው ፕሮጀክቶች አሉን። ለምሳሌ ጎርጎራ ላይ የምንሰራው ፕሮጀክት በሚቀጥለው ስድስት ወር ስትመጡ መስከረም ላይ ስራ የሚጀምር ነው። ይህ ጎርጎራ ላይ የጀመርነው ፕሮጀክት ስታዩትና ሲጀምር ከደስታ በላይ ያበሳጫል። ይሄን የመሰለ ነገር እስካሁን ለምን ተቀመጠ ብሎ የሚያበሳጭ ነገር ነው። እውነት ለመናገር ሲሼልስ፣ ስዊዘርላንድ በርካታ ሀገር ብትሄዱ አሜሪካ እንኳን ብዙም እንደዛ የሚያምር ቦታ የለም። በርካታ ሀገር ብትሄዱ ብዙዎች በብዙ ዋጋ የሚዝናኑበት ቦታ ጎርጎራ ላይ አለ።

ተራራ፣ ጫካ፣ ውሃ እጅግ መልካም የሆነ መልከአ ምድር እና ማራኪ የሆነ ውባት ነው ያለው። አልሰራንበትም። አሁን እኛ የጀመርነው 50፣60 ቁልፍ ያለው ሪዞርት እው። ነገርግን ጎርጎራን እንደምታውቁት ሰፊ ቦታ ስላለው ከእናንተ ውስጥ ሌላ ኢንቨስትመንት አያስፈልግም። በእናንተ ሀገር ውስጥ እንደምታውቁት “ፕሮፐርቲ ኦውን” እንድታደርጉ በኛ ዲዛይን፣ በኛ ኮንትራክተር፣ በኛ ስታንዳርድ የዛ ሪዞርት አካል የሆነ ቪላ አቅሙ ያለው ሰው ይሰራና ከአመት ውስጥ 350 ቀኑን ልክ እንደማንኛውም ሆቴል እየተከራየ ለባለቤቱ ይሰጣል።

በአመት አንዴ ደግሞ ስትመጡ አንድ ወር ለባለቤቱ ክፍት ሆኖ ይሰራል። ይሄ የምታውቁት አሰራር ነው። ኮይሻ ላይ አለ፣ ወንጪ ላይ አለ ገና የምናስባቸው በርካታ ቦታዎች ስላሉ ከአዲስ አበባ ጋር አትጨቃጨቁ እና የንብረት ባለቤት በመሆን ቢዝነስ የሚያመጣ ስትመጡም  ማረፊያ የሚሆን ነገር መስራት ከፈለጋችሁ በእጅጉ የተመቻቸ ነገር ስላለ ብዙ አይደለም አንድ ሚሊየን ዶላር ካለን በቂ ነው ነገ ስራውን መስራት እንችላለን። ይህን የምልበት ምክንያት ፕሮፐርቲ ብቻ ኦውን ማድረግ፣ አፓርትመንት ብቻ ኦውን ማድረግ በቂ አይደለም።

የሚከራይ የሚሰራ ከሆነ እዛ ስላላችሁ ያግዝ እና በፍጥነት ወደ ሀገራችሁ እንድትመለሱ ስለሚያግዝ ጭምር ነው። እና እንኳን ደህና መጣችሁ በመምጣታችሁም ደስተኛ ናችሁ ኢትዮጵያ ውስጥ ትንሽ ውዥንብር አለ ኢትዮጵያ ውስጥ ዲያስፖራውም

በትንሹ ስላዘነ ጥቂት ሃሳቦች መሰንዘር እፈልጋለሁ። በመጀመሪያ ዲያስፖራ እዚህ እያለ ለምን ተደረገ ቢመለሱስ የሚሉ እናንተን እንደ ቤተሰብ ስለምናስብ ስትመጡ ዋሸተን ስትሄዱ የምናደርገው ነገር አይኖርም። ብትሄዱም ብትመጡም። ይህ እሳቤ እናንተን አርቆ ከማየት ነው የሚመጣው። እኛ ለሁሉም ውሳኔዎቻችን ሶስት መሰረታዊ የሆኑ መስፈርቶች አሉ። ማንኛውም አይነት ነገር ስንወስን የዛሬውን እራት ከእናንተ ጋር መብላት እንኳን ስናስብ ከዚህ ጉዳይ አንጻር ፣ምን ጥቅም እና ጉዳት አለው ብለን ነው። የመጀመሪያው በኢትዮጵያ ሉአላዊነት ለአፍታ የሚደራደር ስብእና ያለው ግለሰብም መንግስትም እንዳልሆነ ባለፉት ጥቂት ጊዜዎች ያየን ይመስለኛል። ስለዚህ አንደኛው መስፈርት ሉአላዊነት ነው። ሁለተኛው መስፈርት ብሄራዊ ጥቅም ነው። ለዚህች ሀገር ብሄራዊ ጥቅም ምን ፋይዳ ያስገኛል የሚል መመዘኛ ነው። ሶስተኛው ሀገራዊ ክብር ነው።

ክብር ያላት ሀገር ስለሆነች ምንም ደሃ ብትሆን ሀገራዊ ክብርን በሚመለከት እንደ መስፈርት ይዘን እንሰራለን። ለምሳሌ ዛሬ እራት አብረን ስንበላ ከብሄራዊ ጥቅም አንጻር እነዚህ ሰዎች እያንዳንዳቸድው አስር አስር ሰው እንኳን በሚቀጥለው አመት ቢጋብዙ ከኢትዮጵያ ውጪ በብዙ ሺህ የሚቆጠር በብዙ ሚሊየን የሚቆጠር ፈረንጅ ወደ ኢትዮጵያ ሊጋብዙ ይችላሉ። እኛ ደግሞ በሚቀጥለው አመት ሲመጡ ቢያንስ ቢያንስ አራት ስታንዳርዱን የጠበቀ ሪዞርት አዘጋጅተን አዲስ አበባን ይበልጥ አስውበን ስለምንጠብቃቸው በመጋበዛቸው አያፍሩም። ለኛም ለቱሪዝም ገቢ ያስገኙልናል። እነሱም ተጨማሪ ሰው ያመጣሉ። ይህም ናሽናል ፍላጎቶቻችንን ለመመለስ በሂደት ያግዛል።

ሁለተኛ እኛ ኢትዮጵያዊያን ብንኳረፍ ብንጨቃጨቅ ደግሞ ስርአት ያለን፣ ተገናኝተን ደግሞ አብረን ለመብላት ለመነጋገር የማንቸገር በሀገራዊ ክብር ላይ በጋራ የምንቆም መሆናችንን እዚህ ላላችሁት ብቻ ሳይሆን አኩርፈው ለቀሩትም ጭምር ትምህርት የሚሰጥ ስለሆነ ነው። እኛ ጠላት ብለን የፈረጅነው ሀገር የለም፣ አንድም ሀገር ጠላት ነው ብለን አልፈረጅንም። ነገርግን ሃሳባቸው የማይስማሙን ሀገሮች አሉን። ፖሊሲዎቻችን ቅድም ካልኳቸው መመዘኛዎች አንጻር የማይስማሙን ሀገራት አሉ። ወጣ ገባ የሚሉ ሀገራትም አሉ። ነገርግን የኢትዮጵያን ታሪክ የሚገነዘቡ፣ ኢትዮጵያን የሚያከብሩ፣ የኢትዮጵያን የወደፊት ተስፋ የሚያከብሩ የሚገነዘቡ ሀገራት ደግሞ አሉ እና የኛ አሰራር ከኛ ጋር ሃሳባቸው የሚስማማ ሀገራትን እናጸናለን። እንዳይበተኑ፣

እንዳይሄዱብን እናደርጋለን። ከኛ ጋር ሃሳባቸው የማይስማማ ድህነታችን፣ ረሃባችን ልንሻገር የማንችል መሆናችን የሚታያቸው ሀገራትን ደግሞ ተሳስታችኋል ነጻ የነበርን ነጻ ሆነን የምንቀጥል ምንም ደሃ ብንሆን ክብራችን ላይ የማንደራደር ሀገር መሆናችንን ማወቅ አለባችሁ እያልን ወደኛ ሃሳብ እናቀርባቸዋለን። በዚህ መንገድ ሃሳቦቻችንን የማያውቁ ሀገራት እኛ በትክክል ራሳችንን ስላልሸጥን እንናግርና እንመልሳቸዋለን። ጠላት የሚባል ሀገር ስለሌለ በመነጋገር እናምናለን።

በነገራችን ላይ ናሽናል ዲያሎግ ኢትዮጵያ ውስጥ ይኑር ሲባል አንዳንድ ሀገራት ቅድመ ሁኔታ ያስቀምጣሉ። እንደዚህ እንደዚህ ከሆነ እንነጋገራለን ይላሉ ቅድመ ሁኔታ ካለ እኮ ንግግር አያስፈልግም። የነሱን ሰምተን እናደርግላቸዋለን እንጂ አይሆንም። ንግግር የሚያስፈልገው ጽንፈኛ አመለካከቶች አሉ ወደ ጠረጴዛ መጥተው ተነጋግረን መሃል ላይ እናምጣቸው ለማለት ነው እንጂ እንደዛ የሚያለያየን ሃሳብ ከሌለ መነጋገር አያስፈልግም። በኔ እምነት ኢትዮጵያዊያን ከጫፍ ጫፍ መገንጠልን አይፈልጉም ብዬ አምናለሁ።

ነገርግን አስር አስራምስት ሰዎች መገንጠልን ቢያምኑ ሃሳባቸውን ይዘው መጥተው መገንጠል አልጠቀመም አይጠቅምም ብለን አሳምነን እንመልሳቸዋለን እንጂ ሃሳብህን አታንሳው አንላቸውም። ሃሳቡን እናሳምናቸዋለን። ለምን? የማይጠቅም ሃሳብ ስለሆነና ንግግርን ከውጪም ከውስጥም ስናስብ ትንሽ ልባችንን መክፈት ያስፈልጋል። የኛ አቋም ለማስረጽ ሳይሆን ሌሎቹን አድምጠን የሀገርን ጥቅም፣ ሉአላዊነት እና ክብር እስካልነካ ድረስ ኮምፕሮማይዝ አድርገን አብረን ለመኖር ጭምር የሚያግዝ መሆን አለበት። የንግግሩ ፍሬ ሉአላዊነታችንን የሚነካ ከሆነ ዋጋ የለውም። የንግግሩ ፍሬ ክብራችንን የሚነካ ከሆነ ዋጋ የለውም። ከዛ በመለስ ግን ንግግርን መሻት መጥፎ አይደለም። እንደምታውቁት በአየር የተሞላ ፊኛና በንዴት የተሞላ ልብ አንድ ነው። በአየር የተሞላ ፊኛ በቀጣይነት አየር የምትመግቡት ከሆነ ይፈነዳል። በጥላቻ፣ በብስጭት፣ በክፋት የተሞላ ልብም በቀጣይነት ብስጭትን እየሰበሰበ ከሄደ ይፈነዳል ከነዚህ ሁለት ነገሮች እድሜያችሁን ለማርዘም የሚያስፈልገው ከዛኛውም ነፋስ ቀስ እያሉ መቀነስ እንዳይፈነዳ ከዚህኛውም ብስጭት መቀነስ ያስፈልጋል።

በዚያ መንገድ ነው በጤናና በሰላም ሀገራችንን ለልጆቻችን ማሻገር የምንችለው። በሰከነ መንገድ ማየት ጥሩ ነው። ምንም የግል ጉዳይ አይደለም የጋራ ጉዳይ

ነው ተነጋግረን ተመካክረን የሚሻለውን እየመረጥን መሄድ ይሻለናል። እንደዛ ከሆነ ኢትዮጵያን እናጸናለን አባቶቻችንም እንደዛው ነው ያደረጉት እኛ አሁን እንደምንተብተው አይምሰላችሁ። እየጠየቁ፣ እየጋበዙ፣ እየቀረቡ ነው ሀገር ያጸኑት። እኔ አንድ ወዳጅ አለኝ ሁላችሁም ታውቁታላችሁ። ሼክ መሃመድ ቢን ዛይድ የሚባል የዩናይትድ አረብ ኢሚሬት አልጋ ወራሽ ነው። እንደኛ አይነት የፌዴራል ሲስተም አላቸው። ግን አልጋ ወራሹ እሱ ነውና በአንድ ወቅት አብረን እያለን አንድ ወንድሙ ይደውልለትና "የዱባዩ ሼክ መሃመድ ቢን ራሺድ ይፈልጉሃል ልምጣ ይላሉ" ብሎ ይጠይቀዋል ።ማለትም ወይ ይልቃል ወይ ሸመልስ ልምጣ ብሎ እንደመጠየቅ ማለት ነው። እና ጭቅጭቅ ይነሳል "ሼክ መሃመድ በፍጹም አይመጣም ሰአቱን ንገረኝና እኔ ነኝ መጥቼ የማናግርክ ባለህበት እንጂ አንተ አትመጣም" ይለዋል። በኋላ ወንድምየው ሽምግሎ ጠያቂው ሰው ባለበት ዱባይ እንዲሆን ሆኖ ተጠያቂው ሰው አለቃው ወደ ዱባይ ይሄዳል ሊያናግረው ሲመለስ "ለምንድነው ያደረከው ይሄንን አለው?" "አባቴ የተለያዩ ስቴቶችን አንድ ላይ አድርጎ ዩናይትድ አረብ ኢሚሬትስን የፈጠረው በማዘዝ ሳይሆን በመታዘዝ ነው" አለ። ስለዚህ አብረን ለመኖር አንዳንድ ጊዜ መታዘዝ ያስፈልጋል በዚያ መንገድ ሀገር ማጽናት ጠቃሚ ነው።

ከእናንተ ሀገር ታሪክ አንድ ነገር ለማንሳት የናዚን፣ የጀርመኑን ግጭት ሁላችሁም ታውቃላችሁ። ከ5 ሚሊየን በላይ የአይሁድ ዜጎች የፈጀ ነው። በኋላም ጃፓን የሁለተኛው የአለም ጦርነትን ከመቀላቀሏ ትንሽ ቀደም ብሎ ፐርል ወደብ የሚባለውን የአሜሪካን ቤዝ መትታ የተቀሰቀሰው ጦርነት ብዙ ሚሊየን ሰዎችን ቀጥፏል። እና ያንን ጦርነት ያሸነፈው የአሜሪካ ፕሬዝዳንት ትሩማን ይባላል። ፕሬዚዳንቱ ካሸነፈ በኋላ ማርሻል ፕላን አውጥቶ እነዚህን ሀገራት መገንባት ነበር። ከብዙ ቆይታ በኋላ "በዚያ ጦርነት የሚያስደስትህ ነገር ምን ነበር?" ሲባል "ጦርነቱን ማሸነፌ ሳይሆን አሜሪካ እንደ ጠላቶቻችን የሞራል ዝቅጠት የሌለባት ሀገር መሆኗን በግንባታ ማሳየት መቻሌ ነው" አለ። "ካሸነፍኩ በኋላ ባደረግኩት ቸርነት፣ ባደረግኩት መልካም ነገር ለልጆቻችን የአሜሪካን ታላቅነት የሚያምን ጠላት ሀገር እና የአሜሪካን ልእልና የሚቀበል የጠላት ሀገር መፍጠር መቻሌ ይበልጥ ያስደስተኛል" አለ። በጦርነቱም በሰላሙም በማሸነፉ ማለት ነው። ይሄ በጀርመንና በአሜሪካ መካከል በጣም ሰፊ ልዩነት አለ። በጀርመንና በጃፓን መካከል በጣም ብዙ ልዩነት አለ። በኛ እና በትግራይ ተወላጆች መካከል ያን ያክል ልዩነት የለም። በኛ እና በህወሃት መካከል ልዩነት አለ። ስለዚህ የምንወስነው ውሳኔ ህወሃትን ታሳቢ ያደረገ አይደለም። የምንፈልገውን

ለጊዜው ብዙ ያልተረዳንን የትግራይ ህዝብን ጭምር ሀገርህ ይሻልሃል ለማለት ነው። በዚህ መንገድ ነው ሀገርን የምናጸናው የአምስት አመት ኮንትራት የሰጣችሁን ደግሞ ሰብስበን ለልጆቻችን እንድናስረክብ ጭምር ነው።

የተከበራችሁ ትውልደ ኢትዮጵያዊያን እናንተ በሀገራችሁ ብዙ ነገር ታውቃላችሁ። እንድታስተምሩ የምንፈልገው ነገር እንደነዚህ አይነት መልካም ልምዶችን ለኢትዮጵያም ማስተማር ነው። ይቅርታ በምንም መንገድ ትናንትናን አይቀይርም የይቅርታ ዋና አላማ ነገን ለማቅናት ነው። ትናንትናማ ሆነኮ ስንት ህይወት ወደቀ፣ ስንት ንብረት ወደመ የሚቀየር ነገር የለም። ነገ እንዳይበላሽ ለማቅናት ነው ይቅርታ የሚመጣው እንጂ ትናንትና ሸዋሮቢት ላይ ምንም አይነት በደል አልተፈጸመም ለማለት አይደለም ተፈጽሟል። ግን በደል በደልን እየወለደ እንዳይሄድና ሀገርን እንዳያፈርስ ነገን ለማቅናት ነው ይቅርታ የሚደረገው፣ ሰውም የሚፈታው ከዚህ ጋር ቢያያዝ ጥሩ ይመስለኛል። አንዳንዶች በተለየ መንገድ ተበዳይ ሆነው ይቀርባሉ። ከእስር የተፈቱ ሰዎች ስለግል ቂም ከሆነ ከኔ በላይ የሰደቡት ከኔ በላይ ያዋረድዱት ሰው የለም። በግል ከሆነ ጉዳዩ ያን ኮምፕሮማይዝ የምናደርገው የትልቅ ሀገር ሃላፊነት እጃችን ላይ ስለወደቀ በትልቅ ሀገር ልክ መመላለስ ስለሚኖርብን መሆኑን መገንዘብ ይኖርብናል።

ምናልባት በቀደም እኛም ደንግጠን ነበር የሚል ነገር መከላከያ ተናግሬ ብዙዎች ጥያቄ አድርገውታል። ዲያስፖራዎች እንኳን ይገባችኋልና ይገርማችኋል እኛም ደንግጠን ነበር። ይሄን ስል እኔም ደንግጬ ነበር አንዳንድ ጓደኞቼም ደንግጠው ነበር። ነገርግን እኔ እስከዚህ ቀን እስረኞች እስኪፈቱ ድረስ እስረኞች ከተፈቱም በኋላ ጥሩ እርምጃ ነው የሚል ሰምቻለሁ። ሲታሰሩም እሰር ያለኝ መንግስት የለም ሲፈቱም አንድም መንግስት የጠየቀኝ የለም። በነገራችን ላይ እነዚህ ሰዎች ታስረዋልና ፍታ ብሎ የጠየቀኝ መንግስት የለም ይሄ እውነት ነው። ከውጪዎች ጋር የሚያያዝ ጉዳይ አይደለም። ነገርግን እስረኞቹን በሚመለከት እኛ መሃል ብዙ ንግግሮች ነበሩ። ሁሉን አላነሳም አንድ ሁለቱን ብቻ ላንሳ። ለምሳሌ ደብረሲና ደርሰው እያሉ ጥቂት አመራሮች አሁን እስረኞችን እንፍታ ወያኔዎች ገብተው ከሚፈቷቸው እኛ እንፍታቸውና ሃይላችንን ሰብሰብ አድርገን ሀገራችንን እንከላከል የሚል ሃሳብ በቅንነት ያነሱ ሰዎች ነበሩ። ትላልቅ ሃላፊዎች የኢትዮጵያን ክብር በሚያዋርድ መንገድ እየተሸነፍን ነውና አንፈታም ብለን ወሰንን። ትንሽ ዋል አደር ያለ ጉዳይ መሆኑ እንዲገባችሁ ብዬ ነው።

ሁለተኛው የብልጽግና ስራ አስፈጻሚ ጽሁፍ አዘጋጅተን ያወያየነው ከወር በፊት ነው። አዲስ ሰርፕራይዝ አይደለም ለኛ ያዋጣል ወይስ አያዋጣም ብለን አሁን መንገር የሚቸግረኝን ነገር አንስተን ይጠቅመናል የግል ቂም አይደለም። ሀገር ማጽናት አለብን ጠላት የምናዳክመው በመውጋት ብቻ ሳይሆን አንዳንዴም መልካም ነገር በማድረግም ጭምር ነው ብለን ተወያየን። ይሄ ውይይት እስከታች ድረስ ይቀጥል ብለን አዲስ አበባ እንኳን የሃይማኖት አባቶች፣ ባለሃብቶች፣ ምሁራን ሁሉም ተወያይቶበታል። አሁን ደርሶ ድንገት ሆነብኝ የሚለው ጉዳይ ተቀባይነት የለውም።

ተወያይተንበታል። አዲስ አይደለም። ወር ከቆየ በኋላ አዎ ተወያይቻለሁ ግን እንዲህ አልመሰለኝም እገሌን አልጠበቅኩም ይላሉ። ፖለቲካሊ እስረኞችን በመፍታት እነዚህን ጉዳዮች እናሳካ ነው ያልነው እንጂ እነማን ይፈቱ የሚለውን በቀደም ህዳሴ ግድብ የሚኒስትሮች ስብሰባ እስካደረግንበት ቀን ድረስ እኔም አላውቅም። ወስነናል እንፍታ ብለን አቃቢ ህግ ሲያጠና ቆይቶ ዝርዝር አመጣልን። እነንትና አይቻልም፣ ይቻላል በሚል ተጨቃጭቀን በተወሰኑ ሰዎች ላይ ወስነን መጣን። ግለሰቦች አልነበሩም የንግግሩ ማእከል ይሄ ጄስቸር ያስፈልጋል፣ ዝም ብሎ ድርቅ ያለ ነገር ብቻ አድርገን ሀገራችንን እንዳንጎዳ የሚል ነበር ሃሳቡ።

አሁን በተፈቱ ሰዎች እኔ የተማርኩት ትልቁ ትምህርት እንኳንም ለዲሞክራሲ ብዬ እንኳንም ዲያስፖራዎች እንዳይከፋችሁ ብዬ እንኳንም አንዳንድ ኢትዮጵያ ወዳድ አክቲቪስቶችና ነጋዴ ዩቲዩበሮች እንዳይከፋቸው ብዬ የጦርነት እቅድ አላወያየኋችሁ። አወያይቻችሁ ቢሆን ኖሮ እስካሁን ደብረሲናና ደብረብርሃን ውጊያ ነበር። ምክንያቱም በጣም እቅዱ ውስብስብ ነበር። በጋቸና ግንባር ሄደን ፈንጂ ካለን ረግጠን ተኩስ ካለ እንዲህ አቀናጅተህ፣ በዚህ መስመር ገብተህ ሞተህ በዚህ ሰአት ውስጥ ጋሸናን ትይዛለህ የሚል ነው ውይይቱ። ወደ ጭፍራ ቡርቃ ስትመጣ ይለያያል ባህሪው። ለምሳሌ ከቡርቃ ባቲ በቀጥታ ብትሄድ በጣም አጭር ነው።

እኛ ግን በቀጥታ አልተጓዝንም። በግራ በኩል አስፍተን ሁለት ሶስት ቀን የሚፈጅ መንገድ ተጉዘን ምክን ያቱም ባቲ ከፍታ ቦታ ላይ ስላለ ቀጥታ ከሄድን ጠላት ረዘም ላለ ጊዜ ሊከላከል ይችላል ብለን ስላሰብን በግራ አስፍተን ስንጓዝ ማታ ማታ ስንጓዝ ያው በረሃውን እንዳያችሁት እሾሃማ ነው አያስጉዝም። ማታ ማታ መጓዝ አይቻልም ቀን ቀን ስንጓዝ ከፍተኛ በረሃ አለው መንገድ የለም፣ ውሃ የለም።

ወታደሩ ሽንት እየጠጣ ነው የተጓዘው። ለምን ተደረገ ያላችሁ እንደሆን ሴንትራል ኮማንዱ አጠቃላይ እቅዱን ቢያውቅም የጋሸና ስፔሲፊክ እቅዱ እና በምስራቅ የነበረው እቅድ ይለያያል። ከምንም በላይ ደብረሲናና በሸዋ የነበረው ደግሞ በጣም የተለያየ ነው። በሸዋ ያለው ደግሞ ባለበት ተከላክለህ አቁም ነው የሚያውቀው። እኛ የምናውቀው ቡርቃን ከመያዛችን በፊት ከካዛኪታ በፊት ሃርቡን ቆርጠን ኮምቦልቻንና ደሴን ኮምፕሮማይዝ ማድረግ አለብን። ምክንያቱም እንደሌላው ቦታ እየገፋን እየገፋን ከሄድን ቀናት ስለሚወስድ ኮምቦልቻና ደሴን ጠላት ያጠፋቸዋል። ማጥፋት እንዳይችል አስደንግጠን ነው መውጣት ያለብን ብለን ሃርቡን ቆርጠን ነው የወጣነው። ሃርቡን ለመቁረጥ 990 ኪሎሜትር መጓዝ ነበረበት እዝ ሙሉ፣ መንገድ የለም በዛ በረሃ ውስጥ ይሄን እቅድ ተወያተን ቢሆን ኖሮ ተሳስተሃል ጋሸና ላይ መስበር አያስፈልግም በደብረሲና መጀመሪያ እናድርግ ስትሉ ስራው ሳይሰራ ይቀር ነበር። ምን ለማለት ነው አሁን በወሰነው ውሳኔ ሂደቱን ለኛ ተውት ውጤቱን ብቻ እናንተ....

መመዘኛው ውጤት ከሆነ ብቻ ነው መልካም የሚሆነው ሂደቱ አንዳንድ ጉዳይ ለንግግር ስለማይመች ያው ለ5 አመት እናንተም ባትመርጡን የእናንተ ወላጆች መርጠውናልና በእርግጠኝነት የምነግራችሁ ውጤቱ ያምራል። ባሳየነው ጀስቸር ይመጣል። ነገርግን በዚህ ጩሀት ውስጥ በጣም ብዙ ድምጾች ይቀላቀላሉ። አንዳንዶች እዚህ ፊትለፊት የማያቸው በጦርነቱም ጊዜ ሲፋለሙ የነበሩ ሰዎች ቢቆጡ ቢደነግጡ ቢቃወሙ ምንም ችግር የለም እነሱን ማስተናገድ በደስታ። ነገርግን ጦርነቱን ስናደርግ ጦርነቱ አያስፈልግም አትዋጉ ሲሉ የነበሩ ሰዎች አሁን ትናንትናን ረስተው ዛሬ ደግሞ ከሳሽ ሲሆኑ ትንሽ ኢትዮጵያዊ ስለሆንን እናፍርባቸዋለን። ያሳፍራል እሱ። በአንድ ወቅት ለዚህ ሁኔታ የሚመች ሜታፎር ስላለኝ ለእናንተም እግረመንገድም ልምድ እንዲሆን ልንገራችሁ በአንድ ወቅት አንድ ንጉስ ከንግስቲቱ ጋር ነፋስ ለመውሰድ ትንሽ ወጣ ብለን እንምጣ ብሎ ውሃ አካባቢ ይሄዳሉ።

የሄዱበት የውሃ አቅራቢያ አንድ አሳ አስጋሪ አሳ ለማጥመድ ይፍጨረጨራል። ንጉሱም በማስተዋል ያየዋል። ከብዙ ድካም በኋላ አንድ አሳ አስጋሪው ሲያወጣ ንጉሱ አሳውን በጣም ስለወደድኩት ያምጣልኝና ልግዛው ይላል። አብረው የነበሩ ሰዎችን ጥሩት ሰውዬውን ንጉሱም በጣም ወድጄዋለሁ አሳውን ብሎ አራት ሺህ ብር ከፍሎት አሳውን ይወስዳል። ንግስቲቱ በጣም ይበሳጫሉ። “ይሄን የሚያክል ገንዘብ

ለአሳ እንዴት ይሰጣል?" ብለው ገና ለአሳ አስጋሪው አሳውን አስረክቦ ገንዘብ ሲቀበል ፊታቸውን አይቷል። ንጉሱ ሳቅ ይላሉ ንግስቲቱ ደግሞ አኩርፈዋል። ከዛ አካባቢ ሸሸት ሲል ንግስት ይቆጣሉ ""እንዴት አንድ አሳ አራት ሺህ ብር ይገዛል? ይላሉ።

ንጉሱም አሁን እኮ ገዝቼዋለሁ ጭቅጭቅ አያስፈልግም ግድ የለህም መላ ፈልጌ እንመልሰዋለን ይላሉ ንግስቲቱ። "እሺ መላው ምንድነው" ሲባሉ "አሳ አስጋሪውን ጠርተን አሳው ወንድ ነው ወይስ ሴት ብለን እንጠይቅና ወንድ ካለን አይ እኛ ሴት ነው የምንፈልገው ሴት ነው መልስ እንላለን ሴት ነው ካለን ደግሞ አይ እኛ የምንፈልገው ወንድ ነው መልስ እንለዋለን" ይሉና ንግስቲቱ ንጉሱም ተስማምተው አሳ አስጋሪው ይጠራል። ሲመጣ ይሄን ጥያቄ ይጠየቃል። ቀደም ብሎ ስለገባው አዝማሚያውን ስላወቀ አይ ንጉስ ስለወደዱት የኔ አሣ ጾታ የለውም ይላል። ንጉሱ በጣም ይደሰቱ እና አራት ሺህ ብር ይጨምሩለታል ታዲያ አጋጣሚ ለማመስገን ጎንበስ ሲል ከኪሱ አስርፍ ሳንቲም ትወድቅና ድምጽ እያሰማች ትሸሻለች ይሄ ስምንት ሺህ የወሰደ አሳ አስጋሪ እየተንከባለለ መሬት ላይ ሳንቲሟን ይፈልጋል። ምንጣፍ ነበር እሱንም እያነሳ ይፈልጋል። ንግስቲቱ በቅድሙ ውሳኔ ተበሳጭተዋል እናም "ይሄን የሚያክል ገንዘብ ወስደህ ለአስር ሳንቲም እንዲህ አካባቢውን እያተረማመስክ ትፈልጋለህ?" ብለው ይጠይቁታል። "ንግስት ሆይ እኔ እኮ ለሳንቲሙ አይደለም በቂ ገንዘብ ወስጃለሁ እዚህች ሳንቲም ላይ የንጉሱ ፎቶ አለ።" እና የንጉሱ ፎቶ ወድቆ የሳቸውን ብር ወስጄ መሄድ ልቤ አልፈቀደም" ሲል አሁንም ንጉሱ አራት ሺህ ብር አውጥቶ ይሰጣል። ንግስቲቱ ይሄ ነገር ከቀጠለ ያለው ነገር ሁሉ ሊወሰድ ስለሆነ ጭቅጭቁን ባቆም ይሻለኛል ብላ አሳ አስጋሪውን አስራሁለት ሺህ ብር ወስዶ ሄደ።

የዚህ ታሪክ ፍሬ ነገር ምንድነው? ያላችሁ እንደሆነ ኢትዮጵያ እኔና እናንተ አሳ አስጋሪ ነን. ስራችንን በሀገራችን ነው እየሰራን ያለነው፣ ማንም ጋር አልሄድንም። ጠገብ ያሉ ናቸው መጥተው ለማየት እኛ አካባቢ እንጂ እኛ ከኢትዮጵያ ውጪ አንድ ሜትርም አልተጓዝንም። ቦታችን ላይ ስራችንን እየሰራን እያለን አሁን ማገዝ የሚችሉ መከልከል የሚችሉ ሀገራት ምን አልባት የወደፊት ኢትዮጵያን ብቃት አቅም ያዩ ሀገራት በቅርብ ሁኔታውን ሲከታተሉ ቆይተው ትናንሽ ነገር እናድርግ ሲሉ ቆይተው ጠላቶቻችን በንግስቲቱ የተመሰሉት እስረኛ ስንፈታ ቀድሞ የጮኸው እኮ የተፈታለት አካል ነው። ይሄን ታውቃላችሁ? ምክን ያቱም እስረኛ ባንፈታ ኖሮ እናንተም እግረ ደረቅ ትሆኑ ነበር ቢያንስ የአፍሪካ ህብረት ጉባኤ ይሰረዝ ነበር። ሀገራችሁ መጥታችሁ

የዘንድሮ የአፍሪካ ህብረት ስብሰባ ከሁለት ሳምንት በኋላ የሚካሄደው ፊዚካሊ እዚህ እንዲደረግ የተወሰነበት ዋና ምክንያት ኢትዮጵያ በሚባለው ልክ ስላልሆነች ነው።

በብዙ ሺህ የሚቆጠር ዲያስፖራ ሄዶ እየተዝናና ነው ያለው፣ እስረኛ እየተፈታ ነው ያለው፣ ተስፋ ያለው ሀገር ነው የሚል ነገር ስለፈጠረ ነው። የአፍሪካ ህብረት ስብሰባ እንዲደረግ የተወሰነው ቀላል ግን አልነበረም። እናንተ እግረ እርጥቦች በኪሳችሁ ካመጣችሁት በላይ የኢትዮጵያን ክብር በማስመለስ የነበራችሁ ሚና ከፍተኛ ስለሆነ የንግስቲቱን ጨኸትና ለቅሶ አታድምጡ። እኛ አሳ አስጋሪዎች በእያንዳንዷ ውሳኔ ስሙኒ የማያተርፍ ካልሆነ አናደርግም። ለትርፍ ነው የምንሰራው። ትርፉ ደግሞ ሉአላዊነት፣ ብሄራዊ ጥቅም እና የሀገር ክብር ነው። ይሄን ኮምፕሮማይዝ የማያደርግ ስራ አንሰራም። ለዚህ ደግሞ መቼም አንጠረጠርም ቢያንስ አሁን። ይሄን ያልኩበት ዋናው ምክንያት ውጡ ውጡ ውጡ እያሉ ሲጨቀጭቁን እኮ እኛ እንሞታለን እንጂ የእናንተን ፕሮፖጋንዳ ኢትዮጵያ ውስጥ አይፈጸምም። ስለዚህ በዩቲዩብ እና በፌስቡክ የምትሰሟቸው ንግስቶች ብዙ ነገር እንዳናገኝ የሚፈልጉ ናቸው። ሁለተኛው ሃሳብ ከዚህ ጋር የሚያያዘው እኛ ብዙ የተሰጠን፣ ብዙ የተደረገልን ለምስጋና ጊዜ እንኳን ያላገኘን ህዝቦች ነን። እኔ አሸንፌያለሁ ብዬ በእብሪት የምወጠር ምስኪን አይደለሁም እንዴት እንዳሸነፍኩ አውቀዋለሁ።

ፈጣሪዬ ከኔ ጋር ባይኖር ኖሮ አይሆንም። ወታደሮች ተዋግተናልና ማእረግ አምጣ አሉ፤ የተፈናቀሉ ሰዎች መልሱን አሉ፣ የተጎዱ ሰዎች የምታውቁትን ጠየቁ እሱም ይጠይቃል እስረኛ ፍታ ነው የሚለው። እኛ ታግለን የምትሉ ሰዎች እውነት ነው ታግላችኋል ከምንም በላይ ግን ከኔ ጋር የታገለውን ስለማውቀው እናንተን ብቻ አላደምጥም ለማለት ነው።
አሁን የሚያስፈልገን ጊዜ እና ሃብት ነው። እሱ በእጅጉ ያስፈልገናል። አንደኛ የደረሰብንን ስብራት ለመጠገን፣ የቆሰሉብንን ሰዎች ለማስታመም የፈረሰብንን ሃብት መልሶ ለመገንባት ጊዜ እና ገንዘብ ያስፈልጉናል። በጦርነቱ ጊዜ ከሀገር ክብር ሞት እንዳልነው አሁን ደግሞ ከሰፈር ጭቅጭቅ ግንባታ ያስፈልጋል። ይገርማችኋል ሰሞኑን በዚህች ሶስት አራት ሳምንታት እየመጣችሁ በዚህ ሁሉ ጭቅጭቅ ከደብረሲና እስከ ቆቦ ባለው ብቻ ትናንሽ ፋክቶች ለመስጠት በጥቂት ሳምንታት ውስጥ ከሁለት ሶስት ከተሞች ውጪ መቶ ፐርሰንት በሚባል ደረጃ የቀሩን ከተሞች አሉ መብራት መልሰን ጠግነናል። መብራት ስንመልስ የመብራት ሃይል ኩባንያው ከፍተኛ የገንዘብ ችግር

ስላለበት ከባንክ ተበድረን በጥቂት ሳምንታት የቀሩ ከተሞች አሉ ግን አብዛኛው ላይ መብራት አስገብተናል። ቀጣይ ስልክ መልሰን ስራ አስጀምረናል።

ሶስተኛ በአማራ ክልል ብቻ 1.4 ገደማ ዜጎቻችን ተፈናቅለዋል። ከነዚህ ውስጥ በዚሁ ሁለት ሶስት ሳምንት 1.2 ሚሊየን ወደ ቀያቸው መልሰናል። ሁለት መቶ ሺህ ገደማ ወደ አድርቃይ ያሉ አሉ። በዛ በኩል ያለው ነገር ትንሽ ስራ ስለሚፈልግ ከደብረሲና እስከ ወልዲያ ያለው ግን ተመልሷል። ባለበት ግን ብዙ መታገዝ የሚፈልግ ነው። ሆስፒታል ከዚህ እስከዛ ባለው ርቀት ውስጥ 40 ሆስፒታሎች አሉ 40ውም ቤዚክ ሰርቪስ ጀምረዋል። የሚቀሩትን ነገሮች አሉ ወደ ተሟላ ሰርቪስ ለመድረስ ግን 40ውም ጀምሯል።

ከዚህ እስከዛ 400 ጤና ጣብያ አለ ከሞላ ጎደል ጤና ጣቢያዎቻችን ቤዚክ ሰርቪስ የፌዴራል እና የአማራ ክልል መንግስት በከፍተኛ ቅርበት አሁን ያለው የአማራ ክልል መንግስት ቲም ልማት የሚናፍቅ ስለሆነ በከፍተኛ ርብርብ የተሰራ ስራ ከዚህ ውጪ ንግድ ባንክን ብቻ ብንወስድ ከደብረሲና ጀምሮ እስከ ቆቦ 140 ቅርንጫፎች አሉ። 140ውም ቅርንጫፎች ጉዳት ደርሶባቸዋል እነሱን መልሰን ጠግንን ዛሬ ስራ ይጀምራሉ። ሃያው ምናልባት በጥቂት ሳምንታት ውስጥ ስራ ይጀምራል።

ስለዚህ መልሶ ግንባታ ጊዜ፣ ገንዘብ፣ እቅድና አመራር ይጠይቃል። ውጊያው አመራር ዲማንድ እንደሚያደርገው ሁሉ ይሄም ካልተመራ በስተቀር ባጠረ ጊዜ ውስጥ መልሶ እንደዚህ አይነት ስራ መስራት ያስቸግራል። ለእንደዚህ አይነት ስራ ሲባል እንኳን ግዜ እና ሃብት ያስፈልጋል። የተፈናቀሉ ሰዎች አሁን ብዙ ድጋፍ ያስፈልጋቸዋል። ሆስፒታሎቻችን አሁን በቂ እቃዎች የሏቸውም ተዘርፈዋል። ጤና ጣብያዎቻችን እቃ የላቸውም። የጀመርነውን ሰርቪስ የበለጠ እያሳለጥን ወደሚፈለገው ደረጃ እስክናመጣ ድረስ ሰፋፊ ስራዎች ከፊታችን እንዳለ ማሰብ ያስፈልጋል።

ውጊያ ብቻ ሳይሆን ሀገር መገንባት ያስፈልጋል። ብዙዎቻችሁ የዛሬ 4 ወይም 5 አመት በእርግጠኝነት ዩኒቲ ፓርክ፣ እንጦጦ፣ ፍሬንድሺፕ ምናልባት መከላከያ የመጎብኘት እድል ካገኛችሁ፣ ኢንሳን ካያችሁ የአዲስ አበባን መንገድ ላይ ያለውን ጽድት በእርግጠኝነት አልነበረም። ታውቁታላችሁ ይሄን ነገር በሚቀጥለው ስትመጡ ይሄው የሚጠብቃችሁ ከሆነ ግን ዋጋ የለውም። ብዙ ነገር መዘመንና መሻሻል

አለበት። ገና ብዙ ያልሰራነው ስራ አለ። እነዛን ስራዎች እንድንሰራ የተከልናቸው ነግሮች እንዲበቅሉ ምን ያስፈልጋል ካላችሁ ጊዜ እና ሃብት ያስፈልጋል። ይሄን ለማግኘት ደሞ ሽሚያ ነው። ለምሳሌ ውጊያን ለአንድ ወር ማዘግየት ከተቻለ ብዙ የሚሰራበት ጊዜ ነው። ይሄን ታሳቢ ማድረግ ነው።

ዲፕሎማሲን በሚመለከት ኢትዮጵያ ታላቅ ሀገር ናት። 100 ሚሊየን በላይ ህዝብ ያላት ሀገር ናት። የሊግ ኦፍ ኔሽን መስራች አባል ሀገር ናት ብቸኛ አፍሪካዊ ሀገር፣ የአፍሪካ ህብረት መስራች ሀገር ናት፣ በኢትዮጵያ ልክ ወዳጆቻችንን እያስረዳን እያሳመንን ወደ ቦታው መመለስ ያስፈልጋል እንጂ እንደ ጎረምሳ ብቻ አይሆንም። በክብራችን ሲመጡ የነበረን ጽናት እንደተጠበቀ ሆኖ ከዚያ መለስ ደግሞ ንግግር ያስፈልጋል።

እንግዲህ እድለኛ ከሆናችሁ ከፊታችን በጣም ትላልቅ ፕሮጀክቶች በሚቀጥለው ሳምንታት ጊዜ ሲመቻች ምርቃቶች እንጀምራለን። ለምሳሌ ንግድ ባንክ በጣም ድንቅ ሆኖ ተሰርቷል እንድትጎበኙ በዚሁ አጋጣሚ እንድትጎበኙ እመክራለሁ። እሱ ይመረቃል ሌላብዙ ያዋጣችሁባቸው ፕሮጀክቶች ምርቃት ይካሄዳል። አሁን እኛ ጩኸት አንፈልግም። ሌላውን አረጋግተን ስራዎቻችንን መጨረስ እንፈልጋለን። ዲፕሎማሲው በዚህ አይን ቢታይ ኢትዮጵያን የሚመጥን ዝግጅት ያስፈልጋል።

ከሰሞኑ የወታደር ማእረግና ክብር ጋር በሚያያዝ ከእስረኞች መፈታት በላይ እጅግ ያሣዘነኝ ስሞታ ከወታደሮች ጋር የሚያያዝ ነው። የኢትዮጵያ መከላከያ ሰራዊት ቀደም ብዬ እንዳነሳሁት ከዚህ በፊት እንዲህ አይነት ፈተና ገጥሞት አያውቅም። ከጣልያን ጋር ሲዋጋ፣ ከሶማሊያ ጋር ሲዋጋ ኢትዮጵያ እና ሶማሊያ ናቸው። በደርግና በወያኔ የነበረውም ውጊያ ነው እንጂ የራሱን መከላከያ አፍርሶ ኢትዮጵያን አፈርሳለሁ እያለ ከመጣ ሃይል ጋር አልነበረም። ጣልያን እንኳን ኢትዮጵያን እገዛለሁ እንጂ አፈርሳለሁ እያለ አልመጣም።

ሁለተኛው የመጣው ጠላት ብቻውን አልመጣም ብዙ የሚጋልቡ ሃይሎች ነበሩ። አሁን ያሉ የመከላከያ አመራሮች በጡረታ የተባረሩ፣ የተመለሱትና መከላከያ ውስጥ የነበሩት አሁን ያለው ሴንትራል ኮማንድ የሚባለው ቲም ሲሾም ኢትዮጵያ ውስጥ ነበረች። ጦርነት ከተጀመረ በኋላ ነው ቺፍ ኦፍ ስታፍ፣ ዲፑቲ ቼፍ ኦፍ ስታፍ የሆኑት

እንደምታውቁት አንድ አመት እየተዋጋን በአመት ጊዜ ውስጥ ኢትዮጵያን ከመፍረስ መታደግ ብቻ ሳይሆን ባለፉት 30 አመታት ከነበረን የሀገር መከላከያ ሰራዊት ቁጥር አንጻር ምንም ሳይጋነን ሁለት እጥፍ የሚሆን ሃይል ገንብተዋል። ባለፉት 30 አመታት ከነበረን አየር ሃይል ምንም ሳላጋንን አስር ሃያ ሰላሳ የላቀ አየር ሃይል ገንብተዋል። ይሄን እያደራጁ ነው ኢትዮጵያን ከመፍረስ የታደጉት። ብዙዎችን ፈንጂ እርገጥ እያሉ ማለት ነው። ስናዋጋቸው አንተ አማራ፣ አንተ ኦሮሞ ነህ አላልናቸውም ኢትዮጵያዊ ናችሁ ብለን ነው ሙቱ ያልናቸው። አሸንፈው ሲመለሱ ግን እንትና አማራ ነው፣ ኦሮሞ ነው የሚሉ ሰዎች ስሰማ በጣም ልቤ ያዝናል።

ለሀገር መከላከያ ጀግናዎች በዚሁ አጋጣሚ ማስተላልፈው መልእክት እናንተ ዘራችሁ ኢትዮጵያዊነት ነው። የኢትዮጵያን ባንዲራ መጠበቅ ነው። የኢትዮጵያን ባንዲራ አልጠብቅም ካላችሁ ግን እንደቅድሙ ሁለተኛ የአለም ጦርነት ጋር መሄድ አያስፈልገኝም፣ ጀርመን አልሄድም፣ ጃፓን አልሄድም። እንደወያኔ ትቀጠቀጣላችሁ ማንም ቢሆን። የኢትዮጵያ ከፍታ ብቻ ነው አሸናፊ የሚያደርገን ከዚያ የወረደው ሃሳብ ብዙ ስለማይጠቅም ጣጣችን ስላላለቀ አሁንም አንድ ሆነን አብረን ብንቆም ነው የሚሻለው። ልክ እንዳለቀ ሆነን ክፍፍሉ አይጠቅምም።

የመጨረሻው ሃሳቤ የኢትዮጵያ ዲያስፖራና ከተሜዎች ከእንግሊዝ እግር ኳስ ደጋፊዎች ያነሱ ናቸው። የእንግሊዝ እግርኳስ ደጋፊዎች ማንቺስተር ቢሸነፍ ማሊያውን አውልቆ ከእንግዲህ በኋላ አልለብስም አይልም። ለክለቡ የሚያዋጣውን ነገር አላዋጣም አይል። ሲሸነፍም የማንቺስተር ደጋፊ ነው ሲያሸንፍም ደጋፊ ነው።

እናንተ ኢትዮጵያን አፈርሳለሁ ያለ ሃይል አታፈርስም ብላችሁ ጮሃችሁ በገንዘባችሁ፣ በጊዜያችሁ መንግስታችሁን አለን ብላችሁ ካሸነፋችሁ በኋላ እስረኛ ተፈታ ብላችሁ ማሊያ አውልቃችሁ የምትጥሉ ከሆነ ይሄ የኢትዮጵያዊነት ልክ አይደለም። ብንሸነፍ ኖሮ ምን ሊያጋጥመን ነበር ብዬ አሰብኩ። ለካ አናውቀውም ነበርም ትሉ ነበር? ለማንኛውም አሸንፈንናል፣ እናሸንፋለን፣ የፈረሰውን እንገነባለን ኢትዮጵያ ቅንጣት ነገር እንዳትጠራጠሩ ልጆቻችን ይቺኛዋን ኢትዮጵያ አይረከቡም።

ልጆቻችን እናንተ በወጣችሁበት መንገድ ለስደት አይሄዱም፣ ነጻነቷን ጠብቃ፣ አንድነትቷን ጠብቃ፣ የበለጸገች ኢትዮጵያን ለመፍጠር ከምንም በላይ ከኛ

የሚጠበቀው አንድ መሆን ብቻ ነው። አንድ ብንሆን አለም ቢደመር እንኳን ኢትዮጵያን አይችላትም። ስለዚህ ከስሜት፣ ከብስጭት፣ ከዘር፣ ከመንደር፣ ከሰፈር ወጥተን በኢትዮጵያዊነት ልክ ሆነን ኢትዮጵያን ከፍ እንዳደረጋችኋት ይበልጥ ከፍ እንድናደርጋት አደራ ልላችሁ እወዳለሁ።

**ኢትዮጵያ በልጆቿ ጥረት ታፍራና ተከብራ፣**
**በልጆቿ ደምና አጥንት ነጻነቷን ጠብቃ፣**
**በልጆቿ ላብና ጥረት ብልጽግናዋን አረጋግጣ ለዘላለም ትኑር!**
ጥር 9፣ 2014 ዓ.ም

# ለዘማች የሚዲያ እና ኪነጥበብ ባለሞያዎች የተደረገ የምስጋና ንግግር

ስለ ጦርነትና ስለተገኘው ድል ኮራ ብሎ ለማውራት ለመግባባት የሚያስችለው ትክክለኛው ስብሰብ የዛሬው ነው፡፡ በቅርበት ጉዳዩን የመራ፣ የተራበ፣ ድምጽ ያሰማ፣ የተደበቀ፣ ያበረታ፣ ያከመ ስብሰብ ነው፡፡ ያስቸገሩን ይህንን ሳይሰሙ የሚፎክሩት ናቸው፡፡ ዛሬ ዋና መልዕክቴ ለእናንተ ስለሆነ እርግጠኛ እንድትሆኑ የምፈልገው ኢትዮጵያ አሸንፋለች። እናንተ አሸንፋችኋል። አለም ማሸነፋችሁን በንግግር ሳይሆን በተግባር እናንተ ብዙ ስለማትሰሙ ነው በተግባር አምኗል፡፡ የማይቻሉ የማይሸነፉ በሀገራቸው ጉዳይ የማይደራደሩ ህዝቦች ናቸው የሚለውን አለም በሙሉ ተቀብሏል፡፡ እኛ ነን ለመቀበል አሁን እየተቸገርን ያለነው። እኛ ያገኘነውን ድል ጠላቶቻችን አግኝተውት ቢሆን ኖሮ ልክ እንደግንቦት ሃያ እንደድሮ ነበር የሚሆነው፡፡ እናንተ ጀግኖች ስለሆናችሁ ለጀግኖች የሚገባውን መልዕክት ብቻ ለማስተላለፍ እሞክራለሁ፡፡ የመጀመሪያውና በጣም ወሳኙ መልዕክት እስከአሁን ከሰራችሁት የበለጠው ፈታኝ ስራ ከፊታችሁ ነው ያለው፡፡ እስከአሁን ካገኛችሁት ድል እስካሁን ካገኛችሁት ውጤት የላቀ ትጋትና ድካም የሚጠይቅ ስራ ከፊታችን ነው ያለው፡፡ ነብዩ መሐመድ በሀገራቸው በሳውዲ በነበረው ውጊያ ረዘም ላለ ጊዜ ህዝባቸውን አሰልፈው ተዋግተው ካሸነፉ በኋላ ከተከታዮቻቸው ጋር ስብሰብ ብለው ሰላት እየሰገዱ ባሉበት ቦታ ተከታዮቻቸው “አሸንፈናል አብቅቷል አሁን ልጆቻችንን ሚስቶቻችንን ቄያችንን የምናይበት ጊዜ ነው” ብለው በሚዘጋጁበት ወቅት እሳቸው ተነስተው” ታላቁ ጂሀድ ከፊታችን ነው ያለው” አሉ። ተከታዮቻቸው “ምን እያሉ ነው? ረዘም ላለ ጊዜ ተዋግተን ብዙ ዋጋ ከፍለን አሸንፈን አሁን በቃ በምንልበት ሰአት እንዴት ነው አዲስ ጂሀድ አዲስ ውጊያ አለ ብለው የሚነግሩን” ብለው ሲጠይቋቸው “ትልቁ ውግያ በጋራ የገጠመንን ጠላት ያሸንፍንበት ሳይሆን ያሸናፊ ስነልቦና ተሸክሞ ራስን ማሸነፍ ነው” አሉ ይባላል፡፡

ስለዚህ አሸናፊዎች ራሳችሁ ካላሸነፋችሁ ድሉ ይበላሻል፡፡ አሸናፊ ራሱን የሚገዛበት መንፈስና ስሜት ከሌለው ያስገኘውን አምርቂ ውጤት ሊያበላሽ ይችላል። ያ

እንዳያጋጥም መጠንቀቅ ይኖርብናል፡፡ ያን ለማድረግ የአየሩ ሁኔታ ከፍ ዝቅ እያለ የሚያስቸግራቹ ሰዎች ለውጥና ዘር የሚሻውን እንክብካቤ እንድታስቡት እንድትጠብቁት ነው ላሳስባችሁ የምፈልገው፡፡ ዘር ጥቂት ነው፣ ያንን ጥቂት ዘር ማባዛት እንደሚቻል የሚያምኑ ልምዱም ሞያውም ያላቸው አርሶ አደሮች ዘርን የሚጠብቁበት የሚንከባከቡበት ባህል አላቸው፡፡ ዘር ጥቂት ቢሆንም ጥበቃ ይሻል። አይጥ ከበላው ነቀዝ ከበላው በሚቀጥለው ክረምት የሚዘራ አይኖርም ነገር ግን ለሚቀጥለው ክረምት ማቆየት ከተቻለ ግን ዘር ተባዝቶ ተበራክቶ የተሻለ ነገር የሚያስገኝ ይሆናል።

ዘር ሁለት ነገር ይፈልጋል፤ ተስፋ አድራጊ እና ጠባቂ ተስፋ አድርጎ እቺን ዘር ቆጥቤ ከአይጥ ከነቀዝ ተከላክዬ ባቆይ ይበራከትልኛል ይበዛልኛል የሚል ተስፋ አድራጊ እና ዘሩ ጥቃት እንዳይደርስበት የሚጠብቀውን ሰው ልክ እንደዚሁ ለውጥ በተሰፋ ካልጠበቅነው ካልተንከባከብነው ሊቀጭጭ ሊጠፋ ይችላል፡፡ ኢትዮጵያውያን የለውጥ ሀሳብ የማመንጨት ድህነት የለባቸውም። ለውጥን ተንከባክቦ ማሳደግ ግን ይቸገራሉ ይባላል፡፡ ላለፉት ሀምሳ ስልሳ አመታት በርካታ ኢትዮጵያውያን አስደናቂ ሐሳቦች አፍልቀዋል። ነገር ግን አሳድገው ለፍሬ እንዲበቃ ማድረግ ተቸግረው ቆይተዋል፡፡ ዘር ከተበላሸ ከተበላ አለቀ ነገሩ ዘርን የበላ አርሶ አደር በረክምት ምርት አይጠብቅም ከተበላሸም እንዲሁ ነው፡፡ እኛ ዘር ቆርጥም መሆን የለብንም። ዘር ቆርጥም ማለት የአመቱ በእለት የሚበላ ማለት ነው። ዛሬ እርቦኛል ብሎ ለዓመት የሚያቆየው ዘር ዛሬውኑ በልቶ አመቱን በሙሉ በረሐብ የሚያሳልፍ መጪውንም ክረምት የሚዘራው የሌለው ማለት ነው፡፡ ኢትዮጵያውያን ዘር ቆርጥም ላለመሆን ዘርን የመጠበቅ ልምምድ ማዳበር ይኖርብናል፡፡ ዘር እህል የሚሆነው እንዲሁ ጠብቀን ስላቆየነው አይደለም። አለስልሰን፣ ውሃ አድርሰን ወይ ዝናብ ጠብቀን፣ ዘርተን፣ አርመን፣ ጠብቀን ሰብስበን ነው ዘር ፍሬያማ ሆኖ የሚበራከተው፡፡ ለውጥ እንዲሁ ነው ስለሰማነው ብቻ ውጤታማ አይሆንም። መድከም ይጠይቃል፣ ማረም ይጠይቃል፣ መንከባከብ ይጠይቃል። እሱን ለማድረግ ዝግጁ መሆናችንን እያንዳንዳችን እርግጠኞች መሆን ይኖርብናል፡፡

አሁን የነበረውን ውጊያ የተሸናፊው ያሸናፊ ወገን የሆኑ ሀይሎች የድሉን ምስጢር ትክክል መገንዘብ ይቸገራሉ፡፡ የዚህ ውጊያ የማሸነፊያ ምስጢር የኢትዮጵያን ሐብት፣ የኢትዮጵያ እውቀት፣ የኢትዮጵያን ጉልበት፣ የኢትዮጵያን የማሸነፍ

ስነልቦና እና ጀግንነት መሰብሰብ የቻለ ኃይል አሸንፏል፡፡ ይሄንን ደግሞ የናቀ የረገጠ ተሸንፏል፡፡ ሌላ ምስጢር የለውም የኢትዮጵያን ጉልበት መሰብሰብ፣ የኢትዮጵያን ሀብት፣ መሰብሰብ የኢትዮጵያን ልጆች መሰብሰብ የቻለው ሃይል አሸንፏል። ኢትዮጵያን የናቀው ቡድን ተሸንፏል፡፡ የሚገጥመን ፈተና አሁን ያለው ችግር መሰብሰብን የሚቃረን ነው። እኔ፣ የተዋጋሁ እኔ፣ ያሸነፍኩ እኔ፣ የተጎዳሁ እኔ፣ የቆሰልኩ እኔ የሚለውን በሽታ እኛ ማድረግ መቻል አለብን። አሁን መከላከያ ብንሔድ እና ወታደሮች ብቻ ሰብስበን እኛ ባንኖር እኮ እኛ ጥሩ ነው እኔ ባልኖር እኮ ባልቆስል እኮ ባልሞት እኮ ኢትዮጵያ አታሸንፍም ቢል ኧረ አርቲስቶችም እኮ ነበሩ፣ ጋዜጠኞችም እኮ ነበሩ፣ ካልተባለ በስተቀረ አኛ ካላደረግነው በስተቀረ ድሉ ሙሉ አይሆንም፡፡ ዛሬ አትሌቶች እኛ መካከል የሉም ግን ዘምተዋል። አርቲስቶች ካሜሪካ መተው ዘምተዋል። አትሌቶች ከአሜሪካ መተው ዘምተዋል። የነዚህን ዘማቾች ሚና የሚያውቀው በአውደ ግንባር የነበረ ሰው ብቻ ነው ከዛ ውጭ የነበረ ሰው ሚናቸውን ላይገነዘበው ይችላል። የእኔ እና የእናንተ ዋንኛ ስራ እኔነትን ደፍቀን እኛነታችንን ማጉላት ነው።

ድሉን በጋራ እንዳመጣነው ጠላት እንደመጣብን ወደፊትም በጋራ ስንቆም አሸናፊዎች እንደምንሆን ማሰብ ማስተማር ከኛ ይጠበቃል፡፡ አሁን እየገጠመን ያለው ችግር መርከባችንን አፍርሰን የኛ የምንለውን ጀልባ ለመስራት የሚሞክሩ ኃይሎች መበራከት ነው። ህወሃት ጀልባውን ሳይሆን መርከቡን እንዲዘውር ፈቅደን ሰጥተነው መርከቡ ላይ ተቀምጦ አንድ ቀን መርከቡ ሲፈርስ ጀልባ ያስፈልገኛል ብሎ ዝግጅት ያደርግ ነበር። መርከቡ መርከብ ነውና አልፈረሰም፤ ጀልባውና እሳቤዎቹ ግን ፈርሰዋል። ከእነዚህ መማር ያለብን መርከቡን ማጠንከር መርከቡን ማጽናት እንጂ መርከብ ላይ ተቀምጠን ጀልባ ስለመስራት ማሰብ ማነስ ነው፡፡ ማነስ ደግሞ ሽንፈትን ያስከትላል ሽንፈትን የሚያስከተልበት ዋና ምስጢር ከፊታችን ያለው ውስውስታ ከፊታኝ ያለው ውቅያኖስ ይዞት እየመጣ ያለው ማዕበል በጀልባ አቅም የምንወጣው አይደለም። መርከቡ ራሱ መታደስ መርከቡ ራሱ መጠንከር ካልቻለ ማእበሉ ከፍተኛ ነውና በጀልባ የሚያስቡ ቡድኖች ጉዞ ሊጀምሩ ይችላሉ ጉዞውን ግን አይጨርሱትም። በመርከብ ያሰቡ ብቻ ናቸው። ከፊታቸው ያለውን ነውጥ ተቋቁመው መሻገር የሚችሉት መሻገር ማሻገር ለልጆቻችን የላቀች ሀገር መተው ከፈለግን ጀልባውን ሳይሆን መርከቡን በጋራ እንድናጠናክረው አደራ ልላቹ እፈልጋለሁ፡፡ ከኛ ሚጠበቀው አንደኛው ጥረት ነው፡፡ እንዲሁ በከንቱ በፌስቡክ

ትንተና የሚሳካ ነገር የለም ጥረት ይጠይቃል ብዙ መቆፈር፣ ብዙ ማረስ፣ ብዙ መዝራት፣ ብዙ ማስተማር ይጠበቅብናል። ለዚህ ደግሞ ከአርት እና ከጋዜጠኝነት ሙያ የተሻለ ነገር የለም። በእናንተ ሙያ ብዙ ጥረት ቢታከልበት ኢትዮጵያን መርከቧን የማጽናት የማበርታት ጉልበት ልትፈጥሩ ትችላላችሁ።

ሁለተኛው ጥበቃ ነው፡፡ ዘራችሁ ቅድም ሲነገር እንደነበረው አነቃችሁ፣ አስተማራችሁ ካሸነፋችሁ በኋላ የሚበተን ኃይል ከሆነ ዋጋ የለውም። ብዙ ጠላት ከግራ ከቀኝ ያለን ህዝቦች ስለሆንን መበተን ለኛ አደገኛ ነው፡፡ ይሔንን ደግሞ የሚገነዘብ እንደእናንተ ያለ ጥረት ያደረገ ሰው ነው፡፡ ተንታኝ አይረዳውም ድካሙ አይገባውም አረጋኸኝ ስቃጥላ እንደበላ ተንታኝ አያውቀውም ተንታኞች በጣም የሚያዝኑት ሲተነትኑ እንኳን የስታር ባክስ ቡና መጠጫ እየያዙ ነው በቪዲዮ ላይ ራሱ አይደብቁትም ነገርየውን። ይሔን የምትረዱ ሰዎች በጥረታችሁ ልክ ጥበቃ ማድረግ አለባችሁ ያገኛችሁትን ድል መጠበቅ። ለአንዳንድ ሚዲያዎች ቀደም ሲል ሹክ እንዳልኳቸው እኛ አሸንፈን ስናበቃ ለልጆቻችን የአሸናፊነት ስነልቦና ሳይሆን ተሸናፊ እነደሆንን አድርገን በየሚዲያዎቻችን እንናገራለን፡፡ ተሸንፈው ሸሽተው የሄዱት ግን አልተሸነፍንም ይላሉ፡፡ አሸንፈናል ብቻ ሳይሆን የማሸነፍን ሳይኮሎጂ ለልጆቻችን ማስተላለፍ እንደሚጠበቅብን ማሰብ ያስፈልጋል፡፡ ማረምም እንደዚሁ ያስፈልጋል ድል አስካሪ ስለሆነ አሳሳች ስለሆነ በየመሀሉ የሚበላሽ ነገር ካለ እያረምን እያረቅን እያስተካከልን ህብረታችን ሳይፈርስ የምንቀጥልበትን መንገድ መፍጠር ያስፈልጋል፡፡ እንዲሁም እንክብካቤ ያስፈልጋል።

አርቲስቶች ባለፈው የሰሩት ስራ ላለፉት ሁለት ወራት ሳይሆን ለሚቀጥሉት ሃያ ዓመታት የሚያገለግል ስራ ነው፡፡ አርቲስቶች በግንባር ያለውን ወታደር አይዞህ ብለውት ይሆናል። የተወለደን፣ የሚድህን የሚያድግን ልጅ ደግሞ ይሰሩታል ይቀርጹታል። ይህ ስራቸው ፍሬ እንዲያፈራ የሚዲያ ሰዎች ኢትዮጵያን የምትወዱ ከሆነ የኢትዮጵያን መሰራት የምትፈልጉ ከሆነ በየሚዲያዎቹ ደጋግማችሁ ልታስደምጡን የሚገባው የነዚህን የአርቲስቶች የጭንቅላት ውጤት ነው፡፡ እሱ ነው ትውልድ የሚሰራው፡፡ ያንን ማድረግ ከቻልን ከፊታችን ያለው ወራት የምናከማችበት፣ የምንሰበስብበት የተበተነውን የምናመጣበት ጊዜ ይሆናል አልፎ አልፎ ችግሮች ሲያጋጥሙ የሰው ስሜት ይዘበራረቃል። አሸናፊዎች ኮምፓሳቸው ጽናታቸው ከፊት ያስቀመጡት አላማቸው ብቻ ነው፡፡ ያን ሊያደናቅፍ የሚያስብ


የጠቅላይ ሚኒስትር ጽሕፈት ቤት
Federal Democratic Republic of Ethiopia
OFFICE OF THE PRIME MINISTER

ማንኛውም ኃይል ከውስጥም ይሁን ከውጭ ትንኮሳ ሲያደርግ ከትንኮሳው ባሻገር ኢትዮጵያን እያሰብን መጽናት አለብን፡፡ ኢትዮጵያን እያሰብን የምንጸና ከሆነ እናሸንፋለን፡፡ የድላችን ምስጢር እሱ ነው።

ከጋዜጠኞች የምጠብቀው ሶስት ነገር፡-

1ኛ/ ህብረ ብሔራዊ አንድነታችንን በሚመለከት በከፍተኛ ኃላፊነት ስሜት መስራት ብትችሉ። ብዙ ሰዎች የዛሬ ሃያ አምስት ሰላሳ አመት ሀገር ለቀው የሄዱና ኢትዮጵያን በዚያ መንገድ የሚያስቡ ሰዎች አሉ፡፡ የዛሬ ሰላሳ አመት የኢትዮጵያ ህዝብ ሃምሳ ሚሊየን አይሞላም ዛሬ ከመቶ ሚሊየን ልቋል፡፡ ግማሹ የኛ ህዝብ የምናወራው ቋንቋ አይገባውም ስራ ይጠብቃል። እኛ ስለፈለግን ሳይሆን በማሳመን ብቃታችን ወደአንድ ጎዳና እንደምንሄድ ማሰብ ይፈልጋል። እናንተ የምታውቋትና የምታስቧት አሁን በተሰራው መልኩ በልጆቻችን ውስጥም እንድትኖር ካላደረግን በስተቀረ በመፈለግ ብቻ የምናስበውን አናሳካም፡፡

2ኛ/ ብሔራዊ ጥቅም ነው። ይቺ ሀገር ብሔራዊ ጥቅም አላት። በአጭር ጊዜ፣ በመካከለኛ እና ረዘም ባለ ጊዜ ውስጥ የምታሳካቸው ፍላጎቶች አሏት። የምንሰራቸው ስራዎች ሁሉ እነዛን ብሔራዊ ጥቅሞች ከግምት ውስጥ ያስገባ መሆን አለበት በስሜት በጉልበት ብቻ ሳይሆን በስሌት ጭምር ሊሰሩ የሚገባቸው ለልጆቻችን የሚጣሉ መሰረቶች እንዳሉ አስባችሁ እንድትሰሩ አደራ እላችኋለሁ።

3ኛ/ ዘላቂ ሰላም ነው ግጭት በጣም ቀላልና የሰነፎች ተግባር ነው። ድካም አይጠይቅም። ግጭት አሁን ሁላችን እዚህ እያለን አንድ ሰው ከኛ መሐል ፊትለፊቱ ያለውን ብርጭቆ እንኳን አንስቶ ቢወረውር ሊያውከን ይችላል። ግጭት የሰነፎች ስራ ነው። ሰላም ግን ከፍተኛ ትእግስት፣ ጥረት ብልሀትን ይጠይቃል። ዘላቂ ሰላም ማረጋገጥ ከቻልን ኢትዮጵያ ትጸናለች ትቀጥላለች። ብዙ ውዥንብሮች እንዳሉ ይደመጣል። በውጊያው ያልበሩ፣ በችግሩ ያልነበሩ በመከራው ያልነበሩ ሰዎች አዳዲስ መከራዎች እንዲበራከቱ አሁንም ይቀሰቅሳሉ፡፡ እኛ ከሕብረብሔራዊነታችን አንፃር ከዘላቂ ሰላምና ከዘላቂ ጥቅማችን አንፃር እያሰብን በምንሰራው ስራ መጠንቀቅ የሚያስፈልገን የኢትዮጵያን አንድነትና ፍላጎት የሚቃረን ስራ እንዳልሰራን ማረጋገጥ ብቻ ነው። ያኔ ተኝተን እናድራለን ተኝቶ የሚያሳድር ስራ ጠላት ሲመጣም በአንድነት

ዘምቶ ሀገርን መከላከል በሰላም ጊዜ ደግሞ ዘላቂ ሰላም የሚረጋገጥበትንና አንድ መሆናችንን የማይሸረሸርበትን መንገድ አበርክቶ አጠንክሮ መስራት የሚጠይቅ ስለሆነ ስለሰራችሁት ጀግንነትና ተጋድሎ እንኳን ደስ ያላችሁ፡፡
እናንተ ባትወጡ ኖሮ ምናልባት ማሸነፍ የምንችል እንኳን ቢሆን ዛሬ ግን አሸንፈን ለምስጋና አንበቃም፡፡ እንድናሸንፍ ብቻ ሳይሆን ድሉ እንዲፋጠንም ከፍተኛ አስተዋጽኦ አበርክታችኋል፡፡ ለዚህ ለልጆቻችሁ በኩራት ኢትዮጵያም ደጋግማ የናንተን ገድልና ጀግንነት እንደምትናገር ተስፋ አደርጋለሁ። ከዚህ ቀደም በገጠሙን ውጊያዎች የተሳተፉና ድል ያገኙ አሁን ድጋሚ የተሳተፉ እና ድል ያገኙ ሲኒየር ሞያተኞች ከኛ መካከል አሉ። እነሱን በድጋሚ እንኳን ደስ ያላችሁ ማለት እፈልጋለሁ።

**አመሰግናለሁ!**

ጥር 16፣ 2014 ዓ.ም

# የህዳሴ ግድብ የመጀመሪያ ተርባይን የኃይል ማመንጨት መርሃግብር ላይ የተደረገ ንግግር

ዛሬ እንደወትሮ የተለመደውን ንግግር ለማድረግ ብዙም አቅም የለኝም። ያለፍንበትን ሁለት ሶስት አመታትና ዛሬ የሆነውን ነገር ስመለከት የፈጣሪ ቸርነትና እርዳታ በእጅጉ ያስደምመኛል። ስለሆነም ንግግሬን የማደርገው በአብዛኛው በምስጋና ላይ ብቻ ያተኮረ ይሆናል።

በመጀመሪያ እጅግ የተከበራችሁ የስራ ሃላፊዎች ፕሮቶኮል ዛሬ ስለማይሰራ አጼ ኃይለስላሴን እንዳመሰግናቸው እንዲፈቀድልኝ እጠይቃለሁ። አጼ ኃይለስላሴ በዚያን ጊዜ ማድረግ የሚያስቸግርም ቢሆን መልካም ሃሳብ መልካም ዘር ለልጆቻቸው ማቆየትና ቀጣዩ ትውልድ ሊሰራ እንደሚችል አስበው በዚህ ቦታ ላይ ይሄንን ፕሮጀክት ዲዛይን አሰርተው ቀጣዩ ትውልድ ይገነባዋል የሚል እጅግ ትልቅ ራእይ በመሰነቃቸውና ያም ህልም በልጆቻቸው እውን ስለሆነ ክብርና ምስጋና ይገባቸዋል። የሳቸው ልጅ የሆኑትና ቀጣዩን ትውልድ የሚወክሉት አቶ መለስ ዜናዊ በስልጣን ዘመናቸው መጨረሻ አለማቀፍ ሁኔታው እና ለኢትዮጵያ ሁኔታ ምቹ ሁኔታ እንደሆነ አምነው ፕሮጀክቱ እንጀመርና በሳቸው ቆይታ የፕሮጀክቱ እድገት እምብዛም ያላደገ ቢሆንም በማስጀመራችውና ከሳቸው በኋላ ያሉ አመራሮች እንደሚጨርሱት ተማምነው ለጀመሩት ስራ ክብርና ምስጋና ይገባቸዋል። ከሳቸው በኋላ አቶ ኃይለማሪያም ደሳለኝ ፕሮጀክቱ በጅምር በቁፋሮ ጊዜ ላይ ከነበረበት ተረክበው እስከደረሰበት ደረጃ ድረስ ለማድረስ በሳቸው ጊዜ የነበረው ምቹ ያልሆነው ፖለቲካዊ አውድ ሳያግዳቸው ላደረጉት ተጋድሎ ከሁሉ በላይ ደግሞ እድለኛ ሆነው ዛሬ ከኛ ጋር ሆነው ይሄንን ድል ለማየት ስለበቁ የከበረ ምስጋና እና አክብሮት እንዲሁም እንኳን ደስ አሎት ለማለት እፈልጋለሁ።

ሶስቱ የሀገራችን መሪዎች የሚከተሉት እሳቤ፣ አይዲዮሎጂ፣ የአመራር ስርአትና የተወለዱበት አካባቢ የተለያየ ቢሆንም ኢትዮጵያዊያንን አንድ የሚያደርግና የኢትዮጵያዊያንን ልክ የሚያሳየውን ይሄን ግድብ ሳያቋርጡ ከሃሳብ እስከ ንድፍ

ከንድፍ እስከ ጅማሮ ከጅማሮ እስከ ተግባር ስላስኬዱ ይህ የኢትዮጵያ የወደፊት ጉዞ ምልከታ እንዲሆን ስለሚያግዝ ወደኋላ መለስ ብሎ ማመስገን ማስታወስ ተገቢ ይሆናል። እኛ የጀመሩትን የጨረስን እንጂ ያስጀመርን ስላልሆንን የጀመሩትን አመስግኖ መጀመር ለሚቀጥለውም ስራ አጋዥ ይሆናል ከሶስቱ መሪዎች በኋላ ሁለት ሚኒስትሮችን በተለየ እንዳመሰግን ይፈቀድልኝ። አንደኛው አቶ አለማየሁ ተገኑ ሲሆኑ ይሄንን ፕሮጀክት ያስጀመሩ በቅርበት የመሩ ናቸው። እሳቸውም ዛሬ መታወስ እና መመስገን ይገባቸዋል። ከሳቸው ቀጥሎ ኢንጂነር ዶክተር ስለሺ በቀለ ሁላችሁም እንደምታውቁት በአለም አቀፍ መድረክም ተጋድሎ ያደረጉ ሚኒስትሮች ናቸው። ሁለቱም ለነበራቸው አገልግሎት የኢትዮጵያ ህዝብ እና መንግስት እኔም በራሴ ስም የማመሰግናቸው ይሆናል።

እንዲሁም ሶስት የመብራት ሃይል ሃላፊዎችን ለማመስገን እወዳለሁ። በመጀመሪያ ዶክተር ምህረት ደበበ የቀድሞ የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ሃይል ባለስልጣን ዋና ስራ አስፈጻሚ የነበሩ ጊቤ ሶስትን ያሰሩ፣ ይሄንን ፕሮጀክት ያስጀመሩ፣ ረዘም ላለ ጊዜ ይሄንን ተቋም የመሩና ሀገራቸውን ወደው እንደዚህ አይነት ፕሮጀክት እንዲከወን የረዱ በመሆናቸው፤ ከሳቸው ቀጥሎም ኢንጂነር አዜብ አስናቀ ይሄንን ተቋም በመምራት እና ጅማሮ ስራዎችን በማስቀጠል ያደረጉትን አስተዋጾ እንዲሁም አሁን ያሉትን የመብራት ሃይል ባለስልጣን ዋና ስራ አስፈጻሚ ሶስቱንም ላመሰግናቸው እፈልጋለሁ። ፕሮጀክቱን በሚመለከት በጋራ የጀመሩ ሁለት ማናጀሮች በተለይ ዛሬ መካከላችን የማይገኙትን ኢንጂነር ስመኘው በቀለን በህልፈታቸው ጅማሯቸው፣ ጥረታቸው፣ ልፋታቸው መና ሳይቀር በወንድማቸው ኢንጂነር ክፍሌ ሆሮ ህልማቸውና ሃሳቦቻቸው በላቀና በተሻለ መንገድ እንዲፈጸም ስለሆነ ለኢንጂነር ስመኘው በቀለ እና ኢንጂነር ክፍሌ ሆሮ ከፍ ያለ ምስጋና እንዳቀርብ ይፈቀድለኝ። ከጅማሮ ጀምሮ የስራ አመራር ቦርድ አባላት ሆነው ያገለገሉ ሁሉም የቦርድ አባላት በተለይ ከለውጡ በኋላ ጠንከር ያሉ ውሳኔዎችን የሚጠይቁ ስራ ውስጥ የነበሩ የስራ አመራር ቦርድ በተለይ ዶክተር አብርሃም በላይ እና አቶ ግርማ ብሩ እንዲሁም ጠቅላላ የቦርዱ አባላትን እንዳመሰግን ይፈቀድልኝ።

ህዳሴ ግድብ ላይ የተሳተፉ ሰራተኞች ስራውን ስለሰሩ በዚህ ሁኔታ ውስጥ የሀገራቸውንና የህዝባቸውን ህልም ስላሳኩ ምስጋና የሚገባቸው ቢሆንም በተለየ

መንገድ ማስታወስ የምፈልገው ከሁለት ወር በፊት ለገጠመን ጦርነት በተወካዮቻቸው አማካኝነት የህዳሴ ግድብ ለአፍታ የሚቆም ከሆነ እዚህ ያለን ሰዎች መጥተን ጦሩን ለመቀላቀልና ውጊያን በመዋጋት የሀገራችንን ክብር ለማስጠበቅ ዝግጁዎች ነን ብለው የላኩት መልእክት ሁሌም ከልቤ የማይፋቅ ነው። እዚህ ያሉት ወታደሮችና ጀግኖች ሰራተኞች ባደረጉት ተጋድሎ ግድቡን እውን ማድረግ ብቻ ሳይሆን የቁርጥ ቀንም አለኝታ መሆናቸውን ስላሳዩ ከልብ ላቅ ያለ ምስጋና ላቀርብላቸው እወዳለሁ። እንዲሁም የሀገር መከላከያ ሚኒስቴር እና የጸጥታ አካላት በቅርቡ ፕሮጀክቱን ለማስጨረስ በምናደርገው ጥረት በየመንገዱ በነበረው ተጋድሎ መስዋእትነት እየከፈሉ በእግር በብዙ ኪሎሜትር እየተጓዙ ሲሚንቶ እያጓጓዙ ያሉ የጸጥታ ሃይላትን በሙሉ ላቅ ያለ ምስጋና እንዳቀርብ ይፈቀድልኝ።

የዲያስፖራ አባላት ገንዘብ በማዋጣት ብቻ ሳይሆን አስፈላጊ በሆነበት ሁሉ ድምጽ በማሰማት የኢትዮጵያ ጥቅም የሚከላከል ሃይል ሆነው ላበረከቱት አስተዋጽኦ ዲያስፖራን ከሁሉም በተለየ በህዳሴው ግድብ ላይ ባላቸው ኮሚትመንትና አስተዋጽኦ ላቅ ያለ ምስጋና እንዳቀርብላቸው ይፈቀድልኝ። ቴክኒካል ኮሚቴ ሆነው ያገለገሉ ፐብሊክ ዲፕሎማሲ ላይ ያገለገሉ፣ በተለያዩ የኢንተርናሽናል ሚዲያ ላይ ሆነው እየሰሩ በተለይም በአርብኛ ቋንቋ፣ በግል ፍላጎታቸው ምንም ክፍያ ሳይከፈላቸው ከተለያየ ሀገር ሆነው ተናበው ዛሬም በመካከላችን የሚገኙ የገርድ አምባሳደሮች በመሆን ለመላው የአረብ ህዝብ ይህ ውሃ ተገድቦ የሚቆም ሳይሆን ኢነርጂ ብቻ ጄኔሬት እያደረገ የተፈጥሮ ኮርሱን ጠብቆ የሚጓዝ መሆኑን በማስገንዘብ ደረጃ ከፍተኛ ተጋድሎ ስላደረጉ እነዚህንም እንዳመሰግን ይፈቀድልኝ።

የኢትዮጵያ ህዝብ በጥቅሉ ስላመነነ ገንዘቡን ስላዋጣ አስፈላጊ በሆነበት መድረክ ሁሉ ለዚህ ፕሮጀክት ድምጽ ስለሆነ ይህ ፕሮጀክት ደግሞ እዚህ የአንድነታችን፣ የመነሳታችን፣ የመላቃችንና የአይበገሬነታችን ምልክት ስለሆነ የኢትዮጵያ ህዝብ ላደረገው ከፍተኛ ተጋድሎ ከፍተኛ ምስጋና እንዳቀርብ ይፈቀድልኝ።
እስካሁን ካመሰገንኳቸው አካላት ሁሉ እጅግ በላቀና ከልብ በመነጨና በከፍተኛ ትህትናና በተለየ ሁኔታ ፈጣሪዬን ላመሰግን እወዳለሁ። ፈጣሪ ባይታከልበት ኖሮ ይሄ ፕሮጀክት ዛሬ የደረሰበት ደረጃ ደርሶ ልናስጀምረው እንደማንችል በሂደት ውስጥ ያለፍን ሰዎች እናውቀዋለን። ይህ ፕሮጀክት እጅግ ፈታኝ የነበረ ብቻ ሳይሆን የገዛነውን እቃ ማስገባት የማንችልበት፤ የቀጠርነውን የውጪ ሰራተኛ ማሰራት

የማንችልበት፤ ጫናው ፍልሚያው ተጋድሎው እጅግ አስመራሪ የሆነበትን ጊዜ ሁሉ ፈጣሪ መከናወንን ሰጥቶን ከመሳካቱም ባሻገር ዛሬ እንኳን እንግዶቻችን በጸሃይ እንዳይመቱ እንደዚህ አይነት ውብ ዳመና በመስጠት በከፍተኛ ድምቀት ይህ ምድራዊ ብቻ ሳይሆን ሰማያዊ ቅቡልነት እንዳለው ዳግም ስላረጋገጠልን ፈጣሪያችንን እጅግ አድርጌ አመሰግናለሁ።

በመጨረሻም የታችኛው ተፋሰስ ሀገራት ወንድም የግብጽና የሱዳን ህዝቦች ዛሬ የተጀመረው የሃይል ማመንጨት ስራ ለእናንተም በረከት ነው እና እንኳን ደስ አላችሁ ልላችሁ እፈልጋለሁ። ባልተገባ ሁኔታም ቢሆን ለፈጠራችሁት ተጽእኖ እና ፈተና እጅግ አድርጌ አመሰግናችኋለሁ። ይህ ውሃ መላው የአለም ህዝብ እንዲገነዘብ የሚያስፈልገው ሃይል እያመነጨ ቀደም ሲል የሚያደርገውን ተግባር ለመፈጸም ወደ ሱዳንና ግብጽ የሚሄድ እንጂ በአሉባልታ ሲነገር እንደነበረው የኢትዮጵያ ህዝብና መንግስት ውሃውን ገድበው የወንድም ግብጽንና የሱዳን ህዝብን የማስራብ እና የማስጠማት ፍላጎት እንደሌላቸው ስንናገር እንደነበረው ዛሬ በተግባር ያሳየንበት ቀን ስለሆነ ሁሉንም ወንድም የግብጽንና የሱዳን ህዝብ ብቻ ሳይሆን መላው የአፍሪካ ወንድም ህዝቦችን እንኳን ደስ አላችሁ። ሃሳባችን የቀና፣ ተግባራችን የቀና አድካሚም ቢሆን ፍሬያችን ያማረ ነውና ሁላችሁም የኛን መገድ ተከትላችሁ ከልመና በመውጣት ህዝባችሁን ህይወት ለመቀየር እንድትተጉ አደራ ልላችሁ እፈልጋለሁ።

የህዳሴ ግድብ አሁን ያለበትን ደረጃ በቀላል ምሳሌ ለመግለጽ አንድ ሰው ሃያ ክፍሎች ያለው ሆቴል ለመገንባት ቢነሳ በመጀመሪያ ሪሲፕሽኑን፣ ሬስቶራንቱን አጠቃላይ የሆቴሉን ውቅር ከሰራ በኋላ አምስት መኝታቤቶች አጠናቆ ለምርቃት ወዳጆቹን ቢጠራ ሆቴል አስመርቃለሁ እንደሚለው ሁሉ ከሁለት ወር ሶስት ወር በኋላ ሰባተኛውን ስምንተኛውን አስረኛውን ሩም እየጨረሰ ቢያስገነባ ሩም ባደሰ ቁጥር ሆቴል አያስመርቅም። መጀመሪያ ላይ ሬስቶራንቱን ካሰራውና ከጨረሰው የአልጋ ቁጥር ጋር ካስመረቀ በኋላ በየጊዜው አዳዲስ ክፍሎች ሊጨመሩ ይችላሉ፣ አዳዲስ አሰራሮች ሊጨመሩ ይችላሉ፣ የአገልግሎት አሰጣጥ ስርአት ሊዘምን ይችላል። ግን በየጊዜው ምርቃት አይኖርም ዛሬ አንደኛው ሩም ሬስቶራንት እና ሰርቪስ መስጠት የሚችለው ሆቴል ተመርቋል። ከዚህ በኋላ የሚኖረው ስራ አዳዲስ ሩም፣ አዳዲስ አገልግሎት እንደመጨመር የምታይ ስለሆነ በህዳሴ ግድብ በዚህ ውሃ ጉዳይ መነታረክ ትተን በትብብር መንፈስ በሚያግባባ መንፈስ ግብጽን በሚጠቅም

መንፈስ፣ ሱዳንን በሚጠቅም ሌሎች ተፋሰስ ሀገራትንና እኛን በሚጠቅም መንገድ ትብብር እንድናደርግ ጥሪዬን እያቀረብኩ የኢትዮጵያ ፍላጎት ይሄንን ኢነርጂ በማምረት የጎረቤት ሀገራትን መጥቀም እንጂ ውሃውንም ወደ ግብጽ እና ሱዳን መላክ ብቻ አይደለም።

የኢትዮጵያ ፍላጎት አሁን በሱዳንና በኢትዮጵያ መካከል የኤሌክትሪክ ማስተላለፊያ ገመድ ተቀጥሎ ኢነርጂ እየሸጥንላቸው እንገኛለን። ግብጽ ደግሞ ቀይባህርን ሜድርታኒያን ተሻግሮ ከሌሎች ሀገራት ጋር ግሪስ ኮኔክቲቪቲ አላት። የተገናኘ መስመር አላት። ከሱዳን ወደ ግብጽ ያለውን መስመር ማገናኘት ቀላል ስለሆነ ተጨማሪ የሃይል ማመንጫዎች እየሰራን አውሮፓ ላይ ያለውን የጋዝ ሃይል ማመንጫና ኢንቫይሮመንት የሚበክለውን ነገር እየቀነስን ከዚህ አውሮፓ ኢነርጂ ኤክስፖርት የማድረግ ፍላጎት አለ። ይህ ፍላጎታችን ባዶ ህልም አይደለም። ቀደም ሲል እንደተገለጸው በከፍተኛ ቦታ ላይ የምንገኝ፣ ከፍተኛ ዝናብ የምናገኝ ብዙ ወራጅ ውሃ ያለን ሀገር በመሆናችን በርከት ያሉ ግድቦች ገንብተን ለኛም ለሌሎች ሀገራት የሚተርፍም ኢነርጂ ማምረት እና መሸጥ የምንችል ስለሆንን የምእራቡ አለምና ገንዘብ ያላቸው ሀገራት አሁን ያለውን የውሃ ፖለቲካ መልክ ቀይረው ከኛ ጋር በትብብር አዳዲስ ፕሮጀክቶች በመስራት ለኛም ከድህነት መውጫ፣ ከጨለማ መውጫ ለነሱም ለጋዝ ብከላ መከላከያ እንዲሆናቸው በቀና መንፈስ እንድንሰራ ጥሪዬን አቀርባለሁ። ኢትዮጵያ ማንንም የመጉዳት ሃሳብና ፍላጎት፣ ድርጊት የሌላት፤ የኢትዮጵያ ዋነኛው ፍላጎት 60% የሚሆነውን በጭለማ የሚሰቃይ ህዝብ አንፖል አይተው የማያውቁ እናቶች በጀርባቸው እንጨት ተሸክመው ኢነርጂ ለማምረት የሚጥሩ እናቶችን ድካም ለመከላከልና አሁን ካለንበት ድህነት ለመገላገል ብቻ ያለመ ፍላጎት ነው። ይህም ሲሆን ደግሞ የወንድሞቻችንን ጥቅም በጠበቀ የትብብር መንፈስ መሆኑን ተገንዝባችሁ እስካሁን ለማደናቀፍ የወጣው ጉልበት፣ ጊዜ ገንዘብ ቀርቶ ለልማት በጋራ እንድንቆም፣ ለትብብር በጋራ እንድንቆም በታላቅ ትህትና ከአደራ ጭምር ጥሪዬን ላቀርብላችሁ እፈልጋለሁ።

ፈጣሪ ኢትዮጵያን እና ህዝቦቿን ይባርክ ስንል ቆይተናል። ባርኳል አስጀምሯል የብልጽግና ጉዞ በር ተከፍቷል። ከእንግዲህ ኢትዮጵያን የሚያቆማት ነገር አይኖርም። ኢትዮጵያዊያን ልንገነዘበው የሚያስፈልገው ነገር ቢኖር ከጥቃቅን አጀንዳ እርስበእርስ

ከመበላላት ከማያስፈልጉ ሽኩቻዎች ወጥተን ተደምረን፣ ተሰባስበን እንደ ህዳሴ ኢትዮጵያን እንድንሰራና በከፍታ ማማ ላይ እንድናስቀምጥ ከመናቆር፣ ከማያስፈልግ የተንኮል ፖለቲካ እንድንወጣ በይቅርታ ልብ በጋራ እንድንቆም እጠይቃለሁ። ህዳሴ መከናወኑ ለኢትዮጵያ ሰላም ለኢትዮጵያ ህብረት፣ ለኢትዮጵያ አንድነት በር ከፋች ሆኖ እስካሁን የነበርንበት ግጭትና አላስፈላጊ ትርክት ቆሞ ተባብረን ሀገራችንን እንድናለማ ወደ ብልጽግና እንድንሸጋገር፣ ፈጣሪ የሰጠንን ጸጋና እድል እንድንጠቀም ከማያስፈልጉ የቅጥረኛ አስተሳሰቦች እንድንወጣና ኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊ ሆነን እንድንቆም በታላቅ ትህትና ጥሪዬን አቀርባለሁ።

እንኳን ደስ አላችሁ እንኳን ለዚህ ቀን በቃን መላው የኢትዮጵያ ህዝብ የብልጽግና ጉዞ መጀመሩን ተገንዝቦ በአንድ መንፈስና ልብ በጋራ በመቆም ኢትዮጵያን ወደሚገባት ክብር እንድናወጣት ነጻ ሆና የተረከብናትን ሀገር ነጻና የበለጸገች አድርገን ለልጆቻችን እንድናስረክብ አደራ ለማለት እፈልጋለሁ። ስለሆነው ስለሚሆነው ሁሉ ፈጣሪያችን የተመሰገነ ይሁን!

**አመሰግናለሁ !**

የካቲት 13፣ 2014 ዓ.ም





# የአቡነ መርቆሬዎስ የቀብር ስነስርአት ላይ የተደረገ ንግግር

ብጹአን አባቶች እንዲሁም የዚህች ታሪካዊትና ጥንታዊት የኢትዮጵያ ቅርጽ የሆነች ቤተክርስቲያንና ምእመናን፣ የአባታችን የመንፈስ ልጆች የሆናችሁና በዚህ ስፍራ የተገኛችሁ ሁሉ ሰላም እላችኋለሁ። በዚህ መልክ መገናኘት ደስታ የሚሰጥ ባይሆንም እንኳን ኦርቶዶክስ በችግር ጊዜ እንኳን በመከራም ቀን ቢሆን ሩጫቸውን የጨረሱ አባቶችን በመሸኘት ቀንም ቢሆን ታይቶ የማይጠገብ ታሪክ፣ ባህል፣ ዜማ ማንነት ያላት ቤተክርስቲያን መሆኗን ለኔም ለማያውቁም ለማሳየት እድል ስላገኛችሁና ኦርቶዶክስን ደግመን እንድንወድ፣ እንድናከብር ምክንያት ስለሆኑ አባታችንን ማመስገን እፈልጋለሁ።

እንግዲህ ብጹዕ አባታችን እንደ ጥሩ አባት ሩጫቸውን ጨርሰው ወደሚወዱት፣ ወደአገለገሉት አባታቸው ሄደዋል። ከሳቸው ጋር የነበረኝ የመጀመሪያው ግንኙነት በዋሺንግተን ዲሲ ነው። እሳቸው እንዲመጡ ከሌሎች አባቶችና ወንድሞች ጋር በነበረው ውይይት መጠነኛ ክርክር ነበር። አይሄዱም፣ ሌላ ጊዜ ይመጣሉ የሚልና አባታችን ብዙ ጊዜ አይናገሩም ይላል። በወሳኝ ጊዜ እጅግ ድንቅ ንግግር ግን ይናገራሉ። የመዳን ቀን ዛሬ ነው ብለው "እናንተ ካልፈለጋችሁ አትሄዱም እኔ ግን እሄዳለሁ" ብለው የወሰኑት አባታችን ናቸው። ያ ውሳኔ ዛሬ እሳቸውን በክብር ለመሸኘት ብቻ ሳይሆን እንዲህ ሰብሰብ ብለን ታሪክ ያለን፣ ባህል ያለን የራሳችን ዜማ ያለን መቀበል ማሳደግ መጸለይ መሸኘት የምንችል ህዝቦች መሆናችንን ለማሳየት እድል ስለሆኑን አባታችን ነብሳቸውን በሰላም ከአባታቸው ጋር እንዲያኖር በድጋሚ ምኞቴን እገልጻለሁ። እዚህ በነበራቸው ቆይታ እንደተገለጸው አልፎ አልፎ አባታችንን የመጎብኘት እድል አግኝቻለሁ። አባታችን እንደእናነት ሁሉ በጸሎት በእጅጉ ያግዙኝ ነበር። በእንባ ያግዙኝ እንዲሁም በምክር ያግዙኝ ነበር። እሳቸውን ለማየት ስሄድ ቢያንስ በእንባቸው ፍቅራቸውን ይገልጹልኝ ነበር። አልፎ አልፎም ፈታኝ ነገር

ሲገጥመን መቼም አባት አባት ነውና ቢሮዬ ድረስ እየመጡ ከወንድሞቻቸው ጋር በጽሁፍ፣ ሃሳባቸውን፣ ምክራቸውን፣ ጸሎታቸውን በተደጋጋሚ ገልጸውልኛል። መልእክትም ልከውልኛል። ብጹዕ አባታችን ለኔ የመንፈስ የጸሎት አባቴ ነበሩ። የዛሬው ሃዘን ልክ እንደእናንተ የምጋራውና አባቴን እንዳጣሁ የሚሰማኝ መሆኑን ልገልጽላችሁ እፈልጋለሁ።

ብጹዕ አባታችን እድለኛ ናቸው። ዘመናቸውን በሙሉ የሚያምኑትን አምላክ እና የሚወዷትን ቤተክርስቲያን በታማኝነት አገልግለዋል። መናገር ሲገባቸው ተናግረው፣ መጸለይ ሲገባቸው ጸልየው፣ መምከር ሲገባቸው መክረው በአርምሞ እና በጾጥታ መኖር ሲገባቸውም እንዲሁ ኖረው በብ ያስተማሩን አባት ናቸው። ከኚህ አባት እኔም እናንተም ልንማር የሚያስፈልገው ነገር ኦርቶዶክስ ከነቀኖናዋ፣ ከነትውፊቷ፣ ከነማይጠገብ ማንነቷ ለትውልድ እንድትሸጋገር ከግጭት፣ ከብጥብጥ፣ ከመሰዳደብ፣ ከአላስፈላጊ ነገር ውስጥ ወጥተን ልክ እንደዛሬው በሚያስደንቅ፣ በሚያስከብር ባህሏ እና ብቃቷ እንዲሁም ዜማዋ ሁሌም እያበራች እንድትኖር በትብብር መንፈስ ሁሌም እንድትሰራ በሰከነ መንፈስ ሁሌም አብረን እንድንሰራ ያልተመቸ ነገር እንኳን ካለ በጸሎት እንድናሳልፍ፣ አሁን የጾም የጸሎት ጊዜ ስለሆን ለሀገራችን ኢትዮጵያ እንዲሁም ለአባታችን የነብስ እረፍት እንድትጸልዩ አደራ ልላችሁ እፈልጋለሁ። አባታችን ወደሚወዱት አባታቸው ሄደዋል፤ ነብሳቸው በሰላም ከአባታቸው ጋር እንድትኖር እመኛለሁ።

**አመሰግናለሁ!**

መጋቢት 3፣ 2014 ዓ.ም

# በጽሕፈት ቤቱ በተደረገ የማዕድ ማጋራት ስነ ስርዓት የተደረገ ንግግር

**ሰላም እንዴት ናችሁ?**

የው በአል እየደረሰ ነው። ፋሲካ፣ የረመዳን፣ ኢድም እየደረሰ ነው። በእንደዚህ አይነት ጊዜ የመጠያየቅ እድል ከተገኘ መልካም ስለሆነ ነው ዛሬ የማእድ ማጋራት ስራን እዚህ ማድረግ የፈለግነው ስለመጣችሁና የሃሳባችን ተጋሪ ተካፋይ ስለሆናችሁ እጅግ አድርጌ አመሰግናለሁ።

ኢትዮጵያ የውልደት ስብራቷን፣ መከራዋን፣ ችግሯን፣ በሁለት መንገድ በመጋራት ማለፍ ማሸነፍ ትችላለች ። አንደኛው እንደልማዳችን እንደ ባህላችን እንዳደግንበት ችግርን መካፈል ነው ችግር ሲያጋጥም ተካፍሎ ችግርን ማቅለል ነው። ጥቂቶችን ተጭኖ እንዳይጎዳ ብዙዎች ያንን ችግርና መከራ በማካፈል ያንን ጊዜ ማሳለፍ እንዲችሉ ማድረግ ነው። ሁለተኛው ደግሞ ትግልን መካፈል ነው መከራውን፣ ችግሩን ከስሩ ነቅሎ ለመጣል የሚያስችለው መንገድ ራሱ ትግሉን መካፈል ነው። አሁን እየገጠመን ያለው ያለንን የማናካፍል ችግሩን ደግሞ ለመቅረፍ ትግሉን የማንካፈል ከሆነ ከአጭር ጊዜም አንጻርና ከረጅም ጊዜም አንጻር መከራ የዘለቀባት፣ በስብራት የተሞላች ሀገር ትሆናለች ይሄንን ለመቅረፍ በአጭር ጊዜ ችግሮቻችንን እንካፈላለን።

የጥቂቶች ችግር በብዙ ሰዎች መካፈል ውስጥ እንዲቀል እናደርጋለን። በረጅም ጊዜ ደግሞ በጋራ ራእይ በአንድነት ችግሮቻችንን በመታገል ልጆቻችን ይሄንን መከራ እንዳይደግሙት እንዳይኖሩት ጥረት እናደርጋለን። እነዚህ ሁለት ጉዳዮች ለሀገራችን በጣም አስፈላጊ ጉዳዮች ናቸው። ሁላችሁም እንደምታውቁት ማእድ ማጋራት ለኛ ለኢትዮጵያዊያን የኖረና የምናውቀው እሴት ነው። ሁሉም በየአቅሙ ያለው ከሌለው ላይ እያካፈለ የኖረ ህዝብ ነው። አዲስ የባህል ልምምድ ሳይሆን የኖርንበት መሆኑን

መገንዘብ አስፈላጊ ነው።

ለምሳሌ በጎረቤት ሃዘን ሲያጋጥም ሃዘን ለጊዜው የሚበረታ እየቆየ ግን የሚያልፍ ነገር ስለሆነ ሃዘን የገጠማቸው ሰዎች ጋር ቡናም፣ ምግብም ያለንን ይዘን እንሄዳለን፣ ምግብ እናካፍላለን። ምክንያቱም እነሱ በሃዘን ወቅት ሰርተው ለመመገብ ስለሚቸገሩ እኛ ምግብ ወስደን እናካፍላለን፣ ከነሱ ደግሞ ሃዘንን እንካፈላለን። የእነሱ ሃዘን ይቀላል ሳይበሉ እንዳይጎዱ ከኛ ምግብ ይካፈሉና ያ የመከራና ችግር ሰአት ያልፋል። በሃዘን ጊዜ ጎረቤት ቡና አፍልቶ ባያጽናናው የከፋ ሃዘንና ስብራት ሊያጋጥመው ይችላል። ነገርግን  ያ ሃዘን እዛ ቤት ተጀምሮ እዛ ቤተ አያልቅም። የዙር ጉዳይ ነው ምግብን አካፍለን ሃዘንን ስንካፈል በተራ ደግሞ በኛ ሃዘን እና በኛ ችግር ጊዜ ሰዎች ያንን መከራ እና ችግር እንዲሁ ይካፈላሉ።

ሃዘንን እና መከራን ማካፈል ኢትዮጵያዊያን ልምድ አድርገን ስንኖር ብዙ ሰዎችን ከከፋ ችግርና ስብራት ታድገን እኛም በዛ ውስጥ አልፈን እንደመጣን መገንዘብ አስፈላጊ ነው። በባህላችን በሀገር ቤት እንደምታውቁት እንግዳ ሲመጣ ቤት ያፈራውን ይባላል። ቆሎም ይሁን ምግብም ይሁን ያለውን ሰው አካፍሎ ይበላል። በገጠር ሰው ውሃ ጠምቶት ቢጠይቅ ወተት ወይም ውሃ ወይም ቂጣ ክፈል አይባልም። አሁን አሁን ማስከፈል እንጂ እንደነውር የሚታሰብበት ሀገር ነው። ኢትዮጵያ ምግብን ማካፈል በተለይ በበአላት ጊዜ በፋሲካ፣ በኢድ በእጅጉ የተለመደው ባህላችን ያላቸው ለሌላቸው እያጋሩ ችግርተኞች ያንን ጊዜ በብቸኝነትና እንዳያሳልፉ የማጽናኛና አብሮ የመኖርና የመዝለቅ ባህላችን ውጤት ነው። ይሄም እጅግ አስፈላጊ ነገር ነው።

የመጨረሻው  መልእክት ማካፈል ለራስ ነው፣ መስጠት ለራስ ነው፤ ሰው የዘራውን ያጭዳል። ባካፈልነው ልክ ዛሬ በኛ ባናየው ነገ በልጆቻችን እናገኘዋለን። ዛሬ የተቸገረ ነገ መርዳት ይችላል። ዛሬ የተቸገረ ነገር ህይወት መታደግ ይችላል። ይሄንን አምነን መላው የኢትዮጵያ ህዝብ ብዙ ያለን መሆን አይጠበቅብንም፣ ካለን ጥቂት እየካፈልን ብዙዎችን ማጽናናት ብዙዎችን ጓዳ ማበስ ብንችል የመጪው በአል ኢዱም ፋሲካውም እጅግ ያማረ ብዙዎች በደስታ የሚያሳልፉትና አንድ ቀን ደግሞ በዘራነው ልክ የምናጭደው ይሆናል።

ባንድ ወቅት አንድ እናትና አባት የሌለው ልጅ ትምህርት ቤት የቀን ስራ እየሰራ ሲማር በሆነ ወቅት ስራ አጥቶ የሚበላው አጥቶ እየተቸገረ ትምህርት ቤት እየደረሰ

ይመጣል። ከቀናት በአንዱ ቀን ቁርስ፣ ምሳ ሳይበላ በጣም ተርቦ አንድ ሻል ያለ ቤት ያገኝና አንኳኩቶ እባካችሁ ውሃ ስጡኝ ይላል። በጣም ርቦታል ደክሞታል። ያንን እለት ሲያንኳኳ የከፈተችው ልጅ ልጁ እንደተራበ እንደደከመ ስላየች የጠየቃት ውሃ ቢሆንም፣ በትልቅ ብርጭቆ ወተት ሞልታ አመጣችለት። ልጁ ከጠጣ በኋላ የሚያስከፍልም ከሆነ በኋላ ሊደራደር በጣም ስለራበው ወተቱን ተቀብሎ ጭልጥ አድርጎ ጠጣና ፋታ ካገኘ በኋላ "ስንት ነው የሚከፈለው አላት?" ልጅቱ መቸገሩን አይታ "የሚከፈል የለም መልካም ቀን ይሁንልህ ብላ ሸኘችው።"

ከብዙ አመታት በኋላ አንዷት ልጅ በካንሰር በሽታ ታማ ወደ ሆስፒታል ትሄድና እጅግ ውስብስብ የህክምና ጥበብ የሚጠይቅ ስለነበር ረዘም ላለ ጊዜ ትሞታለች አትተርፍም ከተባለች በኋላ በብዙ የሃኪሞች ጥረት እና ልፋት ትድናለች። ከዳነች በኋላ ከፍተኛ ጭንቀት ይገባታል። በውጪ ሀገር እንደምታውቁት ለህክምና የሚከፈለው ክፍያ ከፍ ያለ ስለሆነ እሷ ያላት ኢንሹራንስ ያንን የወጣውን ወጪ መመለስ የማይችል ከሆነ የአባት እናትን የወረሱትን ሃብት ቤት ያሸጠኛል ብላ ትጨነቃለች። የመክፈያው ፖስታ ሲላክላት በጭንቀት ስንት ብር ይሆን የመጣው እያለች ፖስታውን ስትከፍት "በአንድ ብርጭቆ ወተት ሂሳቡ ተከፍሎልሻል" ይላል። ያኔ በልጅነት አንድ ብርጭቆ ያጠጣችው ሰው ዶክተር ሆኖ ሃኪም ሆኖ በሚያክማት ጊዜ ያ በረሃቡና በችግሩ ጊዜ የነበረው ታውሶት በአንዷት ብርጭቆ ወተት ያን ሁሉ የህክምና ወጪ ሸፈነላት።

ልጅቱ ያን ቀን ወተቱን ስታጠጣው አንድ ቀን ሰው ሆኖ ህይወቴን የሚታደግና እዳዬን የሚጋራ ሰው ይሆናል ብላ አስባ ሳይሆን መልካምነት ስለሚያተርፍ፣ መልካምነት ጊዜ ጠብቆ ስለሚከፍል ሁላችንም ካለን ላይ ተካፍለን በሰላምና በደስታ በአሉን እንድናሳልፍ ዛሬ እድል ገጥሟችሁ እኛ ጋ የመጣችሁ እናት እና አባቶች እንዲሁ እናንተም ቡና ስታፈሉ ጎረቤቶቻችሁን ሳፀነጉ በአልን አንድ ላይ እንድታሳልፉ አደራ እላለሁ።
መልካም በአልን ይሁንልን። ሰላሙ ይብዛልን፣ ፍቅር ይብዛልን፣ መካፈል ይብዛልን። አይዟችሁ መጪው ጊዜ ብሩህ ነው።

**መልካም በአል!**

ሚያዚያ 10፣ 2014 ዓ.ም





# የዋር ኮሌጅ ምርቃት

**ፊልድ ማርሻል ብርሃኑ ጁላ**
**ክቡራን ጄነራሎች እንዲሁም የእለቱ ተመራቂዎች**

ተምሮ መመረቅና የመጨረሻዋን ቀን ማየት በብዙ ድካም ለተማሩ ሰዎች ደስታቸው ስለሆነ እናንተንም ቤተሰቦቻችሁንም እንኳን ደስ አላችሁ ለማለት እወዳለሁ።

ሀገራችን ኢትዮጵያ ትልቅ ሀገር ናት በቆዳ ስፋቷም፣ በህዝብ ብዛቷም፣ በታሪኳም ባላት አንጡራ ሃብትም እጅግ ትልቅ ከሚባሉ ታሪካዊ ሀገራት መካከል አንዷ ናት።

ሀገራችን ኢትዮጵያ ብቻ ሳትሆን የኢትዮጵያ የሀገር መከላከያ ሚኒስቴር ከመቶ አመት በፊት የጦር ሚኒስቴር ተብሎ የተቋቋመ በአፍሪካ እጅግ ግዙፉ ትልቁና ታሪካዊ ተቋም ነው። በርካታ የአፍሪካ ሀገራት የራሳቸው መከላከያ ባልነበራቸው ወቅት መከላከያ ሚኒስቴር ተብሎ የተቋቋመና ከመቶ አመት በላይ እንደ ተቋም የዘለቀ ተቋም ነው። ይህ ተቋም እንደቆይታውና እንደሚጠብቃት ሀገር ልክ ራሱን ማጠናከር ራሱን ማዘመን ለዘመኑ በሚበጅ መልኩ ራሱን ማዘመን ይጠበቅበታል።

መከላከያ የመጀመሪያው ተልእኮ ኢትዮጵያን ማስቀጠል ነው። ኢትዮጵያን ለማስቀጠል ደግሞ ራሱን ማስቀጠል አለበት።ባለፉት አንድ አመት ተኩል ሁለት አመት ገደማ መከላከያ ሀገር ለማስቀጠል ሳይሆን ራሱን ለማስቀጠል ከፍተኛ ተግዳሮት ገጥሞት ነበር። ያ የገጠመው ተግዳሮት ያስከፈለው ዋጋ ቢኖርም በሰው፣ በንብረት፣ በህይወት በርካታ ኪሳራዎች የገጠሙ ቢሆንም እያንዳንዱ ፈተና የራሱ የሆነ እድል ስለሚያመጣ የባለፈው ግጭት ያስከፈለን ዋጋ ቢኖርም መከላከያን እጅግ በዘመነ መንገድ ማስቀጠል ሀገር ማስቀጠል በሚያስችል መልኩ ለማደራጀትና አስተማማኝ ተቋም ለመመስረት ትልቅ እድል ተገኝቷል።

ሁሉም ችግር፣ ሁሉም መከራ፣ ሁሉም አስቀያሚ ጊዜ የራሱ የሆነ እድል ይዞ ይመጣል የሚባለው ለዚህ ነው። የተበላሸ የቆመ የማይሰራ ሰአት እንኳን ቢያንስ በሃያ አራት ሰአት ሁለት ጊዜ ውስጥ ትክክል የሆነውን ጊዜ ይናገራል። መከራና ችግር እኛ እንደምናስበው የሚያጠፉን ብቻ ሳይሆን ኢኖቬሽን የሚያፋጥን እድገትን የሚያፋጥን ከዚያም ውስጥ ለመለወጥ እድል የሚሰጥ ነው። የባለፈው ጦርነት ያስከተለው ብዙ ችግር ቢኖርም መከላከያ ከሚሊሻነት ወደ ወታደርነት፣ ከሽበጥነት ወደ ዩኒፎርም ለባሽነት፣ ሰላምታ ከማያቅ ሰላምታ ወደ መስጠት፣ ስትራቴጂን የሚማርና የሚተነትን ለመሆን እድል አግኝቷል። ይህ ጅማሮ እድል ኢትዮጵያን ባንዲራዋን ሉአላዊነቷን ሀገራዊ ቁመናዋን ወዶ ራሱን ሰጥቶ ለማስቀጠል የሚያስችል ብቃት እንዲፈጥር የዛሬው አይነት ትምህርት ያስፈልጋል።

ሁላችሁም እንደምታውቁት የአለም ፖለቲካና ዲፕሎማሲ አብዛኛውን ቃልና ትምህርት ያገኘው ከመከላከያ ነው። ስትራቴጂ የሚለው ቃል ራሱ የተገኘው ከመከላከያ ነው። ታክቲክ የተገኘው ከመከላከያ ነው፣ ሊደርሺፕ የተገኘው ብዙ አለም የሚገዛበት የሚተዳደርበት የሚመራበት ፍልስፍናና የእውቀት ጥግ በቴክኖሎጂውም፣ በሊደርሺፑም የሚገኘውም የተገኘውም ከመከላከያ ነው። ዛሬ የተመረቃችሁ ተመራቂዎች ሀገር ከእናንተ ብዙ ይጠብቃል። ብዙ ማንበብ፣ ብዙ መቆፈር፣ ብዙ ማወቅ፣ ብዙ መጻፍ ይኖርባችኋል። በዛው ልክ መማር በተማራችሁት የእውቀት መጠን ደግሞ ማስተማር ይጠበቅባችኋል። ትምህርት አያልቅም። አብዝቶ ትምህርትን የሚፈልግ አብዝቶ ጥበብን የሚፈልግ ወታደርም ይሁን ማንኛውም ዜጋ ከራሱ አልፎ ሀገር ለመጥቀም ስለሚችል እውቀትን አብዝታችሁ የምትፈልጉ፣ ያገኛችሁትን እውቀት ደግሞ የምታካፍሉ እንድትሆኑ አደራ ማለት እፈልጋለሁ። መከላከያ በመዝሙሩ ሁሉንም መልእክት አስተላልፏል። ከዛ ውስጥ ጥቂት ስንኞች በማንሳት የእናንተን ሚና መልሼ ማስታወስ እፈልጋለሁ። የእናንተ መሳጩ መዝሙር "ምድራዊ ፈተና በዝቶ ዙሪያው ቢነድ ቢጎመራ
ጥሰነው እናልፋለን የማይሞት ታሪክ ልንሰራ" ይላል። የማይሞት ታሪክ ለመስራት አብዝቶ መማር፣ ታሪክን ማወቅ፣ ልክን ማወቅ መቀጠልና ማስቀጠልን ማወቅ ይፈልጋል።

"የመፈቃቀር አንድነት፣ እኩልነት ነው ዜማችን
የማይጨበጥ ነበልባል እሳት ነን ለጠላታችን " ይህም በጣም ትልቅ መልእክት

ያለው ስንኝ ነው። አንደኛው የሀገር መከላከያ ሠራዊት አባላቶች ብሄር የላቸውም። ለማንኛውም የፖለቲካ ፓርቲ አይወግኑም። ዋነኛ ተልኳቸው ራሳቸውን ማስቀጠልና ኢትዮጵያን ማስቀጠል ነው። ራሳቸውን እንዳያስቀጥሉ፣ ኢትዮጵያን እንዳያስቀጥሉ በሰፈር በመንደር የሚከፋፍላቸውን ሃይል ሁልጊዜ መመለስ ያለባቸው የመፈቃቀር አንድነት እኩልነት ነው። ዜማችን ከዚያ ውጪ ያለው ዜማ እኛ አይዋጥልንም አይገባንም ብለው ማስተማር ይጠበቅባቸዋል። የማይጨበጥ ነበልባል ለመሆንም መማር፣ ቴክኖሎጂንም ማወቅ፣ ዘመን የሚዋጀውንም ሁሉንም ታክቲክ ማወቅ ያስፈልጋል። የመከላከያ ሚኒስቴር ሲመሰረት ስያሜው የጦር ሚኒስቴር ነበር።

ጦርነትን የሚሰራ ጦርነትን የሚያስብ ጦርነት የሚያደርግ ተቋም ነበር። አሁን ያለው ስያሜ ግን ከዛ ተቃራኒ ነው። የሀገር መከላከያ ነው እንጂ የሀገር የጦር ሚኒስቴር አይደለም። የምንፈልገውና የምንመኘው ሰላም የሚደናቀፈው የሚደፈርሰው በግጭት በጦርነት ነው። ይህ ተቋም ግጭትና ጦርነት ተስፋፍቶ የሀገርን ጉዞ እንዳያደናቅፍ በማድረግ መልሶ ለመቀጠል መልሶ ሰላም እንዲቀጥል ለማድረግ ነው። የጦርነት ተቋም ሳይሆን ሰላም አስፋኝ ተቋም ነው። ለዚህ ነው አብዝተን ሰላም እንዲሰፍን እንፈልጋለን የምንለው። ነገርግን ሰላም ሁልጊዜ የሚደፈርሰው በጦርነት ስለሆነ ያ ችግር ሲያጋጥም በእውቀት፣ በቴክኖሎጂ ባጠረ ጊዜና ባጠረ ኪሳራ ሀገርን የሚታደግ ተቋም እንዲሆን ይጠበቃል።

“ፍሙ ከርቀት ይፋጃል፣ ብረት ያቀልጣል ክንዳችን
ኢትዮጵያ በኛ ደም ደምቃ በአጽማችን ፍላጻ ተማክራ
እንደታፈረች እንድትኖር ከዘመን ዘመን ተከብራ
ከመሞት በላይ እንሙት፣ ደማችን ሺህ ጊዜ ይፍሰስ
አየር አፈሯ ይባረክ ምንጊዜም ስሟ ይታደስ።” ይላል የእናንተ መዝሙር። እናንተ ብትሞቱ፣ እናንተ ብትደሙ፣ እናንተ ብትቸገሩ፣ እናንተ ብትጠሙ ኢትዮጵያ ከነክብሯ መቀጠል አለባት። እናንተም የማይሞተውን ታሪኳን መጻፍ አለባችሁ። መከላከያ በጣም ዘመናዊ ቴክኖሎጂን እየታጠቀ ነው ያለው። እውቀት አመራር የሚጠይቅበት ጊዜ ላይ ደርሷል። እንደዚህ አይነት ስልጠና በሀገር ውስጥም፣ በውጪም እየተስፋፋ ይገኛሉ። በእውቀታችሁም፣ በድካማችሁም፣ በደማችሁም አንድ ሆናችሁ ኢትዮጵያን ማስቀጠል ይኖርባችኋል። ዛሬ ትናንት ከነበርንበት በብዙ እጥፍ በተሳካ ቁመና ላይ እንገኛለን። ባዶ እጃችንን ሆነን በእምነት ኢትዮጵያ

አትፈርስም ብለን ነበር። ዛሬ ግን አስተማማኝ መከላከያ ይዘን ኢትዮጵያ ዳግም አትፈርስም ብለን መናገር የሚያስችል አስተማማኝ ሁኔታ ላይ እንገኛለን። አትፈርስም ስንል የሚተነኩሱ፣ ባንዳዎችን የሚልኩ ሃይሎች የሉም እያልን አይደለም። ባንዳዎችን የሚልኳቸው ሃይሎችም ኢትዮጵያን አትሞክሩ ከሞከራችሁ በደማችን፣ በአጥንታችን እኛ ሞተን እናስቀጥላታለን። ሺህ ጊዜ ገጥመውን ሺህ ጊዜ እንዳሸነፍናቸው ከዚህ በኋላም ለጠላቶቻችን ያለን ምክር ደጋግማችሁ ማሰብ አለባችሁ። የኢትዮጵያ መከላከያ ሰራዊት እንኳን ዛሬ ትናንትም አልተሸነፈም። አሁን ያለበት ቁመና ለሽንፈት ቀርቶ ለሙከራም የሚያሳስብ ስለሆነ እኛን ከመሞከራችሁ በፊት ደጋግማችሁ አስቡ።

ማሰብ ተስኗችሁ ወደ ጦርነት የምትሄዱ ከሆነ ግን እንደተለመደው አስተማማኝ ትምህርት የሚሰጥ ተቋም መገንባቱን የምናሳይበት ጊዜ ይሆናል የሚል መልእክት ነው ያለን። በርቱ። መከላከያችን በጣም የሚያኮራ ተቋም ሆኗል። ራሱም ማስቀጥገሉን አስተማምኗል። ኢትዮጵያንም የሚያስቀጥል ተቋም መሆኑን እኛም፣ ሌሎችም እየተማመኑ እያመኑ ያሉበት ጊዜ ላይ ደርሰናል። እንድትበረቱ እውቀትን እንድትፈልጉ አንድ እንድትሆኑና ኢትዮጵያን እንድታስቀጥሉ አደራ ልላችሁ እፈልጋለሁ። ተመራቂ ተማሪዎች በድጋሚ እንኳን ደስ አላችሁ።

የዛሬው ምርቃት ነገ ለምትጀምሩት ትምህርት በር ከፋች መሆን አለበት። ነገ ጀምራችሁ የምትማሩት ግን እንደሚያረጅ በቀጣይነት የምትማሩ፣ የምታስተምሩ፣ የምታድጉና የምትጠብቁ ያድርጋችሁ።

**አመሰግናለሁ!**

ግንቦት 22፣ 2014 ዓ.ም

# የፌዴራል ፖሊስ የእውቅና እና ምስጋና ስነ-ስርዓት

**ክቡር የቀድሞ ፕሬዝዳንት ዶ/ር ሙላቱ ተሾመ**
**ክቡር አቶ ታገሠ ጫፎ**
**ክቡር አቶ አገኘሁ ተሻገር**
**ክቡር ኮሚሺነር ጀነራል ደመላሽ ገ/ሚካኤል**
**ክቡር ፊልድ ማርሻል ብርኃኑ ጁላ**

የተከበራችሁ የክልል ርዕሰ መስተዳድሮች እንዲሁም ሚኒስትሮች ጥሪ የተደረገላችሁ እንግዶች

በሰላም ጊዜ በየመንደሩ፣ በጦርነት ጊዜ በየግንባሩ የሀገሩን ሰላም ለማስጠበቅ ደፋ ቀና የሚለው የፌዴራል ፖሊስ ከብዙ ድል ከብዙ ተቋም ከመገንባት ልፋት በኋላ ቅድም ባየነው መልኩ ክብረ በአሉን ለማክበርና የደረሰበትን የተቋም ግንባታ ሥራ ለህዝቡ ለማሳየት ስላበቃው መላው የፌዴራል ፖሊስ ሰራዊት አባላትን እንኳን ደስ ያላችሁ እንኳን አደረሳችሁ ለማለት እፈልጋለሁ።

ሰዎች ሁሉ ፀጥረጭ ባለው ሌሊት በሰላም ተኝተዋል ምክንያቱም የማይተኙ ሰላም ጠባቂዎች ያለዕንቅልፍ ስለሚያድሩ ነው ይባላል። ለዚህ ደግሞ ግንባር ቀደሙ የፌዴራል ፖሊስ ነው፡፡ ሰላም እፈልጋለሁ ችግር የሚመጣ ከሆነ ግን በኔ ዘመን እንዲመጣ እፈልጋለሁ ምክንያቱም የእኔ ልጆች በሰላም እንዲኖሩ ስለምፈልግ የሚለው አባባል በትክክል የሚሰራው ለኢትዮጵያ ፖሊስ ነው። ኢትዮጵያ ህልውናዋና ሉዐላዊነትዋ ለአደጋ በተጋለጠ ጊዜ ሁሉ ፖሊስ ግንባር ቀደም ተሰላፊ ነውና ይህ ክብር የሚገባው ስለሆነ ሁላችንም ፖሊስን እንኳን ደስ ያላችሁ እንድንላቸው እጠይቃለሁ። እናንተ የሰላም ዘቦች የብርሃን ጥቅም የሚታወቀው ጨለማ በሚከበን ወቅት ሁሉ የህግ አስከባሪዎች ሚና የሚታየው ሰላምና ደህንነታችን አደጋ ላይ ሲወድቅ ነው የሰላምን ዋጋ ብንገነዘብ የሰላምን ዋጋ ብናቅ ላፍታም ቢሆን ወደ ግጭት አናመራም። ሰዎች ወደ መከራ ወደ ግጭት ሲገቡ የሰላም አስፈላጊነትን

የሚገነዘቡ ቢሆንም የሰላም ዋጋ የረከሰ በመሆኑ በእናንተ ሚናና ጥረት እንብዛም ክብር ያልሰጠን ቢሆንም ተኝተን የምናድረው፣ አርሰን የምንበላው፣ ሀገራችንን ለማበልፀግ የምንጥረው እናንተን ተማምነን ነውና የፌዴራል ፖሊስ ሁሉም የሰላምና ደህንነት ተቋማት ተጠናክረው እንዲቀጥሉ የሚያስፈልገው የኢትዮጵያ ብልፅግና መሠረት ሰላም ስለሆነ ነው። በፖሊሶች የከሸፉ ወንጀሎችን ሳይሆን ከፖሊስ እይታ ያመለጡ ወንጀሎችን አግዝፎ የመመልከት ባህል አለን። በየዘመናቱና በየወራቱ በየቀናቱ ፖሊስ ለእኛ የማይነግረን ብዙ ወንጀሎችን ያከሽፋል። ነገር ግን ያከሸፈውን የለፋበትን የደከመበትን መስዋዕትነት የከፈለበትን ሳይሆን አልፎ አልፎ ከፖሊስ እይታ ያመለጠውን እኛ አብዝተን እንናገራለን። ፀጥታና ሰላማችን ለማረጋገጥ ሲዋደቁ ያላከበርናቸውን ፖሊሶች ወንጀል ሲፈፀምብን ጣታችን ልንቀስርባቸውና ልንወቅሳቸው አይገባም ኢትዮጵያ በእጅጉ ለሚያገለግሉዋት ፖሊሶች በቂ ደሞዝ መክፈል ባትችል እንኳን ማክበር መለማመድ ይኖርባታል።

ይህች ሀገር አነስተኛ ደሞዝ ከምትከፍልባቸው ወገኖች መካከል ፖሊስ አንዱ ነው። ለዚህች ሀገር ከፍተኛ ዋጋ ከሚከፍሉት ወገኖች መካከል እንዲሁ ፖሊስ አንዱ ነው። ኢትዮጵያ ከፍተኛ ዋጋ የከፈለችላቸው ያስተማረቻቸው ከምንም ወደ ገዘፈ ማንነት ያደረሰቻቸው ግለሰቦች የፖሊስን ግማሽ ዋጋ ቢከፍሉ ኢትዮጵያችን ምን ልትሆን እንደምትችል ላፍታ እንድታስቡ ጠይቃችኋለሁ የእኛ አላማ በእውነት የሚሰሩ፣ በዕውቀት የሚመሩ፣ በሥነምግባር የዳበሩ፣ ሞያቸውን የሚያከብሩ፣ ለህዝብ የሚኖሩ ፖሊሶች ለኢትዮጵያ ማበርከት ነው፡፡ የጀመርነው የፀጥታ ተቋማት ሪፎርም ወደዚህ ትልልቅ ምዕራፍ የሚያደርሰን ጅማሮ ነው፡፡ ዛሬ ፖሊስ ዘምኖ ባየነው መልክ እንዲሆን በሁሉም መስክ አስተዋጽኦ ላደረጋችሁ የፖሊስ አመራሮችና የሰራዊት አባላት የኢትዮጵያ መንግስት ከፍተኛ ምስጋና ያቀርብላችኋል።

መልካሞች ደፋር ከሆኑ ከፉዎች ኃይል የላቸውም ይባላል የፖሊስ ሪፎርማችን ደፋር የሆኑ መልካሞችን እንዲያፈራ ነው ደፋርነታቸው አላማቸውን ከግብ ለማድረስ ነው፡ ፡ መልካምነታቸው ህዝባቸውን ለመጠበቅ ነው። የኢትዮጵያ ፖሊስ ከወንጀለኞች ጋር የሚዋጋው ከፊት ለፊት የቆሙትን አሸባሪዎች ወንጀለኞች ለመጥላት ሳይሆን ከኃላው የተሰለፉትን በሚሊዮን የሚቆጠሩትን ህፃናት አዛውንቶች አቅመ ደካሞች የመከላከል ኃላፊነት ስላለበት ነው። የኢትዮጵያ ፖሊስ በጕችን ከተኩላዎች

ለመጠበቅ 24 ሰዓት የሚሰራ ሀይል ነው። ብዙ ጊዜ ግን በጐችን ከተኩላዎች የመጠበቂያ ተኩላዎችን ሊያስደስት የሚችል መንገድ አይገኝም። በዚህም ምክንያት ብዙ ተኩላዎች ሲጮሁ ይሰማል የጩኸቱ ትርጉም በጐችን እንደፈለግን እንድንበላ ተውን የሚል ነው። ፖሊሶች በጐችን መታደግ ብቻ ሳይሆን ከተኩላዎች ምስጋና እንደማይገኝ አውቃችሁ በአላማ ፅናት የኢትዮጵያን ንፁሐን ዜጐች ከተኩላዎች የመታደግ ስራችሁን አበክራችሁ እንድትቀጥሉ በታላቅ ትህትና ላሳስባችሁ እፈልጋለሁ።

እንዲህ ዛሬ በዝቶ ዘምኖና ተደራጅቶ የምናየው የኢትዮጵያ ፖሊስ በብዙ ውጣ ውረድ ውስጥ አልፎ እዚህ የደረሰ ኃይል ነው። የፖሊስን ታሪክ መለስ ብለን በወፍ በረር መቃኘት አሁን ለደረስንበትና ነገ ትውልድ ለሚቀበለው ተቋም ምንነት ትርጉም ስላለው አለፍ አለፍ እያልኩ የፖሊስ ታሪክ ለማንሳት እሞክራለሁ። በሀገራችን የፖሊስ ተግባር የተጀመረው በየሰፈሩ አውጫጭኝ፣ ሌባሻይ፣ አፈርሳታንና የመሳሰሉት ልዩ ልዩ አካባቢ ላይ ባሉ የህዝቦች ልምምድ ነው። በኃላ ላይ በሐረር ዳውሪያ የተሰኘ ለሊት ለሊት ሰላምን የሚያስከብር በአሚሩ የሚመራ የፖሊስ ሠራዊት ተመሠረተ። ይህንን የፖሊስ ሰራዊት በሪፎርም አዘምኖ ከሌላው ዘመናዊ እንዲሆን አድርገው ራስ መኰንን አደራጁት። በርካታውን ሰዎች ወደ ቱርክ በመላክ አሰለጠኗቸው።

ይህ ሐይል በአዲስ አበባ ለተመሠረተው ፖሊስ እርሾ ሆኖ እንዳገለገለ ይነገራል። በአፄ ኢያሱ ቀዳማዊ ሌዋ የተባለ ከወታደር ተለይቶ የፖሊስን የተወሰነ ተግባር የሚከውን ሰራዊት አቋቁመው ነበር። ዋና ተግባሩም በከቶሞችና በዋና ዋና ጐዳናዎች ሰላምንና ፀጥታን ማስከበር ነበር። እንዲሁም በጅማ ንጉሳዊ ግዛት ውስጥ አባጅፋር ከተሞቻቸውን፣ ደኖቻቸውንና የበዓላት ቀኖቻቸውን የሚጠብቁ ፖሊስ አደራጅተው ነበር። ኃላም የከተማ ዘበኛ የተባለውን የፖሊስ ሀይል አፄ ምንሊክ አቋቋሙ። ዋና ተግባሩም የውጭ ሀገር ሰዎችን መጠበቅ፣ ሰዓት ዕላፊንና መሠል ፀጥታን ማስከበር ነበር። በ1912ዓ.ም ከትሪፖሊ የመጡት አለቃ ገብሩ በአዲስ አበባ ከተማ የዘበኛ አዛዥ ሆነው ተሾሙ። እሳቸውም ለአስቸኳይ ጊዜ የሚሆነውን በዘመኑ ጥሩንቡሌ የተሰኘውን የፖሊስ ሰራዊት ክፍል አቋቋሙ። ጥሩንቡሌ የተባለው ብዙዎች አባላቱ ትሪፖሊ የነበረው የጣሊያን ቅኝ ግዛት ሰራዊት ስላገለገሉ ነው ይባላል በራስ ተፈሪ ጊዜ የፖሊስ ሰራዊት ተጠናከረ። በተለያዩ ሀገሮች ያገለገሉ የፖሊስ አባላት እየተቀጠሩ ሠራዎት እንዲያሰለጥኑ ተደረገ።

አዲስ አበባ በአስር ክፍለ ከተሞች ተከፍላ አስር የፖሊስ ጣቢያዎች ኖሯት። ኋላም የፖሊስ ሐይሉ መለዮ ለባሽና መርማሪ ተብሎ ተከፈለ እ.ኤ.አ በ1930 ፖሊስ የአራዳ ዘበኛ ተብሎ በይፋ ተቋቋመ። 1936 ዓ.ም የፖሊስ ክፍሎች በአዲስ አበባ፣ በድሬደዋ፣ በቦረና፣በጅማ፣በደሴ በሐረር ተቋቋሙ። ሌሎች አካባቢዎች ግን ነጭለባሽ በሚባለው ሰላም አስከባሪ ሀይል ይገለገሉ ነበር። በ 1937 ዓ.ም የመጀመሪያው የፖሊስ ማሰልጠኛ የሆነው አባዲና የፖሊስ አካዳሚ ተቋቋመ። በኋላ ወደ ሰንዳፋ የተዘዋወረው ይህ ነው ይባላል። የመጀመሪያው የኢትዮጵያ የፖሊስ አዛዥ ምክትል ኮሚሽነር ሻለቃ መኮንን ደመቀ ነበሩ። ከሳቸው ከጥቂት ዓመታት በኃላ ኮሎኔል ፅጌ ዲቡ የመጀመሪያው የኢትዮጵያ ፖሊስ ኮሚሽነር ሆነው ተሾሙ።

በ1966 ደርግ ከቋቋሙት የሠራዊት ክፍሎች መካከል የፖሊስ ሠራዊት ክፍሎች ይገኙበታል። ፖሊስ አገር መጠበቅ ብቻ ሳይሆን መንግስት ሲቋቋምም የራሱን ሚና የተጫወተ የጦር ክፍል ነው። ወታደራዊ መንግስት የተቋቋመው በደርግ ዘመን ነው። በ1984 በወጣው አዋጅ የፌዴራል ፖሊስን፣ እንዲሁም የክልል ፖሊስን የአካባቢ ሚኒሻን ያቋቋመ አዋጅ ነበር። ከሁለት አመት በኃላ 8000 የሚጠጉ ነባር የኢህአዲግ ሠራዊቶች ወደ ፖሊስ ተቀላቀሉ። ይህ ታሪክ ዛሬ ላየነው ፖሊስ መሠረት ነው። የኛ ለውጥ አባቶቻችን የሰሩትን መልካም ሥራ በማስቀጠል አረሙን ነቅሰን በማውጣት ኢትዮጵያን የሚመስል ኢትዮጵያን የሚያገለግል የፖሊስ ሀይል መገንባት ነው።

በዚሁ መሠረት በአዲሱ ሪፎርም በተነደፈው ስትራቴጂ አምስቱ ግቦች በግልፅ ተቀምጠዋል። አንደኛው በማህበረሰቡ ዘንድ ተአማኒ፣ ተደማጭና ተፈሪ እንዲሁም ተከባሪ የሆነ የፀጥታ ሀይል ሆኖ እንዲዋቀር ማድረግ ነው። ሁለተኛ ከየወቅቱ ጋር እያደገና እየተለዋወጠ የሚመጣውን ወደፊት ሊከሰት የሚችለውን የወንጀል ጠባይ የሚመጥን ተቋም እንዲሆን ማድረግ ነው። ሦስተኛው የፀረ ሰላም ሀይሎች እንቅስቃሴን በላቀ የግዳጅ አፈፃፀም ሊያከሽፍ የሚችል ተቋም መገንባት ነው። አራተኛው ከምንከተለው የፌዴራል ስርአት ጋር በተናበበ መልኩ ከክልሎችና ልዩ ልዩ ከፀጥታ ተቋማት ጋር በቅንጅትና በትብብር መስራት ነው። አምስት የክልል ፖሊስ ሀይል በዘመናዊ መልክ እንዲገነባ የፌዴራል ፖሊስ አስተዋፆ እንደሚያደርግ ስትራቴጂው በግልፅ አስቀምጧል።

በዚሁ መሠረት የፌዴራል ፖሊስን አቅም ክህሎትና አደረጃጀት እንዲሁም ትጥቅ በማዘመን ኢትዮጵያን የሚመጥን ለሁለንተናዊ ፈተናዎች በቂ ምላሽ ለመስጠት የሚያስችል ፖሊስ ሰራዊት እየገነባን ነው። የምንገነባው ተቋማትን ነው። የምንገነባው ኢትዮጵያን ሊያፈርሱ ከሚፈልጉ ሀይሎች ኢትዮጵያን ለመከላከል ነው።

የምንገነባቸው ተቋማት ኢትዮጵያን በሰላም ማቆየት ብቻ ሳይሆን ወደ ብልፅግና ለምታደርገው ሽግግር መሠረት ሆኖ በማገልገል ለልጆቻችን የበለፀገች ሰላማዊ ኢትዮጵያን ።በድጋሚ ኢትዮጵያ አትፈርስም ኢትዮጵያን ለማፍረስ የሚመኙ ሀይሎች ይፈርሳሉ። ለመቶ ሀያ ሚሊየን ህዝብ ብዙ የፖሊስ ሀይል ዘመናዊ መሳሪያ ጠንካራ ተቋም ያስፈልጋል። በዚሁ መልኩ የጀመርነውን ፖሊስ እንዲሁም የህዝብ ተቋማት የማጠናከር ስራችንን አጠናክረን የምንቀጥል ይሆናል።

ከፌዴራል ፖሊስ ኢትዮጵያን የሚመስል ቁመና ለማስያዝ የተጀመሩ ስራዎች ተጠናክረው እንደቀጥሉ የዘመነ ተቋም የመገንባት ሥራው ተጠናክሮ እንዲቀጥል ዛሬ በሰልፍ ያየናቸው እነዚህ ወጣቶች ጠንክረውና በርትተው ኢትዮጵያን ባንድራቸውን መለዮአቸውን የሚያከብሩ ታማኝ ሰራዊት እንዲሆኑ እንዲቀረፁ አደራ እላለሁ። እስከአሁን በነበረው ኦፕሬሽን መስዋዕትነት ለከፈላችሁ፣ ለቆሰላችሁ፣ ለደከማችሁ የፖሊስ ሰራዊት አባላት ኢትዮጵያዊያን በተባበረ ክንድ ቁስላችሁን የማከምና ድካማችሁን የመጋራት ስራ መንግስትና ህዝባችን አጠናክረው ይቀጥላሉ።

የተሰጣችሁን የማዕረግ እንዲሁም ልዩ ልዩ ሽልማት በቀጣይም ተጠናክሮ የሚቀጥል ሲሆን የኢትዮጵያ መንግስት አቅም በፈቀደ መጠን የፌዴራል ፖሊስን እንዲሁ እያጠናከረ የኢትዮጵያን ሠላም የማረጋገጡን ሥራ የሚያስቀጥል መሆኑን ላረጋግጥላችሁ እወዳለሁ። ባየነው በሰራችሁት ሁሉ እጅግ ከፍተኛ ደስታና ክብር የተሰማን መሆኑን እየገለፅኩ፤ ይህ ስራችሁ ጅምር መሆኑን አውቃችሁ የተጠናከረ ስራ እንድትሰሩ አደራ ልላችሁ እፈልጋለሁ።

**ኢትዮጵያ በልጆችዋ ጥረት ታፍራና ተከብራ ለዘላለም ትኑር !**
**ፈጣሪ ኢትዮጵያና ህዝቦቿን ይባርክ! አመሰግናለሁ!**



# የህዳሴ ግድብ ሶስተኛው ተርባይን ሙሌት

መላው የኢትዮጵያ ህዝብ እንዲሁም በዚህ ስፍራ በዚህ ታሪካዊ ፕሮጀክት ውስጥ በእውቀት በጉልበት የተሳተፋቹ የኢትዮጵያ ድንቅ ልጆች ከዚህም ባሻገር የዚህን ፕሮጀክት ጠቃሚነት ተገንዝባችሁ ኢትዮጵያን በሀሳብ በተለያየየ መንገድ ስትረዱ የቆያችሁ የኢትዮጵያ ወዳጆች በሙሉ ዛሬ በዚህ ስፍራ ሶስተኛው ዙር የውሃ ሙሌት መጠናቀቁን ሳበስርላችሁ በታላቅ ደስታ ነው፡፡ ዛሬ ከጀርባዬ የምትመለከቱት የሶስተኛው ሙሌት የውሃ አቨርቶፕ ማድረግ ወይም በላይ መፍሰስ እየተከናወነ ይገኛል፡፡ ይህ ክንውን አምና ከነበረው ጋር ለማነፃፀር ብንሞክር አምና በመሀከል ውሃ የሚፈስበት ቦታ አምስት ሰባ አምስት ሜትር ነበር ዘንድሮ ተጨማሪ ሃያ አምት ሜትር ከፍ በማድረግ ስድስት መቶ ሜትር ላይ የውሃው ፍሰት ይታያል ግራእና ቀፀ አምስት ሜትር ከፍ በማድረግ  ስድስት መቶ ሜትር ላይ የውሃው ፍሰት ይታያል፡፡ ግራ እና ቀኝ አምና እምስት መቶ ሰማንያ ምሰት ሜትር ነበር ዘንድሮ ስድስት መቶ አስራ አንድ ሜትር በመድረስ በከፍተኛ ደረጃ ውሃ የመያዝ አቅማችንን እና ኢነርጂ ጀነሬት የማድረግ አቅማንን ከፍ አድርጎታል፡፡ ይህ በዚህ ስራ ለተሳተፉ ሰዎች ሁሉ እና ለመላው የኢትዮጵያ ህዝብ ከፍተኛ ደስታን የሚፈጥር ታላቅ ድል ስለሆነ እንኳን ደስ ያላችሁ እንኳን ደስ ያለን ማለት እፈልጋለሁ፡፡ ሁላችሁም እንደምትገነዘቡት አባይ የኛ የፈጠራ ውጤት አይደለም አባይ የፈጣሪ ስጦታ ነው፡፡ ይህ የፈጣሪ ስጦታ በአግባቡ እንድንጠቀምበት በአግባቡ እንድንገለገልበት ታስቦ የተሰጠን ነው ፈጣሪ እጅ ሰጥቶናል እጃችንን በአግባቡ መጠቀም ማረስ፣ መዝራት፣ መነገድ፣ መገንባት የእያንዳንዱ በነፃ እጅ የሰጠው ሰው ኃላፊነት ይሆናል፡፡ አይን በነፃ ተሰቶናል አይናችንን በአግባቡ መጠቀም መልገል የእያንዳንዱ በነፃ የተሰጠው ሰው ኃላፊነት ይሆናል፡፡ ከተሰጠው በኋላ የማይጠቀም ሰው ቢኖር ተወቃሹ እሱ እንጂ ሰጪው ሊሆን አይችልም በዚሁ አግባብ አባይ ለኢትዮጵያ ብቻ ሳይሆን ለዓለም ተሰጥቷል፡፡

ለዓለም የተሰጠበት መንገድ የዓለም ህዝቦች አስፈላጊ ነው ብለው በሚያምኑበት

በማንኛውም ጊዜ በዚህ ስፍራ መጥተው ሊዝናኑ ሊያዩ ጊዜያቸውን በደስታ ሊያስልፉ የሚያስችል ከፍተኛ ብቃት አለው በዚህ ግድብ ምክንያት ከኋላ በምናየው ቦታ ሰባ ገደማ ደሴቶች አሉ ሰባ ገደማ ሃይላንዶች አሉ እነዚህ ሃይላንዶች ከአርባ በላይ የሚሆነው ሃይላንድ እያንዳንዱ ከ10 ሄክታር በላይ ቦታ ይዟል፡፡ አንድንዶቹ 800 ሄክታር ከ200 ሺ ሄክታርም በላይም ሃይላንድ የሆነ ቦታ ይገኛል፡፡ ዝቅተኛው ሃይላንድ 5 ሄክታር የሚይዝ ነው እያንዳንዱን ሃይላንድ አንድ አንድ ሪዞርት ብናደርገው በመሀል ከውሃ ጋር የሚደረጉ ጨዋታዎችን ብንጨምር ከፍተኛ የሆነ የአሳ ምርት በዚህ ቦታ አለ እስከ ሰባ ሰማንያ ኪሎ የሚመዝኑ አሳዎች አሉ በፊሺንግ አሳን በማጥመድ ደስታ የሚያገኙ ሰዎች ቢኖሩ መተው ሊዝናኑበት ይችላሉ፡፡ እንግዲህ አካባቢውን እንደምታዩት እጅግ ተራራማ እና በጣም ሲበዛ ግሪን ቦታ ነው፡፡ ተራራውን ለሃይኪንግ እንዲሁም ግሪነሪውን ለተለያየ መዝናኛ ቦታ መጠቀም ይቻላል ከዚህ አንፃር አለም መጥቶ በዚህ ቦታ ለመዝናናት የሚያስችለው ትልቅ ስጦታ ነው፡፡

ነገር ግን ግድቡ ከመገደቡ በፊት እንደዚህ አይነት ደስታ በዚህ ቦታ ማግኘት አይቻልም ነበር፡፡ ሙቀቱ ብቻ ሳይሆን የውሃም መቆየት በራሱ ኃይላንድ ፈጥሯል አሣ ፈጥሯል በጣም በርካታ የተፈጥሮ ሀብቶቻችን አጉልተን የምናይበትን እድል ፈጥሮልናል እና አለም ከዚህ አንፃር መገልገል የሚችልበትን ቦታ መሆኑን ተገንዝቦ ለመጠቀም ዝግጁ መሆን ኢንቨስት ለማድረግ ዝግጁ መሆን ይኖርበታል፡፡
ሁለተኛው በነፃ ተቀባይ አፍሪካ ነው አፍሪካ የኢኮኖሚ ትስስር ብሎ ካጸደቀ አመታት ተቆጥረዋል እና የኢኮኖሚ ትስስር አንዱ መንገድ ኢነርጂን ለጎረቤት ሀገሮች መሸጥ ነው፡፡ ይህ ሀይል ሲመነጭ ሙሉ በሙሉ ለኛ ጎረቤት ብቻ ሳይሆን ከዚያም ተሻግሮ ሊጠቅም የሚችል ነው ለዜጎቻችን ይጠቅማል እኛም ለጎረቤት ህዝቦች ኃይል በመሸጥ እንዲገለገሉ ለማድረግ ያስችላል ያስተሳስራል በጋራ እንድንለማ በጋራ እንድናድግ እድል ይከፍታል፡፡

ሶስተኛው በነፃ የተሰጣቸው ሀገራት ሶስቱ ሀገራት ናቸው፡፡ ኢትዮጵያ፣ ሱዳን እና ግብጽ እነዚህ ሶስቱ በነፃ ይሔን ውሃ የመጠቀም እድል የተሰጣቸው ሀገራት የሚገባቸውን ድርሻ በአግባቡ መጠቀም ከቻሉ ለእነሱ ብቻ ሳይሆን ለሌሎች የአፍሪካ ወንድም እና እህቶችም ጭምር መጥቀም የሚችሉ በርካታ ስራዎች ሊሰሩ

ይችላሉ፡፡ እነዚህ ሶስት ሀገሮች የተሰጣቸውን መገንዘብ በተሰጣቸው ልክ መተባበርና በጋራ መቆም ከእነሱ ይጠበቃል፡፡ ነገር ግን አባይ ለሶስቱ ሀገራ እንደተሰጠ ሶስቱም በሚገባቸው ድርሻ መጠቀም እንዳለባቸው የማያምኑ ኃይሎች ካሉ የተፈጥሮን ህግ ያዛባሉ አባይ ለኛ ብቻ የተሰጠ ቢሆን ኖሮ ልክ እንደ አዋሽ እዚሁ በቀረ ነበር ወይንም ወደደቡብ ወደምስራቅ በፈሰሰ ነበር፡፡ አባይ በተፈጥሮ ይህንን ኮርስ ሲይዝ እኛ የሚገባንን ተጠቅመን የሱዳንና የግብጽ ወንድሞቻችን እንዲጠቀሙበት ሰጪው በነፃ የሰጠን ስፍራ እንደሆነ መገንዘብ ያስፈልጋል፡፡

ለዚህም ኢትዮጵያ ለሺህ አመታት አባይን ሳትጠቀም በመቆየቷ ከፍተኛ ቁጭትና ሀዘን ይሰማታል፡፡ ለሺህ አመታት የተሰጣትን አይን አላየችበትም ማለት ነው፡፡ የተሰጣትን እጅ አልራችበትም ማለት ነው ዛሬ ግን እጅግ ደሰታ የሚሰጥ ኩልል ያለ ውሃ በዚህ ስፍራ ማየት ይቻላል፡፡ በርካታ አሳዎች እያጠመዱ መመገብ ይቻላል አጠቃላይ አካባቢውን ለቱሪዝም ምቹ አድርጎ መጠቀም የሚያስችል እጅግ ከፍተኛ የሆነ ሀብት ወይንም አንዳንዶች እንደሚሉት ብሉ ጎልድ መሆኑን መገንዘብ ያስልጋል ሰው እና ሀገር የሚመሳሰል ባህሪ አላቸው አንድ ሰው ምንም እንኳን በተፈጥሮው የሚያምር ቁመና ቢኖረውም በቂ ምግብ ካላገኘ፣ ቆንጆ ልብስ ካለበሰ፣ ካልታጠበ ያሰው የቆሸሸ ነው እና መልካም ስፍራ ላይ የማይግር ስለሆነ ሰዎች በቀላሉ ደሃ መሆኑን በዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ የሚኖር ሰው መሆኑን ተገንዝበው ናቅ አድርገው ሊያዩት ይችላሉ ሰው በተፈጥሮ የተሰጠው ቁመና ብቻ ሳይሆን በምግብ፣ በንጽህና፣ በአለባበስም ጭምር የሚቀየር ስለሆነ ሀገርም እንደዚሁ ናት፡፡

ምንም እንኳን በተፈጥሮ እጅግ ያማረ ጸጋ የተሰጣት ሀገር ብትሆንም ያን አልምታ ተጠቅማ ከልመና ወጥታ ሌሎች ማሳየት ካልቻለች ልክ በጎዳና በቆሸሸ ባደፈ ልብስ እንደሚታየው ሰው ዝቅ ተደርጋ ልትታይ ትችላለች፡፡ ኢትዮጳያን ደሃ ያሰኛት ኢትዮጳያን ለማኝ ያሰኛት ስላልተሰጣት አይደለም፡፡ እጅግ አስደማሚ የሆነ የተፈጥሮ ጸጋዎች አሉዋት ነገር ግን ወንድ አና ሴት ልጆቿ በተባበረ መንፈስ በጋራ ቆመው የሀገርን ጥቅም አስቀድመው ለልማት ቅድሚያ ሰጥተው መስራት ባለመቻላቸው ነው እንጂ በአንድ ግድብ ሰባ ሃይላንድ አለን ማለት ቀላል ሀብት አይደለም ግራ እና ቀኝ ያለውን መልክአ ምድር ብታዩት እጅግ አስደማሚ የሆነ ተራራማ ከተራራም በላይ በጣም ግሪን ቦታ ይታያል፡፡

እንግዲህ ሁላችሁም እንደምታውቁት ኢትዮጵያ በአፍሪካ ውስጥ ያሉ ተራራዎች ከግማሽ በላይ ኢትዮጲያ ውስጥ አለ ይባላሉ ይህንን መጠቀም ብንችል ኖሮ ምን ያክል ተለውጠን በጽዱ ልብስ በጽዱ ቁመና በጽዱ ሁኔታ ደሃ ከመባል የተላቀቅን መሆን እንደምንችል መገንዘብ ይቻላል፡፡

መላው የኢትዮጲያ ህዝብ ሰማንያ አምስት ፐርሰንቱን የአባይ ውሃ ኮንትሪቢውት ስናረግ ቆይተን ላለፉት ዘመናት አለመጠቀማችን የሚያስቆጭ ቢሆንም አሁን መልካም ጅምር በመታየቱ  የሚገባንን ተጠቅመን የሚገባቸውን ለወንድሞቻችን ሰጥተን በጋራ ለማደግ በእኛ በኩል ዝግጁ መሆናችንን በድጋሚ እየገለጽኩ አባይ የኢትዮጵያ ኩራት አባይ የኢትዮጵያ የብልጽገና ጅማሮ መነሻ አባይ ኢትዮጵያዊነት እና የኢትዮጵያ ከፍታ የሚለመልምበት ቦታ መሆኑን ተገንዝበን እስላም፣ ክርስቲያን፣ ጉራጌ፣ ስልጤ፣ ኦሮሞ፣ አማራ፣ ሱማሌ፣ አፋር ሳንል ኢትዮጵያዊ ሁሉ በጋራ በመደመር አንድ ላይ በመቆም ብልጽግናችንን እውን እንድናደርግና ከእርዳታ ከልመና እራሳችንን እንድንገላግል በዚሁ አጋጣሚ ጥሪዬን አቀርባለሁ፡፡

መላው የአፍሪካ ወንድሞቻችን እንኳን ደስ ያላችሁ አባይ እንደተለመደው በድል የሚገባውን አስቀርቶ የሚገባቸውን እየሰጠ መጓዝ ጀምሯል፡፡ መላው የኢትዮጵያ ህዝብ፣ በዚህ የተሳተፋችሁ፣ ገንዘብ ያዋጣችሁ፣ በሙያ የደገፋችሁ፣ በዲፕሎማሲው መስክ የጮሀቹ ሁሉ ልፋታችሁ ፍሬ ስላፈራ እንኳን ደስ ያላችሁ ልል እፈልጋለሁ፡፡ ከሁሉ በላይ  የጀመርነው የእጅ ስራ እንዲከናወን የረዳን፣ የተናገርነው እንዲፈጸም ያገዘን፣ በድካም በፈተና ሁሉ በድካም በጥንካሬ በስኬት እንድንወጣ ያደረገን መልካሙ አምላክ የኢትዮጵያ ፈጣሪ የተመሰገነ ይሁን፡፡ አሁንም ፈጣሪ ኢትዮጵያ እና ህዝቦቿን አብዝቶ ይባርክ ብልጽግናችንን እውን ያድርግ የእጃችንን ሥራ ይባርክ የተጀመረው ድል ይቀጥላል የተጀመረው የብልጽግና ጉዞ ይቀጥላል፡፡ እያንዳንዱ ፈተና ግን የሚያጠነክረን ይሆናልና የምንሸማቀቅበት ሳይሆን የምንማርበት እንዲሆን አደራ እያልኩ፡፡

**እንኳን ደስ ያላችሁ!**
**እንኳን ደስ ያለን ማለት እፈልጋለሁ! እጅግ አድርጌ አመሰግናለሁ!**
ነሃሴ 6፣ 2014 ዓ.ም



# የአረንጓዴ አሻራ መርሃግብር ማጠናቀቂያ በድሬዳዋ ከተማ

**ክቡር አቶ አገኘሁ ተሻገር የፌዴሬሽን ምክር ቤት አፈ ጉባዔ**
**ክቡር አቶ አደም ፋራህ የብልጽግና ምክትል ፕሬዘዳንት**
**ክቡር አቶ ኑርሁሴን የግብርና ሚኒስቴር**
**ክቡር አቶ ከድር የውቧ ድሬዳዋ ከተማ ከንቲባ**

የተከበራችሁ ለዚህ ድንቅ ስራ አፈጻጸም የፍጻሜ እለት ተጋብዛችሁ በዚህ ስፍራ የተገኛችሁ እንግዶች በሙሉ እንኳን ደስ አላችሁ እንኳን ደስ አለን ልላችሁ እወዳለሁ!!

የዛሬው እለት  የተናገርነውን የምንፈጽም ያቀድነውን መፈፀም የምንችል ማቀድ መናገር ብቻ ሳይሆን ፈጽመን በፍጻሜው ላይ መቆም የምንችል ህዝቦች መሆናችንን ለራሳችንም ለአለምም ያሳየንበት ቀን ስለሆነ በግሌ ድርብ ደስታ እና ክብር ይሰማኛል ያ ሚሰማችሁ ከሆነ እናንተንም እንኳን ደስ ያላችሁ፡፡

አረንጓዴ አሻራ እኛ ብዙ የተማርንበት አለምንም የቀሰቀስንበት ተግባር ነው። እኛ ስንጀምረው ያላበረታቱን እኛ ስንጀምረው እምብዛም ያልዘገቡ ሀገራት እንደ መንግስት እየወጡ አንድ ቢሊየን፣ ሁለት ቢሊየን እንተክላለን ማለት ጀምረዋል። ይህንን እኛ በጣም በቀና መንገድ እንመለከተዋለን ምንም እንኳን ኢትዮጵያ ጀምራ እኛ ተከተልን ማለት ባይደፍሩም በተግባር መከተላቸው በራሱ እንደ ድንቅ ነገር ስለሚወሰድ የቀሩ ሀገራትም በዚሁ ተግባር እንዲሳተፉ በጎ ምኞታችንና ፍላጎታችን መሆኑን በዚሁ አጋጣሚ መግለጽ እወዳለሁ፡፡ በአረንጓዴ አሻራ የደን ሀብታችን እንዳይመናመን እየጠፋ ያለውም እንዲያገግም በእጅጉ አግዞናል። ኢትዮጵያ በጣም ትልቅ ሀገር ናት። ወደምዕራቡ ስንሄድ “ምን ያደርጋል ግሪን ሌጋሲ?” ሊባል የሚያስችል የደን ስብስብ አለ ወይም ከፍተኛ ደንና ጫካ ይታያል። ወደ ሰሜን እና

ምስራቅ ስንመጣ ደግሞ በጣም ከፍተኛ ስራ እንደሚጠበቅብን ያሳያል። አሁንም ድሬደዋ አካባቢ የሚያሳየው ጉዳዩ መቀጠል እንዳለበት እንጂ ሰርተን እንደጨረስን አይደለም። ከዚህ አንጻር የደን ሀብታችን እንዲያገግም፣ የጠፋው እንዲመለስ እንዲዋብ የማድረግ ስራ፣ የአፈር መሸርሸር እንዲቆም በቅርቡ ሰምታችሁ ከሆነ አንዱ የምንሰራው ስራ የማይመቻቸው አንዳንድ አካላት ያነሱት በነጻ የምናገኘው አፈር ቀረብን የሚል ነው።

ኢትዮጵያውያን ለአፈር ዋጋ ባንሰጥም አፈራችን እየተሸረሸረ ለሌሎች በነጻ የሚያገኙት ሀብት ስለነበረ በግሪን ሌጋሲ የዝናብ መጠን መጨመር ብቻ ሳይሆን የሚሸረሸረውን አፈር ማስቀረትም እንዲሁ እጅግ አስፈላጊ ስራ ነው፡፡ ሌላው የዝናብ መጠን መጨመር ነው፡፡ የዝናብ ዋጋ የሚገባን በዓመት አንድ ቀን የሚዘንብባቸውን ሀገራትን ስናይ ብቻ ነው።በአመት አንድ ቀን ወይንም ደግሞ ጭራሽ ዝናብ የማያገኙ አገራት አሉ ዝናብ ማለት የጨው ውሃ አይደለም ንፁህ የሚጠጣ ውሀ ነው እኛም እምንጠጣው ዛፎች የሚጠጡት ጅረቶች የሚሞላ ወንዞቻችንን የሚሞላ የከርሰምድረ ሀብታችንን ከፍ የሚደርግ ነው፡፡ እናም የዝናብ ስጦታ እጅግ ድንቅ ስጦታ ነው። ሲከለከል ብቻ የሚገባን ቢሆንም ዝናብ ከፈጣሪ የሚሰጥ በጣም አስፈላጊና ወሳኝ ስጦታ ልንጠብቀው ልንንከባከበው የሚገባ ሀብት ነው።

ይሄንን ደግሞ የድሬዳዋ ሕዝብ በደንብ እንደሚገነዘበው ሀሮማያ ከ10 ዓመት በላይ ከደረቀ በኋላ ግሪን ሌጋሲ ጀምረን በሁለት አመታችን መልሶ እንዴት እንዳገገመ አይታችኋል ዛሬ ሀሮማያ በጀልባ እሚኬድበት ሀይቅ ሆኗል የዛሬ አራት እና አምስት አመት ሀሮማያ ደርቆ ነበር፡፡ ይሄ እዚህ ያያችሁት ምልክት ብዙ ቦታ አለ። ህዳሴ አሁን የያዘውን ውሀ ያያዘው የዝናብ መጠናችንን ስለጨመርን ጭምር ስለሆነ ይህ ስራ እኛ ጋር ብቻ ሳይሆን በመላው አፍሪካ በተለይም በምስራቅ አፍሪካ ባህል ሆኖ እንዲቀጥል መስራት እንደሚጠበቅብን በዚሁ አጋጣሚ ማሳሰብ እፈልጋለሁ።
ከምርት ጋር ተያይዞ በከፍተኛ ደረጃ ምርትና ምርታማነት እንዲጨምር አድርጓል፡ ፡ ከቅርብ ጊዜ ጀምሮ አንዳንድ ነገር ይሰማል ኢትዮጵያ በድርቅ ልትመታ ነው ድርቅ ኢትጵያን ያጠቃታል የሚል ዜና በስፋት ይሰማል እንዲሁም ኢትዮጵያ ስንዴ ገዝታ ስንዴዋ በጀልባ ተጭኗል የሚል ዜናም ተሰምቷል። ኢትዮጵያ ስንዴም አልገዛችም፣ ኢትዮጵያ ድርቅም አይመታትም፡፡ ዋናው የድርቅና የስንዴው ዓላማ ስንዴ ኤክስፖርት እናደርጋለን ስላልን ቀድሞ የማጥላላት ዘመቻ አካል ነው።”ስንዴ

ኤክስፖርት እናደርጋለን እያሉ ስንዴ ያስገባሉ ስንዴ ኤክስፖርት እናደርጋለን እያሉ በድርቅ ተመቱ" ለማለት እንዲያመቻቸው ነው። ለምሳሌ ከአመት በፊት በሰሜኑ የአገራችን ክፍል ችግር ሲያጋጥም የዓለም ሚዲያ በሙሉ ከፍተኛ ድርቅ ስለሚያጋጥም ይሄ ድርቅን ተገን ያደረገ ውጊያ ነውና አቁሙ እንባል ነበር በወቅቱ እኛ ድርቅ በሰሜኑ የአገራችን ክፍል የለም አይኖርም ብንልም ሰሚ አልነበረንም ከአመት በኋላ ድርቅ ያጋጠመን በሰሜን ኢትዮጵያ ሳይሆን በምስራቅ የአገሪቱ ክፍል ነበር ቦረናና ሶማሌ እነዚያ በሰሜን ድርቅ ጋጥማችኋል ብለው በስፋት ሲናገሩ የነበሩ ሀይሎች ሶማሌና ቦረና ሲጠቃ እንኳን ተጨማሪ ድጋፍ ማድረግ ቀርቶ ከአምስት ስድስት አመት በፊት ከአስር አመት በፊት ደረጉትን ድጋፍ ማድረግ አልቻሉም። ስለዚህ ድርቁ እንዲመጣ የመፈለግ ዜና እንጂ ድርቁን ለመከላከል የነበረ ፍላጎት አልነበረም ማለት ነው።

ድርቅ በሰሜን ይመጣል ተብሎ ሳይመጣ ቀርቶ በምስራቅ ሲመጣ ድጋፍ የቀነሰበት ዋናው ምክንያት እነዚህ ሟርተኞች ዋና አላማቸው ችግር መናገር ነው ድርቅ ይመጣል ረሀብ ይመታል ኤክስፖርት ማድረግ አትችሉም አታድጉም የእናንተ ልክ ይሄ አይደለም ብሎ "negative energy" እኛ ላይ መዝራት ነው ይሄን እኛ ላይ አልጀመሩም። ይሄን ተቀብለው የተሸነፉ ሀገራት አሉ። ይሄን እምቢ ብለው ያሸነፉ አገራት አሉ። ለምሳሌ ሕንድን ብንወስድ ላለፉት 70 ዓመታት ያለፈችበት ታሪክ እጅግ አስደማሚ ነው። የዛሬ 70 ዓመት ሕንድ በእንግሊዝ ትገዛ ነበር "እንግሊዝ ሕንድን ከለቀቀች በኋላ ሕንድ አገር ሆና መቀጠል አትችልም" ነው ያሉት። አንደኛ በጣም በርካታ ብሔሮች ብሔረሰቦች ያሉበት "Diversified "የሆነ ማህበረሰብ ስለሆነ ሁለተኛ ከፍተኛ ድህነት የሚታይበት ሀገር ስለሆነ የዛሬ 70 ዓመት የሕንድ የነፍስ ወከፍ ገቢ ከኢትዮጵያ ያንሳል በጣም በጣም ዝቅተኛ ነው በዚህ የተነሳ ከድህነት ልትወጡ አትችሉም የሚል አዋጅ የታወጀበትና Diversified የሆነው የህንድ ህዝብ አልቀበልም በማለት ባለፉት 70 ዓመታት ባደረጋቸው ተጋድሎዎች በተለይ "Green revolution" ብለው በምግብ ራስን ለመቻል "white revolution" ብለው በወተት ምርት ራሳቸውን ለማሳደግ እንዲሁም በኋላ በጤና ዘርፍ ራሳቸውን ከፍ ለማድረግ ደረጉት ጥረት አሁን ከዓለም ትላልቅ ኢኮኖሚ ከገነቡ ከ3 ትሪሊየን በላይ GDP ካላቸው ሀገራት ተርታ ለመመደብ ችለዋል ምን ብለው? አንፈርስም የመፍረስ አዋጅንም አንቀበልም ብለው ኢትዮጵያ ኢሄን መድገም አለባት ብዙዎች ትፈርሳላችሁ ትበተናላችሁ አታድጉም ቢሉንም በህዳሴ፣ በግሪን ሌጋሲ እያሳየን

ያለነው ልምምድ የጀመርነውን መጨረስ የምንችል፣ ያቀድነውን መፈፀም የምንችል፣ የብልፅግናን መሰረት መጣል የምንችል መሆናችንን ነው 20 ቢሊየን እንተክላለን ብለን 25 ቢሊየን ችግኝ ኢትዮጵያን ማልበስ መቻል እኛን በእጅጉ የሚያኮራ ይህንን ድል ማየት የማይችሉ የማይፈልጉ ሀገራት ደግሞ በእጅጉ የሚያሳፍር የኢትዮጵያን ጅግንነት የሚያሳይ ተግባር ስለሆነ መላው የኢትዮጵያን ሕዝብ እንኳን ደስ አላችሁ እንኳን ለዚህ አበቃችሁ ማለት እፈልጋለሁ፡፡

ነገር ግን ኢትዮጵያ ከ25 ቢሊየን ችግኝ በላይ ናት ይህ በቂ አይደለም ሀገራችንን ደራርበን ማልበስ ይጠበቅብናል፡፡ አዲሱ ባህል እንደእኛ ያሉ ጎልማሶች ብቻ ሳይሆኑ ህጻናት አብረው የሚያድጉትን ችግኝ በየቦታው ሲተክሉ ይታያል። በየስፍራው ህጻናት የሚተክሉት ችግኝ ከእነሱ ጋር የሚያድግ ነው ይህንን ባህል እያሰፋን ከሄድን ከመቁረጥ መትከል፣ ከመዋሸት እውነት መናገር፣ ከመጥላት መውደድ፣ ከመግፋት ማቀፍ፣ ይህንን ባህል በደግነትና በነጻ የሚሰጥ ማህበረሰብ አይከስርም። በመውደድ የሚከስር በመትከል የሚከስር በማቀፍ የሚከስር ማህበረሰብ የለም ማህበረሰብን የሚያከስር መግፋት ነው፣ መጥላት ነው፣ ክፉ መናገር ነው፣ ማራቅ ነው ከዚህ የራቀ ተግባር የሚፈጽሙ ሁሉ የተሻለ ሀገር ለመመስረት እጅግ ከፍተና እድል ያላቸው በመሆኑ እኛ ኢትዮጵያውያንም ከእነሱ እንደአንዱ እንድንሆን በመልካም ነገር ላይ ብቻ እራሳችንን እንድናሳትፍ አደራ ማለት እፈልጋለሁ፡፡ እንግዲህ ኢትዮጵያውያን እንደሙቀጫ ወቃጭ መሆን የለብንም። የሙቀጫ ወቃጭ ጠባይ ያስገባውን ነገር ሁሉ ከወቀጠ በኋላ ከወቀጠበት ነገር ላይ ጠቅልሎ ጠርጎ ነው። የሚወስደው አንድም ነገር ተባብረኸኛልና ላስቀርልህ አይልም ተልባውንም፣ ስንዴውንም ጠርጎ ነው የሚወስደው እኛ ኢትዮጵያውያን የኢትዮጵያን የከርሰምድርና የገፀ ምድር ሀብት ጠራርገን የምንወስድ እና የምናጠፋ መሆን የለብንም። አሟጠን መጠቀም ሳይሆን የሚያስፈልገንን መጠቀም እና መቆየት የሚገባውን ለትውልድ የምናቆይ መሆን አለብን፡፡

በሀገራችን ሰዎች “ላሚቱ እንዳትነጥፍ ላሚቱን መንከባከብ ያስፈልጋል ይላሉ” መሬት ይነጥፋል መሬት ከአቅም በላይ ሲጋጥ መስጠት የሚገባውን ተግባር ይቀንሳል ያ እንዳይሆን መሬትን መንከባከብ በእጅጉ አስፈላጊ ነው ያንን ስናደርግ ከዚህ ቀደም እንዳየነው በርካታ ለውጦች ማየት ያስችላል በዝናብም፣ በአእዋፋትም፣ በዱር አራዊትም ከፍተኛ ለውጥ እንዲመጣ ስለሚያደርግ ይህንን ተግባር ሁላችንም

በተባበረ ክንድ ማስቀጠል ይኖርብናል፡፡

እኛ ላለፉት አራት አመታት ችግኝ ስንተክል የሳቁ የተሳለቁ ወንድምና እህቶቻችን አሉ እነዚህ ወንድምና እህቶቻችን ሁለት እድል አላቸው አንደኛው በሚቀጥለው አራት ዓመት አሁንም እየተከልን ስንቀጥል ከባለፈው ስህተት ተምረው ከእኛ ጋር  መትከል ነው ያንን ማድረግ ካልቻሉ ግን የእነሱ ልጆች በደን ውስጥ ሲሄዱ፣ የእነሱ ልጆች ማንጎና አቡካዶ ኤክስፖርት ሲያደርጉ ይስቁባቸዋል ይሳለቁባቸዋል ልጆቻቸው ከሚሳለቁባቸውና ከሚስቁባቸው ለሚቀጥሉት አራት አመታት ከእኛ ጋር ተግተው መትከል ይኖርባቸዋል እንዲሁም ስንተክል የሰነፉ አሉ ባይሳለቁም የሰነፉና ያልተባበሩ አሉ ቅድም በቀረበው ሪፖርት ወደ 30 ሚሊየን የሚጠጋ ሰው አንዳንዱም በድግግሞሽ የተሳተፈበት ስራ ነው ይሄ ቀላል ቁጥር አይደለም ያም ሆኖ ግን መትከል ሲችሉ የሰነፉ ደግሞ ሰዎች አሉ እነዚህ ደግሞ እንደቅድሚ የሚሳለቅባቸውም ባይኖር ውጤቱን ሲያዩ ያፍራሉ ከማፈርም ከልጆቻችን መሳቀቅም እንድንድን ዕድል ስላለን በሚቀጥለው አራት አመት ጥራት ላይ ለገበያ በሚመች አካባቢን በሚያስውብ ሀገር በሚቀይር አግባብ አብረን እንድንተክል ላለፉት አራት አመታት ያመለጣቸውን ወንድምና እህቶቼን ለሚቀጥለው አራት አመታት እንዲሳተፉ በዚሁ አጋጣሚ መጋበዝ እፈልጋለሁ፡፡

አቶ ዑመር እንዳሉት ኢትዮጵያ ውስጥ ችግኝ መትከል ባህል መሆን አለበት የሚቀጥለው አራት አመት ከባለፈው የሚለየው አንደኛ ጥራት ላይ ማተኮር ነው ሁለተኛ ለገበያ የሚውሉ ተክሎች ላይ ማተኮር ነው ሶስተኛው የምንተክለው በተቻለ መጠን “indigenous”  ሀገር በቀል ዛፎች እንዲሆኑ ቦታና ሁኔታውን እየለዩ መትከል ያስፈልጋል። መትከል ከፍተኛ ሀብት የሚወጣበት ነው። በሌላ በኩል ደግሞ ባህል ሆኖ ይቀጥል ስንል ከመቶ ሃያ ሺህ በላይ ነርሰሪዎች ገንብተናል። እነዚህ ነርሰሪዎች ብዙ የስራ ዕድል ፈጥረዋል በጥራት እንዲያዘጋጁ አድርገን በሀገር ውስጥም በጎረቤትም የጀመርነውን የችግኝ ተከላ ባህል የማድረግ ስራ የምናስፋፋ ይሆናል። አናቆምም፣ ህዳሴም ሲያልቅ አናቆምም፣ ግሪን ሌጋሲም ሲያልቅ አናቆምም፣ ስንዴም ኤክስፖርት ካደረግን በኋላ አናቆምም፣ ሻይ ኤክስፖርት እደርጋለን፣ ወተት ኤክስፖርት እናደርጋለን ዓይነቱ ይቀየራል እንጂ የሚቆም ነገር የለም።

በጥቅሉ ለመላው የኢትዮጵያ ሕዝብ ግሪን ሌጋሲን ከጀመርነው በላይ አሳክተናል

ሕዳሴን ባልነው ልክ አሳክተናል በጣም በርካታ ፕሮጀክቶች በተባሉት ልክ እየተሳኩ ነው ስንዴም ከጥቂት ወራት በኋላ ድርቅ ገባ እየተባለ ኤክስፖት አድርገን ጠላት እናሳፍራለን ኢትየጵያውያንን ደግሞ እናስደስታለን ይህ የጀመርነው ተግባር የሚቆም አይደለም እንዲቆም የሚፈልጉ ሀይሎች ሰው ሊገሉ ይችላሉ፣ ሊሳደቡ ይችላሉ፣ እንቅፋት ሊሆኑ ይችላሉ፣ የኢትዮጵያውያን ምልክት እና አርማ እንቅፋት እያነሱ ገዳይን እየገፉ አንድ ሆነው የጀመሩትን ልማት ማሳለጥ ነው በእርግጠኝነት መናገር የምችለው የኢትዮጵያ ብልፅግና መሰረት እየተጣለ ነው ኢትዮጵያ አትፈርስም ኢትዮጵያ ሀያል እና ገናና የበለፀገች ሀገር ሆና ልጆቿ የሚኮሩባት የወጡ የሚመለሱባት ሀገር ትሆናለች እያንዳንዱ ፈተና ይህንን ለማሳካት የሚያበረታን የሚያጠነክረን ይሆናል በሚገርተኞች አንቆምም ተግተን እንሰራለን ሀገራችንን ለብልፅግና እናበቃለን እንኳን ደስ ያላችሁ እንኳን ደስ ያለን መልካም የመዝጊ ፕሮግራም እንዲሆንላችሁ እመኛለሁ፡፡

**አመሰግናለሁ !**

# የድሬዳዋ ነጻ ቀጠና ምርቃት ንግግር

## የድሬዳዋ ነጻ ቀጠና ምርቃት ንግግር

ክቡር አቶ አደም ፋራህ ክቡር አቶ አገኘሁ ተሻገር ክብርት ወ/ሮ ዳግማዊት ሞገስ እንዲሁም አቶ ከድር ጅዋር የተከበራችሁ ሚኒስትሮች የአዲስ አበባ ከተማ ከንቲባ ክቡራን እንግዶች ዛሬ ድሬደዋ የበረሃ ገነት የሚለው ስምዋን ቀይራ በኢትዮጵያ ውስጥ ሁለተኛ ቆንጆ ኢትዮጵያ ለመፍጠር የታደለች ድንቅ ከተማ መሆንዋን የነፃ ንግድ ቀጠና ማለት በኢትዮጵያ ውስጥ የተፈጠረ ሌላ ትንሽ ኢትዮጵያ የራሱ ህግ የራሱ አሠራር ያለው ስፍራ ስለሆነ ድሬደዋ ባቡር ለማስገባት ቴክኖሎጂ ለማስገባት ቀዳሚ ብትሆንም ዛሬም ትንሿን ኢትዮጵያን ለመፍጠር ስለታደለች ድሬደዋዎች እንኳን ደስ ያላችሁ ፡፡

ነፃ የንግድ ቀጠና በእጅጉ ኢትዮጵያ ከተኛችባቸው ዘርፎች አንዱ ነው ብዙ የተኛንበት ያልነቃንበት ጉዳዮች እንዳሉ ይታወቃል በውሃ ጉዳይ አልነቃንም በመሬት ጉዳይ አልነቃንም በህዝብ ቁጥር ማደግና እንዴት መጠቀም እንዳለብን አልነቃንም አጠቃላይ በቀጠናው ባለን ተፅዕኖ የመፍጠር አቅም አልነቃንም ከዛሁሉ ውስጥ እጅግ የሚያስገርመው ግን ነፃ የንግድ ቀጠና ሳንፈጥር እስከአሁን መቆየታችን መተኛት ብቻ ሳይሆን በጥልቅ እንቅልፍ ውስጥ እንደነበር የሚያረጋግጥ ጉዳይ ነው ይህንን ነፃ የንግድ ቀጠናና መሰል ነፃ የኢኮኖሚክ ዞን አሜሪካ በ1930ዎቹ አጋማሽ ነው የጀመረችው ብዙዎቻችን ሳንወለድ ማለት ነው ቻይናም በ1979 ነው የጀመረችው ቻይና ከጀመረች አሁን ወደ አርባ ሁለት ሦስት ዓመት ገደማ አስቆጥሮዋል ቻና ዛሬ ከሃምሳ አራት በላይ መሠል የኢኮኖሚ ፣የኤክስፖርት ፣የፖርት  እና ፍሪ ትሬድ ዞኖች አሉዋት ይህ አሰራር ከመጀመርዋ በፊት ቻይና ጂዲፒዋ ግማሽ ትሪሊየን ወይም አምስት መቶ ቢሊየን ገደማ ነበር ይህን አሰራር ከጀመረች ከአራት አስርተ አመታት በኃላ ዛሬ ቻይና ዘጠኝ ነጥብ ሁለት ሶስት ትሪሊየን ደላር ጂዲፒ አላት

እድገቱ ምን ያክል እንደሆነ መገመት ትችላላችሁ ከዚህም ባሻገር ቻይና ፍሪ ትሬድ ዞን ከመጀመሯ በፊት የፎር ኤንድ ዳይሬክት ኢንቨስትመንቷ ከሃምሳ ሚሊየን ዶላር በታች ነበር ዛሬ በብዙ ሚሊየን የፎር ኤንድ ዳይሬክት ኢንቨስትመንት ያላት ሀገር ናት ከኤክስፖርትም አንፃር ቢታይ በዚያ ጊዜ ዝቅተኛ ኤክስት ፖርት ካላቸው አገራት ተርታ ብትመደብም አሁን ከዓለም አንደኛው ኤክስፖርት የምታደርግ አገር ብቻ ሳይሆን በሁለት ሺ ሦስት(2003) ቻይና ወደ ዓለም ኤክስፖርት ያደረገችው አጠቃላይ ዓለም ተደምሮ ኤክስፖርት ካደረገው በሰባት እጥፍ ይበልጣል ይሄ ሁሉ ነገር የተገኘው እንደነዚህ አይነት ነገሮች ፈጥኖ መማር በመቻላቸው ነው በአፍሪካ ውስጥ መካከለኛው ምስራቅ ቀድመው የነቁና የጀመሩ አገራት አሉ እኛ በጠለቀ እንቅልፍ ውስጥ ሆነን ሳንጠቀምበት የቆየን ቢሆንም አሁን መጀመሩን እንደ መልካም ነገር ወስደን በተለይ ኢትዮጵያዊያን ኢንቨስተሮች ከኢትዮጵያ በላይ በጥልቅ እንቅልፍ ውስጥ ደሞ እናንተ ስላላችሁ መንቃት ያስፈልጋል ያደገች አገር ውስጥ ያለ ሀብታምና ደሀ አገር ውስጥ ያለ ሀብታም አንድ አይደለም ባደገ ሀገር ውስጥ ያለ ሀብታም የተከበረ የተፈራ በሄደበት ቅድሚያ የሚሰጠው ነው በደሀ አገር ውስጥ ያለ ሀብታም ግን ምን አልባት ከየት አመጣው በተብሎ ይጠየቃል እንጂ እንደ ሀብታም አይወሰድም እናንተ መንቃት ይኖርባችኋል እዚህ ስፍራ ውስጥ ሁሉም ኢንቨስት ማድረግ የሚፈልጉ ሀይሎች የተጋበዙ ቢሆንም ኢትዮጵያውያን ግን ያን ግን ሳትቀደሙ ተሸቀዳድማችሁ በኢንፖርትና በኤክስፖርት ስራዎቻችን ላይ እመርታ እንድናመጣ ከመንግስት ጐን ሆናችሁ መስራት ይኖርባችኋል፡፡

በዚህ ቀጣና ውስጥ የሚወጡ ህጐች በአጠቃላይ ኢትዮጵያ ውስጥ ካሉ ህጐች ቀለል ያሉ ናቸው በፋይናንሻል ስርዓቱ በከስተም ስርዓቱ በአብዛኛው ከቢሮክራሲ ጋር የሚያያዝ አሰራር የቀለጠፈ እንዲሆንና ቀለል ያለ እንዲሆን በመንግስት የሚሠራ ሲሆን እናንተም ቀደም ቀደም እያላችሁ አካባቢን የመጠቀም ኤክስፖርታችን የማሳደግ ኢንፖርታችንም ስርዓት ባለው መንገድ ሀገር በሚያሳድግ መንገድ እንዲሆን ማድረግ ይጠበቅባችኋል ይህ ስፍራ በፍጥነት የተሳካ ከሆነ በርከት ባሉት ቦታዎች መሰል የንግድና የኢኮኖሚክ ነፃ ቀጠናዎች ይከፈታሉ ይሄን የምናደርግበት ዋናው ምክንያት ብልፅግና እየመጣ ሲሄድ የፓራዳይም ለውጥ ያስፈልጋል በነበረው ሁኔታ መቀጠል አንችልም አንድ እናት ልጅ ወልዳ በስድስት ወሩ በአንድ አመት በሁለት አመት አዝላ መሄድ የምትችል ቢሆንም ልጁ ሃያ አምስት ሰላሳ ዓመት ከሞላው በኃላ ትላንት ያዘልኩት ያሳደኩት ልጅ ነውና ዛሬም ልዘለው ብትል አይሆንም እሷም

አርጅታለች እርሱም ጐርምሷል ማዘል የቻለችው ልጅ ሳለ ብቻ ነው ኢትዮጵያ አርባና ሃምሳ ሚሊየን ህዝብ ባለበት ሰዓት ተኝታም ቢሆን በኖረችበት መንገድ አሁን ከመቶ ሚሊየን በላይ ዜጐች ይዛ መቀጠል አትችልም መንቃት ያስፈልጋል አዳዲስ አሠራር መማር ያስፈልጋል የቀለጠፈ የአሰራር ሥርዓት መዘርጋት ያስፈልጋል በግብርና ባለፉት ሦስት ዓመታት በክቡር አቶ ዑመር ሁሴን አመራር እጅግ የተሳኩ ነገሮች ጀምረናል በግሪን፣ ሌጋሲ ፣በስንዴ ፣በፍሩት አሁን ደሞ በሻይ አበረታች ጅምሮች አሉ የጋሮ አትክልት ላይ የጓሮ እርሻ ላይ የከተማ እርሻ ላይ የጀመርነው ሥራ ከተሳካ እራሳችንን መመገብ ብቻ ሳይሆን ሽጠን ማትረፍ እንደምንችል ያመላክታል ነግር ግን ይሄ በቂ አይደለም ግብርና የማደግ ትሬንድ ሲያሳይ ፈጥነን ኢንደስቲሪውንና ሎጂስቲክሱን የማናስተሳስር ከሆነ ግብርና ተመልሶ ይሞታል በምዕራብ የአፍሪካ ሀገራት ብዙ ሐገራት ስንዴ ኤክስፖርት ያደርጉ ነበር ሴራሊዮን ለምዕራብ አፍሪካ ሀገራት ኤክስፖርት የማድረግ አቅም ነበራት ዛሬ ግን ኢንፖርት ታደርጋለች ስንዴ ማምረት ብቻውን በቂ አይደለም ስንዴ ተሸጦ ብር መሆን የሚችልበትን አሰራር መዘርጋትም ያስፈልጋልና የነፃ ንግድ ቀጠና እንዲጀመር የተፈለገው ዋናው ምክንያት የተቀላጠፈ ሎጆስቲክስ የንግድ ስርዓት የኤክስፖርት ኢንፖርት ስርዓት ካልዘረጋን በስተቀር በግብርና እየመጣ ያለው እድገት ተመልሶ ይቀለበሳል ለዚህ ደግሞ እያንዳንዱ ዜጋ መንቃት አለበት የበለፀገች ኢትዮጵያን ለልጆቹ ማውረስ የሚፈልግ ዜጋ ሁሉ በሥራ መትጋት በሥራ መተሳሰር እና አዳዲስ ትምህርቶችን መማር ይኖርበታል ግሪን ሌጋሲ የአራቱን ዓመት ዛሬ ዘግተናል ይህ ቦታ የግሪን ሌጋሲ አስፈላጊነት በእጅጉ ያሳያል ግቢው እንዳያችሁት ምንም እንኳን ስፍራው ሞቃት አካባቢ ቢሆንም ገነት እንዲመስል ያደረገው መሠረተ ልማት ዛፎች እና አጠቃላይ ኢንፍራስትራክቸር ነው ኢትዮጵያን እንደዚህ ነው ማየት የምንፈልገው ሁሉ ቦታ አስፋልት ያለበት ሁሉ ቦታ ዛፍ ያለበት ሰዎች ለመዳዝ የሚያስችል ምቹ ዎክ ወይ ያለበት ከዚያ በላይ ግን ፋንክሽናል ቤቶች ያሉበት እንዲዚህ አይነት የሚያማምሩ በስርዓት የተገነቡ ቤቶች ያሉበት ከሆነ ብልፅግና ማለት እሱ ነው ትንሿ ኢትዮጵያ የብልፅግና ምሳሌ ሆና ዛሬ ስለጀመረች ትልቋን ኢትዮጵያ በዚህ መንገድ መፍጥር ከቻልን ብልፅግናችን እውን ሆነ ማለት ነው፡፡

መላው የኢትዮጵያ ህዝብ ዛሬ በምናበስረው የግሪን ሌጋሲ በድል መከናወንና የነፃ ንግድ ቀጠና መከፈት መማር የሚገባን ነገር ክፉ ክፉ ዜናዎች ካንሰሮች ናቸው ክፉ ክፉ ወሬዎች ጐጂዎች ናቸው ጆሮአችን ለክፉ ዜና የተከፈተ መሆን የለበትም

ክፉ ዜና ተናጋሪውንም አድማጩንም ይገድላል ክፉ ነገር የሰማ ሰው ማታ ተኝቶ አያድርም ሲያብሰለስል ነው ኢሚያድረው በተቻለ መጠን ለራሳችሁ ጤንነት ስትሉ ክፉ ከሚያወሩ ሟርት ከሚናገሩ በክፉ ነገር ከተያዙ ሰዎች ልቃችሁ ችግን በመትከል አካባቢያችሁን በማፅዳት የጓሮ አትክልት በማልማት መልካም ነገር በማድረግ ነገር ግን የማይመች ጉዳይ ሲኖርም በጨዋ ደንብ በመገሰፅ ክሪቲ ሳይዝ ሂስ ማቅረብ ይቻላል ስልጡን ለብልፅግና የተነሳ ህዝብ ሆነን በጋራ እንድንቆም ኢትዮጵያን እንድናፀና ልጆቻችን የሚረከቡዋት አገር መልካም እንድንሆን ሁላችንም በምንችለው በምናውቀው ስፍራ የተሻለ ውጤት በማምጣት ጥረት እንድናደርግ አደራ እያልኩ ይህ የነፃ ንግድ ቀጠና አሁን ላለበት ደረጃ ባለፉት ሦስት ወራት አበክረው ለሰሩት ክብርት ወ/ሮ ዳግማዊት ሞገስ ክቡር አቶ ሳንዱቃን ደበበ እንዲሁም አቶ ሮባ እጅግ ከፍ ያለ ምስጋና ላቀርብላቸው እወዳለሁ ጀመርን ማለት ጨረስን ማለት አይደለም ባለፉት ሦስት ወራት በጥት ሰርታችሁ ዛሬ በዚህ መልኩ እንዲከፈት አድርጋችኃላ የዛሬ ሦስት ዓመት ጂዲፒያችን ላይ ኤክስፖርታችን ላይ የንግድ ስርዓታችን ላይ ለውጥ አምጥታችሁ በጋራ ለመገናኘት ያብቃን የምትጀምሩ ብቻ ሳይሆን አሳምራችሁ የምትጨርሱም እንዲያደርጋችሁ በጋራ መስራት እንድትለማመዱ መደመርን አበክራችሁ እንድትወዱና ለኢትዮጵያ ብልፅግና እንድትቆሙ አደራ እያልኩ ድሬዎች እንኳን ደስ ያላችሁ መልካም ጅማሮ ነው የበለጠ ያማረ ይሁንላችሁ።

**አመሰግናለሁ!**

ነሃሴ 8፤ 2014 ዓ.ም

# የሞጆ–ሀዋሳ የስንዴ ማሳ ጉብኝት

ከሞጆ ወደ ሀዋሳ የሚወስደው መንገድ ነው። በጣም በርካታ ሰዎች ወደ ሀዋሳ ሲነዱ የምናየው ደረቅ ቦታ አልፎ አልፎ የሚያማምሩ ዛፎች ዘርዘር ብለው የምናይበት አካባቢ ነው። አሁን ከሞጆ ጀምረን ወደዚህ ስንነዳ ግራ እና ቀኝ ያየነው አጠቃላይ አረንጓዴ መሆን ስንዴው፣ ሽንኩርቱ፣ አጠቃላይ ከግብርና ጋር የሚያያዘው ጉዳይ ገና አምርተን ምርቱን ካየን በኋላ የሚያመጣው ስኬት ሳይሆን ገበያ ላይ ብቻ የሚጠገብ ነው። አይንም ይጠግባል ሆድ ብቻ አይደለም። ይሄንን ማሳ በመንገድ ላይ ማየት እጅግ ተስፋ የሚያጭር ነገር ነው፣ ለኢትዮጵያዊያንም ከኢትዮጵያ እንጠቀማለን ብለው ለሚያስቡ ሀገራትም ጭምር የኛ ዋና አላማ አንደኛው በ"መ" ፊደል ነው ለመለየት እንዲቻል። በጣም በቀለለ መንገድ ለመለየት እንድንችል መራብ መራብ የሚል አሉታዊ ዜናዎች ይበዛሉ። ኢትዮጵያን በሚመለከት እኛ ደግሞ መብላት እንላለን። መብላት የሚያስችል መብራት፣ መብራት የሚያስችል ውሃ፣ መብላት የሚያስችል የሰው ኃይል ስላለን በምግብ ራሳችንን መመገብ የሚያስችል ፖቴንሻልም አለን፣ ማድረግም እንችላለን፣ ኢትዮጵያ ውስጥ መራብ የሚል ቋንቋ ብዙም ቦታ እንዳይኖረው ኢትዮጵያዊያን ማድረግ ይችላሉ በሚለው የመጀመሪያ "መ" መብላት፣ በምግብ ራሳችንን መቻል። በመቻል መራብ የሚለውን አሉታዊ ቃል ማጥፋት ይቻላል። የአማራ ክልልን የሚያክሉ፣ የኦሮሚያ ክልልን የሚያክሉ ክልሎች እንደ ሀገር ከህዝባቸው ቁጥር ሁለት ሶስት እጥፍ የሚመግቡ አሉ። በጣም ሰፊ ቦታ አለን፣ ቦታዎችን አልተጠቀምንበትም፣ የሰው ሃይል አልተጠቀምንም፣ ከሰራን በምግብ ራሳችንን መቻል በትብብር መንፈስ የጋራ አላማ አድርገን ከተንቀሳቀስን አይቸግረንም።

ሁለተኛው "መላክ" ነው እነሱ "ማስገባት" ይላሉ ሁሉን ነገር አስገቡ ይላሉ። እኛ ደግሞ ኤክስፖርት እናደርጋለን። መላክ አለብን እንላለን። በግብርና ምርትም፣ ከዛም ባለፈ በአንዳንድ መጠነኛ ወደ ኢንደስትሪ የገቡና ፕሮሰስ የተደረጉ ምርቶችም መላክ የሚያስችል አቅም ኢትዮጵያ አላት። ግብአት ብቻ ሳይሆን፤ ማስገባት ጣጣ አለበት። አብሮ የውጪ ምንዛሬ ይነሳል፣ ማስገባት ሲባል ደግሞ ለውጪ ምንዛሬው እጥረት

ምክንያት ስለሚሆን ፍለጋ፣ ብድር፣ እርዳታ የሚባል ጉዳይ ተያይዞ ይነሳል ማለት ነው።

ሶስተኛ "መስራት" ነው እነሱ መሰደድ ይላሉ። ስራ ስለሌለ መሰደድን ነው በኛ ላይ የሚያውጁት እኛ ደግሞ ሥራ ለመፍጠር የሚያስችል አውድ አለ፣ የፖሊሲ ግልጽነት አለን፣ መሬት አለን፣ ውሃ አለን የሚያጥረን የፋይናንስ እና ቴክኖሎጂ ነገሮች አሉ። እነሱን ደረጃ በደረጃ እያሟላን በሥራ አጥነት ላይ ያለውን ችግር በመቀነስ የሚሰደደውን እና በየ ባህሩ ላይ የሚሞተውን ሰው ማስቀረት ይቻላል። መስራት ከቻልን፣ መብላት ከቻልን፣ መላክ ከቻልን በተቃራኒው ያለው መራብ ከጠፋ፣ ማስገባት ከቀነሰ፣ መሰደድ ከቀረ በኢትዮጵያዊያን ሉአላዊነትና ክብር ላይ ቀጥተኛ የሆነ ኢምፓክት አለ።

አራተኛ "መልበስ" ነው። እኛ መልበስ ስንል እነሱ መራቆት ይላሉ። መልበስ የምንልበት ዋነኛው ምክንያት እኛ ኢትዮጵያዊያን እንደዛሬ ቴክኖሎጂ ባልነበረበት ዘመን በሸማ፣ በቆዳ ራሳቸውን አልብሰው፣ ኮትኩተው እና አልፎ አልፎም በበሬ አርሰው ራሳቸውን መግበው ክብራቸውን ጠብቀው የኖሩን ህዝቦች አሁን ትራክተር ባለበት ዘመን፣ ለመልበስ ፋብሪካ በተስፋፋበት ዘመን፣ ለመልበስም ከውጪ የምናስገባ ከሆነ ጥገኛ ያደርገናል። ለመብላት ተጠግተን፣ ለመልበስ ተጠግተን ከኖርን ከእርዳታ አንወጣም የሚረዳ ሀገር ደግሞ ሄዶ ሄዶ ክብሩ ሊጠበቅ አይችልም።

ledo calla ikikkini gobbate deerinni heedhanota haaro jireegnu ha'rinishora dancha guma laashateni,mimmitto anga amande yannasi garuni,wolqasi gatuna kattamu lopho aana,latishshu ledooshira,egenosinna woxesi invesitimentetena loosu kaayyo kalaqatte aana,e'o woyyabbeenna daganike hasidhanore hidhate woliqa lexxiteena jiregnu doogo suwisatenni dhage loonse daganno ilamara guma ikkino coye sayissate loonssani yanaati.

Kunni daafira budenna balichooma seekine anffo huwanto, anfoommohanna huwantoomoha loosu aana hosiinisso,hosiinseno kaajjilluni daggaa ilamara sayinisso!

April 28, 2022

# ከመስከረም እስከ መስከረም

## ክፍል ስድሰት - መልዕክቶች

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የጠቅላይ ሚኒስትር ጽሕፈት ቤት

# እንኳን ለ1496 ኛው የመውሊድ በዓል በሰላም አደረሳችሁ።

መውሊድ አላህ በነቢዩ መሐመድ (ሰ.ዐ.ወ) በኩል ለዓለም የሰጠውን በረከት የምናስብበት በዓል ነው። አንድን ነገር የምንጠብቀው፤ ጠብቀንም የምንጠቀምበት ምን እንዳገኘንና እንዴት እንዳገኘን በሚገባ ካወቅነው ብቻ ነው። ያገኘውን በትክክል ያላወቀ ሰው አዲስ ነገር ለማግኘት ሲል ያለውን ነገር ሲጥል ይኖራል። የመውሊድ በዓል ፈጣሪ ለሰው ልጆች ምን ሰጠን? ፈጣሪስ ከሰው ልጆች ምን ይፈልጋል? የሚለውን የምናስታውስበት፤ ይሄንንም በልዩ ልዩ መንገድ የምንገልጥበት በዓል ነው።

ፈጣሪ ማንም ከማይተካት ነፍስ ጀምሮ ለሰው ልጆች ብዙ ነገር ሰጥቷል። የፈጣሪን ስጦታ ከመዘርዘር ይልቅ አለመዘርዘሩ ይመረጣል። የትየለሌ ነውና። ይህ ስጦታ ግን ተሰጥቶ ብቻ የሚቀር አይደለም። የሰው ልጅም ለፈጣሪው የሚያደርገው ነገር አለ። እምነት ባለ ሁለት መንገድ በመሆኑ። ፍጡር ወደ ፈጣሪ – ፈጣሪ ወደ ፍጡር።የመውሊድን በዓል ስናከብር የሰው ልጆች ለሌሎች የሰው ልጆች እያደረጉ ያሉትን እዝነት ማስታወስ አለብን።

ነቢዩ መሐመድ (ሰ.ዐ.ወ) ያደረጉት ነገር ሁሉ ሌሎችን የሰው ልጆች ነጻ የሚያወጣ፣ የሚለውጥና ወደተሻለ ሕይወት የሚመራ ነው። ነቢዩን (ሰ.ዐ.ወ) በዚህ ዕለት የምናስታውሳቸው ከአላህ ተልከው ለሰው ልጆች በፈጸሙት መልካም የመልእክተኛነት አገልግሎታቸው ነው።

ሰው በምድር ላይ የሚፈለገውም፣ የሚታወሰውም በመልካም አገልግሎቱ ነው። የሰው ልጅ መልካም አገልግሎት ደግሞ መለኪያው ለሌሎች በተከፈለው የመሥዋዕትነት መጠን ነው። አገልግሎት ለራስ የሚሰጥ ስጦታ አይደለም። መሥዋዕትነት ተከፍሎም ቢሆን ለሌሎች የሚደረግ ነው። ሌሎችን ለመለወጥ፣ የሌሎችን ሕይወት ለማሻሻል፣ ሌሎችን ነጻ ለማውጣት የሚከፈል መሥዋዕትነት ነው።

መውሊድን የምናከብርበት ይህ ጊዜ የመውሊድን ዕሴቶች በእጅጉ የሚፈልግበት ጊዜ ነው። ለሌሎች የሚደረግን መልካም አገልግሎት ሀገራችን ትፈልጋለች። ወገኖቻችንን ነጻ ለማውጣት የሚከፈልን መሥዋዕትነት፣ የተፈናቀሉ ወገኖቻችንን ለመርዳትና ለማቋቋም የሚደረግን መሥዋዕትነት፣ ሀገራችን በርሀብ እንዳትጠቃ በየማሳው የሚደረግን መሥዋዕትነት፣ መልካም አገልግሎት ለሕዝቡ ለመስጠት በየቢሮው የሚደረግን መሥዋዕትነት፣ ሀገራችን በእጅጉ ትፈልጋለች።

መውሊድ የነቢዩ መሐመድን (ሰ.ዐ.ወ) መልካም አገልግሎት የምናስታውስበት ነው። ለሌሎች የተደረገና የተከፈለ መልካም አገልግሎት። ታሪክንና ማኅበረሰብን የለወጠ መልካም አገልግሎት። የሕዝብን አኗኗርና አስተሳሰብ የለወጠ መልካም አገልግሎት ይታሰብበታል።

አዲሱን መንግሥት በድምፁ ያመጣው ሕዝብና አዲሱን አስተዳደር የመሠረተው መንግሥት እነዚህ ነገሮች በእጅጉ ያስፈልጓቸዋል። ታሪክንና ማኅበረሰብን የሚለውጡ አገልግሎቶች። የሕዝብን አኗኗርና አስተሳሰብ የሚለውጡ አገልግሎቶች ያስፈልጉናል። ሀገራችን የገጠማትን ሦስት ፈተናዎች በቶሎ ፈትተን ወደምንፈልገው የብልጽግና ምእራፍ ለመድረስ ቁልፉ በመሥዋዕትነት የታሸ መልካም አገልግሎትን ዛሬውኑ ለመስጠት መቻል ነው። የሀገራችንን የውስጥ ጠላቶች በፍጥነት አሸንፈን የኢትዮጵያን ኃያልነት ማስፈን አለብን። በዲፕሎማሲው ረገድ የገጠመንን ፈተና እውነትንና ጥበብን ይዘን ማሸነፍ አለብን።

የሕዝባችንን የኑሮ ውድነት በላቀ የአመራር ክሂሎት መጀመሪያ ማሻሻል፣ ቀጥሎም መቅረፍ አለብን።እነዚህን ሦስት ፈተናዎች በድል ለመወጣት ሲቪሉም ሆነ ወታደሩ መሥዋዕትነት ያለበትን መልካም አገልግሎት መስጠት አለበት። ፈተናችን ሁለንተናዊ ነው። አገልግሎታችንም ሁለንተናዊ መሆን አለበት። እንዲሁ የሚተው ሸንቁር መኖር የለበትም። ይሄኛው አይጎዳንም፤ ይሄኛው ምንም አያመጣም፤ ይሄኛው የነ እንትና ነው፤ ይሄኛው ያልቅስ፣ ያኛው ይሙት፤ ያኛው ይፍረስ፣ ይሄኛው ይለቅ፣ ተብሎ የሚተው የሀገር ችግር መኖር የለበትም።

ሁለንተናዊ ሰላምና ብልጽግና የሚመጣው ሁሉንም ዓይነት ፈተናዎች እንደየመልካቸው በማሸነፍ ነው። አንዲት ትንሽ የሰውነት አካል እስከታመመች

ደረስ ጤነኛ ሰው መሆን አይቻልም። ሦስቱን ፈተናዎች ከመፍታት አንጻር ሦስቱ መንገዶች እንደየሁኔታው ጥቅም ላይ መዋል አለባቸው። ጦርነቶችን በአጭር ጊዜ ውስጥ በድል ማጠናቀቅ፤ ይቅርታንና አሳታፊ ውይይቶችን ማካሄድ፤ የኢኮኖሚ ፈተናዎቻችንን የሚፈቱ የማክሮና የማይክሮ ኢኮኖሚ ውሳኔዎችን ማሳለፍ። ለየትኛው ፈተና በመቼ ጊዜ የትኛውን መፍትሔ እንጠቀም? የሚለውን አመራሩ በላቀ ጥበብና ክሂሎት ከፍጥነት ጋር ተግባራዊ ማድረግ አለበት። ሕዝቡም ከችግሩ ጋር ሳይሆን ከመፍትሔው ጋር መቆም ይገባዋል።ኢትዮጵያ በፈተና ብቻ የተከበበች አይደለችም። ኢትዮጵያ በተስፋም ብቻ የታጀበች አይደለችም። የኢትዮጵያ ዕጣ ፈንታ በእነዚህ ሁለቱ ዕድሎች የሚወሰንም አይደለም።

የኢትዮጵያ ዕጣ ፈንታ የሚወሰነው እኛ ከሁለቱ ለየትኛው እየሠራን ነው? በሚለው ነው። ለተስፋዋ ከሠራን ተስፋዋ ያሸንፋል። ለፈተናዋ ከሠራን ፈተናዋ ይበረታል። ‹ብርሃን የሚመጣው ተሠርቶ ነው፤ ጨለማ ግን ብርሃን ባለመኖሩ ብቻ ሊመጣ ይችላል› ይባላል። ብርሃን የሥራ ጨለማ የስንፍና ውጤት ነው።

ተስፋ የሚገኘው በሥራ ነው። ፈተና ግን ተስፋ ባለመኖሩ ብቻ ሊመጣ ይችላል። ተስፋ የሥራ፣ ፈተና ግን የስንፍና ውጤት ሊሆን ይችላል።የምናስበው፣ የምናወራውና የምንሠራው በተስፋችን ላይ ከሆነ ተስፋው ዕውን ሆኖ የምናይበት ጊዜ ቅርብ ነው። የምናስበው፣ የምናወራውና የምንሠራው ስለ ፈተናችን ከሆነ ግን ፈተናችንን ጥልቅና ሩቅ ያደርገዋል። በመንገድ ላይ ስለገጠመው ነፋስና ፀሐይ የሚጨነቅ ሯጭ፣ ወደ ሜዳልያው የሚቀርብበትን ሰዓት ያስረዝመዋል።

ወደ ሜዳልያው መቅረቡን እያሰበ የሚሮጥ ሯጭ ግን፣ የገጠመውን ነፋስና ፀሐይ የሚቋቋምበት ዐቅም ከውስጡ ያገኛል። የዛሬውን የመውሊድ በዓል ስናከብር ‹በመሥዋዕትነት የታጀበ፤ ሕዝብን ሊለውጥ የሚችል መልካም አገልግሎት መስጠት› የሚለውን የመውሊድ ዋናውን ዕሴት በማሰብ እንዲሆን በድጋሚ ለማስታወስ እወዳለሁ። ይሄንን ዕሴት ሀገራችን ዛሬ በእጅጉ እንደምትፈልገውም ለማስታወስ እፈልጋለሁ።
በድጋሚ ለመላው ሕዝበ ሙስሊም፣ መልካም የመውሊድ በዓል ይሁን!!

**ኢትዮጵያ በልጆቿ ጥረት ታፍራና ተከብራ ለዘላለም ትኑር ! !**
**ፈጣሪ ኢትዮጵያና ሕዝቦቿን ይባርክ !** ጥቅምት 7፣ 2014 ዓ.ም

# ክብር ኢትዮጵያን ሲሉ ለተሠዉ ጀግኖቻችን

ኢትዮጵያ የጀግኖች ሀገር ናት፡፡ ልባም ልጆችዋ አጥር ሆነው የጋረዷት፣ ዋጋ ከፍለው ያደመቋት፣ ተቆጥሮ በማያልቅ መሥዋዕትነት ታፍራና ተከብራ የኖረች ሀገር ናት፡፡ የሩቁ ቢዘነጋን እንኳን፣ አምና ጥቅምት 24 ግፍ የተፈጸመባቸው ጀግኖቻችን ታሪክ ፈጽሞ የሚረሳ አይደለም፡፡

እያንዳንዳችን የጀግኖቹ ዕዳ አለብን፡፡ ዛሬ የቆምነው ለእኛ ሲሉ የግፍ ጽዋን በተጎነጩ ጀግኖቻችን አጥንት ላይ ነው፡፡ እነዚያ ብርቅዬ የኢትዮጵያ ልጆች "ከወገኔ በፊት እኔ ልቅደም" ብለው ደማቸውን ለአፈር፣ ሥጋቸውን ለአሞራ ባይሰጡ ኖሮ የዛሬው ቀን ዛሬን ባልመሰለ ነበር፡፡

የሰሜን ዕዝ ሠራዊት የተደራጀው ከአንድ አካባቢ አልነበረም፡፡ አማራና ኦሮሞው፣ ሲዳማና ወላይታው፣ አፋርና ጋምቤላው፣ ጉራጌና ሐድያው ከሁሉም ብሔር ተውጣጥቶ ሀገር እንዲጠብቅ የተደራጀ ሠራዊት ነበር፡፡
ሀገሬን ብሎ ለሃያ ዓመታት ከቤቱና ካሳደገው ቀዬ ተነጥሎ ዱር እያደረ ድንበር ሲጠብቅ ኖሯል፡፡ ሠራዊቱ ለትግራይ ክልልና ለሕዝቡ ከደግነት ውጭ ክፉ ሆኖ አያውቅም።

ጠላት ሲመጣ የሚመክት፣ አዝመራ ሲደርስ የሚያጭድ፣ በማኅበረሰባዊ ተግባራት ላይ የሚካፈል ነበር።

በደምና በላቡ ለከፈለው ደግነት በምላሹ ከሽብር ቡድኑ ሕወሐት የተቀበለው ክህደት ነው።

ኢትዮጵያን ለመውረር የመጡ ጠላቶች እንደ ሽብር ቡድኑ ዋነኛ የጦር ቤዛችንን በመደብደብ አልጀመሩም፡፡ ዋና ዋና መኮንኖችን በመግደልና ከባድ መሣሪያዎቻችንን

ዘርፈው አልተነሡም። የጦርነት ቅዱስ ባይኖርም ለጭካኔም ልክ አለው።

በሸብር ቡድኑ ልክ ኢትዮጵያ ላይ የጨከነ የለም፡፡ ጥቅምት 24 ሠራዊቱ ላይ የክህደት ጥቃት ሲፈጸም የሞቱት እነዚያ ጀግኖች ከመላው ኢትዮጵያ የተውጣጡ እንደመሆናቸው የተፈጸመባቸው ግፍ በኢትዮጵያ ላይ የተፈጸመ ግፍ ነው።

የሸብር ቡድኑ በሰሜን ዕዝ ላይ የፈጸመው ጥቃት መሣሪያ ለመዝረፍ ብቻ የተደረገ ተራ ጥቃት አልነበረም፡፡ በተንኮል የተቀመመና በክፋት የሞላ መሆኑ የተለየ ያደርገዋል፡፡ የገዛ ጓዶቹን አስኮብልሎ በተኛበት ከመግደል ባለፈ ከሬሳው ላይ ልብሱን ገፍፎ የአውሬ ቀለብ እንዲሆን እርቃኑን ሜዳ ላይ ጥሎታል። ይኼን ሲያደርግ የሸብር ቡድኑ ዓላማ ሁለት ነው፡፡ አንደኛ ሠራዊቱ በሐፍረት በትር እየተቀጣ ሞራሉ እንዲላሸቅና የአቅመ ቢስነት ስሜት እንዲሰማው፡፡ ሁለተኛ ሠራዊቱ እርስ በእርስ እንዳይተማመንና “ከፉና ደጉን አብሮ ከተካፈሉኝ ጓዶቼ እንደዚህ ዓይነት ነውር ዛሬ ከተፈጸሙብኝ ነገስ?” ብሎ እንዲጠራጠር ለማድረግ ታስቦ ነበር፡፡ ዳሩ ግን ሠራዊቱ እንደተጠበቀው አልሆነም፡፡

የወንድሞቹ ደም በከንቱ መፍሰስ ያንገበገበው ሠራዊት በፍጥነት ራሱን አደራጅቶ በሦስት ሳምንት ጊዜ ውስጥ የሸብር ቡድኑ ያደራጀውን ኃይል ወደ በርሃ እንዲበተን ማድረግ ችሏል፡፡

የቡድኑን ቁንጮ አመራሮች አብዛኞቹን ይዞ ለሕግ አስረክቧል፡፡የተፈጸመበትን ክህደት በበቀል ሐሳብ ሳይሆን የሕግ ማስከበር መርሕን በተከተለ መንገድ ሲያከናውን ነበር፡፡ በጦርነት ውስጥ ለመርሕ መገዛት ቀላል አይደለም፡፡ ሠራዊታችን ባለፈው አንድ ዓመት ውስጥ ከሸብር ቡድኑ ጋር አያሌ ውጊያዎችን ሲያደርግ ብዙ ዋጋ ከፍሏል፡፡ በየጦር ውሎው በጀግንነት እየተዋጋ ለእናት ሀገሩ ተሠውቷል፡፡

ለሀገርና ለወገን ያለውን አጋርነት በንግግር ሳይሆን በተግባር አሳይቷል፡፡ አሁንም በዱር በገደሉ እየተዋደቀ ነው፡፡

ዛሬ ሽብር ቡድኑ የተሰጠውን የጥሞና ጊዜ እንደ እድል ከመጠቀም ይልቅ እንደ ድል ወሰደው። በአማራና በአፋር ክልል በሚኖሩ ወገኖቻችን ላይ የግፍ በትሩን ቀጥሎበታል፡፡ የጥፋት አጋሩ ሸኔም በኦሮሚያ ክልል ወለጋ አካባቢ ልዩ ልዩ አደጋዎችን እየጣለ ኢትዮጵያና ኢትዮጵያውያንን ረፍት እየነሣ ነው፡፡

ሌሎችም የጥፋት ኃይሎች ከውስጥም ከውጭም ወኪሎቻቸውን አስተባብረው በሙሉ ዐቅማቸው ኢትዮጵያ ላይ መዝመታቸውን ገፍተውበታል፡፡

ሠራዊታችን ብቻውን ተጋፍጦ የድል ዜና እንዲያበስረን መጠበቅም ሞኝነት ነው፡፡ ጠላቶቻችን ተባብረው የደቀኑብን አደጋ ሁላችንም ተባብረን ካልመከትነው ድል የማይታሰብ ነው፡፡ የጠላቶቻችን ኅብረት ለፕሮፓጋንዳ የተፈበረከ ጉዳይ አይደለም፡፡ እውነት ነው፡፡ እነዚህ ኃይሎች ዓላማቸው ግልጽ ነው፡፡ ብረት ያነሡት ሀገር ለማፍረስ እንጂ ሀገር ለመገንባት አይደለም፡፡ የኢትዮጵያን ስም በክፉ የሚያብጠለጥሉ፣ ነገ የሊቢያና የሶርያን እጣ ሊያስታቅፉን እንዲመቻቸው የፈጠሩት ዘዴ መሆኑን ልናውቅ ይገባል፡፡

ጠላቶቻችን በዚህ ደረጃ ሲተባበሩብን እኛ አንድ የማንሆንበት ምንም ምክንያት የለም፡፡ የወንድምና የእኅቶቹ ጥቃት የሚያንገበግበው ሁሉ ጣት ከመጠቆም ወጥቶ ሀገር የማዳን ፍላጎቱን በተግባር መግለጥ አለበት፡፡

ወደፊት ታሪክ ፍርዱን ይሰጣል፡፡ ፈሪውም በፈሪነቱ፣ ሴረኛውም በሴረኛነቱ እንደየግብሩ ይመዘገባል፡፡ የሽብር ቡድኑን ትውልድ በክህደት ሲያስታውሳቸው እንደሚኖር ግልጽ ነው፡፡ በተቃራኒው በግፍ የተሠውት የሰሜን ዕዝ አባላትን ጨምሮ ለሀገር የሚዋደቁ ጀግኖች ስማቸው በወርቅ ይጻፋል፡፡

**ክብር ኢትዮጵያን ሲሉ ለተሠዉ ጀግኖቻችን!!**
**ኢትዮጵያ በልጆቿ ጥረት ታፍራና ተከብራ ለዘላለም ትኑር!!**
**ፈጣሪ ኢትዮጵያንና ሕዝቦቿን ይባርክ!**

ጥቅምት 24፣ 2014 ዓ.ም

# “ኢትዮጵያ” የሚለውን የነጻነት ስም የማስጠበቅ የታሪክ አደራ አለብን!

**ውድ የሀገሬ ልጆች፣**
**የተከበራችሁ የኢትዮጵያ ወዳጆች፣**

ኢትዮጵያ በልጆቿ ጀግንነትና መሥዋዕትነት ክብሯንና ነጻነቷን አስጠብቃ የኖረች ሀገር ናት። ይሄን ወዳጅም ጠላትም ያውቀዋል። ድንበሯን ሊደፍሩ የሞከሩ አይበገሬ ክንዷን አይተዋል። ሊያስገብሯት የቋመጡ አቀርቅረው ተመልሰዋል። ክህደት ለፈጸሙባት ተገቢውን ትምህርት መስጠት፣ ከጀርባ የወጓትን አይቀጡ ቅጣት መቅጣትን ታውቃለች። ለሺህ ዘመናት የተጎናጸፈችው ነጻነትና ሉዓላዊ ክብር በችሮታ የተገኘ አይደለም። ያለ ዋጋ ነጻነትን አጽንቶ መጠበቅ አይቻልምና፤ ኢትዮጵያ የሚለው የነጻነት ስም የደም ዋጋ ተከፍሎበታል፣ ብርቱ ጀግኖች ሞተውለታል።

በታሪክ የምናውቃቸው አባቶቻችው በአስተዳደርና በርእዮተ ዓለም ይለያያሉ፤ ለመብት፣ ለፍትሕና ለእኩልነት በነበራቸው አመለካከት ይለያያሉ። ለኢትዮጵያ የግዛት አንድነት፣ ነጻነትና ሉዓላዊነት ባላቸው ቦታ ግን ልዩነት አልነበራቸውም። በቋንቋ፣ በብሔርና በጎሳ ብዝኃነት ቢኖራቸውም የአልደፈርም-ባይ ቁራጥነታቸው አንድ ያደርጋቸዋል። የግል ፍላጎታቸው የቱንም ያህል የተራራቀ ቢሆን፣ የጋራ ጠላት ሲመጣ ኢትዮጵያዊነት ከግላዊነታቸው በላይ ይቀመጣል።

ድሮም ሆነ ዛሬ የእያንዳንዳችን ፍላጎት፣ የሁላችንም ሕይወት ከኢትዮጵያ በታች ነው። እኛ ኖረን ኢትዮጵያ ከምትሞት እኛ ሞተን ኢትዮጵያ እንድትኖር እንፈልጋለን። የሁላችንም የሆነች፣ ነጻነትና ፍትሕ የሰፈነባት፣ በገናናነቷና በነጻነቷ በዓለም አደባባይ የምትጠራ ሀገር እንድትኖረን ምኞታችን ነው። ለኢትዮጵያ ትልቅ በመመኘት፤ ሀገራችን አንገቷ ቀና እንዲል በመፈለግ፤ ባለፉት ሦስት ዓመታት ዐቅማችን የፈቀደውን ሁሉ አድርገናል። ፖለቲካችን ከመገዳደል ወደ መተጋገል እንዲቀየር ታግለናል።

ኢትዮጵያ የሁላችን ናት ብለን በሰው ሀገር የሚንከራተቱት ሁሉ እንዲገቡ ለማድረግ ሞክረናል። ካለፈው በጎውን ወስደን ጥፋቱን በይቅርታ ለማረም ተንቀሳቅሰናል። “በፍቅር እንደመር፣ በይቅርታ እንሻገር” ብለን አዲስ ምዕራፍ ከፍተናል። የመለያየትና የጥላቻን ግንብ አፍርሰን የመደመርና ኅብረ ብሔራዊ ወንድማማችነት ድልድይን ልንገነባ ቃል የገባነውን ወደ ተግባር ለመተርጎም ዐቅማችን የፈቀደውን አድርገናል። ኢኮኖሚው እንዲያገግምና መዋቅራዊ ለውጥ እንዲያመጣ፤ የዳኝነት ሥርዓታችን እንዲሻሻል፣ የሰብአዊ መብት አያያዛችን እንዲስተካከል፤ የውጭ ግንኙነት መርሖችን ጎረቤት ተኮር እንዲሆን ታግለናል። በዚህ መካከል እንደ ሰው በርትተናል። እንደ ሰውም ደክመናል። እንደሰው አልምተናል፣ እንደ ሰውም አጥፍተናል። በኢትዮጵያ ኅብረ ብሔራዊ አንድነት፣ በኢትዮጵያ ክብርና በኢትዮጵያ ታላቅነት ግን ለአፍታም አዘንብለን አናውቅም።

ኢትዮጵያ የምታጓጓ ሀገር ናት። ከትናንትናዋ ይልቅ ነገዋ ታላቅ ነው። መከራ ማለፍ ነባር ችሎታዋ ነው። ይሄንን የገጠመንን መከራም እናልፈዋለን። ኢትዮጵያ ማሸነፏ አይቀርም። አሁን ኢትዮጵያን ለመታደግ የመጨረሻውን ፍልሚያ የምናደርግበት ጊዜ ላይ ነን። ጠላቶቻችን በውጭና በውስጥ ተቀናጅተው ዘምተውብናል። በአንድ በኩል ታሪካዊ ጠላቶቻችን በራሷ ፈቃድና በራሷ መንገድ ብቻ የምታድግ ኢትዮጵያ ላለማየት የጥፋት በትር ሰንዝረዋል። ኢትዮጵያ አፍሪካዊ በሆነ መንገድ ከተነሣች፣ ተነሥታም ካሸነፈች፣ ከዚህ በኋላ ለማንም የማትመለስ ትሆናለች። ይሄን አፍሪካዊ መንገድ ለማደናቀፍ ሁሉንም ዓይነት የክፋት መሣሪያዎች አሰልፈዋል። የውጭና የውስጥ ጠላቶቻችን የእነርሱን ብርታት በኢትዮጵያ ድካም ላይ ለመገንባት ተነሥተዋል። የኢትዮጵያ ፍላጎት ይዞ ማለፍ እንጂ ጥሎ ማለፍ አልነበረም፤ ለዚህ ነው የውጭ ግንኙነት ፖሊሲያችን በዋናነት ጎረቤት ተኮር እንዲሆን ያደረግነው፤ ይህ ትግል የመላ ጥቁር ሕዝቦች ትግል ነው። ኢትዮጵያ አንበርክኮ ጥቁር ሕዝብን ለማሳፈርና አዲሱን የቅኝ ግዛት ቀንበር ለመጫን የሚደረግ ሤራ ነው።

ጥቁር ሕዝቦች የራሳችን ታሪክ፣ ባህል፣ ማንነትና ክብር እንዳይኖረን ሆን ተብሎ የሚደረግ አንገት የማስደፋት ትግል ነው። ይህ በኢትዮጵያ ላይ የተከፈተ ዘመቻ፣ ኢትዮጵያን በማንበርከክ ጥቁር ሕዝቦች የነጻነትና የአሸናፊነት አርአያ እንዳያገኙ የተከፈተ ዘመቻ መሆኑን ላስታውሳችሁ እወዳለሁ። ለጥቁር ሕዝብ ክብርና ልዕልና ስትሉ፣ በፓን አፍሪካ መንፈስ፣ ሁላችሁም ጥቁር ሕዝቦች፣ ከኢትዮጵያ ጋር

እንድትቆሙ ጥሪ አቀርብላችኋለሁ።
በመጨረሻም ይህ ትግል የሁሉም ኢትዮጵያዊ ትግል ነው። ልጆቻችን ሀገር እንዲኖራቸው የሚደረግ ትግል ነው። ልጆቻችን ክብርና ነጻነትን ለብሰው፣ በዓለም አደባባይ በኩራት ቀና ብለው እንዲሄዱ የሚደረግ ትግል ነው። በዓለም ላይ በክብር የምንጠራበት ስም እንዲኖረን የሚደረግ ትግል ነው። መኖር ወይም አለመኖራችንን የሚወስን ትግል ነው። ያለ ጥርጥር ግን እናሸንፋለን። ኢትዮጵያን ጠርቶ መሸነፍ ፈጽሞ የማይታሰብ ነው።

ጊዜው ሀገርን በመሥዋዕትነት መምራት የሚያስፈልግበት ጊዜ ነው። ከእንግዲህ እኔ መከላከያን በግንባር ሆኜ ለመምራት ከነገ ጅምሮ ወደ ትግሉ ሜዳ እዘምታለሁ። ታሪክ ከሚያደንቃቸው የኢትዮጵያ ልጆች አንዱ ለመሆን የምታስቡ ሁሉ ለሀገራችሁ ስትሉ ዛሬውኑ ተነሡ፤ ግንባር ላይ እንገናኝ፡፡ የእኛ መዝመት የሚፈጥረውን ክፍተት ከግንባር የቀሩት በሙሉ ዐቅማቸው ሸፍነው ይሠራሉ፡፡ በግንባር ያልተሰለፉ የክልልና የፌደራል አመራሮች ከመቼውም ጊዜ በላይ የልማትና አስተዳደር ሥራዎችን በሙሉ ዐቅማቸው ይከውናሉ።

ጎልማሶች በዘዴና በብልሃት አካባቢያቸውን እየጠበቁ፣ አረጋውያን እናትና አባቶች በጸሎት እየተጉ፣ ሁሉም ሰው ተባብሮ የኢትዮጵያን አሸናፊነት ያረጋግጣል። ከዚህ በኋላ በሩቁ ተቀምጠን ተቺና አራሚ የምንሆንበት ጊዜ አይደለም። መደረግ ያለበትን እኛው ራሳችን እናድርገው። ለኢትዮጵያ ከእኛ በላይ ከየትም አይመጣም። ኢትዮጵያ የሚለው ስም የአሸናፊዎች ስም ነው፤ የነጻነት ምልክት ነው። አልጠራጠርም፣ የእኔ ትውልድ ለአሸናፊ ስሙና ለነጻነት ምልክቱ የሚጠበቅበትን ዋጋ ከፍሎ ኢትዮጵያንና ኢትዮጵያዊነትን በክብር መዝገብ ላይ በወርቅ ብዕር ያትማል።

**አመሰግናለሁ ! !**
**ኢትዮጵያ በልጆቿ ጥረት ታፍራና ተከብራ ለዘላለም ትኑር!!**
**ፈጣሪ ኢትዮጵያና ሕዝቦቿን ይባርክ!**
ኅዳር 13፣ 2014 ዓ.ም

# “በድል የታጀበው የመጀመሪያው ምእራፍ”

**ውድ የሀገሬ ልጆች፣**

**የተከበራችሁ የኢትዮጵያ ወዳጆች፣**

ኢትዮጵያ በጀግኖች ልጆቿ ትከበራለች፤ ትታፈራለች። ኢትዮጵያን መገዳደር ይሞከር ይሆናል። ተገዳድሮ ማሸነፍ ግን ትናንትም አልተቻለም፤ ዛሬም አይሆንም፤ ነገም አይቻልም። ኢትዮጵያ የሚለው ስም ሁሌም ከአሸናፊነት ጋር የተያያዘ ነው።

ከጥቂት ጊዜያት በፊት ኢትዮጵያን ሊወጋ የተነሳውን ጠላት በጋራ ሆነን እንድንመክት ጦር ግንባር ላይ የያዝነው ቀጠሮ ጠላትን አንገት ሲያስደፋ ኢትዮጵያን ቀና አድርጓታል። ሀገራችን ታፍራና ተከብራ እንድትኖር ለማድረግ በጦር ግንባር እየተከፈለ ያለው መስዕዋትነት የኢትዮጵያን የአሸናፊነት ስም የሚመልስ መሆኑን እያበሰርኩ፣ ያቀረብኩትን ጥሪ ተቀብላችሁ ሕይወታችሁን፣ ጉልበታችሁን፣ ሀብታችሁን፣ ዕውቀታችሁን፣ ጊዜያችሁንና ሞያችሁን ለሠጣችሁ ሁሉ በኢትዮጵያ ስም ላመሰግናችሁ እወዳለሁ።

በዚሁ አጋጣሚ፣ የመጀመሪያውን ምእራፍ አጠናቅቄ ለተወሰኑ ጊዜያት ወደ ቢሮ መመለሴን እየገለጽኩ፣ ዛሬም ሆነ ወደፊት ጠላቶቻችን ጉልበታቸው ዝሎ፣ የጥላቻና የጠበኝነትን መንገድ ጥለው፣ የፍቅርና የሰላምን መንገድ እስኪመርጡ ትግላችን ይቀጥላል።የእኛ ፍላጎት ሁሌም ሰላምና ፍቅር ነው።

ኢትዮጵያ ሕብረ ብሔራዊ አንድነቷ ተጠብቆ የብልጽግና ጉዞዋ የተቃና እንዲሆን ያለንን ፍላጎት ከጅምሩ አሳውቀን ለተግባራዊነቱ ስንተጋ ቆይተናል። ነገር ግን በተደጋጋሚ ያቀረብነውን የሰላም አማራጭ ባለመቀበል፤ አሳታፊና አካታች

የሆነውን አዲሱን የፖለቲካ ባህላችንን ረግጦ በመውጣት፤ ጥፋትንና እልቂትን ለማስቀረት ሲባል የተደረገውን ትዕግሥት ከቁብ ባለመቁጠር፤ የአንዳንድ የውጭ ጠላቶችን አፍና ድጋፍ በመተማመን፤ አሸባሪው ሕወሓት ከግብር አምሳሎቹ ጋር ሆኖ በሀገራችን ላይ አደጋ ደቅኖ ነበር።

ነገሮች ያለቁና የተጠናቀቁ እስኪመስሉ ድረስ ኢትዮጵያን የማያውቁ ሁሉ በሥጋትና በፍርሐት ተውጠው ነበር። ሠግተው ሊያሠጉን፤ ፈርተው ሊያስፈራሩን የሞከሩ የውስጥና የውጭ አካላትም ነበሩ። ልጣችን የተራሰ፣ ጉድጓዳችን የተማሰ መስሎ የተሰማቸው ነበሩ። የኢትዮጵያን የአሸናፊነት ምሥጢር የሚያውቁት ብቻ በጽናት እስከ መጨረሻው የቆሙበት አጋጣሚም ተፈጥሮ ነበር።

ወደ ትግል የገባነው ሐቅን ይዘን ነውና የኢትዮጵያ አምላክ እንደ ወትሮው ከእኛ ጋር ነበር። ድካማችንን አበርትቷል። ሕዝባችንን ከዳር እስከ ዳር አነቃንቋል። የሠራዊታችንን ቁጥርና ዐቅም ጨምሮልናል። ልባችንን አጀግኖ የኢትዮጵያን አሸናፊነት በዓይናችን አሳይቶናል። ውድቀታችንን ሲመኙ የነበሩትን ሁሉ አሳፍሮ ዳግም የኢትዮጵያን ስም በወርቅ ቀለም እንድንጽፍ አስችሎናል። የዚህ ታሪክ አካል ለመሆን ፈጣሪ ዕድሉን የሰጣችሁ ሁሉ እንኳን ደስ አላችሁ። የኢትዮጵያን ስም ከማድመቅ የበለጠ ዕድል የለምና!!

በዕቅዳችን መሠረት የመጀመሪያውን ምዕራፍ፣ "ዘመቻ ለኅብረ ብሔራዊ አንድነትን" በሁለት ሣምንት ውስጥ አሳክተናል። የመከላከያ ሠራዊት፣ የየክልሎቹ ልዩ ኃይሎች፣ የፌዴራል ፖሊስ አባላት እና የየአካባቢዎቹ ሚሊሻዎችና ታጣቂዎች በከፈላችሁት መሥዋዕትነት ለልጆቻችን የምንነግረው ድንቅ ታሪክ ሠርታችኋል። በሁሉም መስክ በደጀንነት የተሰለፋችሁ ሁሉ የኢትዮጵያ ውድ ሀብቶች መሆናችሁን በዓይናችሁ አይታችኋል።

ትግሉ ገና አልተጠናቀቀም። ነጻ ያልወጡ አካባቢዎች አሉን። አሁን የፈተነን ኃይል ዳግመኛ የኢትዮጵያ ፈተና ሆኖ እንዳይመጣ የሚያስችል ዘላቂ መፍትሔ ልንሰጠው ይገባል። ለዚህኛው ችግር በምንሰጠው መፍትሔ ወደፊት ለክፉ ያሰቡን ሁሉ እጃቸውን እንዲሰበስቡ ማድረግ አለብን። ላለፈው የምናመሰግንበት እንጂ ጨርሰናል ብለን እፎይ የምንልበት ወቅት ላይ አይደለንም።

የተበተነው ጠላት እንዲማረክ ማድረግ አለብን። አካባቢያችንን ከበፊቱ በበለጠ ነቅተን የመጠበቂያ ጊዜው አሁን ነው። ፍተሻና አሰሳዎችን አጠንክረን መቀጠል ይገባናል። ጠላት ያፈረሰውን መልሰን መገንባት፣ የተፈናቀሉትን መመለስ፣ የልማትና የመልካም አስተዳደር ሥራዎቻችንንም ከበፊቱ በበለጠና በፈጠነ መንገድ ማሳለጥ ይጠበቅብናል።

ለሠራዊታችን የምንሰጠውን ሁለንተናዊ ድጋፍ በዓይነትም በብዛትም አጠናክረን የምንቀጥልበት ወቅት ነው። ያልዘመቱ ወገኖች ግማሽ ያህል ጊዜና ጉልበታቸውን ለዘማች ቤተሰቦች መስጠት ይጠበቅባቸዋል፤ እነሱ ለእኛ ሕይወታቸውን ሲገብሩ እኛ ለእነሱ ገንዘብና ጉልበታችንን መስጠታችን ቢያንስ እንጂ አይበዛም። እናም በተገኘው አጋጣሚ ሁሉ የዘማች ቤተሰቦችን መደገፍና ማበርታት አለብን።

ትግሉ በጦር ግንባር ብቻ አይደለም፤ በሁሉም መስክ መፋለም ይገባናል። የገበሬውን እህል አንዲት ፍሬ እንዳትባክን አድገን ወገባችን አሥረን መሰብሰብ አለብን። በዲፕሎማሲውና በፖለቲካው ዘርፍ የምንሠራቸውን ሥራዎች በአዳዲስ መንገዶች እያከናወንን መቀጠል ይገባል። ወጭ ቆጥበን፣ ጊዜና ጉልበት ጨምረን፣ ለሀገራችን ታይቶ በማይታወቅ ሁኔታ መሥራት ከእያንዳንዳችን ይጠበቃል።

በተለይ በተለይ በህልውና ዘመቻው ወቅት ያየነውን የኢትዮጵያውያንን አንድነት እስከ ዓለም ፍጻሜ ሀብታችን አድርገነው መቀጠል አለብን። በገጠርና በከተማ፣ በሀገር ቤትና በውጭ፣ በግንባርና በደጀን፣ ያለን ሁላችን ለአንድ ዓላማ ተሰልፈን አንድ ግብ እያሳካን ነው። ማንም ተነስቶ ኢትዮጵያን ማውረድ ከማይችልበት ማማ ላይ እየሰቀልናት ነው። ይህ አንድነታችን እንዲዘልቅ ከፋፋይ ሐሳቦችን እንመክት። የድል አጥቢያ አርበኞችን እንቃወም። በተጋድሏችን ያገኘነውን ነገር ለማቅለል የሚፈልጉትን ፊት እንንሣቸው። በጋራ ታግለን በጋራ ያስገኘነውን ድል፣ እንደ ቅርጫ ሥጋ ሊመድቡ የሚነሡትን አቃራጮች እናነውራቸው። ያሸነፈችው ኢትዮጵያ ናት። ከዚህ የወረደ ነገር አንቀበልም።

የገጠመን ፈተና ብዙ መከራና ችግር ያስከተለብን ቢሆንም በምንም መንገድ የማናገኛቸውን ዕድሎችም ይዞልን መጥቷል። ከገጠመን ፈተና ይልቅ በዕድሎቻችን

ላይ አተኩረን ከሠራን ኢትዮጵያን ኃያልና ራሷን በሁሉም መስክ የቻለች ሀገር እናደርጋታለን። ከፈጣሪ ቀጥሎ በፈተናችን ጊዜ አብረውን ለቆሙ እና በዓለም አደባባይ ለተሟገቱልን ሁሉ ኢትዮጵያ ከፍ ያለ ምስጋና ታቀርባለች። የጀመርነው ህልውናችንን የማስከበርና ኢትዮጵያን በጽኑ መሠረት ላይ የመትከል ተጋድሏችንን በፍጥነት አጠናቅቀን ወደ ብልጽግና አጀንዳችን በሙሉ ጉልበት በቅርቡ እንደምንመለስ እምነቴ ነው።

**ኢትዮጵያ በልጆቿ ጥረት ታፍራና ተከብራ ለዘላለም ትኑር!!**
**ፈጣሪ ኢትዮጵያንና ሕዝቦቿን ይባርክ!**

# በወቅታዊ ጉዳዮች ላይ የተሰጠ መግለጫ

“ውሳኔዎቻችን በስሜት የሚወሰኑ ሳይሆን ዘላቂ ጥቅምን ያገናዘቡ ናቸው!”

በዘመቻ ለኅብረ ብሔራዊ አንድነት የተጀመረው ማጥቃት አሸባሪውን ሕወሐት ከአማራና ከአፋር ክልሎች በማስወጣት የመጀመሪያውን ግብ አሳክቷል። መንግሥትም የመከላከያ ሠራዊቱ አሁን በያዛቸው አካባቢዎች ላይ እንዲቆይ ትእዛዝ ሰጥቷል፤ ይሄንን ውሳኔ የወሰንነው በስሜት ሳይሆን የሚያስገኘውን ዘላቂ ጥቅም ከግምት አስገብተን ነው። ኢትዮጵያን ዘላቂነት ባለድል የማያደርግ አካሄድ ሁሉ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ለጠላቶቻችን ብርታትን የሚፈጥር፣ የሽብር ቡድኖች እድሜያቸውን የሚያረዝሙበትን ሰበብ እንዲያገኙ መፍቀድ ነው። አለፍ ሲልም በስሜት የሚወሰኑ ወታደራዊ ውሳኔዎች ሀገራችንን በተራዘመ ጦርነት አዙሪት ውስጥ እንድትዘፈቅ ያደርጋል።

ኢትዮጵያን ለማዳከም የተከፈተው ዘመቻ መልከ ብዙ ነው። የሕልውና አደጋው በግልጽ ብቻ አይደለም በስውርም ይፈጸማል። ወታደራዊ፣ ዲፕሎማሲያዊ፣ ኢኮኖሚያዊና የመረጃ ጦርነቶች የሚካሄዱብን በተቀናጀና በረቀቀ መልኩ ነው። እኛ እየመከትን ያለነው ውጊያውን ብቻ ሳይሆን ዘመቻውን ጭምር ነው። የዘመቻው ግንባሮችም ብዙዎች ናቸው። አንዳንዶቹ ፊት ለፊት የሚፈጸሙ ሲሆን፣ አንዳንዶቹም በወጥመድ መልክ የሚከወኑ ናቸው። መንግሥት በኢትዮጵያ ሉዓላዊነትና ህልውና ላይ የተከፈተውን ግልጽና ረቂቅ ዘመቻ ለመመከትና ለመቀልበስ ብሎም በዘላቂነት የኢትዮጵያን አሸናፊነት ለማረጋገጥ የነደፈው ዕቅድ ሁለገብና ሁሉንም ግንባሮች ለመመከት የሚያስችል ስልት ነው።

በሰሜኑ የሀገራችን ክፍል ችግር መከሠት የጀመረው ለውጡን ተከትሎ መሆኑን ሕዝባችን ያውቃል። “እኔ ብቻ የማልገዛት ኢትዮጵያ መፍረስ አለባት” ብሎ የሚያምነው ሕወሐት ክልሉን ምሽግ አድርጎ ችግር መፍጠር የጀመረው በለውጡ

መባቻ ነበር። መንግሥት ሰብአዊና ቁሳዊ ጉዳት እንዳይፈጠር፣ የሕዝብ ሰላምና ደኅንነት እንዳይደፈርስና በኢኮኖሚው ላይ ከባድ ጫና እንዳይደርስ በማሰብ ችግሮችን በሰላማዊ መንገድ ለመፍታት ተሞክሮ ነበር። አሸባሪው ሕወሐት ግን ከጥፋት መንገድ በቀር ሰላማዊ መንገድ የማይታየው ሆነ።

በኢትዮጵያና በኤርትራ መካከል የተፈጠረውን ሰላም መነሻ በማድረግ፣ በሌሎች አካባቢዎች ያለውንም የሥጋት ደረጃ በመመርመር፣ ሠራዊታችንን ከኢትዮ ኤርትራ ድንበር ወደ ሌሎች የሀገሪቱ አካባቢዎች ለማንቀሳቀስ ስንሞክር፣ በትግራይ ሕዝብ ውስጥ መሸጎ የሚገኘው አሸባሪው የሕወሐት ቡድን፣ ሕጻናትን መንገድ ላይ እያስተኛ፣ አረጋውያንንም እንዲለምኑ እያደረገ፣ ሠራዊቱ ከትግራይ እንዳይወጣ ማድረጉ ይታወሳል። ይሄንን በሕዝብ ጥያቄ የተሸፈነ እኩይ ተግባር በአንድ በኩል እያከናወነ በሌላ በኩል ደግሞ ኢትዮጵያን ለመውረር ከሚፈልጉ የውጭ ኃይሎች ጋር በምሥጢር ይደራደር ነበር።

ኢትዮጵያን ለመውጋት ከውጭ ኃይሎች ጋር ያደረጉትን ስምምነት ተግባራዊ ለማድረግ ሲሉ፣ በሕዝቡ ልመና በትግራይ የቆየውንና ሕዝቡን በደሙና በላቡ ሲያገለግል የኖረውን ሰሜን ዕዝን በግፍ መሣሪያውን ለመንጠቅ ዘግናኝ ጥቃት ሰነዘሩ። የሀገር የመጨረሻው ደጀን በሆነው የመከላከያ ሠራዊት ላይ የሚፈጸም ማንኛውም ጥቃት የሉዓላዊነትና የህልውና ጥቃት ነው። የአሸባሪው ሕወሐት ዋና ዓላማም የሰሜን ዕዝ የታጠቃቸውን ትጥቆችና ስንቆች በመንጠቅ ኢትዮጵያን ለመውረርና ለማፈራረስ ነበር። ይሄንንም ከውጭ ጠላቶቻችን ጋር መክሮና ተቀናጅቶ ያደረገው ነበር። የዛሬ ዓመት በጥቅምት መጨረሻ፣ የመከላከያ ሠራዊት በወሰደው አፋጣኝ የማጥቃት ርምጃ ጁንታው ተሸንፎ ወደ ተንቤን በረሐ ፈርጥጦ ነበር። በዚህ የህልውናና ሕግ የማስከበር ዘመቻ የተነጠቅናቸውን መሣሪዎያችና የተማረኩብንን የሠራዊት አባላት አስመልሰናል። ከሽብር ቡድኑ ከፍተኛ አመራሮች የተወሰኑ ወንጀለኞችን ለሕግ እንዲቀርቡ ማድረግ የቻልን ሲሆን አሻፈረኝ ያሉትም እርምጃ ተወስዶባቸዋል።

ሠራዊታችን በትግራይ ሕዝብ ጥያቄ መሠረት ለስምንት ወራት በክልሉ ቆይቷል። በቆይታውም ኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊና ማኅበራዊ አገልግሎቶች እንዲቀላጠፉ መሥዋዕትነት ከፍሏል። መሠረተ ልማቶች እንደገና እንዲገነቡ፣ የሕዝብ አገልግሎቶች

ሥራ እንዲጀምሩ፣ ሰብአዊ እርዳታዎች በተሻለ ሁኔታ ተደራሽ እንዲሆኑ የሚቻለውን ሁሉ አደርጓል። ይኼን በሚያደርግበት ወቅት ሠራዊታችን በሁለት በኩል ዋጋ ሲከፍል ነበር። አንደኛ በዚያ የነበረው ቆይታ በጠላት ፕሮፓጋንዳና የጠላትን ፕሮፓጋንዳ በሚያስተጋቡ የውጭ ሚዲያዎች ያለ ስሙ ስም ተሰጥቶታል። ሁለተኛ የፕሮፓጋንዳ ሰለባ በሆነው የክልሉ ማኅበረሰብ ከጀርባ ለመውጋት ተገደደ።

ሠራዊታችን ደም ከፍሎ በሰጠው አገልግሎት የተረፈው ወቀሳና መጥፎ ስም ሆነ። ለሰብዓዊ ተግባራትና ለመልሶ ግንባታ ከ100 ቢልዮን ብር በላይ ማውጣታችን ከምን ሳይቆጠር አስተዳደሩና የጸጥታ ኃይሉ ባልዋለበት መወቀስ ጀመረ። የትግራይ ገበሬም በአንበጣ ምክንያት የተጓጎለበት የእርሻ ሥራ በጦርነቱ ምክንያት ዳግም ስለተጎዳበት ፋታ ማግኘት ያለበት ደረጃ ላይ ደረሰ። ይሄንን ከግምት ውስጥ በማስገባትም መንግሥት በሰብአዊነት ላይ የተመሠረተ የተኩስ አቁም ስምምነት አድርጎ የመከላከያ ሠራዊቱን ከትግራይ ክልል የማስወጣት ውሳኔ ሊተላለፍ ቻለ።

አሸባሪው ሕወሐትና አንዳንድ ዓለም አቀፍ አጋሮቹ ግን ሠራዊታችን ለሰብአዊነት ብሎ ከትግራይ መውጣቱን እንደ መሸነፍ ሲቆጥሩት ተስተውለዋል። በስምንት ወራት መታከት ውስጥ የቆየው ሠራዊታችን ፋታ ሳያገኝ ማዳከም ስለተፈለገ፣ ከአምስት መቶ ዓመታት በፊት በቀረ የሕዝብ ማዕበል የጦር ስልት አሸባሪው ቡድን ዳግም የማጥቃት እርምጃውን ጀመረ። ይሄንን ወረራ ለመቀልበስ እንዲቻል፣ ለዝግጅት በቂ ጊዜ ወስደን፣ የአመራር ጥበብን፣ የተቀናጀ ዕቅድንና ቴክኖሎጂን በመጠቀም፣ የደረሰብንን ወረራ ስንከላከል ቆይተን የጥፋት እርምጃውን ቀልብሰነዋል። ጠላት ከወረራቸው አካባቢዎችም ተጠራርጎ ወጥቷል።

መንግሥት ህልውና የማስከበር ዘመቻው ባለ ብዙ መልክ መሆኑን ዐውቆ ለሁሉም ግንባር የሚሆን በቂ ዝግጅት አድርጓል። ህልውናችንንና ሉዓላዊነታችንን የምናስከብርበት ሜዳ የጦር ሜዳው ብቻ አይደለም። ከወታደራዊ ዘመቻው ጋር አብረው ልንዘምትባቸው የሚገቡ ሌሎችም ሜዳዎች አሉ። መንግሥት የሚወስናቸው ውሳኔዎች ሁሉንም ግንባሮች መሠረት ያደረጉ እንጂ በተናጠል እይታ የታጠሩ አይደሉም። የመጀመሪያው ዕቅዳችን አሸባሪውን ቡድን ከአፋርና ከአማራ አካባቢዎች ሙሉ በሙሉ ማጽዳት ነው። ይሄንንም መቶ በመቶ ሊባል በሚችል መልኩ አሳክተናል። ሠራዊታችንንም ስትራቴጂያዊ በሆኑ ቦታዎች እንዲሠፍር

በማድረግ የጠላትን እንቅስቃሴ በአንክሮ እንዲከታተል አድርገናል።

ይሄንን እንድንወስን ያደረጉን ብዙ ምክንያቶች አሉ። አንደኛ የግዛት አንድነታችንና ሉዓላዊነታችነን የሚያሠጋ ነገር ከገጠመን በማንኛውም ጊዜና ሁኔታ ወደ ትግራይ ክልል ገብቶ የሀገርን ደኅንነት ለማስከበር የመከላከያ ሠራዊቱ ሕገ መንግሥታዊ መብት ብቻ ሳይሆን ግዴታም አለበት። በሌላም በኩል ሕወሐትና አፈ ቀላጤዎቹ መንግሥትንና ሠራዊቱን ለመክሰስ ወደ አዘጋጁት የሤራ ወጥመድ መግባት እንደሌለብን እናምናለን። በዚህ ወቅት የእኛ ወደ ክልሉ መግባት ከጥቅሙ ጉዳቱ ነው የሚያመዝነው። የትግራይ እናቶች ይሄንን ሁሉ ምስቅልቅል ያመጣባቸውንና ልጆቻቸውን ነጥቆ ያስጨረሰባቸውን አሸባሪ ኃይል መጠየቅ አለባቸው። ሌላው የኢትዮጵያ ሕዝብ ይሄንን አሸባሪ ከጫንቃው ላይ ያስወገደው በመራራ ትግሉ ነው። የትግራይ ሕዝብም እንደ ሌላው የኢትዮጵያ ሕዝብ ሁሉ ይሄንን አሸባሪ ታግሎ የማስወገድ አቅምና ችሎታው አለው። ድጋፍና እርዳታ በአስፈለገ ጊዜም የተቀረው የኢትዮጵያ ሕዝብና መንግሥት ከክልሉ ሕዝብ ጎን ይቆማል።

የማንኛውም ውሳኔያችን መርሕ ኢትዮጵያን ሁለንተናዊ ድል እንድትጎናጸፍ ማስቻል ነው፤ ግዛታዊ አንድነታችን የሚጠበቅበትና በዘላቂነት ኢትዮጵያ አሸናፊ የምትሆንበትን መንገድ መቀየስ ነው። ከእንግዲህ አሸባሪው ኃይል በቃዣ ቁጥር የፈለገውን የሚያደርግበት ሁኔታ የለም። የለም ስንል አይፈልግም ወይም አይሞክርም ማለታችን አይደለም። ነገር ግን እንደ ከዚህ በፊቱ አንድነታችን ጠብቀን እስከቆምን ድረስ መቼም ቢሆን ኢትዮጵያ አትሸነፍም፡፡ የኢትዮጵያ ድል መሠረቱ የጠላት ድክመት ሳይሆን የእኛ ብርታትና ትብብር መሆኑን አውቀን፣ ይበልጥ አንድነታችንን አጠንክረን መቆም ይገባናል፡፡

**ኢትዮጵያ በልጆቿ ጥረት ታፍራና ተከብራ ለዘላለም ትኑር!!**
**ፈጣሪ ኢትዮጵያና ሕዝቦቿን ይባርክ!**

ታህሳስ 15፣ 2014 ዓ.ም

# ወደሀገር ቤት ጥሪን ተከትሎ ለመጡ እንግዶች የተላለፈ መልእክት

የሀገር ልጅነታችሁን እንድታሳዩ ለቀረበላችሁ ጥሪ ምላሽ በመስጠት ወደ ሀገር ቤት የመጣችሁ ወንድም እህቶቼ አንኳን ደህና መጣችሁ!
ሀገር በአንድ ግዙፍ ቤተሰብ ሊመሰል ይችላል።

አንድ ቤተሰብ የቆመበት መሠረት ጥንካሬ የሚታወቀው ከደስታ ጊዜያት ይልቅ ቤተሰቡ ችግር በገባው ወቅት ነው። የፈተና መብዛት አንዳንዱን ቤተሰብ ሲያቀራርበው አንዳንዱን ያራርቀዋል፣ ደካማ መሠረት ያለው ቤተሰብ ውስጥ አደጋ ሲከሰት በቤተሰቡ አባላት መካከል ልዩነቶች አፍጥጠው ይታያሉ፣ ቅሬታዎች ከተደበቁበት ይወጣሉ፤ መቀሳሰር ይበዛል፤ ልጆች ፈተናውን ተጋግዘው በጋራ ከማለፍ ይልቅ "ምን አገባኝ" ሲሉ ይደመጣሉ። የዚያ ቤተሰብ እጣ ፈንታም በመጨረሻ መፍረስ ይሆናል።

በተቃራኒው ጠንካራ መሠረት ላይ ለቆመ ቤተሰብ የፈተና መምጣት አንድነቱን ያጠናክራል እንጂ አያላላውም። ልዩነቶች ቢኖሩ እንኳን ለጊዜው ወደ ጎን ተብለው የቤተሰቡ አባላት ሙሉ ትኩረት ፈተናው ወደሚታለፍበት መንገድ ያነጣራል። ሁሉም እንደ አቅሙ የቻለውን ይታገላል። መውደቅ መነሳቱን እኩል ተካፍለው በመጨረሻ ችግሩ ሲታለፍ ሁሉም እኩል ደስተኛ ይሆናሉ። ይኼ ወቅት ለኢትዮጵያ እንደ ሀገር በእጀጉ የተፈተነችበት ጊዜ ነው። ፈታኞቿ ተባብረው ረፍት ሊነሷት ያልፈነቀሉት ቋጥኝ፣ ያልወረወሩት ድንጋይ የለም።

ኢትዮጵያ ግን በልጆቿ ትብብር አሁንም ጸንታ ቆማለች። የፈተና መብዛት የልጆቿን አንድነት አጎለበተው እንጂ አልሸረሸረውም። አቅሞቿን አስተባብራ እንድትጠቀም ምክንያት ሆናት እንጂ አላሸነፋትም። በመላው ዓለም የሚገኙ ኢትዮጵያውያን ዳያስፖራዎች ሀገራችን ሰው በፈለገችበት ጊዜ ለሀገራቸው የቁርጥ ቀን ልጆች መሆናቸውን አስመስከረዋል ብለን በድፍረት መናገር እንችላለን። አንዳንዶች ኢትዮጵያን ለመድፈር በተነሡ ጊዜ፣ ሌሎች የኢትዮጵያን እውነት በውሸት ለመሸፈን

በተነሡ ጊዜ፣ የተቀሩትም በኢትዮጵያ ላይ ተገቢ ያልሆነ ጫና ለማሳደር በተነሱ ጊዜ፣ ዳያስፖራ ወገኖቻችን ለኢትዮጵያ ሲሉ በአንድነት ቆመዋል። የፖለቲከኞችን በሮች አንኳኩተዋል። አደባባዮችን በሰልፍ አጥለቅልቀዋል፤ ታላላቅ ተቋማትን ሞግተዋል፤ የመሪዎችን የተሳሳተ ፖሊሲ ተጋፍጠዋል፤ ሚዲያዎች የኢትዮጵያን እውነት እንዲያንጸባርቁ ጫና ፈጥረዋል።

ዳያስፖራ ወገኖቻችን ለኢትዮጵያ ብቁ ዲፕሎማት ሆነው ሀገራቸውን አስከብረዋል። ለታላቁ የሕዳሴ ግድባችን ጥብቅና ከመቆም ባሻገር ገንዘባቸው በመላከ የግድቡ ሥራ እንዲፋጠን አስችለዋል። ለተጎዱ ወገኖቻችን በየጊዜው የዓይነትና የገንዘብ ድጋፍ አድርገዋል። የኢትዮጵያ የውጭ ምንዛሪ በተዛባና በተፈተነ ጊዜ ከሚበሉት ቀንሰው ለሀገራቸው ለግሰዋል። ሀገራቸው የህልውና ፈተና ሲገጥማት በቻሉት ሁሉ ግንባር ቀደም ሆነው ተሰልፈዋል። በማኅበራዊ ሚዲያ የሚገጥመንን ፈተና ለመመከት ጊዜያቸውንና ዕውቀታቸውን ሰዉተዋል።

ብዙ የዓለም ሀገሮች ከዳያስፖራ ወገኖቻቸው ጋር የፈጠሩት ጠንካራ ትሥሥር ሀገራቸውን በፖለቲካ፣ በኢኮኖሚ፣ በዲፕሎማሲና በማኅበራዊ መስክ ለማሳደግ ጠቅሟቸዋል። ደቡብ ኮሪያ፣ ሕንድ፣ ቻይናና ሜክሲኮ ለዚህ መልካም አርአያዎች ናቸው። እነዚህ ሀገሮች የተማረ የሰው ኃይል ለማግኘት፣ የሀገራቸውን የውጭ ምንዛሬ ዐቅም ለማሳደግ፣ በየሚኖሩበት ሀገር በሀገራቸው ጉዳይ የፖሊሲ ጫና ለማሳደር፤ የቴክኖሎጂ ሽግግር ለማድረግ፤ የሀገራቸው ጉዳይ የሚኖሩበት ሀገር የውጭ ፖሊሲ አካል እንዲሆን ለማስቻል፤ ቁሳዊና ሰብአዊ ድጋፎችን ለማሰባሰብ፤ የትምህርት የጤናና የግብርና ሥርዓታቸውን ለማዘመን ተጠቅመውበታል።

ከላይ የጠቀስናቸው ሀገሮች የዳያስፖራቸውን ዐቅም በተሻለ ሁኔታ ለመጠቀም ያስቻለው ዘላቂነት ያለው፣ የተደራጀና የተናበበ አሠራር ስለሚከተሉ ነው ዳያስፖራዎቻቸው ከሀገራቸው ጋር ያላቸው ግንኙነት ዘላቂ ነው። የሆኑ ወቅቶችን መሠረት ያደረገ አይደለም። በደስታም ይሁን በፈተና ጊዜ ሀገራቸውን ሁለንተናዊ በሆነ መልኩ ይደግፋሉ። በፖሊሲዎች፣ በሕጎች፣ በአሠራሮች ሂደት ውስጥ ይሳተፋሉ። ገንዘባቸውን በሀገራቸው ባንኮች እንዲቀመጥ ያደርጋሉ፤ በኢንቨስመንት ይሳተፋሉ፤ በችግር ጊዜ ለወገናቸው ድጋፍ የሚያደርጉ ታላላቅ የእርዳታ ድርጅቶችን በመመሥረት በርዳታ ስም ከሚመጣ ጣልቃ ገብነት ሀገራቸውን ነጻ ያደርጋሉ፤

ገሬዎችና ለአነስተኛ ነጋዴዎች የዕውቀት፣ የቴከኖሎጂና የገንዘብ ድጋፍ የሚሰጡ የልማት ማኅለጫ ተቋማትን ያደራጃሉ፤ በተለይም ትምህርትን፣ ጤናንና ግብርናን ለማዘመን የሚችሉ የዕውቀትና የቴከኖሎጂ ሽግግሮችን በማከናወን የሕዝባቸውን የኑሮ ሁኔታ ለማሻሻል ይተጋሉ፤ ይህ ሁሉ እንግዲህ ለዘመድና ለወዳጆቻቸው ከሚያደርጉት ድጋፍ ባሻገር ነው።

እነዚህን ተግባራት ለማከናወን ዐቅምን ሰብሰብ ማድረግ፣ ወጥ በሆነ መልኩ ሥራዎችን መሥራትና በዕቅድ መመራት ያስፈልጋል። ዐቅሞቻችንን በየአካባቢውና በየሁኔታው ከተበታተኑ መሠረታዊ ለውጥ ማምጣት አይቻልም። በምንኖርበት ሀገር ተጽዕኖ ለመፍጠር ያለን ዐቅም የተዳከመ ይሆናል። እርስ በእርሳችን ተጋግዘን በፍጥነት ከመሄድ ይልቅ እርስ በእርሳቸን በመወቃቀስ ጊዜያችን በከንቱ ይጠፋል። ዳያስፖራ ወገኖቻችን እነዚህን ሁሉ እንደሚያስቡባቸው ተስፋ አደርጋለሁ። በየሀገራቸው ከሚኖሩ ሌሎች ጠንካራ የዳያስፖራ ማኅበረሰቦች ልምድ መውሰድ እንደሚችሉ ይታየናል። ለሀገራቸው መጠን የሌለው ፍቅር፤ ሀገራቸውና ወገኖቻቸውን በሚችሉት ሁሉ የመደገፍ የማይነጥፍ ፍላጎት አላቸው። ይሄንንም በየአደባባዩ አስመስክረዋል። ሕይወታቸውን መሥዋዕት ለማድረግ እስከመሰለፍ ደርሰዋል። ሀገራቸው ወደ እናት ሀገራችሁ አንድ ሚልዮን ሆናችሁ ኑ) ስትላቸውም፣ ጨርቄን ማቄን ሳይሉ ይሄው መጥተዋል።

አሁንም በድጋሚ ጥሪያችንን አክብራችሁ ስለመጣችሁ በራሴና በኢትዮጵያ ስም አመሰግናችኋለሁ። የመጣችሁት ወደ ቤታችሁ ነው። እናታችሁ በጓዳዋ ያላትን ሁሉ ታቀርብላችኋለች። የምታቀርብላችሁ ነገር የተሟላ ላይሆን ይችላል። ግን የእናት ቤት ከምንም ይበልጣል። በየመሥሪያ ቤቱ፣ በየንግድ ተቋማቱ በየአገልግሎት መስኮቹ የለመዳችሁትን ዓይነት ቀልጣፋና ዘመናዊ አሠራር ባታገኙ አይግረማችሁ። የእናታችሁ ቤት ነውና እንዴት እናዘምነው ብላችሁ አስቡበት እንጂ እንደ ባዳ አይታችሁ አትለፉት። ሰው ለእናቱ ቤት ይቆረቆራል እንጂ ኣይማረርም።

የተጎዱ አካባቢዎችን እንድትጎበኙ፤ ወገናችሁን እንድታንጹና እንድትደግፉ አደራ እላለሁ። አሸባሪው ሕወሐት በወገናችን ላይ ያደረሰውን ልክ የሌለው ግፍና መከራ በዓይናችሁ አይታችሁ ዓይኔን ግንባር ያርገው ላለው ዓለም እንድትገልጡ ላሳስባችሁ እወዳለሁ። አንዳንድ ተቋማት ባዘጋጁቸው መርሐ ግብሮችም ላይ ተሳተፉ፡ የቱሪስት

መዳረሻዎችንም ጎብኙ፣ የልማት ሥራዎቻችንንም ተመልከቱ። ከሁሉም በላይ ደሞ ከወላጆቻችሁ፣ ከዘመዶቻችሁና ከወዳጆቻሁ ጋር መልካም ጊዜ አሳልፉ። ሀዘኑንም ደስታውንም እኩል መጋራታችን ቤተሰባዊ መሠረታችንን ያጠናከረዋል። መልካም የቆይታ ጊዜ ይሁንላችሁ።

**ኢትዮጵያ በልጆቿ ጥረት ታፍራና ተከብራ ለዘላለም ትኑር!**
**ፈጣሪ ኢትዮጵያና ሕዝቦቿን ይባርክ!**
ታህሳስ 18፣ 2014 ዓ.ም

# ኢትዮጵያ የምትገነባው በዕውቀት ማዕከላት ውስጥ ነው !

ዛሬ የምንመርቀው ቤተ መጻሕፍት ‹አብርሆት Enlightenment› ተብሎ ተሰይሟል። አብርሆት እውነትንና ዕውቀትን መሠረት በማድረግ ከድንቁርና ቀንበር ነጻ የመውጣት ሂደት ነው። እውነትን በአመክንዮ፣ በክርክር፣ በማስረጃ፣ በምርምር፣ የመፈለግ መንገድ ነው። ዕውቀት ወደ እውነት ለመድረስ ሁነኛው ጎዳና ነው ብሎ ያስባል። በአመክንዮ የሚመሠረት የሰው ልጆች ማኅበራዊ ኑሮ በወንድማማችነት ላይ የተመሠረተ፣ መቻቻል ያለበት፣ ነጻነትን የሚያጎላና ለለውጥ ልብን ክፍት ያደረገ እንደሆነ ያምናል፡፡ ስለዚህ የሰው ልጅ ስለራሱ፣ ስለዓለምና ስለሌላውም ሁሉ የተሻለ ዕውቀት እንዲኖረው እና ማኅበራዊ ሕይወቱን በአምክንዮ እንዲመራ ይተጋል።

ሰዎች በተመራመሩ፣ በተማሩና ባወቁ ቁጥር የተሻለ መቀራረብ ይፈጥራሉ ተብሎ ይታመናል። ድንቁርና ጨለማ ነው። በጨለማ ውስጥ ደግሞ ማወቅም መተዋወቅም አይኖርም። የሌለው ነገር ያለ፤ ያለውም ነገር የሌለ መስሎ ይታያል። የማናውቀውን ነገር እንፈራዋለን፤ እንጠላዋለንም። ስለማናውቀው ነገር የምንፈጥረው ሥዕል የተሳሳተ ነው። ለዚህ መድኃኒቱ ደግሞ ማወቅ ነው። ማወቅ መተዋወቅን ያመጣል። የምናውቀውን ነገር እንቀርበዋለን። እናምነዋለን፤ እንዛመደዋለን፤ እንወደዋለን፤ አብረነው ለመኖር ፈቃደኞች እንሆናለን።

የለውጡ ጉዞ ከተጀመረ ጊዜ አንሥቶ ከታሰበባቸው ነገሮች አንዱ ዕውቀት መር የሆነ ማኅበረሰብ መመሥረት ነው። ማኅበረሰቡ ዕውቀትን ባገኘ ቁጥር ይበልጥ ይተዋወቃል፤ ይቀራረባል፤ ይተማመናል። አንዱ ስለሌላው የያዘውን የተሳሳተ ግምት በመተው በትክክለኛው ዕውቀት ላይ የተመሠረተ መረዳትን ይይዛል። ለዚህ ደግሞ የትምህርት ተቋማትን ሪፎርም ማድረግ፤ ነባር ዕውቀቶችን ለሀገራዊ ልማት መጠቀም፤ ምርምሮችንና ጥናቶችን፤ ውይይቶችንና ክርክሮችን፤ ነጻ ሐሳብ መድረኮችን፤ ኪነ ጥበብን ማበረታታት፤ ደራስያንና የሐሳብ መሪዎችን ወደፊት ማምጣት፤ የለውጡ አንዱ መንገድ ሆኖ ቆይቷል።

በለውጡ ዘመን አርአያ ሆነው የተሠሩትን ሥራዎች ስናይ ከኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታቸው በተጨማሪ የአብርሆት ጠቀሜታቸው የጎላ ነው። የአንድነት ፓርክና የአድዋ ሙዝየም ታሪክን ለመጣያና ለመለያያ ሳይሆን ለመተዋወቂያና መተራረሚያ ለማድረግ የቆመ ነው። የመስቀል አደባባይ እድሳትና የሸገር ፓርክ ግንባታ ሃይማኖት፣ ባህልና ኪነ ጥበብ ለሚያመጡት አብርሆት በር የከፈተ ነው። የእንጦጦ የሥዕል ጋለሪ አብርሆትን ከሚያስገኙት ረቂቅ ጥበቦች ለሁለቱ ለሙዚቃና ሥዕል ዕድል የሰጠ ነው። መዝናኛ የሚመስሉት የእንጦጦ ፓርክ፣ የቸርቸር ጎዳናና ወንዝ ዳር ፕሮጀክቶች አእምሮን ከተዋጊነትና ከግጭት አምራችነት ለማስፈታትና የሰከነ የሐሳብ መድረክን እንዲመርጥ ለማድረግ ታስበው የተሠሩ ናቸው። የጎርጎራ፣ የወንጪና የጨበራ ጩርጩራ ፕሮጀክቶች ለአንድ ዓላማ በሕዝቦች መካከል መገናኘትን፣ መተዋወቅን እና መደናነቅን ለመፍጠር ነው። የመለያየትን ግንብ አፍሮ የጎብረ ብሔራዊ አንድነትን መስከ ለመፍጠር ነው።

ኢትዮጵያ የራሳቸውን ፊደል ቀርጸው፣ የራሳቸውን ትምህርት አደራጅተው፣ የራሳቸውን ታሪክ ከጻፉ ጥቂት የዓለም ሀገሮች አንዷ ናት። በእስልምናና ክርስትና ማዕከላት ብቻ ከ250ሺ በላይ በእጅ የተጻፉ መጻሕፍት በየገዳማቱና በየመስጊዶቹ ያሏት ሀገር ናት። በአፍሪካ የመጀመሪያውን ልቦለድ የጻፈች ሀገር ናት። ልጆቿ ዕውቀትን ፍለጋ ከቦታ ቦታ ሲዘዋወሩ፤ ሀገር አቋርጠውም ሲንከራተቱ የኖሩባት ሀገር ናት። ምንም እንኳን ሺ ዘመናትን የተሻገረ የሥነ ጽሑፍ ሥራና የትምህርት ተቋም ቢኖራትም፤ በመቶ ሺዎች የሚጠጉ መጻሕፍትን ብታመርትም፤ ዕውቀትን በማዕከል ይዘው ለዕውቀት ፈላጊዎች ተደራሽ የሚያደርጉ ማዕከላት ግን በብዛትና በብቃት የሏትም።

እስካሁን ከዩኒቨርሲቲዎች ውጭ ያለን ትልቁ ቤተ መጻሕፍት አንድ ነው። እርሱም በ1936 ዓም የዛሬ 78 ዓመት የተከፈተው ብሔራዊ ቤተ መጻሕፍትና ቤተ መዛግብት ነው። እንደ እውነቱ ከሆነ እስከ ዛሬ ድረስ ቢያንስ በዞን ደረጃ አንድ ትልቅ ቤተ መጻሕፍት ሊኖረን ይገባ ነበር። ግን አልሆነም። ይህ አብርሆት ቤተ መጻሕፍት ሲታሰብ አምስት አገልግሎቶችን እንዲያካትት ሆኖ ነው። በሀገር ውስጥም ሆነ በውጭ የተጻፉ መጻሕፍት እንዲገኙበት። አካል ጉዳተኞችን ጨምሮ የተሻለ የማንበቢያ ሥፍራ እንዲኖረው። ዲጂታል አገልግሎት መስጠት እንዲችል። በቂ የሆነ የመኪና ማቆሚያ እንዲኖረውና በአካባቢው ያለውን የመናፈሻ ሥፍራ ለመጠቀም

በሚያስችል ሁኔታ አገልግሎት እንዲሰጥ።

ከሥነ ሕንጻው ጀምሮ ዕውቀትንና ታሪክን እንዲያንጸባርቅ ተደርጎ የተገነባ ነው። ‹አብርሆት ቤተ መጻሕፍት› የተባለውም ዋና ዓላማው እውነትና ዕውቀት ነጻ የሚያወጣውን ማኅበረሰብ ለመመሥረት ስለሆነ ነው። ኢትዮጵያ ለልጆቿ የሥልጣኔን መንገድ መርጣለች። ለጠላቶቿ ደግሞ ክንደ ብርቱ ሆና ትጠብቃቸዋለች። የሥልጣኔው መንገድ ደግሞ መማር፣ መመራመር፣ መወያየት፣ መከራከር፣ በሐሳብ መሸናነፍ፣ ዕውቀትን ማነፍነፍ፣ በአመክንዮ፣ በማስረጃና በመረጃ ላይ መመሥረት ናቸው። በቀጣዩ ዘመን፣ መጀመሪያ ደረጃቸውን የጠበቁ ክልላዊ አብያተ መጻሕፍት እንዲኖሩን፤ በመቀጠልም ዞናዊና ወረዳዊ አብያተ መጻሕፍት እንዲኖሩን እንሠራለን። ኢትዮጵያ የምትገነባው በየደረጃው በሚደራጁ የዕውቀት ማዕከላት ውስጥ ነው።

ለዚህ ደግሞ ባለ አራት ማዕዘን ኅብረት ያስፈልገናል። መንግሥት፣ የአካባቢው ሕዝብ፣ በጎ አድራጊ አካላትና በውጭ የሚኖረው ኢትዮጵያዊ። መንግሥት ቦታዎችን ያመቻቻል፤ አስተዳደሩን ይወስዳል። የአካባቢው ማኅበረሰብ የዐቅሙን አዋጥቶ ግንባታውን ያግዛል። በጎ አድራጊዎችም በግንባታው ላይ ይሳተፋሉ። በውጭ የሚኖረው ኢትዮጵያዊ ደግሞ መጻሕፍቱን በማሰባሰብ፣ በቴክኖሎጂ የተሟላ እንዲሆን በማድረግና ዘመናዊ አሠራር በመዘርጋት አስተዋጽዖ ያደርጋል። እንደዚህ ከሆነ ዕውቀት እንደ ኢትዮጵያ ጅረቶች በየአካባቢው ይፈስሳል፤ ትውልድንም ያጠጣል። የነገዋ ኢትዮጵያ ከዛሬ በእጅጉ የተሻለች ትሆናለች፤ መሠረቷን እውቀት ያደረገች ሥልጡን ሀገር ትሆናለች።

ይህ ቤተ መጻሕፍት ሲታሰብ፣ ሲገነባና ሲሟላ አስተዋጽዖ ያደረጉትን ሁሉ በዚሁ አጋጣሚ ላመሰግን እወዳለሁ። ሕዝቡ ቤተ መጻሕፍቱን ተንከባክቦ፣ እንዳይበላሽ ጠብቆ፤ ሲጎዳ ጠግኖ፤ ሲጎድል አሟልቶ ለልጅ ልጅ በሚተርፍ መንገድ እንዲጠቀምበት አደራ እላለሁ።

**ኢትዮጵያ በልጆቿ ጥረት ታፍራና ተከብራ ለዘላለም ትኑር!!**
**ፈጣሪ ኢትዮጵያና ሕዝቦቿን ይባርክ!**
ታህሳስ 22፣ 2014 ዓ.ም

## “ጀግና ሕዝብ - በቀኝ እጁ ድልን የሚጨብጥ፣ በግራ እጁ ይቅርታና ምህረትን የሚቸር ነው”

ማንኛውም ጉዞ በስኬት ተቋጨ የሚባለው አንድም በየምእራፉ፣ ሁለትም የጉዞው መጨረሻ በስኬት መጠናቀቅ ሲችል ነው። አጠቃላይ ጉዞው ያማረና የሠመረ እንዲሆን እያንዳንዱ ምእራፍ በሚገባ መቋጨት አለበት። የቤቱ ጥንካሬና ውበት የሚመሠረተው ቤቱን ከገነቡት እያንዳንዱ ጡብዎች ጥንካሬና ውበት እንጂ፣ በጣራው ጥንካሬና በግድግዳ ቀለም ብቻ አይደለም። በያንዳንዱ እርከን ውበቱና ጥንካሬው እየተረጋገጠ የመጣ ቤትም፣ በግንባታው መጨረሻ - በድምድማቱ አምሮና ጠንክሮ መቋጨት አለበት። እንዲያ ሲሆን ቤቱ - እድሜው ረጅም፣ ሲኖሩበት የሚያምር ይሆናል፡፡ በሀገራችን ባህል የጋቢ ወይም የነጠላ መጨረሻው መቋጨት ነው። ያልተቋጨ ነጠላ ወይም ጋቢ የመተርተር ዕድሉ ሰፊ ነው።

የሀገራችን ጉዞ በተደጋጋሚ ከሚገጥመው ፈተና አንዱ በተገቢ መንገድ ምእራፎቹንም ሆነ ፍጻሜውን ያለመቋጨት ነው። በዚህ የተነሣም በሂደቱ የተገኙ ድሎች በየምእራፉ ሲዝረከረኩ ይገኛሉ፤ ወይም የታሰበላቸውን የፍጻሜ ውጤት ሳያመጡ ይቀራሉ። ማንኛውም ሀገራዊ ተግባር መለካት ያለበት በሂደቱና በውጤቱ ነው። ሂደቱም ውጤቱም ተገቢውን ደረጃ ጠብቀው ተገቢን ውጤት ማምጣት አለባቸው።

ሀገራዊ ለውጡን ከጀመርን ጊዜ አንስቶ “መንገዳችን መደመር፣ ግባችን ብልጽግና ነው” ብለናል። በመደመር መንገድ ተጉዘን ወደ ሁለንተናዊ ብልጽግና ለመድረስ ደግሞ ሰላም፣ ይቅርታና ፍቅር (ሰ.ይ.ፍ) ዋናዎቹ ዕሴቶቻችን መሆናቸውን ገልጠናል። ሀገራዊ ሰላምን ለማስፈን ሰላማዊ የፖለቲካ መንገድን ብቻ መከተል፤ ያለፉ ቁርሾዎችን በይቅርታ መፍታት፤ የወደፊቱን መንገድ ደግሞ በሕዝቦች ፍቅር ላይ በመመሥረት ኅብረ ብሔራዊ አንድነታችንን ማጽናት አለብን ማለታችን ነው። ከመነሻችን በዋና ዋና ልዩነቶቻችን ላይ ሀገራዊ ምክክር እናድርግ፤ ልዩነቶቻችን በውይይት እንጂ በጠብና በጦርነት አይፈቱም ስንል የነበረው በዚህ የጸና መርሐችን

የተነሣ ነው።

ባለፉት ሦስት ዓመታት ከፍቅር ይልቅ ጠብና ጥላቻን በመረጡ፤ ከሰላም ይልቅ የጦርነትን መንገድ በተከተሉ፤ ከይቅርታ ይልቅ ነባር ቁርሾዎችን ለፖለቲካ ትግል መጠቀም በሚፈልጉ ኃይሎች ቀውስ ተፈጥሮብናል። ይሄም ቢሆን እነዚህን ችግሮች ለመፍታት ሰላማዊውን መንገድ መርጠን ነበር። ነገር ግን እነዚህ ከጥላቻና ከጦርነት፣ ከጠብና ከመከፋፈል ውጭ ህልውና የሌላቸው አካላት ሰላማዊውን መንገድ አልመረጡም። የዘረጋናቸውን የሰላም እጆች ነክሰዋል። ከእኛ ይቅር በሚል መርህ ግማሽ መንገድ ስንቀርባቸው እጥፉን እየሸሹ፣ ልዩነቶች በሰላማዊ መፍትሔ ሊታረቁ ሲችሉ የጸብ መንደር ውስጥ ይዘውን ገብተዋል።

ሀገራችን ከአንድ ዓመት በላይ ከአሸባሪዎቹ ሕወሐትና ከጋሻ ጃግሬው ሸኔ ጋር ጦርነት የገባችው፣ የዘረጋነውን የሰላም እጅ ረግጠው ጦር ስለመዘዙብን ነው። መንግሥት የመጀመሪያ ምርጫው ምንጊዜም ችግሮችን በሠለጠነ መንገድ ለመፍታት ነው። ሰላማዊ መንገድ አድካሚና አታካች ቢመስልም ሰብአዊና ቁሳዊ ጉዳትን በከፍተኛ ሁኔታ ይቀንሳል። ለጦርነት ሊውል የሚችለውን የሰው ኃይልና በጀትም ለብልጽግና ለማዋል ያስችላል። ዳሩ ግን ሰላም በአንድ ወገን ፍላጎት ብቻ የሚገኝ አልሆነም። የቱንም ያህል ብንታገስ፣ የቱንም ያህል ለሰላም ደፋ ቀና ብንል የጠላት ልብ ደነደነ እንጂ አልተለወጠም።

ማንኛውም የሰላም፣ የይቅርታና የፍቅር መንገድ ሊጥሳቸው የማይገቡ ቀይ መሥመሮች አሉ። ኅብረ ብሔራዊ አንድነታችንን የሚከፋፈል፣ የሀገራችንን ክብርና ሉዓላዊነት የሚጥስና የግዛት አንድነታችንን ለአደጋ የሚያጋልጥ ማንኛውንም መፍትሔ ተቀባይነት የለውም። የክህደትና የክፍፍል መንገድን የሚከጅል ሁሉ፣ የኢትዮጵያውያን ክንድ መቅመሱ አይቀርም። ከዚያ በታች ባሉ ጉዳዮች ዙሪያ ችግሮችን በጠረጴዛ ዙሪያ ለመፍታት ድሮም ልባችን ክፍት ነበር፤ ወደፊትም የሰላም እጃችን አይታጠፍም፡፡

ከአሸባሪው ሕወሐትና ከተላላኪው ሸኔ ጋር ያደረግነው ጦርነት ቀይ መሥመሩ በመጣሱ ምክንያት የተከሠተ ነው። አሸባሪወው ሕወሐት ኅብረ ብሔራዊ አንድነታችንን ለመከፋፈል ተነሣ፤ የሀገራችንን ክብርና ሉዓላዊነት ከባዕዳን ጋር

ሆኖ ለመግሠሥ ጦሩን ሰብቆ ሰሜን ዕዝን አጠቃ፤ የግዛት አንድነታችንን ለአደጋ እንዲጋለጥ በር ከፈተ። የቅርብና የሩቅ ጠላቶቻችንም እንደ ፈለጉት እጃችንን ሊጠመዝዙ ምክንያት አገኙ። በሀሰት ፕሮፓጋንዳቸውና ሴራ ባልተለየው የሚዲያ ዘመቻዎቻቸው ኢትዮጵያን በማዋከብ የፍላጎታቸው ተንበርካኪ ሊያደርጓት ሌት-ተቀን ይሮጡ ጀመር።

የጥንካሬና የኩራታችን ምንጭ የሆነው ሕዝባችን ግን በቀላሉ የሚበገር አልሆነም። በሀገር ውስጥ አሸባሪም ሆነ በውጭ ኃይሎች ሉአላዊነቱ ተነክቶበት ሕዝባችን እጁን አጣጥፎ አልተቀመጠም። ቀፎው እንደተነካ ንብ ‹ሆ› ብሎ በመነሳት በሁለት አቅጣጫ የተሰነዘረበትን ጥቃት በብቃት እየመከተ ይገኛል።

ጀግና ሕዝብ ለጭቆና መንበርከክን እንጂ ትህትናና ይቅርታን አይጠላም። አሸናፊ - ድል አጥባቂ፣ ትጉት እና መሐሪ ነው። ሕዝባችን “ውጊያ የሰው፣ ድል የፈጣሪ ነው” ብሎ ያምናል። አሁን ያገኘነውን ድል በሦስቱ የኢትዮጵያውያን የድል ዕሴቶች ብንቋጫቸው መልካም ነው። ድልን በማጥበቅ፣ በትኅትና እና በምሕረት። አሁን ያገኘነውን ድል እንዳይቀለበስ አድርገን በሁሉም መስክ በሩን ሁሉ ማጥበቅ አለብን። በኢትዮጵያዊ ትኅትና ደግሞ አሁን የገጠምነው ጦርነት በሰላም መንገድ እንዲጠናቀቅ እናደርጋለን። በአንድ በኩል ድል አድራጊውን የኢትዮጵያ ክንድ እያሳየን፣ በሌላ በኩል ደግሞ ትጉቱን የኢትዮጵያውያን ልብ እናሳያለን።

በድል አድራጊ የኢትዮጵያ ክንድ ጠላቶቻችን አፈር ልሰው እንዳይነሡ እንመክታለን። በትጉቱ የኢትዮጵያ ልብ ከፉከራና ኩራታችን ቀንሰን ዛሬም ለሰላም በራችን ክፍት መሆኑን እንናገራለን። ጦርነት ውስጥ የገባነው ሰላምን በሌላ በምንም መልኩ ለማምጣት ስላልቻልን ነው። ጦርነት ሰላምን የማረጋገጫ የመጨረሻው አማራጭ ነውና። ከጦርነት ወደ ሰላም ለመምጣት ያልቻሉ ኃይሎችን ወደ ሰላም ጠረጴዛ የምናመጣበት የመጨረሻ ጉልበት ነው። በባህላችንም የግጭት መቋጫው ዕርቅና ይቅርታ ነው። ደም የተቃቡ ጠበኞችን ጭምር እስከማጋባት የሚደርስ የዕርቅና የሰላም ዕሴት ያለን ሕዝቦች ነን።

ኢትዮጵያዊ ድል አድራጊነት ምህረትንም ያውቃል። በአድዋ ጦርነት የተማረኩትን የጣልያን ወታደሮች በአሸናፊ ምሕረት ምረናል። በዚህም ጣልያኖች ራሳቸው

ተገርመው በሰልፍ እስከ ማመስገን ደርሰው ነበር። ያ ታላቅ ኢትዮጵያዊ ዕሴት ነው። ዛሬም ኢትዮጵያ በአሸናፊነት ክብር ላይ ናት። ፍትሕ ያልተለየው ምሕረትን አብሮ በማስኬድ ኢትዮጵያ እንድታሸንፍ እናደርጋለን። በአንድ በኩል በደልና ጥፋትን በፍትሕ መንገድ እያየን፣ በሌላ በኩል ለእርምትና ለይቅርታ ቦታ በመስጠት የምሕረትን መንገድ መከተል አለብን።

ከድላችን ማግሥት አራት ነገሮችን መርሖቻችን አድርገን እንሄድባቸዋለን።

1ኛ - ድላችንን እንዳይቀለበስ አድርገን በሁለንተናዊ መስክ እናጠብቀዋለን።

2ኛ - ድላችን ዘላቂ እንዲሆን በፖለቲካዊና ሰላማዊ መንገዶች እንዲቋጭ እናደርገዋለን።

3ኛ - ድላችንን ለመጠበቅና ድላችን ዘላቂ ለማድረግ እንድንችል በአሸናፊ ምሕረት ግጭቱ የፈጠረውን ውጥረት እናረግባለን። 4ኛ - ያጠፉ እንዲቀጣ፣ የበደለ እንዲክስ የሚያደርግ ሁሉን አቀፍ ፍትሕ በሽግርር እና በተሃድሶ ፍትህ እይታ፣ ሃገራዊ ባህሎቻችን እና እሴቶቻችን ታሳቢ ባደረገ መልኩ ፍትህ እናሰፍናለን። እነዚህ አራቱ መርሖች አንዱ ሌላውን ሳይተካ ሁላችንንም አሸናፊ በሚያደርግ መልኩ እንደ አስፈላጊነታቸው ሁሉንም እንተገብራለን።

በድል፣ በምሕረትና በትኅትና፣ ኢትዮጵያን ዘላቂና የጸናች አሸናፊ እናደርጋታለን።

**ኢትዮጵያ በልጆቿ ጥረት ታፍራና ተከብራ ለዘላለም ትኑር!!**
**ፈጣሪ ኢትዮጵያና ሕዝቦቿን ይባርክ!**
*ታኅሣሥ 29 ቀን 2014 ዓ.ም.*

## የክንደ ብርቱዎች እናት ‘ኢትዮጵያ’ በልጆቿ ትንፋሽ ሰንደቋ ዳግም ከፍ ብሎ ይውለበለባል!

ኢትዮጵያ የሚለው ስም ለሺዎች ዘመናት ከነጻነት፣ ከአሸናፊነትና ከአልደፈር ባይነት ጋር የተያያዘ ስም ነው። ከግሪክ እስከ ሮም ፈላስፎች፣ ከዕብራውያን እስከ ፋርስ አባቶች፣ ከሩቅ ምሥራቅ እስከ ዐረብ ሊቃውንት፤ ከብሉይ እስከ ሐዲስ፤ ከክርስትና እስከ እስልምና፣ ኢትዮጵያ ነጻነት ወዳድነቷ፣ አሸናፊነቷና አልደፈር ባይነቷ ሲነገር ኖሯል። ይኖራልም።

ይሄንን የመሰለው ታላቅ ስም እንዲሁ የሚገኝ አይደለምና፣ ይሄ ለምን ሆነ? ብለን መጠየቅ አለብን። እንዲሁ የሚገኝ ቢሆን ኖሮ ታላላቅ የዓለም ሀገሮች አንድም በወርቅ አንድም በገንዘብ ይገዙት ነበር። ግን አልተቻለም። እንዲህ ያለው የክብር ስም የሚገኘው በታላቅ መሥዋዕትነት ነው። ኢትዮጵያውያን ደግሞ ያለ ምንም ልዩነት፣ ለሀገራቸው መሥዋዕትነትን ለመክፈል ምንጊዜምና መቼም ዝግጁዎች ናቸው። ሺ ዘመናትን ቢያልፉ እንኳን ለሀገሩ መሥዋዕትነት የማይከፍል የኢትዮጵያ ልጅ የለም። እንዲያውም የኢትዮጵያ ልጆች የሆኑትን ካልሆኑት የመለያው ሁነኛ ፈተና፣ ለኢትዮጵያ መሥዋዕትነትን ለመክፈል የሚኖር ቁርጠኝነት ነው። ከሌላው ዓለም መጥተው የኢትዮጵያ ልጆች የሆኑ ወገኖች በታሪክ ውስጥ ታይተዋል። መሥዋዕትነትን ከፍለው አፈሯን ወርሰዋልና። ኢትዮጵያ ውስጥ ተፈጥረው የኢትዮጵያ ልጆች ያልሆኑም አሉ። ለኢትዮጵያ መሥዋዕትነትን ላለመክፈል ብለው ብኩርናቸውን በጥቅም ሸጠው ባንዳነትን የመረጡ ጥቂት አሉ።

የኢትዮጵያ ሕዝብ በደሙ ውስጥ ጀግንነት የሚመላለስ ሕዝብ ነው የሚሉ ብዙዎች ናቸው። በእርሻ፣ በንግድ፣ በመንግሥት ሥራ፣ በሃይማኖት አገልግሎት፣ ሕይወታቸውን የሚገፉ ኢትዮጵያውያን፤ ሀገራቸው የተነካች መሆኗን ሲያረጋግጡ፣ ከመቅጽበት ወደ ወታደርነት ተቀይረው፣ ያገኙትን መሣሪያ አንሥተው፤ መሣሪያ ቢያጡ ወኔያቸውን ሰንቀው፣ ሀገራቸውን በአጥንትና በደም ዋጋ ሊታደጉ ይሰለፋሉ፤ እነሱ ወድቀው ሌላው እንዲቆም፣ እነሱ ተደፍተው ሀገር ቀና እንድትል በአንድ

ነፍሳቸው ይወራረዳሉ። ለዚህ ነው በክፉ ዓይናቸው ለሚያይዋት ጠላቶች “ኢትዮጵያ መቶ ሚልዮን የቁርጥ ቀን ወታደሮች አሏት፤ ይቅርባችሁ አትንኳት” የምንለው።

ይሄንን ምክር ያልሰሙ የውጭና የውስጥ ጠላቶች ኢትዮጵያን ደጋግመው ፈትነዋታል። እርሷም ደጋግማ ፈተናውን አልፋለች፤ ጠላቶቿንም ደጋግማ አንገት አስደፍታለች። ከእነዚህ የፈተና ወቅቶች አንዱ ባለፈው ዓመት የገጠመን ፈተና ነው። ኢትዮጵያን ባለማወቅ በሽታ የተጠቃው አሸባሪው ሕወሐት፣ ጥቅምት 23 ቀን ምሽት፣ ሰሜን ዕዝን አጥቅቶ ኢትዮጵያን ለመድፈር ተነሣ። ይህ አሳዛኝ ሁኔታ ተደራራቢ ክህደት የታየበት ነበር። አሸባሪው ሕወሐት ለሁለተኛ ጊዜ የኢትዮጵያን መከላከያ የማፍረስ ደባውን የተገበረበት እለት ነው። በታሪክ ታይቶ በማያውቅ መልኩ ራሱ የገነባውን መከላከያ በክህደት ራሱ ሊያፈርስ የተነሣ ድርጅት ነው።

ኢትዮጵያ በታሪኳ ብዙ ከሃዲዎች ገጥመዋት ያውቃሉ። እንዲህ ዓይነት ክህደት ግን እንኳን ኢትዮጵያ፣ ዓለምም ገጥሟት የሚያውቅ አይመስልም። ኢትዮጵያውያን እንዲህ ያለውን አስነዋሪ ተግባር እፉኝት የተባለችው እባብ ብቻ እንደምትፈጽመው ነበር በባህላቸው የሚያውቁት። ዛሬ ግን እፉኝት የተደራጀ አሸባሪ ቡድን ሆኖ ነው የገጠማቸው። የእፉኝት ልጆች አባታቸውንም እናታቸውን ገድለው ለመኖርና ለማደግ የሚሞክሩ ከንቱዎች ናቸው።

ጥቅምት 23 ቀን ምሽት የተደረገውን ክህደት ጀግኖቹ የሰሜን ዕዝ አባላት በአስደናቂው ኢትዮጵያዊ የጦር ጥበብ እየተዋጉ፣ መሣሪያቸውን ይዘው ከጠላት ከበባ በመውጣት አከሸፉት። የተሠዉት ተሠውተው፤ የቆሰሉት ቆስለው፣ ኢትዮጵያ በሠፈር ጎረምሳ የምትሰበር ሀገር አለመሆኗን አስመሰከሩ። የሀገሩ መነካት እንደ እግር ቁስል ያንገበገበው ኢትዮጵያዊ ሁሉ፣ ከልሂቅ እስከ ደቂቅ፣ ከሸበት እስከ ኲተት ነቅሎ በመነሣቱ፣ በሦስት ሳምንታት ውስጥ ጠላትን ከስሕበት ማዕከሉ መቀሌ ወደ ተንቤን በረሃ ሸኝቶታል። የተማረኩብንን የሰሜን ዕዝ አባላትና ትጥቃችንን አስመልሰን፣ ለብዙ ጊዜ ቡኑ ከዐይኑ እንዳይርቅ አድርጎ የሰወረውን ስትራተጂያዊ መሣሪያ ወርሰን፤ የተወሰኑ የቡድኑን አባላት ደመስሰን፤ የተወሰኑትንም በቁጥጥር ሥር አደረግን።

የመከላከያ ኃይላችን ሕዝባዊ ኃይል ነው። ለስምንት ወራት ትግራይ ውስጥ በየቦታው

እየተንከራተተ ርዳታ እንዲዳረስ፣ ሰላም እንዲሰፍን፣ በአሸባሪው የፈረሱ መሠረተ ልማቶች እንደገና እንዲገነቡ፤ ከአካባቢያቸው የተፈናቀሉ ወደ ቦታቸው እንዲመለሱ፣ መንግሥታዊ አገልግሎቶች እንዲጀመሩ ለማድረግ ደከሟል። አመሉ ጥፋት፣ ጠባዩ ከህደት የሆነው ይህ አሸባሪ ቡድን ግን የሕዝብ ሰላም ሞቱ፣ የሀገር ዕድገት ሕመሙ ነው። ያለ ጥፋት ማደር፣ ያለ ጦርነት መኖር አይቻለውም። በዚህም የተነሣ ርዳታ እንዳይደርስ፣ ገበሬው እንዳያርስ፣ የፈረሰው እንዳይጠገን፣ የተቋረጠው አገልግሎት እንዳይጀመር፣ ቀድሞ በዘረጋው የጥፋት መረቡ አማካኝነት መቀስቀስ ጀመረ። በዚያም ላይ የፕሮፓጋንዳ አመድ ነሰነሰበት፤ የመከላከያ ሠራዊታችንን መልካም ስም ጥላሸት ቀባው። ኢትዮጵያዊ ጀግንነት መልኩ እንዲጠይም አደረገ።

ይሄን የተመለከተው የኢትዮጵያ መንግሥት ለሕዝቡ ሲባል በሰብአዊነት ላይ የተመሠረተ የተናጠል የተኩስ አቁም ውሳኔ ወስኖ ከትግራይ ወጣ። በዋናነት ዓላማው በተለይ ገበሬው ተደጋጋሚ የእርሻ ወቅት እንዳያልፈው ለማድረግ የታለመ ነበር። “ሞኝ ከሳቁለት ውሻ ከሮጡለት” እንደሚባለው የመንግሥትን ውሳኔ አሸባሪው ወያኔ እንደ ሽንፈት ቆጠረው። አሁንም ካለፈው ጥፋቱ ባለመማር ሕዝቡን በመንጋ አሰልፎ መከላከያን መውጋት ቀጠለ። የክህደት ተግባሩን ገፋበት፤ ከቅርብና የሩቅ ጠላቶቻችን ጋር ተመሳጥሮ ኢትዮጵያን ሊወጋ መጣ።

ኢትዮጵያ የተአምር ሀገር ናት። ምን ዐቅም እንዳላት የሚገለጥበት የራሱ ጊዜ አለው። ለሁለት ጊዜ በተፈጸመበት እፉኝታዊ ክህደት የተመታውን መከላከያ፣ አጠፋዋለሁ ብሎ አሸባሪው ኃይል ሲያስብ፣ በጥቂት ወራት ውስጥ፣ መቶ ሺዎችን መልምሎ፣ አሠልጥኖ፣ አስታጥቆና አሠማርቶ የጠላትን ፍላጎት ለማክሸፍ ተቻለ። ጀግኖች ከየጎሬው ፈለቁ፤ ወጣቶች እምቢ ለሀገሬ አሉ። አረጋውያን የከረመ መሣሪያቸውን ወለወሉ። የቀድሞ ጦር አባላት የመጨረሻውን እድሜያቸውን በግንባር ለማሳለፍ ተመሙ። በውጭ የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን ከጦሩ ጋር ተሰለፉ፤ እናቶች ክንዳቸውን አፈርጥመው ወደ ውጊያ፣ ወገባቸውን ታጥቀው ወደ ስንቅ ዝግጅት ገቡ፤ ነጋዴዎች ከድጋፍ እስከ ግንባር ዘመቱ፤ የመንግሥት ሠራተኞች ሀገራቸውን ከአሸባሪ ደፋሪዎች ሊታደጉ ተመሙ፤ የኪነ ጥበብ ባለሞያዎች፣ አትሌቶች፣ ሐኪሞች፣ ሾፌሮች፣ ጋዜጠኞች፣ ውሎና አዳራቸው በግንባር ሆነ። ኢትዮጵያውያን ተቀየሩ። እንደ በሬ ሲያርሱ የነበሩት ሁሉ እንደ አንበሳ አገሡ። እንደ ፈረስ ለኑሯቸው ሲሯሯጡ የነበሩት ሁሉ እንደ አራስ ነብር ተቆጡ።

ኢትዮጵያ በልጆቿ ኮራች። ኢትዮጵያ ማለት ምን ማለት እንደሆነ ዳግም ለጠላቶቿ አሳየች። የተዋጋነው ከአሸባሪው ወያኔ ጋር ብቻ አልነበረም። ወያኔ መርፌ ነው። መርፌ በሚቀድደው በኩል ሊገቡ የተዘጋጁ ብዙ ገመዶች ነበሩ። ወያኔን ከነግሣንግሡ ነው ድል ያደረግነው። አንዳንዶች በዓለም አቀፍ መድረኮች ይሟገቱለታል። ሌሎች በመረጃ ያግዙታል፤ አንዳንዶች በሳተላይት ይመሩታል፤ ሌሎች ደግሞ ከውስጥ ሆነው ይላላኩለታል፤ በርዳታ ድርጅት ስም፣ በዓለም አቀፍ ተቋማት ስም፤ በሰብአዊ መብት ተሟጋችነት ስም፤ በሚዲያ ስም፤ አብረውት ከአሸባሪው ኃይል ጋር ብዙዎች ተሰልፈው ነበር። ኢትዮጵያ ግን ሁሉንም ድል ነሥታ ታሪኳን አድሳለች።

በሁሉም ግንባሮች፣ በተሰጣችሁ ሥምሪት፣ ይህችን ድንቅ ሀገር ኢትዮጵያን፤ በሕይወት መሥዋዕትነት አክብራችኋታልና፣ የኢትዮጵያ ሕዝብና መንግሥት ኮርተውባችኋል። ጓንት ሆኖ ያገለገለውን የሽብር ቡድን ብቻ ሳይሆን ጓንቱን ያጠለቁት የጠላቶቻችንን እጆች ጭምር ቆርጣችሁ ጥላችኋል። የእናንተ ወላጆች፣ ወንድሞችና እኅቶች፣ ወገኖችና ዘመዶች፣ ልጆችና የልጅ ልጆች በመሆናችን በታሪክ ጎዳናዎች ላይ በኩራት እንድንራመድ አድርጋችሁናል። ይሄንን ጀግንነታችሁን፤ ይሄንን አስደናቂ ጀብዷችሁን ለልጆቻችን በኩራት እንተርካለን። ድርሰትና ፊልም፣ ቅኔና ዜማ እናደርገዋለን። የኢትዮጵያ ተራሮች፣ ሸለቆዎችና ወንዞች የጀግኖቹን ገድል አይተው ተገርመዋል። መቼም እንደነርሱ በታሪክ የታደለ የለም።

ጥንት አባቶቻችን ታሪክ ሲሠሩ ነበሩ። ዛሬም ልጆቻቸው እናንተ ታሪክ ስትሠሩ እነዚህ ተራሮችና ሸለቆዎች፣ ሜዳዎችና ወንዞች አሉ። ባይነግሩንም እንደሚደነቁ እናምናለን። እነ ሞት አይፈሬ፣ እነ ውጊያ ምሳው፤ እነ ምሽግ ደርማሽ፣ እነ ታንክ በጊሌ ማራኪ፣ እንደ ነብር አድብተው፣ እንደ ዘንዶ ቆርጠው ጠልቀው የሚገቡ፤ የእሳት ግማዶች፤ የፍም ትንታጎች፣ የገሞራ ተምዘግዛጊዎች፣ ክንደ ነበልባሎች፤ አቤት ስንቱን ጀግና ይህች ሀገር ወለደችው። አቤት ስንቶቹ ሞትን ራሱን አስደነገጡት፤ ለታሪክ በታሪክ ኖረን፣ ታሪክ ሲሠራ አየን።

እናንተ የኢትዮጵያ ጀግኖች!

ኢትዮጵያ ታላቅ ሀገር ናት። ታላቅ የመከላከያ ተቋም ያስፈልጋታል። ይህ የመከላከያ

ኃይል ጠላትን የሚያሸንፍ ብቻ አይደለም። በጠላት የሚፈራ፣ ገና ሳይዋጋ ውጊያን የሚገታ፤ ኢትዮጵያን ለመንካት ያሰቡ ሁሉ ቀና ብለው ለማየት ፈርተውት ሐሳባቸውን ርግፍ አድርገው እንዲተዉት የሚያደርግ ተቋም። እንዲህ ያለውን ተቋም መገንባት ገና ይቀረናል። ጀምረናል፤ ግን አላገባደድንም። በተለያዩ የትምህርት ደረጃዎች የሚገኙ ወጣቶቻችን ወደዚህ ተቋም መግባት አለባቸው። ተመራማሪዎችና የፈጠራ ሰዎች ያስፈልጉናል። መምህራንና ሳይንቲስቶች ያስፈልጉናል። ስፖርተኞችና የሕክምና ባለሞያዎች ያስፈልጉናል። ፈላስፎችና የኪነ ጥበብ ባለሞያዎች ያስፈልጉናል። የመረጃና የቴክኖሎጂ ባለሞያዎች ያስፈልጉናል።

ይህ የመከላከያ ኃይላችን፣ ኢትዮጵያዊ፣ ዘመናዊ፣ ሁለንተናዊና ዲሲፕሊን ያለው ሆኖ መገንባት አለበት። ኢትዮጵያዊ ስንል ሁሉም የኢትዮጵያ ልጆች የሚሳተፉበት፣ በኢትዮጵያዊ ወኔና ዕሴት ላይ የተገነባ ማለታችን ነው። ዘመናዊ ስንል በሥልጠናው፣ በትጥቁና በአደረጃጀቱ ዘመኑ የደረሰበትን ደረጃ የያዘ፣ እንዲያውም ከነገ የቀደመ ማለታችን ነው። ሁለንተናዊ ስንል በሁሉም ዓይነት ኃይሎች፣ በሁሉም ዓይነት ዕውቀቶች፣ በሁሉም ዓይነት ዕዞች፣ በሁሉም ዓይነት ታክቲኮችና ቴክኒኮች የተሟላ ማለታችን ነው።

ከምንም በላይ መልካም ዲሲፕሊን ያለው ሠራዊት ያስፈልገናል። አንድን ሠራዊት “ሠራዊት” የሚያሰኘው ዲሲፕሊንና መርሆ ነው። ዲሲፕሊን የማይመራው የወታደሮች ስብስብ “ሠራዊት” ሊባል አይችልም። ለሠራዊት ዲሲፕሊንና መርሆ የጥንካሬው ምንጭ፣ የማሸነፉ ምክንያት፣ የአንድነቱ ገመድ፣ የነፍሱ ማረፊያዎች ናቸው። ያለ ዲሲፕሊን የወታደር ብዛት፣ የቴክኖሎጂ አቅም፣ የስትራቴጂ ረቂቅነት ልዩነት አያመጣም። ከእንግዲህ እነዚህ አራት ምሰሶዎች ላይ የቆመ ሠራዊት ከገነባን ያለ ጥርጥር ኢትዮጵያ አትደፈርም፤ በክፉ የሚያያትም ደጋግሞ ይጸጸታል። ይህ እንዲሳካ የሁሉንም ኢትዮጵያዊ ትግል ይፈልጋል። በተለይም ደግሞ እዚህ ያላችሁ መኮንኖች ትልቅ ኃላፊነት አለባችሁ፡፡በተለይም ደግሞ የዛሬ ተሸላሚ መኮንኖች ትልቅ ኃላፊነት አለባችሁ፡፡

የተሰጣችሁ ማዕረግ እና የተሸለማችሁት ሜዳልያ በመጀመሪያ ደረጃ በጦር ሜዳ ውሏችሁ የፈጸማችሁትን ጀብዱ ታሳቢ ያደረገ ነው። ለኢትዮጵያ ብሎ መዋደቅ፣

ለህዝብ ብሎ ዋጋ ለመክፈል መቁረጥ “ጀግና” ከሚል የክብር ስም ባለፈ፣ ጀብዷችሁ በማዕረግና በሜዳልያ መደገፉ ለእናንተ እንደ እውቅና ለሌሎች ደሞ እንደ ትምህርት ሆኖ ያገለግላል።

የሽልማቱ ሁለተኛ ምክንያት ቀብድ ነው። የእናንተ ጀግንነት በአንድ ጦር ሜዳ ላይ ብቻ ካከተመ ለእናንተም ለኢትዮጵያም ኪሳራ ይሆናል። ጀግንነታችሁ ተቋማዊ ቅርጽ እንዲይዝ፤ ትጋታችሁ ከግለሰባዊ እሴትነት አልፎ የሠራዊቱም እሴት እንዲሆን ከዛሬ ጀምሮ በርትታችሁ መሥራት አለባችሁ። በመሪነት ችሎታችሁ ተቋም እንድትገነቡበት፣ የሥራችሁ ፍሬ እንዲበዛ፣ እናንተን የመሰሉ በሙቶና በሺዎች የሚቆጠሩ ጀግኖችን እንድታፈሩበት በማሰብ የተበረከተ ሽልማትና ማዕረግ ነው። ከእናንተ በኋላ የሚመጡ ጀግኖች የእናንተን ፈለግ ሲከተሉ ያኔ ጀግንነት በትውልድ ጅረት ላይ ኩልል ብሎ መፍሰሱን ይቀጥላል፡፡

በዚህ መልኩ የነጻነት ቀለም የሆነች ኢትዮጵያ፣ የክንደ ብርቱዎቹ እናት የተባለችው ሀገራችን፣ በልጆቿ ትንፋሽ ሰንደቅዋ እየተውለበለበ ለዘላለም ይኖራል።

**ኢትዮጵያ በልጆቿ ጥረት ታፍራና ተከብራ ለዘላለም ትኑር ! !**
**ፈጣሪ ኢትዮጵያና ሕዝቦቿን ይባርክ !**
*ታኅሣሥ* 30 ቀን 2014 ዓ.ም.

# የአፍሪካ ህብረት ጉባኤ በአዲስ አበባ

የአፍሪካ ኅብረት ጉባኤ በአዲስ አበባ ውድ አፍሪካዊ ወንድም እህቶቼ፣ አፍሪካዊ ወንድማማችነታችንን ከመቼውም ጊዜ በላይ ማጠናከር በሚያስፈልገን በዚህ ወሳኝ ወቅት፣ የአፍሪካ ኅብረት አባል ሀገራት መሪዎች ተስማምተው የኅብረቱ ጉባኤ በአዲስ አበባ እንዲደረግ በመወሰናቸው በኢትዮጵያ ሕዝብ ስም ምስጋናዬን አቀርባለሁ።

ኢትዮጵያ – የአፍሪካዊነትን ጉዳይ እንደ መጀመሪያ አጀንዳዋ እንጂ እንደ ሁለተኛ አድርጋ ወስዳው እንደማታውቅ ልገልጽላችሁ እወዳለሁ። ለአፍሪካ ነጻነት ያላት አቋም አንድም ቀን ቀንሶ አያውቅም።

ለፓን አፍሪካዊነት የምትሰጠው ቦታ ሁሌም ጉልህ ነው። ጥንትም ሆነ ዛሬ ኢትዮጵያ "ኢትዮጵያ" ናት። በአፍሪካዊነት ላይ አትወላውልም። ይሄን የኢትዮጵያን አቋም ቀደምት የአፍሪካ መሪዎች እንደተገነዘቡት ሁሉ፣ የዚህ ዘመን መሪዎችም በሚገባ ተገንዝበው አጋርነታቸውን በሚያሳይ መልኩ የኅብረቱን ጉባኤ በአካል እዚህ ለማከናወን ያሳለፉትን ውሳኔ ኢትዮጵያ ታደንቃለች።

ወንድማዊ አጋርነታችሁን በምንሻበት በዚህ ወሳኝ ወቅት፣ የኮሮናን መስፋፋትንና ወቅታዊውን የጸጥታ ሁኔታ እንደ ምክንያት በማንሣት የአፍሪካ ኅብረት ጉባኤ በአዲስ አበባ እንዳይካሄድ እንቅስቃሴ ሲያደርጉ የነበሩ አካላት ተግባራቸው ኢትዮጵያን አሳዝኖ ነበር። በዓመት ሁለት ጊዜ ከሚደረጉት የአፍሪካ ኅብረት ጉባኤያት መካከል በኮሮና ምክንያት ተቋርጦ የነበረው የመጀመሪያው ጉባኤ ከሶስት ዓመት በኋላ ዳግም በአዲስ አበባ እንዲካሄድ ከሌሎች የአፍሪካ ሀገራትና ከአፍሪካ ኅብረት ኮሚሽን ጋር በመሆን መንግስት ልዩ ልዩ ዲፕሎማሲያዊ ጥረቶችን ሲያደርግ ቆይቷል።

ጉባኤው እዚህ መካሄዱ የሚኖረውን ትርጉም የተገነዘቡና ኢትዮጵያ በአፍሪካ ጉዳዮች ላይ ያላትን ጠንካራ አቋም፣ ለአፍሪካ ኅብረት እውን መሆን ያበረከተችውን

አስተዋጽኦ እና የአፍሪካ ጉዳዮች በአፍሪካውያን እንዲታዩ ያላትን የጸና መርሕ ከፍ ያለ ዋጋ የሰጡ የአፍሪካ መሪዎች ጉባኤው በአዲስ አበባ መካሄዱን መርጠዋል። በዚህም ኢትዮጵያ ደስ ተሰኝታለች፤ እንኳን ደስ ያለን።

**ውድ የሀገሬ ልጆች፣**

በችግራችንም ሆነ በደስታችንም ጊዜ ቀድመው ከጎናችን የሚቆሙት አፍሪካዊ ወንድሞቻችን እንደሆኑ ይታወቃል። የምንጋራቸው ማንነቶች፣ የሚያስተሳስሩን ታሪኮች፣ የሚያመሳስሉን የጋራ ችግሮች ቁጥራቸው ቀላል አይደለም። ኢትዮጵያ ለእነሱ ሁለተኛ ቤታቸው ናት። ሰው ወደ ቤቱ ሲመጣ እንደ ቤተኛ እንጂ እንደ ባዳ አይስተናገድም። እናም እጃችንንና ልባችንን ከፍተን ልንቀበላቸው፣ ለትዝታ የሚተርፍ ቆይታ እንዲኖራቸው አድርገን ልናስተናግዳቸው፣ በሰላም እንደመጡ በሰላምና በሐሴት አቆይተን ልንሸኛቸው ይገባል።

አሁን ጉባኤውን ለማከናወን የቀረን ሁለት ሳምንት ብቻ ነው። በዚህ ጊዜ ውስጥ አስፈላጊውን ቅድመ ዝግጅት አድርገን ጉባኤውን ማሳካት አለብን። የጉባኤው በአዲስ አበባ መካሄድ ትርጉሙ ብዙ ነው። ሰላማችንና ደኅንነታችንን የምናስመሰክርበት፣ ለአፍሪካ ጉዳዮች ያለንን አቋም በድጋሚ የምናስመሰክርበት፤ የኢትዮጵያን መልካም ሁኔታ ለአፍሪካውያን ወገኖቻችን በተግባር የምናሳይበት፤ ከዚህም አልፎ ኢኮኖሚያዊ ጥቅም የምናገኝበት ጉባኤ ነው። እናም ጉባኤው የተሳካ እንዲሆን ከሁላችንም ብዙ ይጠበቃል።

የጸጥታ አካላት፣ ሆቴሎች፣ የትራንስፖርት አገልግሎት ሰጭዎች፣ እንዲሁም የመዝናኛና ቱሪዝም ሥፍራዎች ከእናንተ ብርቱ ዝግጅት ይጠበቃል። የሚመጡትን እኅትና ወንድሞቻችንን በኢትዮጵያዊ ጨዋነት ተቀብለን፣ ምቾትና ደኅንነታቸውንና ጠብቀን ማስተናገድ አለብን። በተለይም የአዲስ አበባ ከተማ መስተዳድርና ሕዝብ – ለአካባቢ ጽዳትና ጸጥታ ትኩረት ሰጥተው ከዛሬ ጀምሮ የሚጠበቅባቸው ሁሉ እንዲያደርጉ አደራ እላለሁ።

ታላቁ የነጻነት ታጋይና የይቅርታ አባት የሆኑት የቀድሞ የደቡብ አፍሪካ ፕሬዝዳንት ኔልሰን ማንዴላ ስለ ሀገራችን ሲናገሩ “ኢትዮጵያ በምናቤ ውስጥ ሁሌም ልዩ ሥፍራ

አላት” ያሰኛቸው፣ ኢትዮጵያ ቅንነት በተሞላ ፊቷ ተቀብላ ስላስተናገደቻቸው እንጂ በሌላ ምክንያት አይደለም። ይህንን ሊናገሩ የቻሉት፣ የሀገራችንን ፍቅር ያልተለየው እቅፏን በማግኘታቸው ነው። እናም ማንዴላን ባከበርንበት ልክ አሁንም የኅብረቱ አባላትን አክብረን እንድናስተናግዳቸው፣ በኩራት የምንጠቅሰው ኢትዮጵያዊ እንግዳ ተቀባይነትን ከነሙሉ ክብሩ ዳግም እንድንገለጥ አደራ እላለሁ።
ኢትዮጵያ አሸናፊ የምትሆነው በሁሉም መስኮች አሸናፊ ከሆነች ነው። ከእነዚህ አንዱ ደግሞ ለአፍሪካ የገባነውን ቃል ጠብቀንና አጽንተን መቀጠላችን ነው።

ኢትዮጵያ ለአፍሪካ ኅብረት ያላት አቋም መቼም ቢሆን አይለወጥም። የገባችውን ቃልም በማናቸውም ሁኔታ ውስጥ ሆና ማክበሯን ትቀጥላለች። ይሄንን አቋሟን ስለተገነዘቡ አፍሪካውያን ወገኖቻችንን በድጋሚ አመሰግናለሁ።

**ኢትዮጵያ በልጆቿ ጥረት ታፍራና ተከብራ ለዘላለም ትኑር!!**
**ፈጣሪ ኢትዮጵያና ሕዝቦቿን ይባርክ!**
**ጥር 8፣ 2014 ዓ.ም**

# የአፍሪካ ኅብረት የመሪዎች ጉባኤ በሰላም እና በስኬት እንዲጠናቀቅ አስተዋጽዖ ላበረከታችሁ ምስጋና ይድረስ

የዘንድሮው የአፍሪካ ኅብረት የመሪዎች ጉባኤ በመዲናችን አዲስ አበባ እንዲደረግ የአባል ሀገራት መሪዎች መወሰናቸውን ተከትሎ ወንድማዊ አጋርነት የታየበት የኅብረቱ ጉባኤ በተያዘለት መርሐ ግብር መሠረት ተካሂዶ በስኬት ተጠናቅቋል።

የኅብረቱ ጉባኤ ፍሬያማ ውይይት የተካሄደበት፣ ለአህጉራችን የሚጠቅሙ ውሳኔዎች የተላለፉበት፣ ከምንም በላይ ወንድማዊ አጋርነት የታየበት ነበር ማለት ይቻላል።

እውነተኛ ወዳጅነት የሚመዘነው በችግር ጊዜ እንደመሆኑ መጠን፣ ባለፈው አንድ ዓመት ውስጥ ኢትዮጵያ ወዳጅ ስትፈልግ ከማንም ቀድማችሁ ደርሳችሁልናል።

ሌሎችሲሸሹንከጎናችንበመቆምእውነተኛወዳጅነታችሁንአስመስክራችኋል።ለዚህም ኢትዮጵያ ከልብ ታመሰግናችኋለች። አፍሪካውያንን አንድ የሚያደርገን የአንድ አህጉር ሕዝቦች ወይም የአንድ ምድር ልጆች መሆናችን ብቻ አይደለም።ከወንዞቻችን በላይ ታሪካዊ ሁነቶች ይበልጥ ያስተሣሥሩናል፤ ከመልክአ ምድሩና ከአየር ንብረቱ በበለጠ የምንጋፈጣቸው ችግሮች ያመሳስሉናል።

በክፉም በደጉም አብረን ነበርን፤ ወደፊትም አብረን እንዘልቃለን።ዕጣ ፈንታዎቻችን ተመሳሳይ ናቸው። የአንዳችን ቁስል ሌላችንን ማመሙ፤ የአንዳችን ሰቀቀን ለሌላችን መሰማቱ ጥብቅ ቤተሰቦች አድርጎናል። የወዳጅነታችን መሠረቱ ጥቅም ሳይሆን እውነተኛ ወንድማማችነት ነው።

ትናንት ቀደምቶቻችን በጀመሩት አንድነት፣ ዛሬ ጠብቀን ባቆየነው ኅብረት፣ እና ነገ እውን በሚሆነው የተግባር ቅንጅት የአፍሪካ ክብር ከፍ ይላል፤ በዓለም መድረክ ድምጻችን ጎልቶ መደመጥ ይችላል። “ለአፍሪካዊ ችግር አፍሪካዊ መፍትሔ”

የመፈለግ ጉዟችን ሁላችንንም ከስኬት ጫፍ እንደሚያደርሰን ምንም ጥርጥር የለውም።በመንገዱ ላይ ዕንቅፋት ይገጥመን ይሆናል፤ ፈተናዎች ዕረፍት አልሰጥ ብለው እንቸገር ይሆናል፤ ነገር ግን እጅ ለእጅ ተያይዘን እናልፈዋለን።

ዛሬ የተሻገርነው ፈተና ለእኛ ትምህርት፣ ከእኛ በኋላ ለሚመጣው ትውልድ የጥንካሬ ምንጭ መሆኑ አይቀርም።የኅብረቱ ጉባኤ በስኬት እንዲጠናቀቅ ደፋ ቀና ሲሉ የነበሩ ብዙዎች ናቸው። እንግዶቻችን በሰላም ወደ ሁለተኛ ቤታቸው አዲስ አበባ መጥተው ደኅንነታቸው ተጠብቆ እንዲቆዩ የጸጥታ ኃይሎች በሚገባ ኃላፊነታቸውን ተወጥተዋል።

ጉባኤው ምንም ዓይነት ችግሮች እንዳይገጥሙትና የጉባኤው ተሳታፊዎች በከተማዋ ምቾት ያለው ቆይታ እንዲኖራቸው ለማስቻል የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ያሳየው ትጋት፣ የከተማው ነዋሪዎች ያሳዩት ትዕግሥትና ተባባሪነት፣ ሆቴሎችና አገልግሎት ሰጪዎች ኢትዮጵያዊ ጨዋነት በተላበሰ መንገድ ለማስተናገድ ያደረጉት ደፋ ቀና የሚደነቅ ነው።

የሚዲያ ባለሞያዎች ጉባኤው ተደራሽ እንዲሆን የፈጠሩት ቅንጅት ውጤታማ ነበር። ጉባኤውን በንቃት የመሩትን የኅብረቱን ጽሕፈት ቤት ሠራተኞች ጨምሮ ለጉባኤው ስኬት አስተዋጽዖ ያበረከቱ አካላትን ኢትዮጵያ ታመሰግናለች።

ኢትዮጵያ በልጆቿ ጥረት ታፍራና ተከብራ ለዘላለም ትኑር!!ፈጣሪ ኢትዮጵያና ሕዝቦቿን ይባርክ!

ጥር 29 ቀን 2014 ዓ.ም.

# ኢትዮጵያ በታላቁ ሩጫ ላይ ናት

**እንኳን ለ21ኛው የታላቁ ሩጫ ዝግጅት አደረሳችሁ፤**

ኢትዮጵያ በታላቁ ሩጫ ላይ ስለሆነች፥ ታላቁ ሩጫ ለእኛ ከጤና፣ ከመዝናኛና ከኢኮኖሚ ጥቅሞቹ በላይ መሆኑንም ነው የገለጹት።

የኢትዮጵያ ሩጫ አሸናፊ ሆኖ ብቻ እንዲጠናቀቅ ሳይሆን ኢትዮጵያችን ሪከርድ እንድትሰብር ጭምር እንፈልጋለን ነው ያሉት።

የምንወዳደረው ከብዙ ሯጮች ጋር መሆኑን የጠቆሙት ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ፥ የምንፎካከረውም ከድህነት፣ ከጎጠኝነት፣ ከብልሹ አሠራር ከዋልታ ረገጥነት፣ ከውጭና ከውስጥ አፍራሾች ጋር ነው ብለዋል።

ያለ ምንም ጥርጥር ግን ኢትዮጵያ ታሸንፋለች፤ ማሸነፍ ብቻ ሳይሆን ሪከርድን ማንም እንዳይደረስበት አድርጋ ትሰብረዋለች ሲሉ መልዕክታቸውን አስተላልፈዋል።

ታላቅ ሩጫ በምሥራቅ አፍሪካ ሀገሮች፣ ከዚያም በመላዋ አፍሪካ፤ ብሎም በመላው ዓለም የኢትዮጵያን ስም የሚያስጠራ ታላቅ ክንዋኔ ሆኖ እንደሚስፋፋ እምነታቸው መሆኑን ገልጸው፥ ለዚህም መንግሥት አስፈላጊን ድጋፍ ሁሉ እንደሚሰጥ አረጋግጠዋል።

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ ያስተላለፉት መልዕክት ሙሉ ቃል እንደሚከተለው ቀርቧል፦

ታላቁ ሩጫ ለእኛ ከጤና፣ ከመዝናኛና ከኢኮኖሚ ጥቅሞቹ በላይ ነው። ምክንያቱም ኢትዮጵያ በታላቁ ሩጫ ላይ ስለሆነች። ድህነትንና ኋላ ቀርነትን፣ ግጭትንና ጦርነትን፣ መለያየትንና መከፋፈልን ከኋላዋ ጥላ፤ ብልጽግናንና ሥልጣኔን፣ ሰላምንና

መቻቻልን፣ አንድነትንና መግባባትን ለማስፈን ኢትዮጵያ ወደፊት እየሮጠች ነው።

አንድ የስፖርት ሰው ማሸነፍ ከፈለገ አምስት ነገሮች ያስፈልጉታል። የአካል ብቃት፣ በቂ ዝግጅት፣ ትጥቅ፣ ዲሲፕሊንና በመወዳደሪያው ላይ በጊዜውና በቦታው መገኘት። ኢትዮጵያም መደመር በሚባለው ጎዳና ብልጽግና የተባለውን ሜዳልያ ለማግኘት እየሮጠች ነው። በዚህ ሩጫ እንድታሸንፍ በሁለም መስኮች የመወዳደር ብቃት እንዲኖራት ማድረግ አለብን። ኢትዮጵያውያን በቂ የአካል፣ የመንፈስና የአስተሳሰብ ዝግጅት ያስፈልገናል። ለድሉ የሳይንስና የቴክኖሎጂ ትጥቅ ወሳኝ ነው፤ ራሳችንን ከብዙ አጥፊ ነገሮች የሚጠብቅ ሀገራዊ ዲሲፕሊን ያስፈልጋል። የምንወዳደረው ከዓለም ጋር ስለሆነ በተገቢው መድረክ፣ ጊዜው ሳያልፍብን ተወዳዳሪ ሆነን መገኘትም አለብን። ዛሬ በዚህ ታላቅ ሩጫ ላይ የምትሳተፉ ሁሉ እያንዳንዱን ምእራፍ ስትሮጡ እየሮጠች ያለችውን ኢትዮጵያን እንድታስቧት አደራ እላለሁ።

የኢትዮጵያ ሩጫ አሸናፊ ሆኖ ብቻ እንዲጠናቀቅ አንፈልግም። ኢትዮጵያችን ሪከርድ እንድትሰብር ጭምር እንፈልጋለን። የምንወዳደረው ከብዙ ሯጮች ጋር ነው። ከድህነት ጋር እንፎካከራለን፤ ከጎጠኝነት ጋር እንፎካከራለን፤ ከብልሹ አሠራር ጋር እንፎካከራለን፤ ከዋልታ ረገጥነት ጋር እንፎካከራለን፤ ከውጭና ከውስጥ አፍራሾች ጋር እንፎካከራለን፤ ያለ ምንም ጥርጥር ግን ኢትዮጵያ ታሸንፋለች፤ ማሸነፍ ብቻ ሳይሆን ሪከርድን ማንም እንዳይደረስበት አድርጋ ትሰብረዋለች።
ታላቁ ሩጫ እንዲመሠረትና ታላቅነቱን እንዳከበረ እንዲቀጥል ያደረጉትን ሁሉ ላመሰግናቸው እወዳለሁ። በተለይም የሀገራችን ኩራት፤ የኢትዮጵያ የቁርጥ ቀን ልጅ፤ በመከራዋም ሆነ በደስታዋ ቀድመው ከሚደርሱላት አንዱ የሆነውን አትሌት ኃይሌ ገብረ ሥላሴን በዚሁ አጋጣሚ በራሴና በኢትዮጵያ ስም አመሰግነዋለሁ። ታላቅ ሰው ማለት ታላቅነቱን እንደጠበቀ፤ ለሀገሩ ታላቅ ሥራ የሚሠራ ማለት ነው። ሰው ያልፋል፤ ታሪክና ሥራ ግን ሲናገሩና ሲያስከብሩ ይኖራሉ። ኃይሌ በዓለም አደባባይ ኢትዮጵያን በክብር አስጠርቷታል፤ ለብዙ ተተኪ አትሌቶች አርአያ ሆኗል። በተለያዩ ጥረቶች የሚገኝን ገንዘብ እንዴት ወደ ኢንቨስትመንት መቀየር እንደሚቻል ኃይሌ ምሳሌ ነው። ኃይሌ አትሌት ብቻ ሳይሆን መካሪ፣ አስታራቂ፣ ሽማግሌ ነው። ሀገሩ ስትደፈርም እንደ ነብር የሚቆጣ፣ በኢትዮጵያ ጉዳይ ቀልድ የማያውቅ መሆኑን በተደጋጋሚ አይተናል። ኢትዮጵያ እንደ ኃይሌ ያሉ ሚልዮኖችን ትፈልጋለች።

ባለፉት ሃያ ዓመታት ታላቁ ሩጫ በመቶ ሺዎች የሚቆጠሩ ኢትዮጵያውያንን ማሰባሰብ ችሏል፤ በዓመት አንዴ ስለ ሰላም፣ ስለ ፍቅር፣ ስለ አብሮነት ልባቸውን እንዲሰጡ አድርጓል። በሐይማኖታዊ በዓላት አብረው መሆን ያልቻሉ ዜጎች በታላቁ ሩጫ ተቃቅፈው ይሮጣሉ፤ በብሔረሰባዊ መሰባሰቦች አንድ ላይ መሆን ያልቻሉ ሕዝቦች ታላቁ ሩጫን ጠብቀው ይገናኛሉ። ኃይሌን በታላቁ ሩጫ ስናመሰግነው ዝግጅቱ ለአትሌቲክስ ከሚያበረክተው አስተዋጽኦ አኳያ ብቻ ሳይሆን፥ ኢትዮጵያዊ መሰባሰብን፣ ኢትዮጵያዊ ትስስርን፣ ኢትዮጵያዊ መቀራረብን የምንፈጥርበት፤ በብሔር፣ በቋንቋና በሐይማኖት የማንታጠርበት፣ የሁላችን የሆነ ታላቅ ዝግጅትን ስላስጀመረልን ጭምር ነው።

በዚህ አደባባይ በታላቁ ሩጫ ለመሳተፍ የመጣችሁት ሁሉ ኢትዮጵያን በልባችሁ ይዛችሁ እንደምታሸንፉ አምናለሁ። ብሔር፣ እምነት፣ የፖለቲካ አመለካከትና ጾታ ሳይለያችሁ አንድ ላይ ዛሬ እንደሮጣችሁት ሁሉ፤ ኢትዮጵያ በሁሉም ነገር አሸንፋ ሪከርድ እንድትሰብር አንድ ሆናችሁ በዓለም አደባባይ እንድትሮጡ አደራ እላለሁ። ይሄ ታላቅ ሩጫ በምሥራቅ አፍሪካ ሀገሮች፣ ከዚያም በመላዋ አፍሪካ፤ ብሎም በመላው ዓለም የኢትዮጵያን ስም የሚያስጠራ ታላቅ ክንዋኔ ሆኖ እንደሚስፋፋ አምናለሁ። ለዚህም መንግሥት አስፈላጊን ድጋፍ ሁሉ ይሰጣል። ለኢትዮጵያ እንሩጥ፤ አንድ ሆነን ከሮጥን ኢትዮጵያ ታሸንፋለች።

**ኢትዮጵያ በልጆቿ ጥረት ታፍራና ተከብራ ለዘላለም ትኑር!!**
**ፈጣሪ ኢትዮጵያና ሕዝቦቿን ይባርክ!**
ጥር 15፣ 2014 ዓ.ም

# “ድርቅ በተፈጥሮ ቢመጣም ርሃብ ግን የሥንፍናችን ውጤት ነው”

የዘንድሮው የአፍሪካ ኅብረት የመሪዎች ጉባኤ በመዲናችን አዲስ አበባ እንዲደረግ የአባል ሀገራት መሪዎች መወሰናቸውን ተከትሎ ወንድማዊ አጋርነት የታየበት የኅብረቱ ጉባኤ በተያዘለት መርሐ ግብር መሠረት ተካሂዶ በስኬት ተጠናቅቋል።

የኅብረቱ ጉባኤ ፍሬያማ ውይይት የተካሄደበት፣ ለአህጉራችን የሚጠቅሙ ውሳኔዎች የተላለፉበት፣ ከምንም በላይ ወንድማዊ አጋርነት የታየበት ነበር ማለት ይቻላል።

እውነተኛ ወዳጅነት የሚመዘነው በችግር ጊዜ እንደመሆኑ መጠን፣ ባለፈው አንድ ዓመት ውስጥ ኢትዮጵያ ወዳጅ ስትፈልግ ከማንም ቀድማችሁ ደርሳችሁልናል።

ሌሎች ሲሸሹን ከጎናችን በመቆም እውነተኛ ወዳጅነታችሁን አስመስክራችኋል።ለዚህም ኢትዮጵያ ከልብ ታመሰግናችኋለች። አፍሪካውያንን አንድ የሚያደርገን የአንድ አህጉር ሕዝቦች ወይም የአንድ ምድር ልጆች መሆናችን ብቻ አይደለም።ከወንዞቻችን በላይ ታሪካዊ ሁነቶች ይበልጥ ያስተሣሥሩናል፤ ከመልክአ ምድሩና ከአየር ንብረቱ በበለጠ የምንጋፈጣቸው ችግሮች ያመሳስሉናል።

በክፉም በደጉም አብረን ነበርን፤ ወደፊትም አብረን እንዘልቃለን።ዕጣ ፈንታዎቻችን ተመሳሳይ ናቸው። የአንዳችን ቁስል ሌላችንን ማመሙ፤ የአንዳችን ሰቀቀን ለሌላችን መሰማቱ ጥብቅ ቤተሰቦች አድርጎናል። የወዳጅነታችን መሠረቱ ጥቅም ሳይሆን እውነተኛ ወንድማማችነት ነው።

ትናንት ቀደምቶቻችን በጀመሩት አንድነት፣ ዛሬ ጠብቀን ባቆየነው ኅብረት፣ እና ነገ እውን በሚሆነው የተግባር ቅንጅት የአፍሪካ ክብር ከፍ ይላል፤ በዓለም መድረክ ድምጻችን ጎልቶ መደመጥ ይችላል። “ለአፍሪካዊ ችግር አፍሪካዊ መፍትሔ”

የመፈለግ ጉዟችን ሁላችንንም ከስኬት ጫፍ እንደሚያደርሰን ምንም ጥርጥር የለውም።በመንገዱ ላይ ዕንቅፋት ይገጥመን ይሆናል፤ ፈተናዎች ዕረፍት አልሰጥ ብለው እንቸገር ይሆናል፤ ነገር ግን እጅ ለእጅ ተያይዘን እናልፈዋለን።

ዛሬ የተሻገርነው ፈተና ለእኛ ትምህርት፣ ከእኛ በኋላ ለሚመጣው ትውልድ የጥንካሬ ምንጭ መሆኑ አይቀርም።የኅብረቱ ጉባኤ በስኬት እንዲጠናቀቅ ደፋ ቀና ሲሉ የነበሩ ብዙዎች ናቸው። እንግዶቻችን በሰላም ወደ ሁለተኛ ቤታቸው አዲስ አበባ መጥተው ደኅንነታቸው ተጠብቆ እንዲቆዩ የጸጥታ ኃይሎች በሚገባ ኃላፊነታቸውን ተወጥተዋል።

ጉባኤው ምንም ዓይነት ችግሮች እንዳይገጥሙትና የጉባኤው ተሳታፊዎች በከተማዋ ምቾት ያለው ቆይታ እንዲኖራቸው ለማስቻል የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ያሳየው ትጋት፣ የከተማው ነዋሪዎች ያሳዩት ትዕግሥትና ተባባሪነት፣ ሆቴሎችና አገልግሎት ሰጪዎች ኢትዮጵያዊ ጨዋነት በተላበሰ መንገድ ለማስተናገድ ያደረጉት ደፋ ቀና የሚደነቅ ነው።

የሚዲያ ባለሞያዎች ጉባኤው ተደራሽ እንዲሆን የፈጠሩት ቅንጅት ውጤታማ ነበር። ጉባኤውን በንቃት የመሩትን የኅብረቱን ጽሕፈት ቤት ሠራተኞች ጨምሮ ለጉባኤው ስኬት አስተዋጽዖ ያበረከቱ አካላትን ኢትዮጵያ ታመሰግናለች።

**ኢትዮጵያ በልጆቿ ጥረት ታፍራና ተከብራ ለዘላለም ትኑር!!ፈጣሪ ኢትዮጵያና ሕዝቦቿን ይባርክ!**

ጥር 29 ቀን 2014 ዓ.ም.

# “ድርቅ በተፈጥሮ ቢመጣም ርሃብ ግን የሥንፍናችን ውጤት ነው”

በየአሥር ዓመቱ እየተመላለሰ እንደሚጎበኘን ድርቅና ርሃብ ልክ በታሪካችን የፈተነን ጠላት የለም።
አያሌ ውድ ዜጎቻችንን ሕይወት ቀጥፏል። በምግብ ራሳችንን ያለመቻል ችግር ህጻናትን ለመቀንጨር፣ ወጣቶችን ለስደት፣ አረጋውያንን ለጉስቁልና፣ የቀንድና ጋማ ከብቶቻችንን ለእልቂት ዳርጓል።

ቅኝ ሊገዙን የመጡ የውጭ ወራሪዎች በርሃብና ችነፈር ልክ አልፈተኑንም። ዳር ድንበራችን እንዳይነካ፣ ሉአላዊነታችን እንዳይደፈር የምናድርጋቸው ተጋድሎዎች በርሃብና ችነፈር ላይ አለመደገማቸው ምን ያህል ዋጋ እንዳስከፈሉን አስረጅ አያሻውም። ርሃብ የሀገራችን ምስል ላይ ጥቁር ነጥብ አስቀምጦአል።

በምግብ ራሳችንን ባለመቻላችን ምክንያት ብሄራዊ ህልውናችን ጥላ አጥልቶበት መታየቱ ሊቆጨን ይገባል። የእለት ጉርሳችንን አሸንፈን እስካልተገኘን ድረስ በየትኛውም ዘርፍ የምናስመዘግበው ስኬት ትርጉሙ ይደበዝዛል።
በግብርና ምርቶች ላይ የምናሳየው ድክመት በኢኮኖሚው ብቻ ሳይሆን በማህበራዊም፣ በፖለቲካውም፣ በዲፕሎማሲና በሌሎች ዘርፎችም ላይ ተጽእኖ አለው።
ለግብርና ተስማሚ ለም መሬትና ወንዞች ኖረውን የእርዳታ በሮችን የምናንኳኳው፣ ታሪክ ኖሮን ጎልተን የማንታየው፣ እምቅ የዲፕሎማሲ አቅም እያለን በዓለም መድረኮች የማንደመጠው በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ጊዜ እየጠበቀ በሚጎበኘን ድርቅ እና ርሃብ ምክንያት ነው።

ተደጋግሞ እንደሚባለውም ድርቅ በተፈጥሮ ቢመጣም ርሃብ ግን ሰው ሠራሽ ነው፤ ሥንፍናችንና ደካማ የግብርና ፖሊሲዎቻችን የፈጠሩት ችግር ነው።

በምግብ ራስን የመቻል ጉዳይ፣ በዘላቂነት ከርሃብና ቸነፈር የመላቀቅ ጉዞ ለጥቂቶች የሚተው፣ ወይም ለጥቂት ጊዜ የሚቀነቀን አጀንዳ አይደለም፤ እንደ ሀገር ተባብረን ልናሸንፈው የሚገባ የጋራ ጉዳያችን ነው።

ገልጠን፣ መርምረንና ለፍተንበት የምንለውጠው እንጂ ሸፋፍነንና ደብቀን ፈጽሞ ሊንሻገረው አንችልም። ያለን ምርጫ አንድ ነው፤ ተረባርበን ዘላቂ መፍትሄ መስጠት።

ባንኮች ባለፉት ሁለት አሥርት ዓመታት አርሶ አደሩና አርብቶ አደሩ የቆጠበውን ገንዘብ ተጠቅማችሁ የአገልግሎትና የግንባታው ዘርፍን ፋይናንስ በማድረግ በኩል ለውጥ እንዳመጣችሁ ሁሉ፤ ግብርናውንም ፋይናንስ በማድረግ የምትክሱበትን መንገድ መቀየስ አለባችሁ።

ከምርጥ ዘርና የግብርና ግብዓትና መሳሪያዎች አቅርቦት ጋር በተገናኘ መሥራት ለሚፈልጉ አካላት ልዩ ልዩ ማበረታቻዎችን መንግሥት ያዘጋጃል።

በኩታ ገጠም የሚያርሱ አርሶ አደሮችም ሆኑ በሠፋፊ የመስኖ ግብርና ላይ የሚሠማሩ የግል ኢንቨስተሮች በተለያዩ መንገዶች ይበረታታሉ።

ከዚሁ ጋር በተያያዘ፣ በአሁኑ ሰዓት በድርቅ ምክንያት እየተሰቃዩ የሚገኙ የሶማሌና የቦረና አርብቶ አደር ወገኖቻችን አፋጣኝ እርዳታችንን ይሻሉ።

በመኖና የውሃ እጦት ከብቶቻቸው እየረገፉ ነው። ድርቁ ያስከተለው ርሃብ የሕጻናቱንና የአረጋውያኑን ሕይወት እያሳጣ ነው። ክረምቱ እስኪደርስላቸው እንጠብቅ ከተባለ ብዙ ወገኖቻችንን እናጣለን።

ለድርቅና ርሃብ ዘላቂ መፍትሔ ለመስጠት እየተረባረብን፣ አፋጣኝ ምላሽ ለሚሹ ወገኖቻችንም አቅማችን የፈቀደውን እንድናደርግ በዚሁ አጋጣሚ ጥሪዬን አቀርባለሁ።

**ኢትዮጵያ በልጆቿ ጥረት ታፍራና ተከብራ ለዘላለም ትኑር!!**
**ፈጣሪ ኢትዮጵያና ሕዝቦቿን ይባርክ!**
የካቲት 18 ቀን 2014 ዓ.ም

# እንኳን ለዐድዋ ድል 126ኛ ዓመት አደረሳችሁ

ጀግኖች እናቶቻችንና አባቶቻችን ቅኝ ተገዥነትንና ባርነትን፣ የበታችነትንና ውርደትን እምቢ ብለው ታሪክ የሠሩበትን የዐድዋ ድል በዓል ለማክበር በመቻላችን ዕድለኞች ነን፡፡ በዓሉ ነጻ የወጣንበት አይደለም፡፡ ነጻነታችን እንዳይደፈር በክንዶቻችን ያስጠበቅንበት እንጂ፡፡ እኛ የነጻነት በዓል የለንም፤ የድል በዓል እንጂ፡፡ ይህ ምን ጊዜም ስንኮራበት የምንኖር ታሪካችን ነው፡፡

የዐድዋ ድል አፍሪካውያን፣ እስያውያንና ደቡብ አሜሪካውያን የባርነትን ቀንበር እንዲሰብሩ፤ የቅኝ ግዛትን ሸክም እንዲያስወግዱ፤ የበታችነትን ፖሊሲ እንዲያስቀይሩ አድርጓቸዋል፡፡ የዐድዋ ድል በጥቁርና በነጭ መካከል የነበረውን የተበላሸ ትርክት የቀየረ፤ የጥቁር ሕዝቦችን ማንነት ያስመሰከረ ገድል ነው፡፡ ኢትዮጵያን መንካት የሚያስከትለው መዘዝ ምን እንደ ሆነ አስተምሮ ያለፈ ደማቅ ሐውልት ነው፡፡

የዐድዋ ድል ውድ ገንዘብ ነው፡፡ ወደ ብዙ ነገሮች ሊመነዘር የሚችል፡፡ ጥያቄው ግን ‘ይሄን ውድ ገንዘብ ለተገቢው ነገር መንዝረን ተጠቅመንበታል ወይ?’ የሚለው ነው፡፡ ኋላ ቀርነትን ለማስወገድ፤ ድህነትን ለማጥፋት፤ ረሃብን ከመገለጫነት ለማስቀረት፤ ዴሞክራሲንና ፍትሕን ለማስፈን፤ አንድነትንና ወንድም/እኅትማማችነትን ለማጽናት፣ ያደረግነውን ጥረትና ያገኘነውን ስኬት ስንመዝነው፣ የዐድዋ ድል በተገቢው መንገድ ተመንዝሮ ጥቅም ላይ እንዳልዋለ ያሳየናል፡፡

ባርነትንና ቅኝ ተገዥነትን፣ የበታችነትንና ውርደትን እምቢ ብለን የከፈልናቸው መሥዋዕትነቶች በሀገራችን ሉዓላዊነት፣ ክብርና ነጻነት ላይ ወሳኝ ለውጥ አምጥተዋል፡፡ የማትደፈር፣ በነጻነቷ ዘለዓለም የምትኖርና ሉዓላዊት የሆነች ሀገር እንድትኖረን አድርገዋል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ ከእነዚህ እኩል እምቢ ልንላቸው የሚገቡን ነገሮች ነበሩ፡፡ እነርሱን እምቢ ባለማለታችን ታሪካችንና ጉዟችን ምርቅና ፍትፍት እንዲሆን አድርጎታል፡፡ ነጻነታችን፤ ድላችን፣ ክብራችንና ኩራታችን ሙሉ እንዳይሆን አድርጎታል፡፡

የቅኝ ግዛትና የባርነትን ያህል - ድህነትና ኋላ ቀርነትን ለምንድን ነው አምርረን ያልታገልነው? የበታችነትና የውርደትን ያህል ረሃብንና ኢዴሞክራያዊነትን ለምንድን ነው መሥዋዕትነት ከፍለን አሽቀንጥረን ያልጣልነው? በቅኝ ከመገዛትና በባርነት ከመማቀቅ የሚታደጉን ጀግኖች የጦር መሪዎችን ያፈራነውን ያህል፣ በድህነትና በኋላ ቀርነት ከሚመጣ ውርደት የሚታደጉን መሪዎች ያላፈራነው ለምንድን ነው? በቅኝ ገዥዎቻችን ላይ አንድ ሆነን የተነሣነውን ያህል በድህነትና በኋላ ቀርነት ላይ አንድ ሆነን ለመነሣት ያልቻልነው ለምንድን ነው? ባርነትን እንመረራለን፤ ቅኝ ተገዥነትን እንጸየፋለን፤ ከእነዚህ ጋር ለአንድ ቀንም ውለን ለማደር ፈቃደኞች አይደለንም፡ ፡ ታድያ ከኋላ ቀርነትና ለድህነት ጋር ለሺህ ዘመናት ለመኖር እንዴት ቻልን? ለምን አላንገሸገሹንም? ለምን አላስመረሩንም? አንድ ሆነን ያገኘነውን የዐድዋ ድል ተከፋፍለን እንዴት እናከብረዋለን?

ቅኝ ገዥዎችን ያሳፈርንባቸው፤ ወራሪዎችን የቀጣንባቸው የድል ቀናት ሞልተውናል፡ ፡ እየደጋገመ የሚያጠቃንን ድርቅና ረሃብ፤ እጅ ተወርች ያሠረንን ኋላ ቀርነት፣ ዛሬም ስንዴ እንድንለምን የሚያደርገንን ድህነት የቀጣንባቸውን የድል ቀናት የምናከብረውስ መቼ ይሆን?

እኛ ስለ ዐድዋ ስንናገር - እነርሱ ስለሚረዱን እህል፤ እኛ ስለ ማይጨው ስንተርክ - እነርሱ ስለሚሰጡን ርዳታ፤ እኛ ስለ ካራማራ ስናወራ - እነርሱ ስለሚሰደዱት ወገኖቻችን፤ እኛ ስለ ዶጋሊ ድል ስንኮራ - እነርሱ ስለ ሕጻናት መቀንጨር እየነገሩን ይገዳደሩናል፡፡ በጀግኖች እናቶቻችንና አባቶቻችን ገድል እንዳንኮራ በሰነፎቹ ልጆቻቸው ምክንያት ሊያሸማቅቁን የሚፈልጉ ብዙዎች ናቸው፡፡ ይሄ ነው ታሪካችንን ምርቅና ፍትፍት ያደረገብን፡፡

የዐድዋ ድል ልጆች ሆይ!

የዐድዋን ድል እንደ ውድ ገንዘብ መንዝረን መጠቀም ከፈለግን፣ ሐሳባችንንም፣ ብዕራችንንም፣ ዕውቀታችንንም፣ክህሎታችንንም፣ ጉልበታችንንም ሦስት ነገሮችን በዋነኛነት ለማጥፋት እናውላቸው፡፡ ድህነትን፣ ኋላ ቀርነትንና መከፋፈልን፡፡ እነዚህ ሦስቱ ጠላቶቻችንን በዐድዋ ገጥመን እንዳሸነፍናቸው አፍረው ከተሸነፉ፣ ኢትዮጵያ

በቀድሞ ጀግኖቿ የምትኮራ ብቻ ሳትሆን፣ በአዲሶቹ ጀግኖቿም በክብር የምትጠራ ሀገር ትሆናለች፡፡ የመጀመሪያውን ዐድዋ በክብር የሚያስጠራው ሁለተኛው ዐድዋ ነው፡፡ ሁለተኛው ዐድዋ ደግሞ በሦስቱ የኢትዮጵያ ዋና ዋና ጠላቶች በድህነት፣ በኋላ ቀርነትና በመከፋፈል ላይ የሚደረገው ዘመቻ ነው፡፡ እነዚህን ድል ካደረግን ሌሎች ችግሮች ሁሉ በእነዚህ ትከሻ ላይ የተቀመጡ ናቸውና በራሳቸው ጊዜ ድል ይሆናሉ፡፡

የዐድዋ ድል 126 ዓመት ሆነው፡፡ እነዚህ ሦስቱ ጠላቶቻችን ከዐድዋም በፊት ነበሩ፡፡ አሳዛኙ ነገር ግን ከዐድዋ ድል በኋላም መቀጠላቸው ነው፡፡ ብረትን መቀጥቀጥ እንደ ጋለ ነው ብለን በፋሺዝም ላይ የሰነዘርነውን በትር ወደ እነርሱ አዙረነው ቢሆን ኖሮ፣ ዛሬ ኢትዮጵያ በሁለመናዋ የበለጸገች ሀገር በሆነች ነበር፡፡ በድህነትና በኋላ ቀርነት ውስጥ ሆነን፤ ከዚያም ብሶ ተከፋፍለንና ተለያይተን ቀጣዮቹን የዐድዋ ድል በዓላት ማክበር የለብንም፡፡ 130ኛውን፣ 140ኛውንና 150ኛውን
የዐድዋ ድል በዓል፣ በበለጸገችው ኢትዮጵያ ዐደባባዮች፣ በኅብረ ብሔራዊ አንድነት ጸንተን እንድናከብራቸው የመቁረጫው ጊዜ አሁን ነው፡፡ ዐድዋና ኋላ ቀርነት፤ ዐድዋና ድህነት፤ ዐድዋና የእርስ በእርስ መከፋፈል አብረው አይሄዱም፡፡ ጨለማና ብርሃን ናቸው፡፡

**መልካም የድል በዓል ይሁንልን!**

**ኢትዮጵያ በልጆቿ ጥረት ታፍራና ተከብራ ለዘላለም ትኑር !!**
**ፈጣሪ ኢትዮጵያና ሕዝቦቿን ይባርክ !**

**ጠቅላይ ሚኒስትር ዶ/ር ዐብይ አህመድ**
የካቲት 23 ፣ 2014 ዓ.ም

# የብሔራዊ ምክክሩ አሳታፊነት የሚሳካው ሁሉም ኢትዮጵያዊ በቀናነትና በባለቤትነት ሂደቱን መደገፍ ሲችል ነው

ኢትዮጵያ በተለያዩ ዘመናት ታሪክ የሚቀይሩ ወርቃማ የለውጥ ዕድሎች ገጥመዋታል። ፖለቲካችንን አንድ ደረጃ ወደፊት የሚያስፈነጥሩና ቀጣይ ዘመናችንን ብሩህ የሚያደርጉ አያሌ የለውጥ ችቦዎች ተለኩሰዋል። እነዚያ ለውጦች የሚያመሳስላቸው አንድ ነገር አለ፤ ቁጭት። በቁጭት ተጠንስሰው፣ በቁጭት ተካሂደው፣ በቁጭት ይጠናቀቃሉ። አብዛኛውን ጊዜ የለውጥ ምዕራፎች በሚጀምሩበት ወቅት የምንሰንቃቸው የለውጥ ሐሳቦች ዳር ከመድረሳቸው በፊት ሲኮሰምኑ በተደጋጋሚ አይተናል። በለውጥ በሂደት ወቅት ግባችንን ለማሳካት ከመተባበር ይልቅ በጥቃቅን ጉዳዮች እርስ በእርስ መጓተቱን ስለምናስቀድም በመጀመሪያ ያስጎመጀ የነበረው የለውጥ ፍሬ በመንገዱ መሐል ተጨናግፎ ይቀራሉ። መጨናገፋቸውን ልብ የምንለው ዘግይተን በመሆኑ ዕድሎቹ ካለፉ በኋላ እንደ ሀገር መልሰን እንቆጭባቸዋለን።

እኛ የቀደመውን ትውልድ “ይሄንና ያንን ቢያደርግ ኖሮ” እያልን እንደምንወቅሰው ሁሉ፣ የቀደመው ትውልድም ከእሱ በፊት የነበረውን ትውልድ ሲኮንን ነበር። ከዚህ የታሪክ አዙሪት ለመውጣት እስካልወሰንን ድረስ ነገ የእኛም ዕጣ ካለፈው የተለየ አይሆንም። ዛሬ በቸልታ የምናልፋቸው አጋጣሚዎች ተደምረው ነገ ላይ የልጅ ልጆቻችን እኛን የሚወቅሱበት ምክንያት ይሆናል። ይህ እንዳይሆን ዛሬ እጃችን ላይ የሚገኙ የለውጥ ዕድሎችን ሁሉ አሟጥጠን ለመጠቀም መረባረብ አለብን።

ለዘመናት እየተንከባለሉ ዛሬ ላይ የደረሱ የፖለቲካ ፈተናዎቻችንን በጉልህ መቅረፍ የሚያስችለንና መጻዒ ዘመናችንን አዲስ መሠረት ላይ የማቆም ዐቅም ያለው ብሔራዊ የምክክር ሂደት ዛሬ በእጃችን ላይ ያለ ወርቃማ ዕድል ተደርጎ ሊወሰድ ይችላል።

ይህን ወርቅ የሆነ አጋጣሚ የስንት ልፋት እና የስንት ታሪክ ሂደት ውጤት መሆኑን ዘንግተን እንደ ጠጠር ከቆጠርነው በቀላሉ ልናጣው እንችላለን። በተቃራኒው እንደ ዕንቁ አክብረንና ተከባክበን ከተጠቀምንበት ዋጋው ከፍ ያለና ታሪክ ቀያሪ ዕድል ይሆናል። ልጆቻችንም "አባቶቻችን እንዲህ በማድረጋቸው ሀገራችን እዚህ ከፍታ ላይ ደርሰች" ብለው የሚያመሰግኑበትን አጋጣሚ ይፈጥራል።

አካታች ብሔራዊ ምክክሩ ስኬታማ እንዲሆን ሒደቱ ተቀባይነት ያለው ሆኖ መከናወን አለበት። ይኸም የሚሆነው ሁላችንም የምክክር ሂደቱን በበላይነት የሚመራውን የምክክር ኮምሽን በተለያዩ መንገዶች መደገፍ፣ ማትጋትና ማጽናት ስንችል ነው። በዚህ ጉዳይ ዳር ቆሞ መገኘት በታሪክ ፊት የሚያስወቅስ ተግባር ነው። ሁሉም አካል በባለቤትነት ስሜት ለምክክር ሂደቱ አስተዋጽዖ በማድረግ ተሳትፎውን ያረጋግጣል እንጂ አንዱ ጋባዥ ሌላው ተጋባዥ እንደሆነ አድርጎ መቁጠር ከታሪክ ተጠያቂነት ነጻ አያደርግም።

በመንግሥት በኩል እስከ ታችኛው የአስተዳደር መዋቅር ድረስ የተቋቋመው የምክክር ኮሚሽን በቅልጥፍና መሥራት እንዲችል አስፈላጊውን ሁሉ ድጋፍ ከማድረግ ወደ ኋላ አይልም። የክልል መስተዳደሮች ቀናነት፣ ባለቤትነትና ታሪካዊ ኃላፊነት በተሞላበት ሁኔታ ለኮሚሽኑ ሥራ አስፈላጊ የሆነውን ግብአት በማቅረብ ለሥራው ምቹ ሁኔታ ሊፈጥሩ ይገባል። ተፎካካሪ ፓርቲዎች በውይይቱ እንደሚሳተፍ ብቻ ሳይሆን እንደ ሂደቱ ባለቤት ለሂደቱ ቅልጥፍናና ስኬት አስፈላጊውን ሁሉ እንድታደርጉ በትኅትና እጠይቃለሁ።

ምሁራን ኮሚሽኑ አስተያየትና ምክረ ሐሳባችሁን በሚፈልግበት ጊዜ ብቻ ሳይሆን በቅድሚያ ተነሣሽነት፤ የሂደቱ ንቁ ተሳታፊ በመሆን የታሪካዊ ጉዟችን እና የዘመን አሻራችን ለሆነው ምክክር አስተዋጽዖዋችሁ የላቀ እንዲሆን እማጸናለሁ። የሃይማኖት አባቶችና የሀገር ሽማግሌዎች ሀገር ስምምነትን በምትፈልግበት በዚህ ወቅት አማካይ ሆናችሁ ሁሉን የማስማማት አደራ አለባችሁና የመቀራረቢያውን መድረክ በማገዝ ሀገራዊ ግዴታችሁን እንድትወጡ ከልብ በመነጨ ትኅትና እጠይቃለሁ።

የሁሉም ኃላፊትነት ተደምሮ የሚወድቀው በሀገርና በሕዝብ ትከሻ ላይ ነው። ሁላችንም ልዩነቶቻችንን አቻችለን በኃላፊነት ስሜት መንቀሳቀስ አለብን።

ሕዝብ ያላከበረው እና ሕዝብ ያልደገፈው እንቅስቃሴ ውጤቱ መና ነውና መላ ኢትዮጵያውያን ድጋፋችሁ፣ ተሳትፏችሁ፣ክብራችሁና ጸሎታችሁ ከኮሚሽኑ እንዳይለይ ከታላቅ አክብሮት ጋር እጠይቃለሁ።

**ኢትዮጵያ በልጆ ጥረት ታፍራና ተከብራ ዘላለም ትኑር!**
**ፈጣሪ ኢትዮጵያና ሕዝቦቿን ይባርክ**
መጋቢት 23 ቀን 2014 ዓ.ም.

# እንኳን ለብርሃነ ትንሣኤው በሰላም አደረሳችሁ

የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስን ትንሣኤ ስናስብ ቀድሞ ወደ አዕምሯችን የሚመጣው ክህደት፣ ሤራና ፍርደ ገምድልነት ለጊዜው ያሸነፉ ቢመስሉም በመጨረሻ እንደሚሸነፉ ነው። ትንሣኤው ተበስሮ እውነትና ደግነት ድል አድርገው እስኪታዩ ድረስ፣ ክፋትና ውሸት እንደ ቋጥኝ ገዝፈው ታይተዋል፣ እንደ ተራራ የማይነቀነቁ ሆነው ቆይተዋል።

የኢየሱስ ክርስቶስ ትንሣኤ የአራት ወገኖችን ሤራ ያፈረሰ ነው። በቃሉ ትምህርት በእጁ ተአምራት ያልተደሰቱ፤ የአዳምን ጥፋት እንጂ የአዳምን ድኅነት የማይፈልጉ፤ በእነርሱ መንገድ ካልሆነ በቀር ምንም ነገር ለመቀበል ፈቃደኞች ያልሆኑ አራት ወገኖች የሠሩት ወጥመድ በትንሣኤው ተወግዷል። የሤራው ጠንሳሽ ጥንተ ጠላት ዲያብሎስ ነው። እርሱ የሰው ልጆች የጥንት ጠላታቸው ነው። ምንም ቢሆን በሰው ልጆች ላይ ያለውን አቋም አይቀይርም። የሰው ልጆች እርሱ በሚፈልገው የክፋትና የስሕተት መንገድ ቢሄዱለት እንኳን፣ ለሰው ልጅ ጠላት መሆኑን አይቀይረውም።

ዓላማው የሰውን ልጅ ማጥፋት እንጂ ከሰው ልጅ ጋር ወዳጅነት መፍጠር አይደለምና። የሰውን ልጅ ከምድረ ገጽ ለማጥፋት የታቀዱ የጥፋት ወጥመዶችን ሁሉ የዘረጋው፣ አባሪ ተባባሪ ፈልጎ ሰውን ከፈጣሪው ለመለየት፣ ሰውን እርስ በርሱ ለማጋጨት፣ ኑሮውንም የጨለማና የመከራ ለማድረግ ሲሠራ የኖረው ዲያብሎስ ነው።
ብዙ ጊዜ ግን እርሱ በግልጥ አይታይም። አሠራሩንና አካሄዱን የሚያውቁ፤ የሐሰትና የክፋት አባት መሆኑን የተረዱ፤ የመልካም ነገር ሁሉ ጠላት መሆኑን የተገነዘቡ ብቻ ተንኮሉንና ክፋቱን ያውቁበታል። ሌሎች ግን እርሱ ባጠመደው ወጥመድ ወድቀው ከገዛ ወገኖቻቸው ጋር ሲጋጩና ሲፋጩ ይገኛሉ። ጦሩን ከሚሰብቀውና ቀስቱን ከሚወረውረው ጋር ሳይሆን፣ ከቀስቱና ከጦሩ ጋር ይገጥማሉ።

ዲያብሎስ ኢየሱስ ክርስቶስን ለመስቀል ሦስት ተላላኪዎችን አሠማርቶ ነበር። እነዚህ ሦስት ተላላኪዎች ከዚያ ቀን በፊት እርስ በርሳቸው የማይስማሙ፤ አንድ ዕቅድ ዐቅደው፣ አንድ ሥራ ሠርተው፣ ለአንድ ግብ ሊሠማሩ የማይችሉ ናቸው። ዲያብሎስ ያደረገው አንድ ነገር ነው። የጋራ ጠላት ፈጠረላቸው። የጋራ ዓላማ ግን አልፈጠረላቸውም። ጠላታቸውን የሚያጠፉበት ምክንያት የተለያየ ነው። ጠላታቸውን ለማጥፋት ያላቸው ፍላጎት ግን አንድ ነው።

ዲያብሎስ ሦስቱን ሲያሠማራ የራሱ ዓላማ ነበረው። እርሱም የሰው ልጅን ድኅነት ማስቀረት ነው። ሦስቱም ተላላኪዎች ሳያውቁት የዚህ ዓላማ ፈጻሚዎች ናቸው። እነርሱ ግን ለየራሳቸው ዓላማ የተሠማሩ መስሏቸው ነበር። የሚገርመው ነገር፣ በመጨረሻ ሦስቱም ተላላኪዎች ጠፍተዋል። ቢሸነፍም ያልጠፋው የላካቸው ዲያብሎስ ነው። ምንጊዜም የጥፋት ተላላኪ ዕጣ ፈንታው ይሄ ነውና። ዲያብሎስ የአዳምን ድኅነት ለማስቀረትና በምድር ላይ ብቸኛ ገዥ ሆኖ ለመኖር ሦስት አካላትን ለጥፋት አሠማራ። ይሁዳ፣ የአይሁድ ካህናትና ሮማውያን። ይሁዳ ዓላማው ገንዘብ ነው። ገንዘብ እስከሰጡት ድረስ ራሱንም ጭምር ለመሸጥ ዝግጁ ነበር። ኢየሱስ ክርስቶስ የሰጠው የሐዋርያነት ክብርና ሥልጣን ለእርሱ ምኑም ነው። ዋናው ገንዘብ ነው። በአንድ ወቅት አንዲት ሴት ያመጣችው ሽቱ ተሸጦ ለድኾች እንዲሰጥ ሐሳብ አቀረበ። አልተሳካለትም። የሽቱው ዋጋ 300 ዲናር ነበር። ቢሸጥ ኖሮ ከዐሥር አንዱን 30 ብር ያገኝ ነበር። ያ ሲቆጨው ነው የኖረው። ዲያብሎስ የተጠቀመበት ይሄን ጤናማ ያልሆነ የገንዘብ ፍላጎቱን ነው። በዚህ የተነሣ ክርስቶስን በ30 ብር ለመሸጥ ተስማማ።

የአይሁድ ጥያቄ ደግሞ የጥቅም ጥያቄ ነው። ለብዙ ዘመናት ሕዝቡን እየበዘበዙ ሲጠቀሙበት ኖረዋል። እነርሱ ብቻ ዐዋቂና ፈራጅ ሆነው ሲጠቀሙ ኖረዋል። አሁን ለድኾች የሚያስብ፣ ከኃጢአተኞችና ከምስኪኖች ጋር የሚውል፤ ለደካሞች የሚራራ፤ ለሰው ልጅ ክብር ሲል የራሱን ክብር የሚተው መምህርና ጌታ መጣባቸው። ሕዝቡ የሚጠቅመውን ዐወቀ። በዘርና በቋንቋ፣ በአኗኗርና በሀብት ተለያይተው የነበሩትን አንድ አደረጋቸው። ሰው የአይሁድን ካህናት መከተሉን ትቶ ክርስቶስን ተከተለ። ይህ ነገር ጥቅማቸውን ነካው። በዚህ ምክንያት ከቅኝ ገዥዎቻቸው ጋር መተባበርን መረጡ።

ሮማውያን በዚያን ጊዜ መካከለኛው ምሥራቅን በቅኝ ይገዙ ነበር። አይሁድ ሮማውያንን በጠላትነት ነበር የሚያዩዋቸው። ነጻነታቸውንና ማንነታቸውን የቀሟቸው ጠላቶቻቸው ናቸው። ሮማውያን በሕዝቡ ላይ አያሌ ግፎችን ፈጽመዋል። የአይሁድ ካህናት ግን ከክርስቶስ ይልቅ ገራፊዎቻቸውንና አሣሪዎቻቸውን መረጡ። ሮማውያን በክርስቶስ ላይ የተነሡበት ዓላማቸው የሥልጣን ጥያቄ ነው። ኢየሱስ ክርስቶስ ለሕዝቡ የነጻነትን ወንጌል አስተማራቸው። አዲስ ሕይወትና አዲስ መንገድ ነው አሳያቸው። ይህ የሮማውያንን ሥልጣን የሚነቀንቅ መስሎ ተሰማቸው። ስለዚህም ከአይሁድ ጋር ተባበሩ።

ከሁሉም ኋላ ሆኖ የጥፋት ወጥመዱን የሚያጠምደውና፣ የጥፋት መንገዱን የሚያዘጋጀው ዲያብሎስ ለሦስቱም የሚፈልጉትን እየነገረና እያሳየ፣ ሦስቱንም ለራሱ የጥፋት ዓላማ አሠማራቸው። እነርሱ ግን ለየራሳቸው ዓላማ የሠሩ መስሏቸው ነበር። የዲያብሎስ ዕቅዱ የርሱን ዓላማ አሳክቶ እነርሱ አጨብጭበው እንዲቀሩ ማድረግ ነው። ይሁዳ እየመራ፣ የአይሁድ ካህናት ሕዝቡን አሳምጸውና ሽብር ፈጥረው፣ ሮማውያን ደግሞ ሥልጣናቸውን ተጠቅመው በክርስቶስ ላይ ይሙት በቃ ፈረዱ። እርሱም በመስቀል ተሰቅሎ ሞትን ተቀበለ።

የትንሣኤው ብርሃን የላኪውንም የተላላኪዎቹንም ተንኮል አፈረሰው። ወጥመዳቸውንም በጣጠሰው። ኢየሱስ ክርስቶስ ሙስናና መቃብርን አጥፍቶ በሦስተኛው ቀን ተነሣ። የዲያብሎስና የሦስቱ የጥፋት ተላላኪዎች ተንኮል የተሳካው ለሦስት ቀናት ብቻ ነው። ይሁዳም 30 ብሩን ሳይጠቀምበት ታንቆ ሞተ። የአይሁድ ካህናትም እንኳንስ ሊሳካላቸው በ70 ዓመተ ምሕረት ሀገራቸውን ጥለው ለሺ ዓመታት ተሰደዱ። ሮማውያንም ቀስ በቀስ ግዛቶቻቸውን እየለቀቁ ዛሬ የደረሱበት ደረሱ። ኢየሱስ ክርስቶስ ግን ዛሬም አለ። የትንሣኤው በዓል ይሄንን ነው የሚመሰክርልን።

ይሄን ነገር በሀገራችን በኢትዮጵያ አንጻር መመልከቱ መልካም ነው። ዛሬም ከኋላ ሆኖ ሀገራችንን ለማፍረስ ወጥመድ የሚያጠምድ፣ ተንኮል የሚሠራው ጠላት ማነው? ዓላማው ይህችን ሀገር ማጥፋት ብቻ የሆነ፤ ሊያጠፋን እንጂ ሊወዳጀን የማይፈልገው ጠላት ማነው? ምንም ብናደርግለት ይህችን ሀገር ካላጠፋ በቀር የማይረካው ማነው? ይህ ጥንተ ጠላት የሚያሠማራቸው የጥፋት ተላላኪዎቹስ እነማን ናቸው? አንዳንዶቹ ለገንዘብ፣ ሌሎቹ ለጥቅም፣ ሌሎቹም ለሥልጣን ብለው ከዚህ ጥንተ ጠላት ጋር አብረው የሚሠሩት እነማን ናቸው? እነዚህ የጥፋት

ተላላኪዎች የራሳቸውን ፍላጎትና ዓላማ የሚያሳኩ መስሏቸው ይሆናል። ካሳኩም የሚያሳኩት እነርሱን ጭምር ሊያጠፉቸው የሚፈልገውን የኢትዮጵያን ጥንተ ጠላት ፍላጎት ብቻ ነው።

ይሁዳም ከሥሯል፤ የአይሁድ ካህናትም ከሥረዋል። ሮማውያንም ከሥረዋል። የጥፋት ተላላኪዎች መጨረሻ እንደዚህ ነውና። ለጊዜው የማይገናኙ ተገናኝተው፤ የማይተባበሩ ተባብረው፤ አጥፊና ጠፊ ተወዳጅተው፣ በክርስቶስ ላይ ሲነሡ፤ ለጊዜው የተሳካላቸው መስሏቸው ነበር። መጨረሻው ግን ኪሣራ ነው። ኢትዮጵያን ለማጥፋት የተነሡ ሁሉ ለጊዜው የሚሳካላቸው ይምሰላቸው እንጂ መጨረሻቸው ኪሣራ ነው። ጥቂት ቀናት የተሳካላቸውና ያሸነፉ ቢመስላቸውም ኢትዮጵያ ሞተው እንደሚቀሩ ሀገራት አይደለችም። ከሙታን ትነሣለች። ጠላቶቿንም ታሳፍራለች። አሳፍራም ታከሥራለች።

**በድጋሜ መልካም የትንሣኤ በዓል!**
**ኢትዮጵያ በልጆቿ ጥረት ታፍራና ተከብራ ለዘላለም ትኑር!!**
**ፈጣሪ ኢትዮጵያና ሕዝቦቿን ይባርክ!**
ሚያዚያ፣ 15 ቀን 2014 ዓ.ም.

# እንኳን ለዒድ አል ፈጥር በዓል በሰላም አደረሳችሁ

ፈጣሪ ለሰው ልጆች ደስታ ሲል የሰጠውን የዒድ በዓል መላው ሕዝበ ሙስሊም በሐሴት ያከብረዋል። የደስታው ምንጭ መብላት መጠጣቱ፣ መልበስና ማጌጡ አይደለም፤ ከራስ ባለፈ ከሌሎች ጋር በአብሮነት ማሳለፉ እንጂ። ሕዝበ ሙስሊሙ ያሉትን መልካም ነገሮች ይዞ እርስ በእርሱ እየተጠያየቀ፣ አብሮነቱንና አንድነቱን የሚያሳይበት፣ ያለው ከሌለው የሚረዳዳበት፣ ያገኘው ካላገኘው ምግብና ፍቅርን ተጋርቶ የሚያሳልፍበት ዕለት ነው።
እነዚህ እሴቶችና የበዓሉ ትሩፋቶች ከእምነቱ ተከታዮች ባለፈ ለሌሎችም መትረፍ የሚችሉ ናቸው።

ከዒዱ አስቀድሞ ሙስሊሙ ወር ሙሉ ከክፉት ርቆ ደግትን ይለምዳል፤ ከዓለማዊ ተግባር ርቆ መልአይካዎችን ይመስላል። መላአክት አይበሉም፤ አይጠጡም፤ በፍጹም ልባቸው የፈጣሪን ትዕዛዝ ይፈጽማሉ። ሕዝበ ሙስሊሙም በረመዳን ወር ከዚህ የተለየ አያደርግም። ወሩ አላህ (ሱወ) እጅግ ውድ ስጦታዎቹን የሰጠበት፣ ቁርአን ወደ ምድር የወረደበት፣ የጀሃነም በሮች ተዘግተው የጀነት በሮች የተከፈቱበት፣ አማኙ እንደ እምነቱ ጽናትና እንደ አላህ (ሱወ) እዝነት ምናዳዎችን የሚያገኝበት የተቀደሰ ወር ነው።

በቁርአን አማኙ ከፈጣሪው ጋር ተነጋግሯል፤ የሚበጀውን የሕይወት መንገድ መርጦ እንደ ፈጣሪው ትእዛዝ ለመኖር ዕድል አግኝቷል። በስግደት፣ በጸሎት፣ በደግ ሥራና በእዝነት ወደ ፈጣሪ ቀርቦ በጥሞና የሚያስብበት፣ ሁሉም ራሱን የሚመዝንበት የተባረከ ወቅት ነው - ረመዳን። በዚህ ምክንያት የረመዳን ወር ሲጠናቀቅ ሕዝበ ሙስሊሙ ወሩ አለቀልን ከማለት ይልቅ አለቀብን ማለትን ያስቀድማል። ይኽ ቅዱስ ወር በሕይወቱ ውስጥ ዳግም የሚመጣበትን አጋጣሚ እየናፈቀም ይቆያል።

ለዚያም ነው የረመዳን ወር በሕዝበ ሙስሊሙ ዘንድ እጅግ ታላቅ ቦታ ከሚሰጣቸው ወሮች መካከል ቀዳሚው የሆነው። የረመዳን ጾም ደምቆ እንደተጀመረ ሁሉ በድምቀት አልቆ እነሆ ለዒድ አል ፈጥር በዓል ደርሰናል። ሁላችንንም እንኳን አደረሰን!
የዘንድሮው ረመዳን በኢትዮጵያ ፍቅርና ሀገራዊ አንድነት የታየበት ሆኖ በማለፉ ከመቼም ጊዜ የተለየ ተደርጎ በታሪክ ሲታወስ ይኖራል። "ከዒድ እስከ ዒድ" የተሰኘው ሀገራዊ ንቅናቄ ብዙዎችን ከመላው ዓለም አሰባስቦ በእናታቸው ቤት፣ በወገናቸው መሐል እንዲያሳልፉ ዕድል ፈጥሯል።

ከመዲና ከተማችን ጀምሮ በክልል ከተሞችና በየቀየው በተዘጋጁ የጎዳና ላይ የኢፍጣር ፕሮግራሞች ወንዱ - ሴቱ፣ ሙስሊሙ - ክርስቲያኑ፣ ትንሹ-ትልቁ ኅብረትና አንድነቱን አሳይቷል። ኢትዮጵያም በልጆቿ ወንድማማችነት ደስ ተሰኝታለች።

ፈጣሪም የሚፈልገው ይኼንን ነው። በቅዱስ ቁርአኑ ላይ በግልጽ እንደሰፈረው "ልቦቻችሁን የሰበሩ ጠላቶቻችሁ ቢሆኑም እንኳ በአላህ ፈቃድ ወንድም ሊሆኑዋችሁ ይችላሉ» በማለት ሁሉም የአደም ልጆች በአንድነት ሳይከፋፈሉ እንዲያምኑ፣ ፈጣሪ ያደረገላቸውንም እንዲያስታውሱ፣ በሰው ልጆች መሐል ፍቅርና መረዳዳት እንደሚያስፈልግ አበክሮ ይገልጻል። የቱንም ያህል የሐሳብ ልዩነት ቢኖረን፣ በባህልና በወግ - በቋንቋና በልማድ ብንለያይ፣ ያለን አንድ ሀገር እስከሆነ ድረስ፣ እነዚህ ልዩነቶችን ተሻግረን ወንድማማችና እኅትማማች እንድንሆን፣ እርስ በእርስ እንድንተሳሰብ የፈጣሪ ትእዛዝ ያሳስባል። ‹የአላህ እጅ ሰብሰብ ብለው በአንድነት በቆሙ ሰዎች መካከል ይገኛል› የሚለው የእምነቱ አስተምህሮም ለዚህ ጥሩ ማሳያ ነው።

ውድ ወገኖቼ፣
በትንሽ በትልቁ እልህና ጠበኝነትን የሚቀሰቅሱ የሸይጣን እጆች በበዙበት በዚህ ወቅት ከሁላችንም የሚጠበቀው ትዕግሥትና ሰከን ብሎ ነገሮችን በጥሞና መመርመር ነው። የነብዩ መሐመድ (ሰዐወ) ሕይወት አበክሮ እንደሚያስገነዝበን የተመኙትን ለመጨበጥ፣ ከምንም ነገር በላይ ረጋ ብሎ ማሰብን ይጠይቃል። ማሰላሰል እና ትዕግሥት ይጠይቃል። በሐዲሳቸው ላይ እንደተጠቀሰው፣ ጥድፊያ እና ችኮላ ከሸይጣን ሲሆኑ፣ ማሰላሰል እና ትዕግሥት የአላህ ናቸው ብለዋል።

በቁርአንም ላይ “አላህ (ሱወ) ታጋሾችን ይወዳል” ተብሎ ተጽፏል። ነቢዩም በሌላ ሐዲሳቸው “ማንም ቢሆን፣ ከትዕግሥት የበለጠና የተሻለ በረከት ሊያገኝ አይችልም” ማለታቸው ተጠቅሷል። የታገሠ ሰው፣ ሥነ ሥርዓት ይኖረዋል። ራሱን ለመመዘንና ሌሎችን ለማየት ጥሞና ይኖረዋል። ነቢዩ መሐመድ (ሰዐወ) ለአንድ ሰዓት ያክል፣ ራስን በጥሞና ማየትና መመዘን 70 ዓመት ከመጸለይ የበለጠ ዋጋ እንዳለው ለተከታዮቻቸው አስተምረዋል። እኛም እንደ ሕዝብ ለውዲቷ ሀገራችን በጥሞና እንድንጸልይ፣ በሚዛናዊ ምልከታ እንድንራመድ፣ ለመልካምነትና ደግነት ራሳችንን እንድናስገዛ፣ የሸይጣን እጆችን በትዕግስትና በማስተዋል በትር እንድንረታ አበክሬ እጠይቃለሁ።

ሀገርን መገንባት እጅግ ብርቱ ድካም የሚጠይቅ መሆኑን ሁላችን እንረዳዋለን። በዐረብኛ ‹ከፍ ያለ ቦታ መድረስ የሚፈልግ ቢኖር ብዙ ሺህ ሌሊቶችን ሳይተኛ ማሳለፍ አለበት› የሚል ወርቃማ አባባል አለ። እኛም ከሌሎች አልባሌ ነገሮች ራሳችንን ቆጥበን፣ ዕውቀትና ጉልበታችንን ከፍ ያለ ቦታ ለመድረስ እናውለው።

ኢትዮጵያ፣ ገና አሁን ከጦርነት የወጣች ሀገር ናት። ከዚያ በፊት አንበጣና ኮሮና ጫና አሳርፎብን ነበር። እሱም ሳይበቃ ድርቅ ቁጥሩ ቀላል ያልሆነ ወገናችንን ክፉኛ ጎድቶታል። ብዙ ያጣነው ነገር አለና ስለጎደለብን መታገሥና በርትተን መሥራት እንጂ ተስፋ መቁረጥ የለብንም። መንግሥት የሚችለውን ሁሉ ያደረጋል። እናንተም ለሀገር ህልውና ሲሉ የተሠዉ ጀግኖችን ወደ ሕይወት መመለስ ባትችሉ በሕይወት ያሉትን መርዳት፣ ቤተሰባቸውን መደገፍ ይገባችኋል። ስለ መረዳዳት ለሕዝበ ሙስሊሙ ማስረዳት ለቀባሪው እንደ ማርዳት ተደርጎ እንደሚቆጠር ዐውቃለሁ። እናም ሰውን ከሰው ሳትለዩ፣ እከሌ ሙስሊም ነው ክርስቲያን ነው ሳትሉ፣ ከዚህና ከዚያ ወገን ብላችሁ አንዱን ከሌላው ሳትለዩ ዐቅማችሁ የፈቀደውን በማድረግ ለተጎዱ ወገኖቻችን እንድትደርሱላቸው በትኅትና እጠይቃችኋለሁ።

በድርቁም ሆነ በግጭቶች የተሰደዱትን ወገኖቻችንን ወደ ቀዬአቸው እንዲመለሱ እናግዛቸው። ከሥራቸው ለተፈናቀሉ ሥራ እንፍጠርላቸው። ቤት ለወደመባቸው ቤት እንሥራላቸው። ከብቶቻቸው የሞቱባቸውን አርብቶና አርሶ አደሮች እንደ ዐቅማችን እናግዛቸው። እምነት ሳይለያየን ሁላችንም ተባብረን የወደቀ ወገናችንን በማንሣት ለሀገርና ለሕዝብ ያለንን ፍቅር ለዓለም እናሳይ። ጠብን በፍቅር ስናሸንፍ፣

ከወደቅንበት ተጋግዘን ለመነሳት ስንጣጣር፣ እንደ አገር አስበን ስናደርግ ሰውም ፈጣሪም ደስ ይሰኛል። ከዒድ እስከ ዒድ፣ ሁላችንንም የሚመለከት የህዝብ በዓል፣ የሀገር በዓል ይሆንልናል። የዚህ በዓል በደመቀ ሁኔታ መከበር፣ የሁላችንም ድምቀት፣ የሁላችንም ክብር እንደሆነ ማወቅ ይገባናል።

በድጋሚ፣ እንኳን ለታላቁ የዒድ አል ፈጥር በዓል አደረሳችሁ፣ አደረሰን!!

ዒድ ሙባረክ!

**ኢትዮጵያ በልጆቿ ጥረት ታፍራና ተከብራ ለዘላለም ትኑር!!**
**ፈጣሪ ኢትዮጵያና ሕዝቦቿን ይባርክ!**

ሚያዚያ 23 ቀን 2014 ዓ.ም.

# እንኳን ለ1443ኛው ዓመተ ሒጅራ የዒድ አል አድሐ ዐረፋ በዓል በሰላም አደረሳችሁ፣ አደረሰን

የዒድ አል-አድሐ ዐረፋ በዓልን ስናስብ ቀድሞ ወደ አዕምሯችን የሚመጣው በመንፈሳዊውም ይሁን በሥጋዊው ዓለም ታላቅነት የሚመጣው በፈተና ውስጥ በጽናት ለማለፍ በመቁረጥ እንደሆነ ነው። ነብዩ ኢብራሒም በአላህ (ሱ.ወ) ታዝዘው ልጃቸው እስማኤልን ለመሰዋት ሲነሱ አጋጣሚው ለአባትም፣ ለልጅም ቀላል አልነበረም። እጅግ ከባድ የሆነ የስሜት ፈተና ሲገጥማቸው ነበር። ከአባትነት ስሜት ከሚመነጨው ፈተና ባለፈ፣ ጠላት ሸይጣንም፣ በእርጅና እድሜያቸው ያገኙትን ልጅ ለመሰዋት መዘጋጀታቸው ጅልነት መሆኑን እየጠቀሰ ከመንገዳቸው ሊያስቀራቸው በተደጋጋሚ ፈትኗቸዋል። ነብዩ ግን አልተረቱለትም። መስዕዋት የሚሆነው ልጃቸው እስማኤልም የገዛ ፍርሃቱን አሸንፎ፣ አባቱ የአላህን ትዛዝ እንዲፈጽሙ ሲያበረታቸው ነበር። የዘንድሮውን የዐረፋ በዓል የምናከብረው የሥነ ልቦና ጥንካሬአችን በሚፈተኑ አጋጣሚዎች መካከል ሆነን ነው። በአንድ በኩል ሰላማችንን የሚረብሹና ጦራቸውን ሰብቀው ሊወጉን አድብተው የሚጠብቁ ጠላቶች በተራቀቀ ሴራ አቅማችንን ሊያዳክሙ ይተጋሉ። በሌላ በኩል የሕዳሴ ግድብ ግንባታችን ወደ ሦስተኛውና ዋናው ምዕራፍ ለማሸጋገር ከጫፍ ደርሰን ተስፋውንና ጠላቶቻችን የደቀኑብን ስጋት በቅርብ ርቀት እየተመለከትን ነው።

ዐረፋ የመስዕዋት በዓል ነውና ይሄንን በዓል ከሙስሊም ዜጎቻችን ጋር ስናከብር መስዕዋት ለመሆን ፍላጎት ማሳየት ብቻውን እንደ ሀገር የሚገጥሙንን ፈተናና አደጋዎች ሊያስወግድልን እንደማይችል በማሰብ ነው። ያለንበት ወቅት እስከ መጨረሻው ጸንቶ መቀጠልን ይሻል። የእኛ አቋም መወላወል የሚጠቅመው ጠላቶቻችንን ነው። እኛን ለማሸነፍ ሌላ ቦታ መሄድ አይገባቸውም፤ ጦር መስበቅ፣ ነጋሪት መጎሰወም ሳይጠበቅባቸው እኛን ለማሸነፍ የእኛኑ አቋም መዋዠቅ ይጠቀማሉ። በእኛ መካከል የሚፈጠረው አለመግባባት ለእኛ የድክመታችን ምንጭ፣

ለጠላቶቻችን ደሞ አቅማቸውን የሚያሳድግ አጋጣሚን ይፈጥራል። ለውጥ ስንጀምር አብረውን ሊታገሉ፣ በጉዟችን ጽንተው ሊቆሙ፣ የመስዕዋትነት ጊዜው ሲደርስ አብረውን ሊሰዉ ፍላጎት ያሳዩ ብዙዎች ነበሩ። ሰበብ ፈልገው የተለዩን፣ አኩርፈው የቀሩ፣ የቁርጡ ቀን ሲደርስ ሽርተት ያሉ ሰዎች ቁጥራቸው ቀላል አይደለም። ልክ እንደ እስማኤል በአቋማቸው ጸንተው ዛሬም ለመሰዋት የማያመነቱ፣ በርትተው ሌሎችን የሚያበረቱ እውነተኛ የሀገር ልጆችም አሉ።

ውድ የሀገሬ ልጆች፣

ማንም ሰው በተፈጥሮው ክፉ ሆኖ አይፈጠርም። ከልጅነት እስከ እውቀት ክፋትን እየተማረ፣ ቀስ በቀስ ተንኮልና ጭካኔን እየለመደ ይመጣል እንጂ። በጊዜ ሂደት ከላይ በሚደርባቸው የክፋት ጋቢዎች ምክንያት ቀድመው የነበሩት ደግነትና ጥሩነት በልቡ ጓዳ ውስጥ በጥልቁ ተሰውረው ይቀራሉ። የሐይማኖት አስተምህሮዎች ዓላማም ተዳፍኖ የሚኖረውን ይሄን የሰውን መልካምነትና ደግ ጠባይ ከተደበቀበት ፈልፍሎ ማውጣት ነው። ለመልካም ተግባር የሚጸኑ ሰዎች በመንፈሳዊውም ሆነ በሥጋዊው ዓለም ትልቅ ሥፍራ ይሰጣቸዋል። ነብዩ ኢብራሒም ለሰው ልጆች ሁሉ አርአያ ከሚሆኑ ጻድቅ ሰዎች መካከል አንዱ ናቸው። በሕይወት ዘመናቸው ከልብ በመነጨ ስሜት ሰዎችን የሚወድዱ፣ ራሳቸውን ለእውነትና ለፈጣሪ የሰጡ፣ በደግነት የሚያስተናግዱና ካላቸው ላይ ከፍለው ለሰዎች የሚያጋሩ ነበሩ። ከነብዩ ኢብራሒም መልካምነትን ተምረን የዐረፋን በዓልና ከዚያ በኋላ ያሉ ቀኖችን በመተጋገዝና መደጋገፍ እንድናሳልፍ ይጠበቃል።

ሕዝበ ሙስሊሙ ብቻ ሳይሆን ሌላውም ሕዝባችን በመረዳዳትና በመተሳሰብ ኢትዮጵያን ከፈተና አውጥተን ወደ ምናስበው ስኬት ልናበቃት ይገባል። በቀና ልቦና አቅማችን የፈቀደውን መልካም ነገር በመፈጸም፣ በየተሰማራንበት ዘርፍ ለኢትዮጵያ የሚመጥነውን በማድረግ፣ ለሰላምና ለብልጽግናዋ በመትጋት፣ ለልጅ ልጅ የሚተርፍ አሻራ በማኖር እውነተኛ ኢትዮጵያዊነታችንን ማስመስከር አለብን።

**በድጋሚ መልካም የዐረፋ በዓል እንዲሆንላችሁ እመኛለሁ፣**
**ዒድ ሙባረክ!!**
**ኢትዮጵያ በልጆቿ ጥረት ታፍራና ተከብራ ለዘላለም ትኑር!!**
**ፈጣሪ ኢትዮጵያና ሕዝቦቿን ይባርክ!**

ሀምሌ 2 ቀን 2014 ዓ.ል

# ዛሬም እንደ ትናንቱ ፈተናዎችን በድል ተሻግረን፣ እጃችንን ለምስጋና እንዘረጋለን

## የተከበራችሁ የሀገራችን ሕዝቦች፣ ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት፣

ኢትዮጵያ የሚለው ስም ለችግሮች ያለመንበርከክ፣ በፈተና ሳይበገሩ የማለፍና እንቅፋቶችን ተሻግሮ ድል የማድረግ የክብር ስም ነው፡፡ ሀገራችን በታሪኳ ያለ ፈተና ያሳለፈቻቸው ዘመናት እጅግ ጥቂቶች ናቸው፡፡

በብርቱ ልጆቿ ጥረትና በፈጣሪ ቸርነት የሚገጥማትን የችግር ውርጅብኝ እየተቋቋመች እዚህ ደርሳለች፡፡
ዛሬም የሀገራችንን ብርቱ አቅም ሊገዳደር የመከራ ዶፍ በዙሪያችን ቢያስገመግም፤ እንደ ሐምሌ ክረምት በችግር ደመናቸው ሕይወታችንን ሊያጨልሙ የሚቋምጡ ኃይሎች ቢሰበሰቡም መጓዛችንን አናቆምም፡፡

በጽኑ ማንነታችንና በፈጣሪ እገዛ ለምንታመነው እኛ ሁሌም ከክረምቱ ባሻገር የሚመጣው ብሩህ ጸደይ ጎልቶ ይታየናል፤ ከጨለማው ማዶ ደማቅ ብርሃን እንዳለ እናውቃለን፡፡
የትናንቱን ጨለማ እንዳለፍነው ሁሉ፥ የዛሬውን ጽልመት የማንሻገርበት ምክንያት እንደሌለ እያመንን፣ ብርታትና ጥንካሬውን ለሚቸረን ፈጣሪ ዛሬም ምስጋና ከማቅረብ አንቦዝንም፡፡
አመስጋኝነት ያለፈውን ዘመን በአሸናፊነት፣ ያለንበትን ወቅት በዕድለኝነት፣ መጪውን ጊዜ ደግሞ በብሩህ ተስፋ እንድንመለከተው የሚያድርግ ታላቅ ኃይል አለው። በአንጻሩ አማራሪነትና ምስጋና ቢስነት የተሸናፊነትና የዕድለ ቢስነት ሥነ ልቡናን ይፈጥራል፡፡

ራሳችንንና ሌሎችን በአዎንታዊነትና በፍቅር መመልከት እንዳንችልም ያደርገናል። በምሬትና በምስጋና ቢስነት የተጠመደ ግለሰብም ሆነ ሕዝብ የጎደለው እንጂ በእጁ ያለው ጸጋ አይታየውም፡፡

የደረሰበት በደል እንጂ የተሰጠው ዕድል አይጎላለትም፡፡
የሚመጣው መከራ እንጂ ከፊቱ ያለው ደስታ በኅሊናው አይሳልም። አመስጋኝ ሰው በመከራውና በጭንቁ ውስጥ ድሉንና ዕድሉን ማየት የሚችል ነው፡፡ ከወጀቡና ከማዕበሉ ይልቅ የመርከቧን ጥንካሬ ያያል፡፡ ከፈተናና ከችግሩ ግዝፈት ይልቅ፣ ሁሉንም በአንድነትና በፈጣሪ ርዳታ ለማሸነፍ የሚቻል መሆኑን ያስባል፡፡

የአክሱምና ቀደምት ሥልጣኔዎች፣ የላሊበላና በዙሪያው የነበሩ ምሥጢራዊ የኪነ ሕንጻ እምርታዎች፣ በሐረርና በዙሪያው አብቦ የነበረው የከተሜነት መነቃቃትና ዕድገት፣ በጊቤ ዙሪያ የነበሩ ንግድን ከግብርና ያጣመሩ ሥልጣኔዎች፤ በገዳ ሥርዓት ዴሞክራሲን የማስተዋወቅ ጥረቶች፤ በወላይታ፣ በከምባታ፣ በሐላባ፣ በሐድያ፣ በዳውሮና ከፋ ዙሪያ የነበሩ ከመካከለኛው ምሥራቅ እስከ አውሮፓ ድረስ የንግድና የዲፕሎማሲ ግንኙነት የተመሠረተባቸው አስተዳደሮች፤ በጎንደር የተማከለ መንግሥታዊ አስተዳደር የመፍጠር ሙከራ፤ በአፋርና በሶማሊ የነበረው መረጃንና ማዕከላዊነትን መሠረት ያደረገው የአስተዳደር ሥርዓት፣ በጋምቤላ የነበረው ለሴቶች የተለየ የክብር ቦታ የሚሰጠው ሥልጣኔ፣ በቤኒሻንጉል የነበረው የሙዚቃና የሙዚቃ መሣሪያዎች ልህቀት፤ እንዲህም በሌሎቹም አካባቢዎች ታይተው የነበሩትን ሥልጣኔዎች ወደ ኋላ ዞር ብለን በማየት ልንኮራባቸው የሚገቡ ሀብቶቻችን ናቸው። የምንኮራባቸውን ትናንቶች የሰጠንን የኢትዮጵያን አምላክ ማመስገን ያለብንም ለዚህ ነው፡፡

በውስጥ የነበሩ ዘመነ መሳፍንትን የመሰሉ መከፋፈሎችን፤ ከውጭ የመጡ የቅኝ ግዛት ጫናዎችን ሀገራችን በማይታይ ኃይል ተቋቁማቸዋለች፡፡ ታሪኳና ማንነቷ ሳይጠፋ፣ እንደ አድማስ ድንጋይ ጠንክራ ለዘመናት መቆየቷ ተአምር ሊባል የሚችል ነው። ዘመናዊቱ ኢትዮጵያ ከመበታተን ወደ አንድነት በተሰበሰበችበት ሂደት ውስጥም ጦርነቶችና ግጭቶች፣ ወረራዎችና የሥልጣን ሽኩቻዎች እልፍ ሆነው ተከሥተዋል፡፡

የሀገረ መንግሥት ግንባታው መልክ ይዞ ሳይጠናቀቅ፣ ባለፉት ሃምሳ ዓመታት ውስጥ ፈጣንና ተከታታይ ሥር ነቀል ለውጦች ሀገራችንን ገጥመዋታል፡፡ አብዮቶች፣ የእርስ በርስ ጦርነቶች፣ ወረርሽኞች፣ ከፍተኛ ርሃቦች፣ ሰው ሠራሽና ተፈጥሯዊ ቀውሶች ጎርፍ ሆነው ቢግተለተሉም ኢትዮጵያን ነቀነቋት እንጂ አላፈረሷትም፡፡ በቅርብና በሩቅ ያሉ ታሪካዊ ጠላቶቿ በየጊዜው እየተነሡ ገዝግዘው ሊጥሏት ያላደረጉት ጥረት፣ ያልሸረቡት ደባ አልነበረም።

ስሟን ጥላሸት ሊቀቡ ሞክረዋል፤ በዓለም አቀፍ መድረኮች ላይ ፍትሕን ደጋግመው ነፍገዋታል። ያላትን የባሕር በር አሳጥተው ሊያፍኗት ሞክረዋል። ከሆዷ የሚፈልቁትን ወንዞቿን እንዳትጠቀም ሊያደርጉ በተንኮል የተጠለፉ ውሎችንና በክፋት የተሸመኑ ስምምነቶችን አድርገዋል። በዚህ ሁሉ መሐል፣ ኢትዮጵያችን እንደ ወርቅ በእሳት ተፈትና፣ በልጆቿ ጥረትና በፈጣሪዋ ፈቃድ ተጠብቃ እንደ ሀገር መቀጠል መቻሏ እጅግ ይደንቃል፡፡ ሀገራችን እነዚህን ሁሉ መከራዎች መሻገሯን ስናስብ ለፈጣሪ ምስጋና እንድናቀርብ ምክንያት ይሆነናል፡፡

ያለፉት አራትና አምስት ዓመታት በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ ታይቶ በማይታወቅ ደረጃ ተስፋና መከራ፣ አንድነትና ልዩነት፣ ዓለም አቀፋዊ አድናቆትና ውግዘት፣ እመርታና ጉተታ፣ ነጻነትና ግጭት ያስተናገድንበት ጊዜ ነው ማለት ይቻላል። ኢትዮጵያ የቁርጥ ቀን ልጆቿን ያገኘችበት ብቻ ሳይሆን ያጣችበትም ጊዜ ነው። ቀረ፣ ሊያበቃለት ነው የተባለው ታላቁ የሕዳሴ ግድባችን፣ ሙሌቱ ተገባድዶ ኃይልን ማመንጨት ጀምሯል። የድርቅና የጉስቁልና ምድር የተባለች ሀገር ቢልዮን ችግኞችን በመትከልና በየሥፍራው ፓርኮችን በማበጀት የምድረ ገነትነት ግስጋሤዋን ቀጥላለች። የህልውናዋ ዋስትና የምዕራባውያን ስንዴ እንደሆነ ሲያስቡ፣ ኢትዮጵያ ግን በጀመረችው የበጋ ስንዴና ሰፋፊ የእህልና የአትክልት እርሻዎቿ ከራሷ አልፋ ለሌሎች ለመትረፍ ጫፍ ላይ ትገኛለች። በአንድ ወቅት የአፍሪካ የቆሻሻ መጣያ ለመባል የደረሰችው አዲስ አበባ ስሟን የሚመጥን መልክ ልትይዝ ዳር ዳር እያለች ነው፡፡

ያጋጠሙን ፈተናዎች ብዙ ውድ ዋጋዎች አስከፍለውናል፡፡ እነርሱን ባሰብናቸው ቁጥር ያመናል፡፡ ካጣነው በላይ ግን ያገኘነው ይበልጣል፡፡ መከራው አልገታንም፤ ፈተናው አላሸነፈንም፡፡ ለዚህም ለፈጣሪ ብዙ ምስጋና እናቀርባለን።

ውድ የሀገሬ ልጆች፣
ወንድም በወንድሙ ላይ የጨከነበትን፣ አብረን የኖርን ቀርቶ አብረን የዋልን በማይመስል መልኩ የተጋጨንባቸውን፣ በረባው ባልረባው የሰው ሕይወት የተቀጠፈባቸውን፣ ዒላማ እንጂ ዓላማ በሌላቸው ሰዎች የወገኖቻችን ደም በከንቱ የፈሰሰባቸውን ያለፉትን ጥቂት ዓመታት ዞር ብለን ስናይ ልባችን በኀዘን ይሰበራል። እንደ ትውልድም ሐፍረት ይሰማናል፡፡

በሰሜኑና በምዕራቡ የሀገራችን ክፍሎች ጦርነቶችና ግጭቶች ያስከፈሉንን የሰው ሕይወትና የወደመውን የሀገር ሀብት ስናስብ ዓይኖቻችን ብቻ ሳይሆኑ ነፍሶቻችንም ያነባሉ። በአንድ ወቅት በምሥራቁና በደቡቡ የሀገራችን ክፍል ላይ ተከሥቶ የነበረው ጥፋት ያደረሰው ጉዳትና ሰቆቃም የሚረሳ አይደለም። እያነባንም ቢሆን ግን እናመሰግናለን፡፡ ከሆነብን የተደረገልን ይበልጣልና፡፡

አንገቷን ለመስበርና ወገቧን ለማጉበጥ የወረደባትን መዓት ሁሉ ችላ፣ ኀዘኗን በሆዷ፣ ፈተናዋን በክንዷ ተሸክማ አልፋ፤ ሀገራችን ኢትዮጵያ ዛሬም በጽናት መቀጠሏና አቅጣጫዋን ሳትስት በመንገዷ ላይ መገሥገሷ በርግጥ አስደናቂ ምሥጢር ነው።
በጥፋት ውስጥ ልማትን፣ በኀዘን ውስጥ መጽናናትን፣ በችግር ውስጥ በረከትን፣ በጨለማ መካከል ብርሃንን እያበራ የታደገንና ለሀገራችን ድጋፍና መከታ የሆነን የኢትዮጵያ አምላክ ነው፡፡ ይሄንን ጥላ ከለላ፣ አምባ መከታ፣ ጋሻ መሸሻ የሆነ አምላክ ማመስገን የኢትዮጵያውያን ሁሉ የአንድነት ዜማ መሆን ይገባዋል፡፡

ለውጡ የመጣው የኢትዮጵያን ጥቅም ለማስከበር ብቻ መሆኑን የተረዱ፣ በተለይ በዓባይና በአፍሪካ ቀንድ ላይ ከፍተኛ ፍላጎት ያላቸው አካላት በቀጥታና በተዘዋዋሪ መንገዶች የጥፋት ናዳቸውን ሲኅርፉት ነበር።

ታላላቅ የምዕራባውያን ሚዲያዎችና ተቋማትም የመንግሥቶቻቸውን ዐቅም ተማምነው በሀገራችን ላይ ዘምተዋል። ኢኮኖሚዋንና ዓለም አቀፍ ገጽታዋን ለማጥፋት የሚችሉትን ሁሉ ሲያደርጉ፣ ወዳጆቻችንን እንዲርቁን በእጅ አዙር ጠፍረው ለመያዝ ሲሞክሩ ነበር። ዳሩ ግን የእነሱ ጥረትና ሙከራ ያንቀላፋውን ኢትዮጵያዊ አንድነትና ቁጣ ቀሰቀሰው እንጂ አልጣለውም፡፡ የዐድዋ ድልም በእኛ ዘመን ተደገመ፤ ያንዣበበው ሀገር የመበታተን ጥቁር ደመናም ተገፈፈ።

ይህም የኢትዮጵያ አምላክ ምንጊዜም ከእኛ ጋር መሆኑን ያየንበት የዘመናችን ትንግርት ነበር፡፡ ባለፉት ሁለት ዓመታት ውስጥ ኢትዮጵያ ላይ የወረደውን ዓይነት ዓለም አቀፍ ጫናና ተጽዕኖ ብዙ ሀገራት መቋቋም ተስኗቸው ፈራርሰዋል። የኢትዮጵያ አምላክ ግን ለጠላቶቻችን ንክሻ አሳልፎ አልሰጠንም፡፡ ተንገዳግደን እንድንቆም፣ ሽብርክ ብለን እንድንጸና፣ ደክመን እንድንበረታ ዐቅምና ብርታት ሆኖናል፡፡

ይሄው ዛሬም ኢትዮጵያ ዓለምን እያስደነቀችም እየታዘበችም ቀጥላለች፡፡ መጪውን ዘመን በዚህ ክንደ ብርቱ መከታዋ ላይ ሆና ለመሻገር በተስፋ አርቃ ትመለከታለች። በታሪክ የሰማነውን የኢትዮጵያን ጽናት በዓይናችን ላሳየን፤ በኛም ዘመን ታሪክ ለሠራልን፣ ለኢትዮጵያ ፈጣሪ ለኢትዮጵያ አምላክ ምስጋና ይድረሰው።

እንደ ኢትዮጵያ ያለ በዘመናት መካከል ካገጠሙት ችግሮች በላይ ቆሞ በልዕልና የሚያሸበርቅ ሀገር ማነው? የቋንቋ፣ የባህልና የሃይማኖት ብዝኃነትን ከአንድነት ጋር አገናዝበው ለረጅም ዘመን የዘለቁ ሀገራትስ ስንት ናቸው? በከርሰ ምድራቸውና በገጸ ምድራቸው ላይ በሀብት የተሞሉ፣ አየርና ውኃቸው የተባረከላቸው፣ የልብ ጀግንነትንና የአእምሮ ብሩህነትን በጥምረት የታደሉ፣ እንደ ኢትዮጵያ ያሉ ሀገራት ስንት ናቸው? ሁሉም ዓይነት የጥቁር ሕዝቦች መልክና ገጽታ እንደ ፈርጥ ተሠራጭተው የሚያብረቀርቁባት ሀገር ከኢትዮጵያ ሌላ ማናት? በነጻነትና በሉዓላዊነት የአፍሪካ ተምሳሌት የሆነችስ ሀገር ከኢትዮጵያ ሌላ ከወዴት ይገኛል? ከጥንት እስከ ዛሬ የሌሎች ሀገር ስደተኞችንና መጻተኞችን በሀገራቸው እንደራሳቸው ልጆች ያስተናገዱ እንደ ኢትዮጵያ ያሉ ሀገራትስ እነማን ናቸው?

የውስጥ ፈተናውንና የውጪ ጫናውን ተቋቁመው በዓለም የስፖርት መድረክ ላይ በድል ላይ ድል የሚቀዳጁ ኢትዮጵያውያን አይደሉምን በስፖርት አደባባይ የእናት ሀገራቸውን ሰንደቅ ከፍ አድርገው እያውለበለቡ፣ ድል ባደረጉበት ሜዳ ላይ እጆቻቸውን ወደ ሰማይ ዘርግተው ፈጣሪያቸውን የሚያመስግኑ ኢትዮጵያውያን አይደሉምን? በርጋታ ካሰብንና በጥሞና በረከታችንን ከቆጠርን፣ እኛ ኢትዮጵያውያን ከምሬት ይልቅ አመስጋኞች ልንሆንባቸው የሚገቡ እጅግ ብዙ ሌሎች ምክንያቶችና መንሥኤዎች አሉን። ለዚህም ነው ልቡናችን በተረዳቸውም ሆነ አስበን ባልደረስንባቸው ብዙ ጉዳዮች ላይ ቆመን ፈጣሪን ልናመስግንና ልናከብር የሚገባን። የዛሬዎቹ የኢትዮጵያ ችግሮች የከፍታዋ መሰላሎችና የእመርታዋ ድልድዮች እንጂ

የውድቀቷ መቃብሮችና የመደናቀፊያ መሰናክሎች አይሆኑም። እነዚህ ሁሉ የክፉት ኃይላት የሚረባረቡብን፣ መጪውን ብሩህ ዘመን አይተው እንጂ ተስፋ ቢስ ድሆች መሆናችን አስጨንቋቸው አይደለም፡፡

በወርቅ የተሞላ ቤት እንጂ ባዶ ቤት የጠላትን ልብ አይስብምና፡፡ ቢያንስ ለጠላቶቻችንና በጎአችንን ለማይመኙ አካላት የታያቸው ዐቅማችንና እንደ ሀገር ያለን ዕምቅ ሀብት ለእኛም ሊታየን ይገባል። ምክንያቱም ወደ ፊትና ወደ ከፍታ በፍጥነት የመውጫ መንገዱ አመስጋኝነትና ያለንን በጎ ነገር በአድናቆትና በክብር ለመቀበል መቻል ነው። ባለፈችበት ወጣ ገባ መንገድ ሁሉ ሀገራችንን ጠብቋታልና ቸር አምላክ ዛሬም ምስጋና ይግባው።
ከከርሰ ምድሩ እስከ ጠፈሩ፣ ከእምነቱ እስከ ታሪካዊ ሀብቱ፣ ከአየር ንብረቱ እስከ ባህል ብዝኃነቱ፣ ከጀግንነቱ እስከ ነጻነት ወዳድነቱ፣ ፈጣሪ የለገሠንን የተከማቸ ረቂቅ ብልጽግና በማሰብ እናመስግነው። እርስ በርስም ከመጠላላትና ከመጋጨት ወጥተን አንዳችን ሌላችንን ማድነቅና ማመስገን ባህላችን ይሁን፡፡

ባልፈውና በጎደለው እያማረርንና ብሶት እያወራን መጪውን ትውልድ አናድክመው። ይልቁንም አንዳችን ሌላችንን፤ የዛሬዎቹ የትናንቶቹን፣ እናመስግን፡፡ ከሁሉም በላይና በፊት ደግሞ በዘመናት መካከል የረዳንን ፈጣሪ ቆም ብለን እናመስግን። ወዳጆቻችን ሲለወጡ፣ አጋሮቻችን ፊታቸውን ሲያዞሩ፣ ጎረቤቶቻችን ባዳ ሲሆኑ አይተናል፡፡ የማይለወጠው የኢትዮጵያ ኃይል፣ ረድኤት፣ ጋሻና መከታ ፈጣሪ ብቻ ነው፡፡

በዓመቱ ካሉት 365 ቀናት አንዷቷን ቀን ምስጋናችንን በጋራ ለፈጣሪ ለማቅረብና ውለታውን ለማሰብ ብንወስን የሚበዛ አይመስለኝም፡፡ ከቀኑስ ለአንዲት ደቂቃ ያህል የምናደርገውን ሁሉ አስቀምጠን በያለንበት ቆም ብለን፣ የፈጣሪን ውለታና ቸርነቱን አስበን፣ የኢትዮጵያን አምላክ ማመስገን አለብን፡፡ መጪውን ዓመትና ዘመን በምሬትና በብሶት፣ በጥላቻና በቂም፣ በበቀልና በቁርሾ ከምንቀበለው ይልቅ፣ በአድናቆትና በምስጋና፣ በመረዳዳትና በይቅርታ ልንቀበለው ይገባል፡፡

የጽንፈ ዓለም ሁሉ ፈጣሪና የመልካምነት ሁሉ ምንጭ የሆነውን ፈጣሪ እንደ ሀገርና እንደ ሕዝብ፣ እንደ መሪና እንደ ዜጎች፣ በየቋንቋችንና በየእምነታችን ከልባችን እናመስግነው። ከክፉ ወረርሽኝ ጠብቆናል፣ ከአንበጣ መንጋ ታድጎናል፤ ድርቅ

መቅሰፍት እንዳይሆን ከበር ቆሞልናል፤ ከቅርብና ከሩቅ የተነሣብንን የማፈራረስ አደጋ ቀልብሶልናል፤ የጀመርናቸውን ታላላቅ ፕሮጀክቶችና የታላቁን ግድብ የውኃ ሙሌት እውን እንዲሆን ረድቶናል፤ ሀገራችንና ሕዝባችንን ከጥንት እስከ ዛሬ ድረስ በምሥጢራዊ አሠራሩ ጠብቆልናል፡፡

ክብር ምስጋን ለእርሱ፣ ከዘላለም እስከ ዘላለም ይሁን ብለን፣ ለአንድ ደቂቃ በያለንበት ቆመን ለኢትዮጵያ አምላክ ምስጋና እንድናቀርብ ጥሪዬን አስተላልፋለሁ።

**ኢትዮጵያ በልጆቿ ጥረት ታፍራና ተከብራ ለዘላለም ትኑር!!**
**ፈጣሪ ኢትዮጵያና ሕዝቦቿን ይባርክ!**
ሀምሌ 20 ቀን 2014 ዓ.ም.

# እንኳን ለአዲሱ ዓመት አደረሳችሁ፣ አደረሰን

ዘመን አልፎ ዘመን ሊተካ፣ አሮጌ ምዕራፍ ተዘግቶ አዲስ ምዕራፍ ሊገለጥ፣ መጪውን ዘመን ልንቀበለው በምንዘጋጅበት በዛሬው የዋዜማ ምሽት ላይ ሆነን፣ ዐይነ ሕሊናችን ያሳለፍነውን ዓመት በትውስታ፣ መጪውን ደሞ በአዲስ ተስፋ ማስተናገዱ አይቀርም።

ያገባደድነውን ዓመት ስናስብ ትውስታችን በብዙ መልካምና እኩይ አጋጣሚዎች ተሞልቶ እናገኘዋለን። በአንድ በኩል ዓመቱ ጠላቶቻችን ግንባር ፈጥረው ጥቃታቸውን ያጠነከሩብን፣ ገሚሶቹ በሀገር ውስጥ ንጹሐን ለሞት ጭዳ ሊያደርጉ ጦር ያዘመቱበት፣ ገሚሶቹ በውጪ ዓለም አቀፍ ጫና በሚያሳድሩ መድረኮችና ሚዲያዎች አማካኝነት የቅጥፈት ዘመቻ ያጧጧፉበት፣ እንደ ሀገር የተፈተንንበት ዓመት ነው።

በሌላ በኩል ተስፋችንን የሚያለመልሙ፣ ወደፊት እንድንጓዝ ስንቅ የሚሆኑ ድሎች የተመዘገቡበትም ዓመት ነበር። ተደራጅተው በዘመቱብን ቁጥር ተደራጅተን መመከት እንደምንችል ያሳየንበት፣ የማዕቀብ ውርጅብኞችን መሻገር ወደሚያስችሉ መንገዶች ጥርሳችንን ነክሰን የገባንበት፣ በምግብ ራስን የመቻል ጉዟችን ተስፋ የፈነጠቀበት፣ ሉአላዊነታችን እንዲታፈር የሚያስችል ዐቅም እንድናደረጅ እድል የተፈጠረበት ጊዜ ስለነበር፣ ዓመቱን በምሬት ብቻ ሳይሆን በምስጋናም ጭምር እንድናስበው ያደርገናል።

አዲሱን ዘመንን በጉጉት ስንቀበለው እንደ መስከረም አደይ ተስፋችን እንደሚፈካ፣ እንደ አዝመራው ውጥናችን ፍሬ አፍርቶ እንደምናይ፣ እንደ በጋ ወንዝ ሰላማችን ከአደፍራሾች እንደሚጠራ፣ ጭጋግ ጭለማው ከላያችን ተገፍፎ ብርሃን እንደሚፈነጥቅብን በመተማመን ነው። ይኽ እምነታችን እንዲሳካ ከዘመኑ ጋር

እኛም አብረን መቀየር ይኖርብናል።

ምክንያቱም የእኛ መለወጥ ነው የዘመኑን ለውጥ እውነተኛ የሚያደርገው። እኛ ሳንቀየር፣ አሮጌ አስተሳሰባችንን አውልቀን ሳንጥል፣ ዓመት ሄዶ ሌላ ዓመት ቢመጣ የዘመን ለውጡ የቁጥር እንጂ ሌላ ሊሆን አይችልም።

ውድ የሀገሬ ልጆች፣
አሁን አንድ፣ ምንም ያልተነካ ተአምር ሊሠራበት የሚችል ውድ ሀብት ከፊታችን ቆሞ ይጠብቀናል። የመለወጥ እድሎችን የያዘ ዓመት። ዓመቱ ብንጠቀምበትም ባንጠቀምበትም መሄዱን አይተውም። ልክ እንደ ወራጅ ውኃ ያገኘውን ሁሉ ይዞ ይጓዛል። ከልደት እስከ እርጅና፣ ከእርጅናም እስከ ሞት ያደርሳል። መምሸትና መንጋት፣ ሳምንታትና ወራት፣ ዓመታትና ዘመናት ከኛ ቁጥጥር ውጭ ናቸው። ወቅቶችና ጊዜያትን መቁጠር ብቻ፣ መኖርን የማይገልጠው ለዚህ ነው። ውኃ ይዞት የሄደ ሁሉ ዋናተኛ አይባልምና። አንዳንድ ጊዜ እንዲያውም ከዋናተኛ በላይ ውኃ ይዞት የሚሄድ ነገር በፍጥነት ይጓዛል። ችግሩ፣ ፍጥነቱ ወዳልፈለገው ቦታ ይዞት እየተላተመ በመከራ ይጓዛል።

በጊዜ ውስጥ መሄድ ግን ከዚህ ሁሉ ይለያል። በማይቀየረው ጊዜ የሚቀየር ታሪክ ለመሥራት መጓዝ ነው። ሲቻል ከጊዜ መቅደም፣ ሳይቻል ከጊዜ ጋር አብሮ መጓዝ ነው። በጊዜ ውስጥ መጓዝ ጊዜ ወደሚወስደው የተለመደ ጉዞ ሳይሆን በጊዜ ውስጥ ልናሳካው ወደምንፈልገው ግብ ለመጓዝ መቻል ነው።

አዲስ ዓመት ማክበር ትርጉም የሚኖረው በጊዜ ውስጥ ለማለፍ የምንችል ከሆነ ነው። ጊዜ ይዞን ለሚሄድ ሰዎች አዲስ ዓመት የሚባል ነገር የለም። የጊዜ ዑደት ከጥንት እስከዛሬ የታወቀ፣ የተለመደ ነገር በመሆኑ። በሌሎች ያልተደረገ ነገር በእኛ ላይ ስለማይደረግ፤ ከዚህ በፊት ያልሆነ ነገር ዛሬ አዲስ ነገር ስለማይሆን። ሁሉም ቀናት፣ ሁሉም ሳምንታት፣ ሁሉም ወራት አምናም ነበሩ።

በጊዜ ውስጥ የሚያልፉ ሰዎች አዲስ ዐሻራ በየዘመኑ ያሳርፋሉ። ትናንት ያልታሰበና ያልተደረገ አዲስ ዐሻራ። ታሪክን ይቀይሩታል፤ አስተሳሰብን ይቀይሩታል፤ የሰውን ልጅ የአኗኗር ዘይቤ ይቀይሩታል። አዲስ ዕይታ፣ አዲስ ዓለም፣ አዲስ ምዕራፍ፣ አዲስ

መንገድ፣ አዲስ ሀብት፣ አዲስ ቴክኖሎጂ፣ አዲስ፣ አሠራር፣ አዲስ ዘይቤ ይፈጥራሉ። በዚህም ምክንያት ትናንትን ከትናንት ወዲያ፣ ዛሬን ከትናንት፣ ነገን ከዛሬ ይለዩታል። አዲስ ነገር በማድረግ፣ ዘመኑ ብቻ ሳይሆን ቀኑም አዲስ እንዲሆን ያደርጋሉ። ዓለም ዘወትር ስታስታውሳቸው የምትኖረው እንዲህ ያሉትን ሕያው ሰዎች ነው። ጊዜ ብዙዎችን ሲሽር በማይሻር ሥራቸው ሕያውነትን ተጎናጽፈው ጊዜን ራሱን አሸንፈውታልና።
ውድ ኢትዮጵያውያን፣

ሀገራችን ጊዜን የሚያሸንፉ ሕያዋን ዜጎች ትፈልጋለች። ዘመኑ እንደ ቁጥሩ አዲስ እንዲሆንላት አዲስ ሥራ በአዲሱ ዘመን የሚሠሩ ዜጎች ትፈልጋለች። ነባር ችግሮቿን በአዳዲስ መፍትሔዎች የሚተኩ፤ ነባር ፈተናዎቿን በአዳዲስ መድኃኒቶች የሚፈውሱ፤ ነባር ዕንቅፋቶቿን አንሥተው አዳዲስ መንገዶች የሚገነቡ፤ የተለመዱ የታሪክ አንጓዎቿን በአዳዲስ የታሪክ ምዕራፎች የሚቀይሩ፤ የርሃብ ታሪኳን በብልጽግና፤ የጦርነት ታሪኳን በዘላቂ ሰላም፤ የመከፋፈል ታሪኳን በኅብረ ብሔራዊ አንድነት፤ የግጭት ታሪኳን በወንድምና እኅታማችነት፤ የኋላቀርነት ታሪኳን በዘመናዊነት፤ የሚቀይሩ ሕያዋን ጀግኖች ትፈልጋለች። አዲሱ ዓመት በርግጥም አዲስ እንዲሆንላት አዲስ ታሪክ የሚጽፉላትን ትፈልጋለች።

የዘንድሮ መስከረምና ጥቅምት፣ የካቲትና ግንቦት ካምናው፣ ከካቻምናው፣ ከጥንቱ፣ ከቀደምቱ የተለየ ሆኖ እንዲከበር የሚያደርጉ፣ ዘመን ቀያሪ ልጆች ትፈልጋለች። የዘመን መቀየር አይቀሬ ነገር ነው። ዘመንን ራሱን መቀየር ግን የጀግኖች ሥራ ነው። አረንጓዴ ዐሻራ፣ የበጋ ስንዴ፣ የቱሪዝም ሀብቶቻችንን በራሳችን ዐቅም የመጠቀም ጅማሮ፣ ሀገራዊ ችግሮቻችንን በውይይት የመፍታት ውጥን፣ ከውጭ ተጽዕኖ ለመላቀቅ በገቢ ራስን የመቻል እንቅስቃሴ፣ የዚሁ አካል ነበሩ። ዘመንን የመቀየር ፍላጎት ውጤቶች።

እነዚህ ግን ማሳያዎች እንጂ ፍጻሜዎች አይደሉም። አገልግሎት አሰጣጥን ከሌቦች በማጽዳት፣ የፍትሕ ሥርዓቱን ውጤታማ በማድረግ፣ የኑሮ ውድነትን ጫና በመቀነስ፣ የአምራች ዘርፉን ድርሻ በማሳደግ፣ ኅብረ ብሔራዊ አንድነትን በማጠናከር፣ ግጭቶችን በማስወገድ፣ ግብርናን ይበልጥ በማዘመን፣ የውጭ ግንኙነትን ይበልጥ በማጠናከር፣ መልካም አስተዳደርን በማስፈን፣ ዴሞክራሲን በማጽናት፣ ያለንን

የተፈጠር ጸጋ በሚገባ በመጠቅም፣ ወዘተ. የሚቀሩን ነገሮች አሉ። እነዚህ ሁሉ፣ ዘመን የሚቀይሩ ጀግኖችን ይፈልጋሉ።

አዲሱን ዓመት አዲስ እናድርገው። በራሱ ጊዜ የሚሄድና የሚመጣን ዓመት፣ አዲስና አሮጌ ማለት ትርጉም የለውም። የራሳችንን አዲስና አሮጌ ዘመን እንፍጠር። አሮጌው ዘመን ለዕጽዋትም፣ ለእንስሳትም፣ ለግዑዝ ነገሮችም አሮጌ ሆኗል። አዲሱ ዓመትም ለእነዚህ ሁሉ አዲስ ነው። ሰው የመሆናችን ልዩነት የሚፈጠረው የራሳችንን አዲስ ዓመት ራሳችን ስንፈጥረው ነው። ያን ማድረግ የምንችለው ደግሞ አዲስ ሥራ በመሥራት ነው።

አምና ያልነበረ ለውጥ፣ ሥራና ተአምር ከፈጠርን ዓመቱ አዲስ ዓመት ይሆናል፤ በአምናው በሬ ዘንድሮም ካረስን ግን ምኑን አዲስ ዓመት ሆነው ለኢትዮጵያችን አዳዲስና ዘመናዊ አሠራሮች፣ አዳዲስ መፍትሔዎች፣ አዳዲስ መንገዶች፣ አዳዲስ ዕይታዎች፣ አዳዲስ ዐሻራዎች፣ አዳዲስ ምርቶች፣ አዳዲስ የኪነ ጥበብ ሥራዎች፣ አዳዲስ ቴክኖሎጂዎች፣ አዳዲስ የሳይንስ ግኝቶች፣ አዳዲስ ፍልስፍናዎች፣ አዳዲስ የአገልግሎት አሰጣጥ መንገዶች፣ አዳዲስ ፕሮጀክቶች፣ አዳዲስ መሠረተ ልማቶች፣ አዳዲስ የዕውቀት ብልጭታዎች፣ አዳዲስ የግብርና ዘይቤዎች በማምጣት ዘመኑን አዲስ እንድናደርገው ጥሪዬን አቀርባለሁ።

በድጋሚ ዘመኑን በአዲስ ሥራ አዲስ አድርገነው አዲስ ዓመት እንዲሆንልን እመኛለሁ።

**ኢትዮጵያ በልጆቿ ጥረት ታፍራና ተከብራ ለዘላለም ትኑር!!**
**ፈጣሪ ኢትዮጵያና ሕዝቦቿን ይባርክ!**
ጳጉሜን 5፣ 2014 ዓ.ም

# እንኳን ለብርሃን መስቀሉ አደረሳችሁ

አስቸጋሪው የክረምት ወቅት ወጥቶ፣ የጠራውና አስደሳቹ የመጸው ወቅት በሚጀምርበት ወቅት ላይ እንገኛለን። የሞላው ወንዝ ይጎድላል፤ ፈታኙ ጭቃ ይደርቃል፤ ጥሻው ይገለጣል፤ ጨለማውም ይበራል፤ ብርዱ ይቀልላል፤ ሜዳና ተራራው በአበባ ያጌጣል። በዚህ ወቅት ነው ተሠውሮ የኖረው መስቀል የተገኘበትን በዓል የምናከብረው።

ኢትዮጵያውያን የሚያስተሣሥረን ገመድ ሊበጠስ የማይችል ጠንካራ መሆኑን ከሚያሳዩን ወቅቶች አንዱ ወርሃ መስከረም ነው። አብዛኞቹ የሀገራችን ብሔረሰቦች የዘመን መለወጫ በዓላቸውን፣ ወይም ደግሞ የዓመቱን ታላቅ የምስጋና በዓላቸውን የሚያከብሩት በዚህ በመስከረም ወቅት በተቀራራቢ ጊዜ ነው። ይህ እንደ እንግዳ ደራሽ፣ እንደ ውኃ ፈሳሽ በድንገት ወይም በአጋጣሚ የሆነ አይመስልም። መነሻው አንዳች የጋራ ዕሳቤ እንደሚኖረው ይጠቁመናል። መነሻው የአንድነታችን፤ የአከባበሩ ልዩ ልዩ መሆን ደግሞ የኅብራዊነታችን ማሳያ ነው።

በአብዛኛው አከባበራችን ደመራው፣ ችቦው፣ የወጣትና የልጆች ፌሽታ፣ ለሽማግሌዎች የሚሰጠው ቦታ፣ ምርቃቱ፣ መልካም ምኞቱ ተቀራራቢ ነው። ይህ ነገር ከሰሜን እስከ ደቡብ፣ ከምዕራብ እስከ ምሥራቅ ተመሳስሎና ተቀራርቦ ሲከበር ስናይ፣ ኢትዮጵያ የምትባለው ሀገራችን የተሣሠረችበትን ውስጣዊ ሥር እንድንመረምር ያደርገናል።

ደመራው ሲለኮስ ጨለማው በብርሃን፤ ቁርና ብርዱ በሙቀት፤ ድብርቱ በተስፋ ይተካል። አስቸጋሪውንና ፈታኙን ወቅት መሻገራችንን ደመራው ያበሥራል። ማንም ባይነግረንም የመስኩ አበባና የሰማዩ ጥራት፣ የወፎች ዝማሬና የጅራፉ ጩኸት መስከረም እንደጠባ ይመሰክራል። አበባው ወደ ፍሬ፣ ፍሬው ወደ ምርት የሚሸጋገረው በዚህ ወቅት ነው። በጎመን የከረመ ማጀት በገብስ ገንፎና በልዩ

ልዩ እሸት ሰብሎች መሞላት ይጀምራል። ከክረምቱ ጋር አስፈሪ የነበሩት ወንዞች በመስከረሙ ግርማ ጉልበታቸው ላልቶ ዘመዳሞች ለመጠያየቅ፤ ተማሪዎች ወደ ትምህርት ገበታቸው ለመመለስ ይሰናዳሉ። ወቅቱ ይዟቸው በሚመጣቸው ክብረ በዓላትና ልዩ ልዩ ሁኔታዎች ምክንያት መስከረም ለኢትዮጵያችን ትልቅ ተምሳሌት ነው።

ውድ ኢትዮጵያውያን፣

በአስቸጋሪና በፈታኝ ሁኔታዎች ውስጥ አልፈን እዚህ ደርሰናል። መንገዳችን ጨለማ፣ እግራችን ቆጤማ እንዲሆን ብዙ ተሠርቶብናል። ከድጡ ወደ ማጡ እንድንወርድ ያልተፈተለ ሤራ የለም። እንጀራችንን የበሉ ተረከዛቸውን አንሥተውብናል። ወንዙ እንዲሞላብን፣ ጎርፉ እንዲደርስብን፣ ናዳ እንዲወርድብን ብዙ ተሠርቶ ነበር። የኢትዮጵያ አምላክ ግን አሳልፎ አልሰጠንም።

ስለ ረሃብ እየተነገረብን፣ ምድሪቱ አትረፍርፋ ሰጠችን። ስለ በረሃማነት እየተሟረተብን ሀገራችን አረንጓዴ ለበሰች። ስለ ኪሣራ እየተለፈለፈ፣ ኢኮኖሚያችን ፈተናዎቹን እየተሻገረ ቀጠለ። ከግራ ከቀኝ እየተዋከብን ሦስተኛውን ዙር የሕዳሴ ግድብ ሞልተን ተርባይናችንን አስነሣን። እንድንለያይ መዓት እየተወራ፣ የሕዝባችን አንድነት እንደ ብረት ጠነከረ፤ እንደ አልማዝ አበራ። ደከመዋል ተብሎ ሲዘመትብን፣ በጽናት ቆመን አሳየን። የትም አያደርሷቸውም የተባልንባቸው ፕሮጀክቶቻችን በመጠናቀቅ ላይ ናቸው።

ይህ ሁሉ አልሳካ ሲል ደግሞ ትእግሥታችን እንደ ፍርሃት፣ ሰላም ፈላጊነታችን እንደ ድክመት ተቆጥሮ ሦስተኛ ዙር ጥቃት ተፈጸመብን። የታገሥነው በዚህም ሆነ በዚያ ወገን የሚያልቀው የእኛው ሕዝብ ነው ብለን ነው። እነሱ ሲከፉ እኛ የለዘብነው፣ የአንድ ሀገር መንግሥትና የአንድ ሀገር ዐመጸኛ እኩል ለሕዝብ አያስቡም ብለን ነው። ከጸብ ይልቅ ፍቅር ይሻላል ስንል ምላሹ እብሪት እየሆነብን ጭምር በንግግር ፋንታ ኃይል የመጠቀም ፍላጎት አላደረብንም። ከጦርነት በላይ ከሰላም እናተርፋለን ብለን እየተወጋንም ቢሆን የሰላም እጃችን ከመዘርጋት አልተቆጠብንም። ሰላም ግን በአንድ ወገን ፍላጎት ብቻ አይመጣም።

በዚህ የተነሣ ሀገራዊ ሕልውናችንን ለማስጠበቅ ስንል ወደ መከላከል እንድንገባ ተገድደናል። የዛሬው ብቻ ሳይሆን የመጭውም ትውልድ አደራ አለብን። ኢትዮጵያን ከመጥፋት ለመታደግ፣ ሕዝብን ከብተና ለማዳን እና ሀገር እንደ ሀገር ቀጥላ የልጅ ልጆቻችን ሉአላዊት ኢትዮጵያን እንዲወርሱ ስንል የመጨረሻውን የመከላከል አማራጭ ወስደናል። አሁንም እያደረግን ያለነው የመከላከል ውጊያ ይኼንን ታሪካዊ አደራ ለመወጣትና ብሔራዊ ጥቅሞቻችንን ከአደጋ ለመከላከል ያሰበ ነው።

ለኢትዮጵያ መንግሥት ስለ ሰላም ማስተማር ማለት ለዓሣ ዋናን ለወፍ መብረርን ማስተማር ነው። ‹ሰላም› ራሷ የኢትዮጵያ መንግሥት የከፈለላትን ዋጋ ያህል የከፈለላት የለም። የገጠመን ወረራ በሰላማዊ መንገድ እንዲጠናቀቅ ከሚፈለግብን በላይ አድርገናል። የእኛን ጥረት በተገቢ መንገድ የሚያወድስና የሌላኛው ወገን እምቢታ በተገቢው ልክ የሚያወግዝ ግን ጥቂት ነው። ለሰላም የተዘረጉ እጆች ሰላምን የሚመርጡት፣ ጦር ለመያዝ ስለማይችሉ አይደለም፤ ሰላምን ስለሚመርጡ ብቻ ነው። ለሰላም የዘረጋነው እጅ ምንም ዋጋ ስላላገኘ ጦር እንዲይዝ እየተገደደ ነው።

በተለያዩ አካባቢዎች፣ በከተማና በገጠር፣ በአርሶና በአርብቶ አደር መንደሮች፣ በሀገር ውስጥና በውጭ ሀገር፣ በመሐልና በግንባር ሆናችሁ የብርሃነ መስቀሉን በዓል ለምታከብሩ ሁሉ፤ አንድ ነገር ላረጋግጥላችሁ እወዳለሁ። ኢትዮጵያ በዚህ ዓመት በሁለት እጆቿ እየሠራች ፈተናዋን ትሻገረዋለች። በአንድ እጇ ብሔራዊ ጥቅሟን በሚገባ አስጠብቃ ችግሯን ለመጨረሻ ጊዜ ለመፍታት ትታገላለች። በሌላ በኩል ደግሞ ሕዝባችን በወዙ ጎተራው እንዲሞላ፤ ምሳውን በብድር ሳይሆን ከራሱ ማሳ ዘግኖ እንዲመገብ የሚችልበትን ስትራቴጂ ነድፈን መንቀሳቀስ እንጀምራለን።

ይህ ጉዞአችን "የሌማት ትሩፋት" ይባላል። ዓላማው በቀላል መንገድ ገበታችንን በተመጣጠነ ምግብ መሙላት ነው። የጓሮ አትክልትና ፍራፍሬ፣ ቀላል የዶሮ ርባታ፣ ቀላል የወተት ላሞች ርባታና የዓሣ ርባታን ይይዛል። አሁን ያለንበት ዘመን በአነስተኛ ቦታዎች፣ ቀላል ቴክሎጂዎችን በመጠቀም፣ በምግብ ራሳችን ለመቻል የሚያስችሉ ዕድሎች የተፈጠሩበት ዘመን ነው። ታላላቅ የእርሻ መሬት የሌላቸው ሀገሮች ይሄን መንገድ ውጤታማ ሆነውበታል። አረንጓዴ ዐሻራን ውጤታማ እንዳደረግነው ሁሉ፣ ወገባችንን አሥረንና እጅጌያችንን ሰብስበን ጎተራና ማጀታችን እንዲሟላ ከዚህ

ዓመት ጀምሮ ታጥቀን እንሠራለን።

የመስቀል በዓል ያለፈውን ፈተና የምናስወግድበትና ለመጪው ተስፋ የምንሰንቅበት ነው። የአከባበሩ ሥነ ሥርዓትና የሽማግሌዎች ምርቃት ይሄንን ያሳየናል። ኢትዮጵያም በዚህ ዓመት የከረሙ ችግሮቿን እንድትፈታና ገበታዋን ለልጆቿ በሚያስፈልጋቸው ምግብ እንድትሞላ፣ ኢትዮጵያን የምንወድ ሁሉ ቆርጠን እንድንነሣ በዚህ አጋጣሚ ጥሪ አቀርባለሁ።

**በድጋሚ እንኳን ለመስቀል በዓል አደረሳችሁ፣ አደረሰን።**
**ኢትዮጵያ በልጆቿ ጥረት ታፍራና ተከብራ ለዘላለም ትኑር ! !**
**ፈጣሪ ኢትዮጵያና ሕዝቦቿን ይባርክ !**
መስከረም 16፣ 2015 ዓ.ም

# እንኳን ለኢሬቻ በዓል አደረሳችሁ

የጉዳ ሥርዓት ባለቤት የሆንከው የተከበርከው የኦሮሞ ሕዝብ፤
የተከበራችሁ የኢትዮጵያ ሕዝቦች ከሁሉ፤
አስቀድሜ እንኳን ከክረምቱ ወደ ብርሃናማው መጸው ተሸጋገራችሁ፤ እንኳን ደስ አላችሁ ማለት እፈልጋሁ፡ ሰው ሠራሽ እና ተፈጥሯዊ ችግሮች እንዲሁም ከትንሽ አስከ ትልቅ ጠላቶቻችን የደቀቤፆንን አደጋ አሳልፎ ለመጸው ብርሃን ላቢቃን ፈጣሪ ምስጋና ይግባው፡ ኦሮሞ ከጉዳ ሥርዓት በወረሰው ዕሴት ክረምት አልፎ መጸው ሲገባ ፈጣሪውን ያሰግናል፡ የክረምቱን ጨለማ ×ሳፈህ፣ እህልን አብቅለህ፣ ማሳውን አሳምረህ የመጸውን ንጋት ስላሳየሆን ፈጣሪ ምስጋና ይግባህ ይላል፡፡ርጥፍ ሣር ይዞም “መሬሆ “መሬሆ እያለ ወደ መልካ በማቅናት የኢሬቻ ሥርዓትን ይከውናል፡፡

ኢሬቻ ከረምት አሰፎ መጸው ሲገባ ፈጣሪ የሚመሰገንበት በታላቅ ሥነ ሥርዓት የሚከበር ነው፡፡ በድጋሚ የኦሮሞ ሕዝብን፣ በአጠቃላይ የኢትዮጵያ ሕዝብን እንኳን አደረሳችሁ ስል ታላቅ ደስታ ይሰማኛል-፡ ኢሬቻ የሰላም መድረከ ነው፡ ለኢሬቻ ወደ መልካ የሚሄዱ ርጥብ ር በእጃቸው ይዘው የኢሬቻ ሥርዓትን ከመከወናቸው በፊት ሦስት ጥያቄዎችን መመለስ አለባቸዉ። የገዳ አባቶች “በመካከላችሁ ሰላም አለ?” ለፈጣሪስ ሰላማ ናችሁ?” “ከተፈጥሮስ ጋር ሰላም ናችሁ?” ብለው ይይቃሉ፡፡ ወደ መልካ ለኢሬቻ የሄደው የበዓሉ አከባሪም መልካውን በርጥብ ሣር ከመንካቱ በፊት ሰላም ነው ብሎ ይመልሳል፡ ከዛም በርጥብ ሣሩ መልካውን ነከቶ “መሬሆ “መሬሆ በማለት ፈጣሪውን ያመሰግናል፡፡ ለዚህም ኢሬቻን የሚያውቅ ሰው ቂምና በቀልን ትቶ ሰላምን ይሰብካል፡፡

አንድነትና ሰላምን ትብብርና ወንድማማነትን ያጠናከራል፡ ከፈጣሪ ላገኘው የከበረ ስጦታ ዕውቅና ይሰጣል፡፡ በተፈጥሮ ያለውን መስተበርና ትብብር ያደነቀ ለፈጣሪው ምስጋና ያቀርባል፡፡ ልምላሜን የፈጠረ አምላከ ለሰው ልጅ ምስጋና ያገኛል፡፡ የሰው

ልጅ ፈጣሪ የሰጠውን ርጥብ ሣር ይዞ ተፈጥሮን ያደንቃል ፈጣሪን ያመሰግናል፡፡ ኢሬቻን የሚያከብር ከራሱ፣ ከነረቤቱ፣ ከውስጥና ከውጪ በሀገሩ እና ሩቅ ላለው ሰው ሰላማዊ መሆን አለበት፡፡

ለኢሬቻ የሚሄድ ሰው ጥላቻን ትቶ ዕርቅ ማውረድ አለበት ከኢሬቻ ሲለስም ቂምና ጥላቻን እንዲሁም ያለፈ ጉዳትን ከማስታወስ ራሱን መቆጠብ አለበት፡ ኢሬቻን ማከበር በጋራ ምጋናን ማቅረብ ነው፡ የተፈጥሮ ሕግ እንዳይስተጓጎል ፈጣሪ በፍጡራን እንዳያዝን ፈጣሪን መለመን ነው። ስለዚህ ኢሬቻ ዕርቅ ነው። ሰላም ነው ፍቅርና አንድነት ነው። ይህ ደግሞ የገዳ ሥርዓት ባህልና ዕሴት ነው: ኢሬቻ የንጽሕና መድረክ ነው፡፡ ኢሬቻ በሐሳብ መንጻትን ይፈልጋል፡ ቂም መያዝና ስም ማጥፋት ከኢሬቻ ዕሴቶች ተቃራኒ ናቸው። ለኢሬቻ የሚሄድ ሰው ይቅር ባይ የሆንከው ፈጣሪ በማለት እጁን ዘርግቶ አምላኩን ይለምናል ያመሰግናል፡፡

በኢሬቻ ሰማይና ምድርን የፈጠረ አምላከ ይመሰገናል፡፡ሐቅን ማዛባት እውነትን መደበቅ ነውር እንደሆነ ይሰበካል፡፡ የተፈጥሮና የፍጡራን ሕግ የሚታወቅበት ነው፡: የመጸው ወቅት የፈጣሪ የእጅ ሥራ የሚደነቅበት ነው። ከጨለማ ምዕራፍ ወደ ብርሃን ከክረምት ወደ መጸው ከቡቃያ ወደ አዝመራ የምንሸጋገርበትም ነው። ይህን የፈጣሪ ሥራ የሆነውን የተፈጥሮ ኡደትን “መሬሆ “መሬሆ በማለት የሚደነቅበት የኢሬቻ በዓል የብርሃንና የምርቃት ቀ› ነው: ኢሬቻ የወንድማማችነት እኅትማማችነትና የአንድነት ቀን ነው።

በገዳ ሥርዓት በጋራ ቶ በጋራ መብ መተባበርና አብሮ ቆም ለሐቅ መታገልና በችግር ጊዜ መረዳዳት የገዳ ሥርዓት የቀደመ ባህል ነው። ኢሬቻ አንድነትና ወንድማማችነት እትማማችነት የሚጠነከርበት ነው። ኅብረት የሚጠነከርበት የፍቅር የወዳጅነት በጋራ የመኖር ምንጭ ሆኖ የሚያገግል ነው ይህ ትልቅ ዕሴት የሰው ልጆችን ሁሉ እኩል ማየትና ማከበር በመቅረብ መረዳትን የሚያስተምር ነው። ስለዚህ የሉ አከባሪ ይህን የኢሬቻ ሥርዓትን በማኩብር ፈጣሪን ያመሰግናሉ። ኢሬቻ በዘር በጾታ እና በእድሜ በሃይማኖትና በየትኛውም መሥፈርት ሰውን ኢይከፋፍልም። ለዚህም ነው ዛሬ ላይ ሁሉም ብሔር ብሔረሰቦች በአንድነት የሚያከብሩት በዓል የሆነው። ለዚህም ነው ከኢትዮጵያውያን አልፎም የውጭ ሀገር ቱሪስቶችን መሳብም የቻለው። የኛ እንደ ሀገር እና ህዝብ የባህልና ወግ ባለፀጎች ነ፤ የሃይማኖት መቻቻል እና አብሮ

መኖርን የሚያጠናከሩ የባህል ሥርዓቶች እሉን እንዳችን የእንዳችንን ጉድለት ከመፈለግ ይልቅ መደማመጥን ያበረታታል ቂምና ጥላቻን ከመዘመር ሰላምና እውነትን መውደድን ያጠናከራል። የዘፈቀደ እና የስንፍና ኑሮ የኛ አይደለም። ለሁሉም ነገ ሕግ አለን።በሥርዓትና ወግ ለመኖር እንገደዳለን፤ጀግንነት እንጂ ከህደት እኛን አይገልጸንም። በታሪክ ውስጥ በአንድነት እንጂ በልዩነት ተከበረን ተፈርተንም ሆነ አሸንፈን አናውቅም። አንድ ሆነን ስንቆም በሁሉም ግንባር ድልን እንደምንጎናጸፍ አይተናል የትኛውንም የሚሸረብብንን ሤራ ማክሸፍ እንደምንችል በተጨባጭ አሳይተናል።

ያለፈው አራት አመት ልምዳችንም ይህንኑ ነው የሚገልጸው። ጠላቶቻችን ወድቀዋል ሲሉን ተነስተን ፈርሰዋል ሲሉን ተገንበተን አይተውናል። አሁንም ብዙ ነጻነታችንን እና ሉዓላዊነታችንን የሚፈታተኑ አሉ፤ ከመንገዳችን ን ሊያሰናከሉን አይችሉም። ሐቅ አለን፤ እውነት ላይ ቆን እንታገላለን ፈጣሪም ከኛ ጋር ነው። ለየትኛውም ምድራዊ ኃይል አንንበረከም። ትልቁ ጠላታችን የሆነውን ድህነት ለማሸነፍ መሥራት ይገባናል። የሥራ ባህላችንን በማሻሻል በሁሉም የልማት መስኮች ተሠማርተን ለማሸነፍ በቁጭት መትጋት አለብን። ችሣን የመቋቋም አቅማችን በንቃታችን ተደራጅተን አንድነታችንን በጠበቅንና በተጨባጭ ሠርተን ባሳየነው ልክ በችግር በፈተና ጊዜ ካሳለፍነው ልምዳችን ተምረናል።

እንደ ኢሬቻ ያሉ ታላላቅ ከብረ በዓላትን እንደ አንድነታችን ማጠናከሪያ መሣሪያ ይዘን በአጭርና በረዥም ጊዜ የያዝነውን የብልፅግና ጉዟችንን ለማደናቀፍ የተከፈተብንን ዘመቻዎች ሁሉ ጥሰን በማለፍ የያዝነውን ራእይ ለማሳካት በአንድነት እንድንራ ጥሪዬን አቀርባለሁ። የዘንድሮ ኢሬቻ ወደ አዲስ ምዕራፍ የምንሸጋገርበት እና በድል ላይ ድል የምናስመዘግብበት እንዲሆንልን እመኛለሁ። ዓመቱ የስኬትና የድል ይሁንልን።

**ኢትዮጵያ በልጆቿ ጥረት ታፍራና ተከብራ ለዘላለም ትኑር!**
**ፈጣሪ ኢትዮጵያና ሕዝቦቿን ይባርክ!**

መሰከረም 20፣ 2015 ዓ.ም

# ከመስከረም
# እስከ መስከረም

ጥር ፳፻፲፰ ዓ.ም.